# መጽሐፈ ሳሙኤል - ሁለተኛ

## መግቢያ

### አሰያየሙ

በመጀመሪያ መጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛና መጽሐፈ ሳሙኤል ሁለተኛ አንድ መጽሐፍ ነበሩ (የመጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛን መግቢያ ይመ)።

### ሥነ ጽሑፋዊ ገጽታው፤ ጸሓፊውና፤ የተጻፈበት ዘመን

ከመጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛ መግቢያ፣ "ሥነ ጽሑፋዊ ገጽታው፣ ጸሓፊውና የተጻፈበት ዘመን" የሚለውን ክፍል ይመ።

### ይዘትና መሪ ሐሳብ፡- ንግሥናና ቃል ኪዳን

መጽሐፈ ሳሙኤል ሁለተኛ ሁሉን ነገር ያካተተ ባይሆንም ዳዊት የእግዚአብሔር እንደራሴ በመሆን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመራ እውነተኛ ንጉሥ አድርጎ ያቀርበዋል። ዳዊት ንጉሥ መሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ በይሁዳ ነገድ ዕውቅናን ያገኘው በኬብሮን ሲሆን (ም 1-4)፣ ከዚያም በሕይወት ከተረፉት የሳኦል ወንዶች ልጆች አንዱ የሆነው ኢያቡስቴ እንደ ተገደለ ወዲያውኑ፣ በቀሩት ነገዶች ተቀባይነት አገኘ። የዳዊት አመራር ወሳኝነት ያለው፣ ውጤቱም ያማረና የሰመረ ነበር። ኢየሩሳሌምን ከኢያቡሳውያን በመማረክ የመናገሻ ከተማውና መኖሪያው አደረጋት (5፥6-14)። ጥቂት ቈይቶም የእግዚአብሔርን ታቦት ከአሚናዳብ ቤት ወደ ኢየሩሳሌም አመጣው፤ ራሱን ዳዊትንና ሕዝቡን የሚገዛ እውነተኛው ንጉሥ እግዚአብሔር መሆኑን በሕዝቡ ሁሉ ፊት ተናገረ (ም 6፤ መዝ 132፥3-5)።

በዳዊት ዘመነ መንግሥት እግዚአብሔር ሕዝቡን አበለጸገው፤ የገባውንም ቃል ኪዳን ለመፈጸም (ዘፍ 15፥18 ይመ)፣ የግዛቱን ዳር ድንበር ከግብፅ እስከ ኤፍራጥስ (ም 8) ለማስፋት ይችል ዘንድ በጠላቶቹ ላይ ድልን አጐናጸፈው። ዳዊት፣ ቤተ ንጉሥ፣ የዙፋኑ (የታቦቱ) ማረፊያና እስራኤላውያን እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ስፍራ እንዲሆን ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ፈለገ። ነገር ግን ነቢዩ ናታን ለእግዚአብሔር ቤት የሚሠራለት ዳዊት ሳይሆን በተቃራኒው ለዳዊት ቤት የሚሠራለት (ሥርወ መንግሥት) ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ገልጸለት፤ ይህ ለዳዊት የተሰጠው ተስፋ ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ለመሆኑም በም 7 ላይ ተገልጾአል። ይህን ታላቅ ቁም ነገር የያዘው ምዕራፍ ለዳዊት ስለ ተገባለት ቃል ኪዳን እንዲሁም ስለ ቃል ኪዳኑ መመሥረት (መዝ 89፥34-37 ይመ) በስፋት ያስተምራል፤ ቃል ኪዳኑም በሔዋን ዘር በኩል በዚያ ጥንታዊ ጠላት ላይ የሚገኘውን የማያዳግም ድል የሚያረጋግጥ ተስፋ ነው (ዘፍ 3፥15 እና ማብ ይመ)። ይህ ሴምንና ዘሮቹን (ዘፍ 9፥26-27 እና ማብ ይመ)፣ አብርሃምንና ዘሮቹን (ዘፍ 12፥2-3፤ 13፥16፤ 15፥15 እና ማብ ይመ)፣ ከዚያም ይሁዳንና ንጉሣዊ ዘሮቹን (ዘፍ 49፥8-11 እና ማብ ይመ) የሚያመለክት ተስፋ እዚህ ላይ የዳዊትን ንጉሣዊ ቤተ ሰብ ሲያመለክት ይታያል። ከዚያ በኋላም ነቢያት ያ ከዳዊት ቤት ተወልዶና በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጠው እውነተኛው የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆኖ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ስም የማስተዳደሩን ተግባር በትክክል የሚፈጽም መሆኑን የተናገሩለት እርሱ ጊዜው ሲደርስ ይገለጣል (ኢሳ 9፥6-7፤ 11፥1-16፤ ኤር 23፥5-6፤ 30፥8-9፤ 33፥14-16፤ ሕዝ 34፥23-24፤ 37፥24፡25 ይመ)፤ እነርሱም የተሰጣቸውን የተስፋ ድል በዚህ ዐይነት አብረውት ይጐናጸፋሉ (ሮሜ 16፥20)።

ጸሓፊው ታላቅ ክብር ያገኘውና አገዛዙ የሰመረለትን የዳዊትን መንግሥት በሚገባ ከገለጸ በኋላ፣ በም 10-20 ላይ ደግሞ የዘመነ መንግሥቱን አስከፊ ገጽታ፣ ደካማነቱንና ዐላማው እንደታሰበው ዳር ሊደርስ አለማቻሉን ይገልጻል። ዳዊት በኀጢአቱ ተጸጽቶና ንስሓ ገብቶ (12፥13)፣ ልበ አምላክ መባሉን እንደ ያዘ ቢቆይም እንኳ በዚያው ሊቀጥል ባለመቻሉና ሳይታዘዝ በመቅረቱም ከተግሣጽና፣ ከቅጣት አላመ ለጠም (12፥10-12)። ከቤርሳቤህ ጋር የሠራው ኀጢአት (ም 11፥12)፣ የወንዶች ልጆቹ ጥፋት (13፥21፤ 14፥1፡33፤ 19፥4-6) አይቶ እንዳላየ፣ ዐውቆ እንዳላወቀ ሆኖ ሳይወቅሳቸው፣ ሳይገሥጻቸው መቅረቱ፣ የኢዮአብ ዐመፅ (3፥29፡39፤ 20፥10፡23)፣ በቤተ ሰቡና በአገሪቱ ውስጥ ሁከት፣ ብጥብጥና ደም መፋሰስን አስከትሎአል። የአቤሴሎም ዐመፅ አባቱ ከኢየሩሳሌም ሸሽቶ እንዲወጣ አድርጎታል፤ ይህም ሁሉ ሆኖ እግዚአብሔር ዳዊትን አልተወውም፤ ዘመነ መንግሥቱም ከእርሱ በኋላ ለተነሡት ነገሥታት ዘመነ መንግሥት የአስተዳድር መለኪያ፣ ማነጻጸሪያ ለመሆን በቅቶአል (2ነገ 18፥3፤ 22፥2 ይመ)።

መጽሐፉ የሚዘጋው ዳዊት ከጠላቶቹ ሁሉ ለታደገው አምላክ በሚያቀርበው ውዳሴና ምስጋና (መዝ 22፥31-51) እንዲሁም ከዳዊት ቤት ተነሥቶ "ሰዎችን በጽድቅ የሚገዛው" (23፥3-5) ንጉሥ የሚመጣበትን ጊዜ በተመለከተ የተሰጠውን ተስፋ ፍጻሜ ለማየት በጕጕት በሚጠባበቅ ቃል ነው። እነዚህ የዝማሬ ቃላት አብዛኛው የሐናን ዝማሬ ዐቢይ ሐሳብ የሚያንጸባርቁ ናቸው (1ሳሙ 2፥10)፤ ሁሉም መሠረታዊውን ታሪክ የሚያዋቅሩና የሚተረጕሙ ናቸው።

### የድርጊቱ ቅደም ተከተል

ከመጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛ መግቢያ "ቅደም ተከተል" የሚለውን ይመልከቱ።

**አስተዋፅኦ**

ከዚህ ቀጥሎ የመጽሐፈ ሳሙኤል ሁለተኛ አስተዋፅኦ ባጭሩ ቀርቦአል፤ ስለ አጠቃላዩ አስተዋፅኦ የመጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛን መግቢያ አስተዋፅኦ ይመልከቱ።

4. ዳዊት በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ፤ የሳኦል መንግሥት በተከታታይ ኀይሉና ብርታቱ እየቀነሰና እየደከመ ሄዶ በመጨረሻ ወደቀ (1ሳሙ 16፥1 – 2ሳሙ 5፥5)
   ሀ) ዳዊት ገና በእረኝነት ሳለ ተቀባ፤ ለንጉሥ ሳኦል ወታደርነት ዐደረ፤ ሕይወቱን ለማትረፍ ሸሸ (1ሳሙ 16-26)
   ለ) ዳዊት በፍልስጥኤም ምድር ጥገኛ ሆነ፤ ሳኦልና ወንዶች ልጆቹ በጦርነት ላይ ሞቱ (1ሳሙ 27-31)
   ሐ) ዳዊት በይሁዳ ላይ ነገሠ (2ሳሙ 1-4)
   መ) ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ (2ሳሙ 5፥1-5)
5. ዳዊት ያከናወናቸው ሥራዎችና ያገኘው ታላቅ ክብር (2ሳሙ 5፥6-9፡12)
   ሀ) ዳዊት ኢየሩሳሌምን ድል አድርጎ ያዛት፤ ፍልስጥኤማውያንንም አሸነፈ (2ሳሙ 5፥6-25)
   ለ) ዳዊት ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም አመጣ (2ሳሙ 6)
   ሐ) እግዚአብሔር ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ዘርዓ መንግሥት ለዳዊት እንደሚሰጠው ቃል ኪዳን ገባለት (2ሳሙ 7)
   መ) የዳዊት መንግሥቱ ሰፋለት፤ በውስጥ አስተዳደሩም ፍትሕ አሰፈነ (2ሳሙ 8)
   ሠ) ዳዊት ከዮናታን ጋር የገባውን ቃል ኪዳን እስከ መጨረሻው ጠበቀ (2ሳሙ 9)
6. የዳዊት ዘመነ መንግሥት ድክመትና ውድቀት
   ሀ) ዳዊት የዝሙት በደል ፈጸመ፤ ነፍስም አጠፋ (2ሳሙ 10-12)
   ለ) ዳዊት ልጆቹን አምኖንንና አቤሰሎምን በሞት አጣ (2ሳሙ 13-20)
7. የመጨረሻው የዳዊት ዘመነ መንግሥት ገጽታ (2ሳሙ 21-24)

## ዳዊት የሳኦልን ሞት ሰማ

1፥4-12 ተጓ ምብ - 1ሳሙ 31፥1-13፤ 1ዜና10፥1-12

1 ሳኦል ከሞተ በኋላ፣ ዳዊት አማሌቃው
ያንን ድል አድርጎ በመመለስ፣ በጺቅላግ
ሁለት ቀን ቈየ:: 2በሦስተኛውም ቀን የተቀ
ደደ ልብስ የለበሰ፣ በራሱም ላይ ትቢያ የነሰነሰ
አንድ ሰው ከሳኦል ሰፈር መጣ:: ወደ ዳዊት
እንደደረሰም፣ ወደ መሬት ለጥ ብሎ በአክብ
ሮት እጅ ነሣ::
3ዳዊትም፣ "ከወዴት መጣህ?" ሲል ጠየ
ቀው::
እርሱም፣ "ከእስራኤላውያን ሰፈር ሸሽቼ
መምጣቴ ነው" በማለት መለሰለት::
4ዳዊትም፣ "ምን ነገር ተፈጠረ?" ሲል ጠየ
ቀው::
እርሱም "ሰዎቹ ከጦርነቱ ሸሽተዋል፤ ብዙ
ዎቹ ወድቀዋል፤ ሞተዋል፤ ሳኦልና ልጁ ዮና
ታንም ሞተዋል" አለ::
5ከዚያም ዳዊት ወሬውን የነገረውን ወጣት፣
"ሳኦልና ልጁ ዮናታን መሞታቸውን እንዴት
አወቅህ?" ሲል ጠየቀው::
6ወሬ ነጋሪው ወጣትም እንዲህ አለ፤ "ድን
ገት ወደ ጊልቦዓ ተራራ ወጥቼ ነበር፤ እዚያም
ሳኦል ጦሩን ተደግፎ ሳለ፣ ሠረገሎችና ፈረሰ
ኞች ተከታትለው ደረሱበት፤ 7ወደ ኋላውም
ዞር ሲል እኔን ስላየ ጠራኝ፤ እኔም፣ 'ምን
ልታዘዝ' አልሁ::
8"እርሱም፣ 'አንተ ማን ነህ?' ሲል ጠየቀኝ፤
"እኔም 'አማሌቃዊ ነኝ' ብዬ መለስሁለት::
9"ከዚያም፣ 'እኔ በሞት ጣር ውስጥ እገኛለሁ፤
ነፍሴ ግን አልወጣችም፤ እባክህ በላዬ ቆመህ
ግደለኝ' አለኝ::
10"መቼም ከወደቀ በኋላ እንደማይተርፍ
ስላወቅሁ፣ በላዩ ቆሜ ገደልሁት፤ በራሱ ላይ
የነበረውን ዘውድና የክንዱን አንባር ወስጄ
እነሆ፤ ለጌታዬ አምጥቻለሁ::"
11ከዚያም ዳዊትና አብረውት የነበሩት ሰዎች
ሁሉ ልብሳቸውን ቀደዱ:: 12ለሳኦልና ለልጁ
ለዮናታን፣ ለእግዚአብሔር ሰራዊትና ለእስራ
ኤል ቤት አዘኑ፤ አለቀሱ፤ እስከ ማታም ድረስ
ጾሙ፤ የወደቁት በሰይፍ ነበርና::
13ዳዊትም ወሬውን ያመጣለትን ወጣት፣
"ከየት ነው የመጣኸው?" ብሎ ጠየቀው::
እርሱም፣ "እኔ የአንድ መጻተኛ አማሌቃዊ
ልጅ ነኝ" ብሎ መለሰ::
14ዳዊትም፣ "ታዲያ እግዚአብሔር የቀባውን
ለማጥፋት እጅህን ስታነሣ እንዴት አልፈራ
ህም?" ሲል ጠየቀው::
15ዳዊትም ከጕልማሶቹ አንዱን ጠርቶ፣
"በል ቀረብና ውደቅበት" አለው:: እርሱም
መታው፤ ሞተም:: 16ዳዊትም፣ "እግዚአ
ብሔር የቀባውን ገድያለሁ' ስትል የገዛ
አፍህ መስክሮብሃልና፣ ደምህ በራስህ ላይ
ይሁን" አለው::

## ዳዊት ለሳኦልና ለዮናታን የተቀኘው የሐዘን እንጕርጕሮ

17ዳዊትም በሳኦልና በልጁ በዮናታን ሞት
ምክንያት ይህን የሐዘን እንጕርጕሮ እየተ
ቀኘ አለቀሰ፤ 18እንዲሁም የቀስት እን
ጕርጕሮ የተባለውን ለይሁዳ ሕዝብ እንዲ
ያስተምሩ አዘዘ፤ ይህም በያሻር መጽሐፍ
ተጽፎአል::

19"እስራኤል ሆይ፤ ክብርህ በኰረብቶችህ
ላይ ተወግቶ ሞቶአል፤
ኃያላኑ እንዴት እንደዚህ ይውደቁ!

1፥1 ዘፍ14፥7፤ዘኍ13፥29፤ኢሱ22፥8፤1ሳሙ26፥10፤30፥17፤1ዜና10፥13
1፥2 ዘፍ37፥7፤1ሳሙ4፥12፤20፥41፤2ሳሙ4፥10፤ኢዮ2፥12፤ሕዝ27፥30
1፥6 ቊ21፤1ሳሙ28፥4
1፥8 ቊ13፤1ሳሙ15፥2፤27፥8፤30፥13፥17
1፥9 መሳ9፥54
1፥10 2ነገ11፥12
1፥11 ዘፍ37፥29፤ዘኍ14፥6
1፥13 ቊ8፤1ሳሙ14፥48
1፥14 1ሳሙ12፥3፤26፥9
1፥15 2ሳሙ4፥10፡12
1፥16 ዘሌ20፥9፤ማቴ27፥24-25፤ሐሥ18፥6
1፥17 ቊ26፤ዘፍ50፥10፤ሕዝ32፥2
1፥18 ኢሱ10፥13
1፥19 2ሳሙ3፥38፤23፥8፤መዝ29፥11፥45፥3

1፥1 *ከሞተ በኋላ፤* ኢሱ 1፥1፤ መሳ 1፥1 ይመ:: የመጽሐፈ ሳሙኤል አንደኛ ትረካ በዚህ መጽሐፍም ላይ ይቀጥላል፤ ሁለቱ መጻሕፍት መጀመሪያ በአንድ መጽሐፍ ተጠቃልለው ነበር (በመጀመሪያ የሳሙኤል መጽሐፍ የመጽሐፉ አሰያየም የሚለውን ይመ):: *ዳዊት አማሌቃውያንን ድል አድርጎ በመመለስ፤* 1ሳሙ 30፥26 ይመ:: *በጺቅላግ፤* የ1ሳሙ 27፥6 ማብ ይመ::

1፥2 *የተቀደደ ልብስ የለበሰ፣ በራሱም ላይ ትቢያ፤* የ1ሳሙ 4፥12 ማብ ይመ:: በተጨማሪም ኢሱ 7፥6፤ ሐሥ 14፥14 ይመ::

1፥8 *አማሌቃዊ፤* በቍ 3 ላይ ያለውን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ይህኛው አማሌቃዊ፣ የሳኦል ሰራዊት አባል ነው ብሎ መደምደም ተገቢ አይደለም:: ይህ ሰው፣ "ወደ ጊልቦዓ ተራራ ወጥቼ ነበር" (ቍ 6) በማለት የተናገረው እውነት ይምሰል እንጂ፣ ትክክል ላይሆን ይችላል:: ምናልባት በውጊያ ላይ የወደቁትን ወታደሮች ንብረትና የጦር መሣሪያ ለመዝረፍ በማሰብ በዚያ ስፍራ ተገኝቶ ሊሆን ይችላል:: የሳኦል መሞት በአንድ አማሌቃዊ እንደበት መነገሩ እንደ ምፀት የሚቈጠር ነው (1ሳሙ 15 ይመ)::

1፥10 *በላዩ ቆሜ ገደልሁት፤* አማሌቃዊው የተናገረው ሐሳብ በ1ሳሙ 31፥3-6 ላይ ሳኦል ራሱን እንደ ገደለ ከሚገልጸው ታሪክ ጋር ይቃረናል:: አማሌቃዊው ስለ ሳኦል አሟሟት የፈጠራ ወሬ ያወራው ዳዊት እንደሚሸልመው በማሰብ ነበር:: አማሌቃዊው የዳዊትን መልስ በትክክል ማወቅ ባለመቻሉ ሕይወቱን ለሞት ዳረገ (ቍ 15 ይመ):: *ዘውድና... አምጥቻለሁ፤* ፍልስጥኤማውያን ሳኦል በወደቀበት ቦታ ከመድረሳቸው በፊት አማሌቃዊው ደርሶ ነበር ማለት ነው (1ሳሙ 31፥8-9 ይመ)::

1፥11 *ልብሳቸውን ቀደዱ፤* የ1ሳሙ 4፥12 ማብ ይመ::

1፥12 *አዘኑ፤ አለቀሱ፤* ዳዊትና ተከታዮቹ ሐዘናቸውን የገለጹት በተለመደው የመካከለኛው ምሥራቅ የሐዘን አገላለጽ መሠረት ነው (ዘፍ 23፥2፤ 1ነገ 13፥30፤ ኤር 22፥18 ይመ):: *ጾሙ፤* 3፥35፤ 1ሳሙ 31፥13 ይመ::

1፥13 *አማሌቃዊ፤* ምናልባት ዳዊት በቅርብ ጊዜ ከአማሌቃውያን ጋር መጋጨቱን ይህ ሰው አላወቀ ይሆናል (ቍ 1፤ 1ሳሙ 30 እና የ1ሳሙ 15፥2 ማብ ይመ)::

*1፥14፤* ዳዊት፣ "እግዚአብሔር የቀባው ሰው የከበረ ነው" በማለት የተናገረው እውነት ቢሆንም፣ አማሌቃዊው ግን ስለዚህ ጥልቅ ሐሳብ ምንም ነገር ላይገነዘብ ይችላል (የ1ሳሙ 24፥6 ማብ ይመ):: *እግዚአብሔር የቀባውን፤* የ1ሳሙ 9፥16 ማብ ይመ::

1፥15 *ውደቅበት፤* ዳዊት የሳኦልን ሞት በደስታ ስላልተቀበለው፣ የሳኦል ገዳይ ነው ብሎ ባመነበት አማሌቃዊ ላይ የሞት ፍርድ ፈረደበት (የቍ 10 ማብ፤ እንዲሁም 4፥10 ይመ)::

1፥16 *ደምህ በራስህ ላይ ይሁን፤* አማሌቃዊው ራሱ በሰጠው ምስክርነት በራሱ ላይ ሞት አመጣ (ኢሱ 2፥19፤ 1ነገ 2፥37 ይመ)::

1፥17 *እንጕርጕሮ፤* በጥንታዊው የመካከለኛው ምሥራቅ የአገር መሪዎች ወይም የጦር ሜዳ ጀግኖች ሲሞቱ የሙሾ ግጥም መደርደር የተለመደ ነበር::

1፥18 *የቀስት እንጕርጕሮ፤* ከዚህ ቀደም የደረሰባቸው ተመሳሳይ ሽንፈት እንዳይደገም (የሕዝ 21፥9 ማብ ይመ) በሚለማመዱበት ጊዜ በቀስት አወራወር አስተማማኝ ዕውቀት ይኖራቸው ዘንድ፣ ለመቀስቀሻነት እንዲያንጐራጕሩት ዳዊት ለሕዝቡ ሳያስተምራቸው አልቀረም:: *በያሻር መጽሐፍ፤* የኢሱ 10፥13 ማብ ይመ::

1፥19 *ክብርህ፤* የእግዚአብሔርን የኪዳን ሕዝብ እንዲመሩ በአምላካዊ ሥልጣን የተሾሙትን ሳኦልንና ዮናታንን የሚመለከት ነው፤ እነዚህ መሪዎች በእስራኤል ጠላቶች ላይ ወሳኝ ድሎችን ተጐናጽፈዋል (1ሳሙ 14፥47-48 እና ማብ ይመ):: *በኰረብቶችህ፤* የጊልቦዓን ተራራ የሚመለከት ነው (ቍ 21፥25፤ 1ሳሙ 31፥1 ይመ):: *ኃያላኑ እንዴት እንደዚህ ይውደቁ፤* የዳዊት እን

20“ይህን በጌት አትናገሩ፤
በአስቀሎናም መንገዶች አታውጁት፤
የፍልስጥኤም ቈነጃጅት አይደሰቱ፤
ያልተገረዙት ሴቶች ልጆች እልል አይበሉ።
21“እናንተ የጊልቦዓ ተራሮች ሆይ፤
ጠል አያረስርሳችሁ፤
ዝናብም አይውረድባችሁ፤
የቍርባን እህል የሚያበቅሉም ዕርሻዎች
አይኑራቸው፤
በዚያ የኀያሉ ሰው ጋሻ ረክሶአልና፤
የሳኦል ጋሻ ከእንግዲህ በዘይት
አይወለወልም።
22ከሞቱት ሰዎች ደም፣
ከኀያላኑም ሥብ፣
የዮናታን ቀስት ተመልሳ አልመጣችም፤
የሳኦልም ሰይፍ በከንቱ አልተመለሰችም።
23“ሳኦልና ዮናታን በሕይወት እያሉ፣
የሚዋደዱና የሚስማሙ ነበሩ፤
ሲሞቱም አልተለያዩም፤
ከንስርም ይልቅ ፈጣኖች፣
ከአንበሳም ይልቅ ብርቱዎች ነበሩ።
24“እናንት የእስራኤል ቈነጃጅት ሆይ፤
ሐምራዊ ቀሚስና ቀጭን ፈትል ላለበሳችሁ፣
ልብሶቻችሁንም በወርቅ ዘቦ ላስጌጠላችሁ፣
ለሳኦል አልቅሱለት።
25“ኀያላን እንዴት እንዲህ በጦርነት ወደቁ!
ዮናታን በኰረብቶችህ ላይ ተወግቶ ሞቶአል።
26ወንድሜ ዮናታን ሆይ፤ እኔ ስለ አንተ
አዘንሁ፤
አንተ ለእኔ እጅግ ውድ ነበርህ፤
ፍቅርህ ለእኔ ድንቅ ነበረ፤
ከሴት ፍቅርም ይልቅ ግሩም ነበር።
27“ኀያላኑ እንዴት ወደቁ!
የጦር መሣሪያዎቹስ እንዴት ከንቱ ይሁኑ!”

## ዳዊት የይሁዳ ንጉሥ ሆነ

2 ከዚህ በኋላ ዳዊት፣ “ከይሁዳ ከተሞች ወደ
አንዲቱ ልውጣን?” ብሎ እግዚአብሔርን
ጠየቀ።
እግዚአብሔርም፣ “አዎን ውጣ” አለው።
ዳዊትም፣ “ወደ የትኛዪቱ ልሂድ?” ሲል
ጠየቀ።
እግዚአብሔርም፣ “ወደ ኬብሮን” ብሎ መለሰ
ለት።
2ስለዚህ ዳዊት ከሁለቱ ሚስቶቹ ከኢይዝ
ራኤላዊቷ ከአኪናሆምና የቀርሜሎሳዊው
የናባል ሚስት ከነበረችው ከአቢግያ ጋር ወደ
ዚያ ወጣ። 3እንዲሁም ዳዊት አብረውት የነ
በሩትን ሰዎች ከነቤተ ሰቦቻቸው አመጣ
ቸው፤ እነርሱም በኬብሮን ከተሞች ተቀ
መጡ። 4የይሁዳም ሰዎች ወደ ኬብሮን
መጡ፤ በዚያም ዳዊትን ቀብተው በይሁዳ
ቤት ላይ አነገሡት።
ሳኦልን የቀበሩት የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች
መሆናቸውን ለዳዊት በነገሩት ጊዜ፣ 5እር
ሱም የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ይህን እንዲ
ነግሩ መልእክተኞች ላከ፤ “በእንዲህ ዐይነት
ሁኔታ ጌታችሁን ሳኦልን በመቅበር በጎነት
አሳይታችኋልና እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤
6አሁንም እግዚአብሔር ጽኑ ፍቅሩንና ታማኝነ
ቱን ይግለጥላችሁ፤ እናንተ ይህን ስላደረጋ
ችሁ፣ እኔም እንደዚሁ በጎ ነገር አደርግላች
ኋለሁ፤ 7እንግዲህ ጠንክሩ፤ በርቱ ጌታችሁ
ሳኦል ሞቶአልና፤ የይሁዳ ቤትም እኔን
ቀብተው በላያቸው አንግሠውኛል።”

1፥20 ኢሱ13፥3፤ 1ሳሙ18፥6፤31፥8፤ ሚክ1፥10
1፥21 ቊ6፤ዘፍ 27፥28፤ዘዳ11፥17፤ 1ነገ18፥35፤17፥1፤ 18፥1፤2ዜና6፥26፤ ኢዮ36፥27፤38፥28፤ መዝ65፥10፤147፥8፤ ኢሳ5፥6፤18፥4፤ 21፥5፤ኤር5፥24፤ 12፥4፤14፥4፤ሕዝ 31፥15፤አሞ1፥12
1፥22 ዘዳ32፥42፤ ኢሳ34፥3፡7፤49፥26
1፥23 ዘዳ28፥49፤ መሳ14፥18
1፥24 መሳ5፥30
1፥26 ቊ17፤1ሳሙ 18፥1፤20፥42፤ ኤር22፥18፤34፥5
1፥27 1ሳሙ2፥4
2፥1 ዘፍ13፥18፤ 23፥19፤1ሳሙ23፥2፡ 11-12
2፥2 1ሳሙ25፥42 ፡43
2፥3 ዘፍ13፥18፤ 23፥2፤37፥14፤1ሳሙ 27፥2፤1ዜና12፥22
2፥4 መሳ21፥8፤ 1ሳሙ2፥35፤11፥1፤ 30፥31፤2ሳሙ5፥3-5፤ 1ዜና12፥23-40
2፥5 መሳ17፥2፤ 1ሳሙ23፥21፤ 2ጢሞ1፥16
2፥6 ዘፀ34፥6
2፥7 ኢሱ1፥6፤ መሳ5፥21

ጕርጕሮ ዋና ሐሳብ ነው (ቍ 27 ይመ)። በዳዊት አባባል ውስጥ የሳኦልንና የዮናታንን ጠንካራ ጐንና መልካም ተግባሮቻቸውን ከማ ውሣት ውጭ የቂመኝነት ሐሳብ አልነበረበትም።

1፥20 *በጌት አትናገሩ፤ በአስቀሎናም፤* ከእስራኤል ድንበ ሮች እጅግ የሚቀርቡትንና የሚርቁትን የሚያሳዩት ጌትና አስ ቀሎና የፍልስጥኤም ዋና ከተማዎች እንደ መሆናቸው፣ የፍልስ ጥኤምን ሕዝብ ሁሉ የሚወክሉ ናቸው። ዳዊት የእግዚአብሔር የኪዳኑ ሕዝብ ጠላቶች በእስራኤል መሸነፍ እንዲደሰቱና (1ሳሙ 31፥9-10 ይመ) የጌታም ስም በክፉ እንዲነሣ አልፈለገም (ዘፀ 32፥12፤ ዘኍ 14፥13-19፤ ዘዳ 9፥28፤ ኢሱ 7፥9፤ ሚክ 1፥10 ይመ)። *ያልተገረዙ፤* የ1ሳሙ 14፥6 ማብ ይመ።

1፥21 *እናንተ የጊልቦዓ ተራሮች፤* ዳዊት እጅግ ከማዘኑ የተነሣ፣ የእስራኤል ሕዝብ የተሸነፈበትን ሳኦልና ዮናታን የወደቁበትን ምድር አምርሮ ይረግማል (ኢዮ 3፥3-26፤ ኤር 20፥14-18 ይመ)። *ከእንግዲህ በዘይት አይወለወልም፤* የቈዳ ጋሻ ጥንካሬውን እንደ ያዘ ለብዙ ጊዜ ይቈይ ዘንድ ይወለወል ነበር (የኢሳ 21፥5 ማብ ይመ)።

1፥23 *ሲሞቱም አልተለያዩም፤* ዮናታን አባቱ በዳዊት ላይ ያሳየውን ጥላቻና ያደረሰውን በደል ቢቃወምም እንኳ፣ ለእስራኤል ደኅንነት ሲል ከአባቱ ጐን ጦር ሜዳ በመሰለፍ ሕይወቱን ሰጠ።

1፥26 *ከሴት ፍቅርም ይልቅ፤* ዳዊት ከሚስት ፍቅር ይልቅ የጓደኛ ፍቅር ይበልጣል ማለቱ አይደለም፤ ዐረፍተ ነገሩ ዮናታን በአባቱ ምትክ እንዲነግሥ እግዚአብሔር የመረጠው እርሱን ሳይ ሆን ዳዊትን መሆኑን ገና ከመጀመሪያው ያወቀ ቢሆንም ለዳዊት ያለውን ታማኝነት እስከ መጨረሻው መጠበቁን የሚያሳይ ነው (የ1ሳሙ 20፥13-16 ማብ ይመ)።

1፥27 *የጦር መሣሪያዎቹስ፤* ምናልባት ሳኦልንና ዮናታንን የሚያሳይ ዘይቤያዊ አገላለጽ ሳይሆን አይቀርም።

2፥1 *ዳዊት... እግዚአብሔርን ጠየቀ፤* የጠየቀው በሊቀ ካህኑ በአብያታር አማካይነት በኤፉድ ነው (የዘፀ 28፥30፤ 1ሳሙ 2፥28፤ 23፥2 ማብ ይመ)። *ከይሁዳ ከተሞች ወደ አንዲቱ፤* ምንም እንኳ ሳኦል ቢሞትና ዳዊትም ከራሱ ነገድ ውስጥ አብዛኞቹ ወዳጆቹና ከእርሱ ጋር ቅርበት የነበራቸው ሆነው ቢያገኛቸውም (1ሳሙ 30፥26-31)፣ ቃል በተገባለት ዙፋን ላይ ለመቀመጥ የጌታን ምሪት ሳይጠይቅ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ምድር ለመመለስ አልደፈረም። *ኬብሮን፤* ጥንታዊትና የታወቀች ከተማ ናት (ዘፍ 13፥18፤ 23፥2፤ ኢሱ 15፥13-15፤ የ1ሳሙ 30፥3 ማብ ይመ)፤ ይህች ከተማ በይሁዳ ነገድ ክልል ውስጥ የምትገኝ ነበረች።

2፥2 *ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪናሆም፤* የ1ሳሙ 25፥43 ማብ ይመ። *ከአቢግያ፤* 1ሳሙ 25 ይመ።

2፥3 *አብረውት የነበሩትን ሰዎች፤* 1ሳሙ 22፥2፤ 23፥13፤ 30፥3፡9 ይመ።

2፥4 *ዳዊትን ቀብተው፤* የ1ሳሙ 2፥10፤ 9፥16 ማብ ይመ። ከዚህ በፊት ዳዊት ቤተ ሰቡ ባለበት በሳሙኤል ተቀብቶ ነበር (የ1ሳሙ 16፥13 ማብ ይመ)። ለሁለተኛ ጊዜ መቀባቱ ንጉሥ እንዲሆን በእግዚአብሔር የተመረጠ ለመሆኑ በራሱ ነገድ ይፋ ዕውቅና እንዲያገኝ ነው። *በይሁዳ ቤት ላይ፤* የስምዖን ነገድም በዚህ ተግባር ሳይሳተፍ አልቀረም (ኢሱ 19፥1፤ መሳ 1፥3 ይመ)፤ ይሁን እንጂ የይሁዳ ቤት በማንኛውም መንገድ ቍልፍ የሆነውን የሥራ ድርሻ ሲቈጣጠር ይታያል። *ሳኦልን የቀበሩት፤* የ1ሳሙ 31፥13 ማብ ይመ። *የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች፤* የ1ሳሙ 11፥1፤ 31፥12 ማብ ይመ።

2፥7 *ጌታችሁ... ሞቶአልና፤ የይሁዳ ቤትም እኔን ቀብ ተው በላያቸው አንግሠውኛል፤* ለኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ዳዊት ያቀረበው የመጨረሻ ሐሳብ የይሁዳ ቤት እንዳደረገው ሁሉ፣ የኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ንጉሥነቱን እንዲቀበሉት የሚያደርግ የተሸፋፈነ ጥሪ ነው። ሆኖም ድጋፋቸውን ለማግኘት ሲባል የቀረበው ጥሪ ተቀባይነት አላገኘም (1ሳሙ 2፥8-9 ይመ)።

## በዳዊት ቤትና በሳኦል ቤት መካከል የተደረገ ጦርነት

3፥2-5 ተጓ ምብ - 1ዜና 3፥1-4

8በዚህ ጊዜ የሳኦል ሰራዊት አዛዥ የኔር
ልጅ አበኔር፣ የሳኦልን ልጅ ኢያቡስቴን ወስዶ
ወደ መሃናይም አሻገረው፤ 9እርሱንም በገለዓድ፣
በአሴር፣ በኢይዝራኤል፣ በኤፍሬምና በብንያም
እንዲሁም በእስራኤል ሁሉ ላይ አነገሠው።
10የሳኦል ልጅ ኢያቡስቴ በእስራኤል ላይ
በነገሠ ጊዜ ዕድሜው አርባ ዓመት ነበረ፤
ሁለት ዓመትም ገዛ። የይሁዳ ቤት ግን
ዳዊትን ተከተለ። 11ዳዊት በኬብሮን ንጉሥ
ሆኖ እስራኤልን የገዛው ሰባት ዓመት ከስድ
ስት ወር ነበረ።
12የኔር ልጅ አበኔር፣ ከሳኦል ልጅ ከኢያ
ቡስቴ አገልጋዮች ጋር ሆኖ ከመሃናይም ተነ
ሥተው ወደ ገባዖን ሄዱ። 13እነርሱንም የጽሩያ
ልጅ ኢዮአብና የዳዊት ሰዎች ወጥተው በገ
ባዖን ኵሬ አጠገብ ተገናኟቸው፤ አንዱ ወገን
በኵሬው ወዲህ ማዶ፣ ሌላው ወገን ደግሞ
በኵሬው ወዲያ ማዶ ተቀመጠ።
14ከዚያም አበኔር፣ ኢዮአብን፣ "ከእናንተም
ከእኛም ጐልማሶች ይነሡና በፊታችን በጨበጣ
ውጊያ ይጋጠሙ" አለው።
ኢዮአብም፣ "ይሁን እሺ ይጋጠሙ" ብሎ
መለሰ።
15ስለዚህ ከብንያም ለሳኦል ልጅ ለኢያቡ
ስቴ ዐሥራ ሁለት፣ ለዳዊት ደግሞ ዐሥራ
ሁለት ሰዎች ተነሥተው ተቈጠሩ። 16ከዚያም
እያንዳንዱ ሰው የባላጋራውን ራስ በመያዝ
ሰይፉን በጐኑ እየሻጠበት ተያይዘው ወደቁ።
ስለዚህም በገባዖን የሚገኘው ያ ቦታ "የሰይፍ
ምድር"[ሀ] ተባለ።
17የዚያን ዕለቱ ጦርነት እጅግ ከባድ ነበር፤
አበኔርና የእስራኤል ሰዎች በዳዊት ሰዎች
ድል ሆኑ።
18ሦስቱ የጽሩያ ወንዶች ልጆች ኢዮአብ፣
አቢሳና አሣሄል እዚያው ነበሩ። አሣሄል
እንደ ዱር ሚዳቋ በሩጫ ፈጣን ነበረ፤ 19ወደ
ቀኝ ወይም ወደ ግራ ሳይል አበኔርን ተከ
ታተለው። 20አበኔርም ወደ ኋላው ዞወር ብሎ
በመመልከት፣ "አሣሄል! አንተ ነህ?" ሲል
ጠየቀው።
እርሱም፣ "አዎን እኔ ነኝ" ብሎ መለሰለት።
21ከዚያም አበኔር፣ "ወደ ቀኝህ ወይም ወደ
ግራህ ዘወር በልና አንዱን ጐልማሳ ይዘህ
መሣሪያውን ንጠቀው" አለው። አሣሄል ግን
እርሱን መከታተሉን አልተወም ነበር።
22እንደ ገናም አበኔር፣ "እኔን መከታተል
ብትተው ይሻልሃል፤ እኔስ ለምን ከመሬት ጋር
ላጣብቅህ? ከዚያስ የወንድምህን የኢዮአብን ፊት
ቀና ብዬ እንዴት አያለሁ?" አለው።
23አሣሄል ግን መከታተሉን አልተወም፤
ስለዚህ አበኔር በጦሩ ጫፍ ሆዱን ወጋው፣
ጦሩም በጀርባው ዘልቆ ወጣ፤ አሣሄልም

2፥8 ዘፍ32፥2፤ 1ሳሙ14፥50፤2ሳሙ3፥27፤4፥5፤1ዜና8፥33 19፥39
2፥9 ዘኍ32፥26፤ ኢሱ19፥24-31፤ 1ዜና12፥29
2፥11 2ሳሙ5፥5
2፥12 ኢሱ9፥3
2፥13 2ሳሙ8፥16፤ 19፥13፤1ነገ1፥17፤ 1ዜና2፥16፤11፥6፤ 27፥34
2፥16 መሳ3፥21
2፥17 1ሳሙ17፥8፤ 2ሳሙ3፥1
2፥18 1ሳሙ26፥6፤ 2ሳሙ3፥30:39፤10፥7 ፤11፥1፤14፥1፤16፥10፤ 18፥14፤19፥22፤ 20፥8፤23፥24፤ 24፥3፤1ነገ1፥7፤ 2፥5:34፤1ዜና2፥16፤ 11፥26፤12፥8፤27፥7፤ ምሳ6፥5፤ማሕ2፥9
2፥22 2ሳሙ3፥27
2፥23 2ሳሙ3፥27፤ 4፥6፤20፥12

ሀ16 ዕብራይስጡ፣ *ሔልቃዝ ሀዙሪም* ይባላል፤ ትርጕሙም፣ *የመቃቃሚ ምድር ወይም የጠላፉ ምድር* ማለት ነው።

2፥8 *የኔር ልጅ አበኔር፤* 1ሳሙ 14፥50 ይመ። *የሳኦል ሰራዊት፤* ለእርሱና ለቤተ ሰቡ እስከ መጨረሻው በታማኝነት የቆመ አነስተኛ ቍጥር ያለው ቋሚ ሰራዊት ነው (1ሳሙ 13፥2:15፤ 14፥2:52 ይመ)። *ኢያቡስቴም፤* በመጀመሪያ እስባኦል ተብሎ ይጠራ ነበር (1ዜና 8፥33) ፤ የመጽሐፈ ሳሙኤል ጸሓፊ ግን ኢያቡስቴ ብሎ ጠራው፤ ትርጕሙም "አሳፋሪ" ማለት ነው (የ4፥4 ማብ ይመ)። "በኣል" የተባለው ቃል እስከዚህ ጊዜ ድረስ ጥቅም ላይ የዋለው "ገዥ" ወይም "ሹም" በሚለው ትርጕም ጌታን ለማሳየት ነበር። በኋላ ግን የከነዓናውያን አምላክ ከነበረው ከበኣል ጋር በመያያዙ ውዝግብር ስላስከተለ፣ ጌታን በዚህ ስም መጥራት ቀረ፤ ጸሓፊውም በዚያ ጊዜ የነበረውን ስሜት በማስተዋል ገልጦታል። *የሳኦልን ልጅ፤* የ1ሳሙ 14፥49፤ 31፥2 ማብ ይመ። *አሻገረው፤* በሳኦል ሞት ምክንያት የሥልጣን ክፍተት ተፈጥሮ ስለ ነበር፣ አበኔር ለራሱ የሥልጣን ፍላጎት ሲል ኢያቡስቴን መሣሪያ በማድረግ፣ በተፈጠረው ሁኔታ ለመጠቀም ርምጃ ወሰደ (3፥11 የ4፥1 ማብ ይመ)። ኢያቡስቴ በእስራኤላውያን ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ እንደ ነበረው የሚገልጽ ማረጋገጫ የለም፤ *መሃናይም፤* ከፍልስጥኤም ግዛት ውጭ ሆና ከዮርዳኖስ ማዶ የምትገኝ የገለዓድ ከተማ ናት።

2፥9 *አነገሠው፤* አበኔር የሳኦል የወንድም ልጅ በመሆኑ (የ1ሳሙ 14፥50 ማብ ይመ)፣ የሳኦል ሥልጣን ከቤተ ሰቡ ሳይወጣ እንዲቀጥል ይፈልጋል። ፍላጎቱም ካለው የዝር ግንኙነት ጋር ብቻ ሳይሆን፣ ከግል ጥቅምም ጋር የተያያዘ ነበር። *በገለዓድ... በእስራኤል ሁሉ ላይ፤* የኢያቡስቴ ግዛት በዚህ መልክ መገለጡ፣ ትክክለኛ ግዛቱ ምሥራቃዊውንና ምዕራባዊውን ዮርዳኖስ የሚጨምር ቢሆንም እንኳ፣ እጅግ የተወሰነ ግዛት እንደ ነበረ ያሳያል፤ "በእስራኤል ሁሉ ላይ" የሚለውም ምኞትን እንጂ ትክክለኛ የሆነውን ግዛት አያመለክትም። ዳዊት የስምዖንና የይሁዳን ምድር አስተዳድሮአል፤ ፍልስጥኤማውያንም አብዛኛው ሰሜናዊውን የነገዶች ምድር ተቈጣጥረውት ነበር።

2፥11 *ሰባት ዓመት ከስድስት ወር፤* ኢያቡስቴ በመሃናይም የነበረውን የሁለት ዓመት አገዛዝ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ቍ 10)። ኢያቡስቴ እንደ ሞተ ወዲያውኑ ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ስለ ነገሠ (5፥1-5)፣ ብዙ ሳይቈይም መናገሻ ከተማውን ወደ ኢየሩሳሌም አዛውሮ ስለ ነበር (5፥6-21)፣ የዳዊትንና የኢያቡስቴን የግዛት ዘመን ምን ያህል እንደ ሆነ በትክክል ለይቶ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው። ይህ ችግር በአግባቡ መፍትሔ ማግኘት የሚችለውም ኢያቡስቴ የአባቱ ተተኪ መሆኑ እስኪታወቅ ድረስ የተወሰኑ ዓመታት ማለፋቸውንና፣ ሁለቱ የአገዛዝ ዓመታትም ዳዊት በኬብሮን ከነበሩት የመጨረሻዎቹ ሁለት ወይም ሦስት ዓመታት ጋር በመጠኑ የሚስማሙ መሆናቸውን በመቀበል ነው።

2፥12፤ የዳዊት ግዛት ከይሁዳ ወደ ሰሜን እንዳይስፋፋ ለመገደብ አበኔር ቀድሞ እርምጃ ወሰደ። ገባኦን ቤተ ሰቡ የነበሩ ባት በብንያም ነገድ ምድር የምትገኝና በፍልስጥኤማውያን እጅ ያልወደቀች ከተማ ናት።

2፥13 *የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ፤* የ1ሳሙ 26፥6 ማብ ይመ። ኢዮአብ በዳዊት ዘመነ መንግሥት ከፍተኛ ኀላፊነት የነበረው ታላቅ ሰው ቢሆንም እጅግ ጨካኝ የጦር አዛዥ ነበር (10፥7-14፤ 11፥1፤ 12፥26፤ 1ነገ 11፥15-16 ይመ)። ንጉሥ ዳዊት እንኳ እርሱን ለመቈጣጠር ያልቻለበት ጊዜ ነበር (3፥39፤ 18፥5:14፤ 1ነገ 2፥5-6)፤ በመጨረሻም ገደብ ባልነበረው ጭካኔውና በዳዊት ዙፋን ላይ ሰሎሞንን በማንገሥ ፈንታ አዶንያስን ለማንገሥ ባውጠነጠነው ሤራ የሞት ፍርድ ተፈርዶበታል (1ነገ 2፥28-34)። *የዳዊት ሰዎች፤* በዳዊት ዙሪያ የነበሩ በሞያቸው የተካኑ ጥቂት ጦረኞች ነበሩ (1ሳሙ 2፥1-2፤ 23፥13፤ 27፥2፤ 30፥9 ይመ)።

2፥15 *ከብንያም፤* በዚህ ጊዜ ኢያቡስቴ አብዛኛውን ድጋፍ ያገኘው ከራሱ ነገድ ነበር።

2፥17 *የዚያን ዕለቱ ጦርነት እጅግ ከባድ ነበር፤* ከግራ ቀኙ ወገን ዐሥራ ሁለት ዐሥራ ሁለት ወታደር ተመርጦ የተካሄደው ፍልሚያ (የ1ሳሙ 17፥4 ማብ ይመ) የታሰበውን ውጤት ማምጣት ስላልቻለ በሁለቱ ወገን ጦርነት ተካሄደ፤ የዳዊት ሰራዊት የድሉ ባለቤት ሆነ (3፥1 ይመ)።

2፥21 *አበኔር... ዘወር በልና፤* አሣሄል እንዳይገደል አበኔር ጥረት አድርጎ ነበር፤ ሆኖም ግን ጥረቱ ሳይሳካ ቀረ።

2፥22 *የወንድምህን የኢዮአብን ፊት ቀና ብዬ እንዴት አያለሁ?* አበኔር ደም የመበቀልን ልማድ ተግባራዊ በማድረግ በእርሱና በኢዮአብ መካከል የነበረው ጠብ እየከረረ እንዲሄድ አልፈለገም ነበር (የ2፥27 ማብ ይመ)።

እዚያው ወደቀ፤ ወዲያው ሞተ። እያንዳንዱም ሰው አሣሄል ወድቆ ወደ ሞተበት
ስፍራ ሲደርስ ይቆም ነበር።
24ኢዮአብና አቢሳ ግን አበኔርን ተከታተሉት፤
እየሳደዱም ወደ ገባዖን ምድረ በዳ በሚወስደው
መንገድ ከጋይ አጠገብ ወዳለው ወደ አማ ኮረ
ብታ ሲደርሱ ፀሓይ ጠለቀች። 25ከዚያም የብን
ያም ሰዎች ወደ አበኔር ተሰብስበው ግንባር
በመፍጠር በኮረብታው ጫፍ ላይ ተሰለፉ።
26አበኔር ኢዮአብን ጠርቶ፣ "ይህ ሰይፍ
ዘላለም ማጥፋት አለበትን? ውጤቱ መራራ
መሆኑን አንተስ ሳታውቀው ቀርተህ ነውን?
ሰዎችህ ወንድሞቻቸውን ማሳደዱን እንዲያ
ቆሙ ትእዛዝ የማትሰጣቸውስ እስከ መቼ
ድረስ ነው?" አለው።
27ኢዮአብም፣ "ሕያው እግዚአብሔርን!
ይህን ባትናገር ኖሮ፣ ሰዎቹ እስኪነጋ ድረስ
ወንድሞቻቸውን ማሳደዱን ባላቆሙም ነበር"[ሀ]
ብሎ መለሰ።
28ስለዚህ ኢዮአብ ቀንደ መለከቱን ነፋ፤
ከዚያም በኋላ ሰዎቹ በሙሉ እስራኤልን
ማሳደዱን ተው፤ ውጊያውም በዚሁ አበቃ።
29አበኔርና ሰዎቹም ሌሊቱን ዓረባን አልፈው
ሄዱ፤ ከዚያም ዮርዳኖስን በመሻገር ቢትሮንን[ሀ]
ሁሉ ዐልፈው ወደ መሃናይም መጡ።
30ከዚያም ኢዮአብ አበኔርን ማሳደዱን
ትቶ ተመለሰ፤ ሰዎቹንም ሁሉ አንድ ላይ
በሰበሰባቸው ጊዜ፣ ከዳዊት ሰዎች አሣሄልን
ሳይጨምር፣ ዐሥራ ዘጠኝ ሰዎች መጥፋ
ታቸው ታወቀ። 31የዳዊት ሰዎች ግን ከአበ
ኔር ጋር ከነበሩት ሦስት መቶ ሥልሳ ብንያ
ማውያን ገደሉ። 32አሣሄልንም ከወደቀበት
አንሥተው በቤተ ልሔም በአባቱ መቃብር
ቀበሩት። ከዚያም ኢዮአብና ሰዎቹ ሌሊቱን
ሁሉ ሲገሠግሡ አድረው፣ ሲነጋ ኬብሮን
ደረሱ።

3 በዳዊት ቤትና በሳኦል ቤት መካከል የነበ
ረው ጦርነት ብዙ ጊዜ ቈየ፤ ዳዊት እየበ
ረታ ሲሄድ፣ የሳኦል ቤት ግን እየተዳከመ መጣ።
2ዳዊት በኬብሮን ሳለ፣ ስድስት ወንዶች
ልጆች ተወለዱለት፤
የበኵር ልጁ፣ ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪና
ሆም የተወለደው አምኖን፤
3ሁለተኛው፣ የቀርሜሎሳዊው የናባል ሚስት
ከነበረችው ከአቢግያ የተወለደው ኪልአብ፣
ሦስተኛው፣ ተልማይ ከተባለው ከጌሹር ንጉሥ
ልጅ ከመዓካ የተወለደው አቤሴሎም፣
4አራተኛው፣ ከአጊት የተወለደው አዶንያስ፤
አምስተኛው፣ ከአቢጣል የተወለደው ሰፋጥያ፣
5ስድስተኛው፣ ከዳዊት ሚስት ከዔግላ የተ
ወለደው ይትረኃም ነበር፤ እነዚህ ዳዊት
በኬብሮን ሳለ የተወለዱለት ናቸው።

### አበኔር ከዳዊት ጋር ተባበረ

6የሳኦል ቤትና የዳዊት ቤት በጦርነት ላይ
በነበሩበት ጊዜ፣ አበኔር በሳኦል ቤት ላይ
ኀይሉን ያጠናክር ነበር። 7ሳኦልም የኢዮሄልን
ልጅ ሪጽፋን በቁባትነት አስቀምጦአት ነበር፤
ኢያቡስቴም አበኔርን፣ "ለምንድን ነው ከአ
ባቴ ቁባት ጋር የተኛኸው?" አለው።
8አበኔርም በኢያቡስቴ ንግግር እጅግ ስለ
ተቈጣ እንዲህ አለ፤ "እኔ ለይሁዳ የምወ
ግን የውሻ ጭንቅላት ነኝን? ለአባትህ ለሳ
ኦል ቤት ለወንድሞቹና ለዘመዶቹ ታማኝ
ነቴን እስከ ዛሬ ድረስ አሳኳደልሁም፤ አንተ
ንም አሳልፌ ለዳዊት አልሰጠሁም፤ አሁን
ግን አንተ ከዚህች ሴት ጋር በፈጸምሁት
ነገር ትከሰኛለህን? 9እግዚአብሔር ለዳዊት
በመሐላ የሰጠውን ተስፋ እዳር እንዲደርስ ሳላ
ደርግ ብቀር እግዚአብሔር በአበኔር ላይ ክፉ
ያድርግበት፤ ከዚያ የባሰም ያምጣበት፤ 10የማለ
ለትም መንግሥትን ከሳኦል ቤት አውጥቶ፣ ከዳን
እስከ ቤርሳቤህ ባለው በእስራኤልና በይሁዳ

[ሀ]27 ወይም፣ በዚህ ግለቶ ይህን ባትናገር ኖሮ ሰዎቹ ወንድሞቻቸውን ማሳደዱን ባቆሙ ነበር ወይም፣ ይህን ባትናገር ኖሮ ሰዎቹ እስኪነጋ ድረስ ወንድሞቻቸውን ማሳደዱን ባቆሙ ነበር

[ሀ]29 ወይም ግለቶ ወይም ሸለቆ የዕብራይስጡ ቃል ትርጉም በትክክል አይታወቅም።

2፥26 ዘዳ32፥42፤ ኤር46፥10፡14፤ናሆ 2፥13፤3፥15
2፥28 መሳ3፥27፤ 2ሳሙ18፥16፤20፥23
2፥29 ዘፍ32፥2፤ ዘዳ3፥17
2፥32 ዘፍ49፥29
3፥1 2ሳሙ2፥17፤ 5፥10፤22፥44፤1ነገ 14፥30፤አስ9፥4
3፥2 1ሳሙ25፥43፤ 2ሳሙ13፥1
3፥3 1ሳሙ25፥42፤ 2ሳሙ13፥1፡28፡37፤ 14፥32፤15፥8
3፥4 1ነገ1፥5፡11፤ 2፥13፡22
3፥6 1ሳሙ14፥50
3፥7 ዘፍ22፥24፤ 2ሳሙ16፥21-22፤ 21፥8-11፤1ነገ1፥3
3፥8 1ሳሙ17፥43፤ 2ሳሙ9፥8፤16፥9፤ 2ነገ8፥13
3፥9 1ሳሙ15፥28
3፥10 መሳ20፥1፤ 1ሳሙ25፥28-31፤ 2ሳሙ24፥2

2፥26 *ይህ ሰይፍ ዘላለም ማጥፋት አለበትን?* አበኔር የእርስ በርስ ጦርነት የሚያመጣውን መዘዝ በመፍራት ፍልሚያ እንዲቆም ሐሳብ አቀረበ።

2፥27 *ሕያው እግዚአብሔርን!* የመሐላ አነጋገር ነው (የ1ሳሙ 14፥39 ማብ ይመ)።

2፥28 *ውጊያውም በዚሁ አበቃ!* በይፋ ይካሄድ የነበረው ጦርነት ለጊዜው ቢቆምም፣ ጥላቻው ግን አልተፋቀም (3፥1 ይመ)።

2፥29 *ዓረባን!* የዘዳ 1፥1 ማብ ይመ።

3፥2-5! የሳኦል ቤት እየተዳከመ ሲሄድ፣ የዳዊት ቤት እየተጠናከረ መምጣቱን በኬብሮን ከተወለዱት የዳዊት ልጆች ስም ዝርዝር መረዳት ይቻላል (ቍ 1)። ስድስቱ ወንዶች ልጆች እያንዳንዳቸው ከተለያዩ ሴቶች መወለዳቸው፣ ዳዊት በኬብሮን በኖረበት ጊዜ አራት ሌሎች ሚስቶች ማግባቱን (2፥2 ይመ)፣ በተዘዋዋሪ መንገድ ያሳያል። ከዘዳ 17፥17 ጋር የሚቃረነውን በአንድ ሚስት ያለ መወሰንን ልማድ (5፥13)፣ ጸሐፊው በቀጥታ አያወግዘውም፤ ይሁን እንጂ በዳዊት ቤተ ሰብ ውስጥ የተፈጠረው ቀውስ ይህን ጉልቶ እንዲታይ አድርጎአል (ም 13-19፤ 1ነገ 1፥2 ይመ)። *አምኖን!* ከአደገ በኋላ እኅቱን ትዕማርን በመድፈሩ፣ ወንድሙ አቤሴሎም ገደለው (ም 13 ይመ)። *ከኢይዝራኤላዊቷ ከአኪናሆም!* የ1ሳሙ 25፥43 ማብ ይመ።

3፥3 *ኪልአብ!* በ1ዜና 3፥1 ላይ ዳንኤል ተብሎ ተጠርቶአል። *አቢግያ!* 1ሳሙ 25 ይመልከቱ። *አቤሴሎም!* አምኖንን በመግደል የእኅቱን የትዕማርን መደፈር ተበቀለ፤ ራሱን ለማንገሥ በማሰብም በአባቱ በዳዊት ላይ ዶለተ (ም 13-18 ይመ)። *ከተልማይ ልጅ ከመዓካ!* ዳዊት ከመዓካ ጋር መጋባቱ ያለ ጥርጥር የፖለቲካ እንድምታ ነበረው፤ በኢያቡስቴ ሰሜን አዋሳኝ በኩል የተልማይን ድጋፍ በማግኘት፣ ዳዊት የሰሜኑን መንግሥት በደቡብና በሰሜን በኩል ለማስፋፋት ቻለ። *ጌሹር!* ከገሊላ ባሕር በስተ ሰሜን ምሥራቅ የምትገኝ ሲሆን (ኢሱ 12፥5፤ 13፥11-13)፣ ትንሿ የሶርያ ከተማ መንግሥት ናት (ኢሱ 12፥5፤ 13፥11-13 ይመ)።

3፥4 *አዶንያስ!* ሰሎሞን ከመንገሡ በፊት ዙፋኑ ላይ ለመውጣት በመፈለጉ ተገደለ (1ነገ 1፥2 ይመ)።

3፥7 *ሪጽፋ!* 21፥8-11 ይመ። *ለምንድን ነው ከአባቴ ቍባት ጋር የተኛኸው?* የአበኔር ድርጊት ዙፋን ለመንጠቅ ሲል ያውጠነጠነው ሤራ አካል ሳይሆን እንዳልቀረ ኢያቡስቴ ጥርጣሬ አደረበት (ከቍ 6 ጋር ያነጻጽሩ)። በዚህ ዘመን ንጉሥ ያስቀመጣትን ቍባት የራስ ማድረግ ትልቅ ግምት ይሰጠው ነበር (የ12፥8 ማብ፤ እንዲሁም 16፥21፤ 1ነገ 2፥22 ይመ)።

3፥9 *እግዚአብሔር በአበኔር ላይ ክፉ ያድርግበት!* የተለመደ የርግማን መግለጫ ነው (የ1ሳሙ 3፥17 ማብ ይመ)። *እግዚአብሔር... በመሐላ የሰጠውን ተስፋ!* ዳዊት የሳኦል መንግሥት ወራሽ እንዲሆን በእግዚአብሔር የተወሰነ መሆኑ፣ በሰፊው ተሠራጭቶ ነበር (የ2፥4፤ 1ሳሙ 16፥3፤ 25፥28 ማብ ይመ)።

3፥10 *መንግሥትን... አውጥቶ!* አበኔር ከዙፋኑ በስተ

ምድር ላይ የዳዊትን ዙፋን ለመመሥረት የሰ
ጠው ተስፋ ነው።” 11ኢያቡስቴም አበኔርን
አጥብቆ ፈርቶት ስለ ነበር፣ እንደ ገና አንዲት
ቃል እንኳ ሊመልስለት አልደፈረም።
12ከዚያም አበኔር ለዳዊት፣ “ምድሪቱ የማን
ናት? ከእኔ ጋር ተስማማ፤ እነሆ እስራኤል
ሁሉ ወደ አንተ እንዲመለስ እኔ እረዳሃለሁ”
ብለው ለዳዊት እንዲነግሩለት መልክተኞች
ላከ።
13ዳዊትም፣ “ይሁን እሺ፣ ከአንተ ጋር ስም
ምነቱን አደርጋለሁ፣ ነገር ግን ከአንተ አን
ዲት ነገር እሻለሁ፤ ይኸውም ወደ እኔ ስት
መጣ በመጀመሪያ የሳኦልን ሴት ልጅ ሜል
ኮልን ይዘህልኝ እንድትመጣ ነው፤ ያለዚያ ግን
ወደ እኔ እንዳትመጣ” አለ። 14ከዚያም ዳዊት፣
“የመቶ ፍልስጥኤማውያን ሸለፈት ማጫ የከ
ፈልሁባትን ሚስቴን ሜልኮልን ስጠኝ” ብሎ
ወደ ሳኦል ልጅ ወደ ኢያቡስቴ መልክተ
ኞች ላከበት።
15ስለዚህም ኢያቡስቴ መልክተኛ ልኮ፣ ሜል
ኮልን ከባሏ ከሌሳ ልጅ ከፈልጢኤል ወሰ
ዳት። 16ባሏም እስከ ብራቂም ከተማ ድረስ
እያለቀሰ ተከትሎአት ሄደ፤ ከዚያም አበኔር፣
“በል በቃህ! ወደ ቤትህ ተመለስ” አለው።
ስለዚህም ተመለሰ።
17አበኔር ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር
ተመካከረ፤ እንዲህም አለ፤ “ባለፈው ጊዜ
ዳዊት በላያችሁ እንዲነግሥ ፈልጋችሁ ነበር፤
18*እግዚአብሔር* ለዳዊት፣ ‘በባሪያዬ በዳዊት ሕዝ
ቤን እስራኤልን ከፍልስጥኤማውያን እጅና
ከጠላቶቻቸው እጅ እታደጋቸዋለሁ’ ብሎ
ተስፋ ስለ ሰጠው፣ ይህን አሁኑኑ አድርጉት።”
19እንዲሁም አበኔር ለብንያማውያን ራሱ
ሄዶ ይህንኑ ነገራቸው፤ ከዚያም እስራኤልና
መላው የብንያም ቤት ለማድረግ የፈለጉ

3፥13 ዘፍ43፥5
3፥14 1ሳሙ18፥27
3፥15 ዘዳ24፥1-4፤
25፥44
3፥16 2ሳሙ16፥5፤
17፥18
3፥17 መሳ11፥11
3፥18 1ሳሙ9፥16፤
2ሳሙ8፥6
3፥19 1ዜና12፥2፤
16፥29

3፥20 1ዜና12፥39
3፥21 2ሳሙ5፥3፤
1ነገ11፥37
3፥27 ዘፀ21፥14፤
መሳ3፥21፤2ሳሙ2፥
8:22:23፤4፥1፤1ነገ2፥
5:32

ትን ሁሉ ለዳዊት ለመንገር ወደ ኬብሮን
ሄደ። 20አበኔር ከሃያ ሰዎች ጋር ዳዊት ወዳለበት
ወደ ኬብሮን መጣ፤ ዳዊትም ለአበኔርና አብረ
ውት ለነበሩት ሰዎች ግብዣ አደረገላቸው።
21ከዚያም አበኔር ዳዊትን፤ “ከአንተ ጋር ቃል
ኪዳን እንዲያደርጉ፣ ልብህ እንደተመኘውም
ሁሉን እንድትገዛ ፈጥኜ ሄጄ፣ ለጌታዬ ለን
ጉሡ መላውን እስራኤልን ልሰብስብ” አለው።
ስለዚህ ዳዊት አበኔርን አሰናበተው፤ በሰላ
ምም ሄደ።

## ኢዮአብ አበኔርን ገደለው

22የዳዊትና የኢዮአብ ሰዎች በዚያኑ ጊዜ
ብዙ ምርኮ ይዘው ከዘመቻ ተመለሱ። አበ
ኔር ግን ዳዊት በሰላም አሰናብቶት ስለ ሄደ፣
በኬብሮን አልነበረም። 23ኢዮአብና አብሮት
የነበረው ሰራዊት ሁሉ እዚያ እንደ ደረሱ፣
የኔር ልጅ አበኔር ወደ ንጉሡ መምጣቱን፣
ንጉሡ እንዳሰናበተውና እርሱም በሰላም እንደ
ሄደ፣ ኢዮአብ ሰማ።
24ስለዚህ ኢዮአብ ወደ ንጉሡ ገብቶ እን
ዲህ አለ፤ “ምን ማድረግህ ነው? እነሆ አበ
ኔር መጥቶልህ እንዴት በሰላም እንዲሄድ
አሰናበትኸው? 25የኔርን ልጅ አበኔርን ታው
ቀዋለህ፤ የመጣው ሊያታልልህ፣ መውጣት መግ
ባትህን ለማወቅና የምታደርገውን ሁሉ ሊሰልል
ነው።”
26ከዚያም ኢዮአብ ከዳዊት ዘንድ ወጣ፤ አበ
ኔርን እንዲያመጡትም መልክተኞች ላከ፤ መልክ
ተኞቹም ከሲይር የውሃ ጉድጓድ አጠገብ መለ
ሱት። ዳዊት ግን ይህን አላወቀም ነበር። 27አበኔር
ወደ ኬብሮን በተመለሰ ጊዜ፣ ኢዮአብ በቈይታ
የሚያነጋግረው በመምሰል ዞር አድርጎ ወደ
ቅጽሩ በር ይዞት ሄደ፤ እዚያም የወንድሙን የአ
ሣሄልን ደም ለመበቀል ሲል፣ ሆዱ ላይ ወግቶ
ገደለው።

ጀርባ የሚገኝ እውነተኛው ኀያል ሰው ነበር። *ከዳን እስከ ቤርሳ ቤህ፤* የ1ሳሙ 3፥20 ማብ ይመ።

3፥12 *ምድሪቱ የማን ናት?* ምድሪቱ የአበኔር ወይም የዳዊት መሆኗን ለማስገንዘብ የቀረበ መልስ አዘል ጥያቄ ነው፤ ቀጥሎ ከሚገኘው ዐረፍተ ነገር አንጻር ሲታይ፣ መልሱ በመጀመሪያ የተጠቀሰውን የሚመለከት ይመስላል። *ከእኔ ጋር ተስማማ፤* አበኔር ለሳኦል ቤት የነበረው ታማኝነት ጉዳት የማያመጣበት ለመሆኑ ዋስትና እንዲሰጠው ይፈልጋል።

3፥13 *የሳኦልን ሴት ልጅ ሜልኮልን፤* ሳኦል ሜልኮልን ቀደም ሲል ለዳዊት የሰጣት ቢሆንም እንኳ (1ሳሙ 18፥27)፣ ዳዊት ከቤተ መንግሥቱ ከሸሸ በኋላ ለሌላ ሰው ድሮለት ነበር (1ሳሙ 25፥44)። እንደ ሰሜናውያን ሽማግሌዎች አስተሳሰብ፣ የዳዊትና የሜልኮል ዳግም ግንኙነት ዳዊት የሳኦል ዐማች እንደ መሆኑ፣ ሕጋዊ የዐልጋ ወራሽነቱን መብት የሚያጠናክር ነው።

3፥14 *ዳዊት... ኢያቡስቴ መልእክተኞች ላከበት፤* ዳዊት በአበኔር በታቀደው የማታለያ ዘዴ ከመጠቀም ይልቅ ኢያቡ ስቴ ነገሩን በይፋ ዐውቆት፣ ሜልኮል እንድትመለስለት ፈለገ። ኢያቡስቴ የአበኔርን ፍላጎት ለመቃወም ዐቅም እንደሌለውም ዳዊት ያውቃል (ቍ 11 ይመ)። *የመቶ ፍልስጥኤማውያን ሸለፈት፤* 1ሳሙ 18፥25 ይመ። ሳኦል ዳዊትን የመቶ ፍልስጥኤማውያንን ሸለፈት እንዲያቀርብ ጠይቆት ነበር፤ ዳዊት ግን የሁለት መቶ ፍልስጥኤማውያንን ሸለፈት አመጣ (1ሳሙ 18፥27)።

3፥16 *ብራቂም፤* ወደ ኬብሮን በሚወስደው መንገድ ላይ የምትገኝ መጨረሻዋ የብንያማውያን ከተማ ናት (16፥5፤ 17፥18 ይመ)።

3፥17 *ከእስራኤል ሽማግሌዎች፤* የልዩ ልዩ ነገዶች ጥምር አመራር፣ መደበኛ የመንግሥት ሥልጣን የሌለውን ብሔር ዐቀፍ የአስተዳደር አካል መሥርቶአል፣ (የዘፀ 3፥16፤ የኢዩ 1፥2፤ የማቴ 15፥2፤ የሐሥ 24፥1 ማብ፤ እንዲሁም 1ሳሙ 8፥4፤ 2ሳሙ 5፥3፤ 5፥13 1ነገ 8፥1:3፤ 20፥7፤ 2ነገ 10፥1፤ 23፥1 ይመ)። *ዳዊት... እንዲነግሥ ፈልጋችሁ ነበር፤* ለኢያቡስቴ ርዳታ የመጣለት በአብዛኛው ከብንያም ነገድና (2፥15 እና ማብ ይመ) ከዮርዳኖስ ማዶ ከሚገኘው ከገለዓድ ምድር ነበር (2፥8፤ 1ሳሙ 11፥9-11፤ 31፥11-13 ይመ)።

3፥18 *እግዚአብሔር ለዳዊት... ተስፋ ሰጠው፤* በዚህ ጊዜ ዳዊት ንጉሥ እንዲሆን ሳሙኤል የቀባው መሆኑ በሁሉም ዘንድ ታውቆአል (5፥2 ይመ)። ሳሙኤል እጅግ የተከበረ የእግዚአብሔር ነቢይ በመሆኑ፣ አበኔር የዳዊትን መቀባት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ተስፋ አድርጎ ተመለከተው።

3፥19 *እንዲሁም አበኔር ለብንያማውያን... ነገራቸው፤* ሳኦልና ቤተ ሰቡ ከብንያም ነገድ በመሆናቸው፣ ዙፋኑን ወደ ይሁዳ ነገድ ስለማስተላለፍ አበኔር ከብንያማውያን ጋር የተነጋገረው በጥንቃቄ ነበር፤ እነርሱም በዚሁ መስማማታቸውን ገለጹ፤ ይሁን እንጂ አበኔር ነገሮችን ለራሱ ዐላማ በሚበጅ መንገድ ለማስፈጸም በውክልና ከመንቀሳቀስ በላይ የሚያልፍ ሰው አልነበረም።

3፥21 *ከአንተ ጋር ቃል ኪዳን እንዲያደርጉ፤* 5፥3 እና ማብ ይመ።

3፥25 *የመጣው ሊያታልልህ... ነው፤* ወንድሙን አሣሄልን ስለ ገደለበት ኢዮአብ አበኔርን ናቀው (2፥18:23፤ 3፥27)፤ እንደ አድርባይ በመቍጠርም በዳዊት ፊት ሊያዋርደው ፈለገ። አበኔር በሰሜኑ የእስራኤል ነገዶች ዘንድ ተሰሚነት ያለው ሰው እንደ መሆኑ፣ ከዳዊት ሰራዊት ጋር ከተቀላቀለ፣ ኢዮአብ የራሱን ሥልጣን የሚቀናቀነው መሰለው።

3፥27 *ኢዮአብ... ሆዱ ላይ ወግቶ ገደለው፤* የኢዮአብ አበ ኔርን መግደሉ እንደ ውጊያ ተግባር ወይም እንደ ትክክለኛ በቀል

28ዳዊት ይህን ነገር ቈይቶ በሰማ ጊዜ እን
ዲህ አለ፤ "እኔም ሆንሁ መንግሥቴ ከኔር
ልጅ ከአበኔር ደም በእግዚአብሔር ፊት
ለዘላለም ንጹሕ ነን፤ 29ደሙ በኢዮአብ ራስና
በአባቱ ቤት ሁሉ ላይ ይሁን፤ ፈሳሽ ነገር
የሚወጣው ወይም አሠቃቂ የቈዳ በሽታ[ሙ]
ያለበት፣ በምርኵዝ የሚሄድ አንካሳ፣ ወይም
በሰይፍ ተመቶ የሚወድቅ ወይም የሚበላው
ያጣ ራብተኛ ከኢዮአብ ቤት አይታጣ።"
30አበኔር ገባዖን ላይ በተደረገው ጦርነት የኢ
ዮአብንና የአቢሳን ወንድም አሣሄልን ገድሎት
ስለ ነበር፣ እነርሱም አበኔርን ገደሉት።
31ከዚያም ዳዊት ለኢዮአብና አብሮት ለነበ
ረው ሕዝብ ሁሉ፣ "ልብሳችሁን ቀዳችሁ፣ ማቅ
ለብሳችሁ በአበኔር ፊት አልቅሱ" አላቸው፤ ራሱ
ንጉሥ ዳዊትም አስከሬኑን አጀበ። 32ከዚያም
አበኔርን በኬብሮን ቀበሩት፤ ንጉሥም በአበኔር
መቃብር ላይ ጮኾ አለቀሰ፤ ሕዝቡም ሁሉ
እንደዚሁ አለቀሱ።
33ንጉሥም ለአበኔር ይህን የሐዘን እንጕርጕሮ
ተቀኘ፤

"አበኔር እንደ ተራ ሰው ይሙት?
34እጆችህ አልታሰሩም፤
እግሮችህ በእግር ብረት አልገቡም፤
ሰው በክፉ ሰዎች ፊት እንደሚወድቅ
አንተም እንደዚሁ ወደቅህ።"

ሕዝቡም ሁሉ እንደ ገና አለቀሱለት።
35ከዚያም ሕዝቡ ሁሉ እህል በሚቀምስ
በት ሰዓት ወደ ዳዊት መጥተው ምግብ
እንዲበላ አጥብቀው ለመኑት። ዳዊት ግን፣
"ፀሓይ ከመጥለቋ በፊት እንጀራ ወይም ሌላ
ነገር ብቀምስ፣ እግዚአብሔር ክፉ ያድርግብኝ
ከዚያም የባሰ ያምጣብኝ" ብሎ ማለ።
36ሕዝቡም ሁሉ ይህንኑ ተመለከቱ፤ ደስም
አላቸው፤ በእርግጥ ንጉሡ ያደረገው ሁሉ ሕዝ
ቡን ደስ አሰኛቸው። 37እንዲሁም በዚያን ዕለት
ሕዝቡ ሁሉና እስራኤል በሙሉ ንጉሡ የኔር
ልጅ በአበኔር ሞት እጁ እንዳልገባበት ዐወቁ።
38ከዚያም ንጉሡ ለራሱ ሰዎች እንዲህ አለ፤

3፥28 ቍ37፤ ዘዳ21፥9
3፥29 ዘሌ15፥2፤ 20፥9፤1ነገ2፥31-33
3፥31 ዘፍ37፥34፤ መዝ30፥11፤35፥13፤ 69፥11፤ኢሳ20፥2
3፥32 ዘኍ14፥1፤ ምሳ24፥17
3፥33 ዘፍ50፥10
3፥34 ኢዮ36፥8፤ መዝ2፥3፤149፥8፤ ኢሳ45፥14፤ናሆ3፥10
3፥35 ሩት1፥17፤ 1ሳሙ31፥13፤2ሳሙ 12፥17፤ኤር16፥7
3፥37 ቍ28
3፥38 2ሳሙ1፥19
3፥39 መሳ18፥26፤ 2ሳሙ2፥18፤16፥9፤ 18፥11፤1ነገ2፥32፤ መዝ41፥10፤101፥8
4፥1 2ሳሙ3፥27
4፥2 ኢሱ9፥17
4፥3 ነህ11፥33
4፥4 ዘሌ21፥18፤ 1ሳሙ18፥1፤31፥9፤ 2ሳሙ9፥8፡12፤ 16፥1-4፤19፥24፤ 21፥7-8፤1ዜና 8፥34፤9፥40
4፥5 ሩት2፥7፤ 2ሳሙ2፥8
4፥6 2ሳሙ2፥23
4፥7 ዘዳ3፥17
4፥8 ዘኍ31፥3፤ 1ሳሙ24፥4፤25፥29፤2 ሳሙ20፥21፤ 2ነገ10፥7

"በዛሬዪቱ ዕለት በእስራኤል መስፍንና ታላቅ
ሰው መውደቁን አላወቃችሁምን? 39ምንም
እንኳ ዛሬ የተቀባሁ ንጉሥ ብሆንም፣ እኔ ደካማ
ሰው ነኝ፤ እነዚህ የጽሩያ ልጆች እጅግ በርትተ
ውብኛል። እግዚአብሔር ለክፉ አድራጊ የእጁን
ይስጠው።"

## ኢያቡስቴ ተገደለ

4 አበኔር በኬብሮን መሞቱን የሳኦል ልጅ
ኢያቡስቴ በሰማ ጊዜ ወኔ ከዳው፤ መላው
እስራኤልም ደነገጠ። 2በዚህ ጊዜ የሳኦል ልጅ
ኢያቡስቴ የወራሪ ጭፍራ ቡድን መሪዎች
የሆኑ ሁለት ሰዎች ነበሩት፤ አንዱ በዓና
ሌላው ደግሞ ሬካብ ይባሉ ነበር። እነርሱም
ከብንያም ነገድ የብኤሮት ተወላጅ የሆነው
የሬሞን ልጆች ነበሩ፤ ብኤሮት ከብንያም
ክፍል እንደ አንዱ ትቈጠራለች። 3የብኤ
ሮት ሕዝብ ወደ ጊቴም በመሸሽ እስከ ዛሬም
በመጻተኝነት እዚያው ይኖራልና።
4የሳኦል ልጅ የዮናታን ሁለት እግሮቹ ሽባ
የሆኑ አንድ ልጅ ነበረው። እርሱም የሳኦ
ልና የዮናታን አሟሟት ወሬ ከኢይዝራኤል
በመጣ ጊዜ የአምስት ዓመት ልጅ ነበረ።
ሽባ የሆነውንም በዚህ ጊዜ ሞግዚቱ አንሥ
ታው በጥድፊያ ስትሸሽ በመውደቁ ነው።
ስሙም ሜምፊቦስቴ ይባል ነበር።
5በዚህ ጊዜ የብኤሮታዊው የሬሞን ልጆች
ሬካብና በዓና ወደ ኢያቡስቴ ቤት ለመሄድ
ተነሡ፤ እርሱም የቀትር ጊዜ ዕረፍት ለማ
ድረግ ዐልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ፣ ሙቀት ሲ
ሆን እኩለ ቀን ላይ ደረሱ፤ 6ስንዴ እንደ
ሚፈልግም ሰው ሆነው ወደ ቤቱ ውስጥ
ዘልቀው በመግባት ሆዱ ላይ ወጉት። ከዚያም
ሬካብና ወንድሙ በዓና ሾልከ ብለው ወጡ።
7ወደ ቤቱ ውስጥ የገቡት ኢያቡስቴ በመኝታ
ክፍሉ ውስጥ ተኝቶ ሳለ ነበር፤ ወግተው
ከገደሉትም በኋላ ራሱን ቈርጠው በመውሰድ፣
ሌሊቱን ሁሉ በዓረባ መንገድ ተጓዙ። 8የኢያቡስ
ቴንም ራስ ወደ ኬብሮን ዳዊት ዘንድ አምጥተው

[ሙ]29 የዕብራይስጡ ቃል ማናቸውንም ዐይነት የቈዳ በሽታ የሚ
ያመለክት ነው።

ተቈጥሮ ይቅርታ ሊያስጠው አይችልም (ከዘኍ 32፥12፤ ከዘዳ 19፥11-13 ጋር ያነጻጽሩ)። አበኔር አሣሄልን የገደለው በጦርነት ላይ ነበር (2፥23፤ እንዲሁም የ2፥21 ማብ ይመ)።

3፥29 *ደሙ በኢዮአብ ራስና በአባቱ ቤት ሁሉ ላይ ይሁን፤* አበኔርን በመግደል ሤራ ውስጥ የግልም ሆነ የመንግሥት እጅ ያልነበረበት መሆኑን ዳዊት ከገለጸ በኋላ (ቍ 28)፣ ኢዮአብን ረገመው፤ እንዲፈርድበት ለእግዚአብሔር ልመና አቀረበ። ዳዊት ከሰሜኑ የእስራኤል ነገዶች ጋር የነበረው ግንኙነት በመዋለል ላይ በነበረበት በዚህ ወሳኝ ወቅት ኢዮአብን በሕዝብ ፊት ለፍርድ ለማቅረብ የተረጋጋ ሁኔታ አይታይበትም ነበር (ቍ 39)። ስለዚህ የኢዮአብ ወንጀል እስከ መጀመሪያዎቹ የሰሎሞን የሥልጣን ዓመታት ድረስ የፍርድ ውሳኔ አላገኘም ነበር (1ነገ 2፥5-6፡29-35)።

3፥31 *ኢዮአብ፤* እርሱም ከሐዘንተኞች ጋር አብሮ ለመቀመጥ ተገደደ፤ ይህም የሆነው ምናልባት ኢዮአብ በአበኔር ግድያ እጁን ያስገባ መሆኑ በይፋ ስላልታወቀና፣ ለጊዜውም ቢሆን ዳዊትም ጕዳዩ በምስጢር እንዲያዝ ስለፈለገ ነው።

3፥32 *በኬብሮን፤* በዚያን ጊዜ የዳዊት መናገሻ ከተማ ነበረች። *ንጉሡም በአበኔር መቃብር ላይ ጮኾ አለቀሰ፤* የአበኔር መሞት የዳዊትን መንግሥት አንድነት ሊያናጋ ስለሚችል፣ ዳዊት በግድያው እጁ እንደሌለበት ለሕዝቡ ለመግለጽ፣ የተቻለውን ሁሉ አድርጎአል፤ በዚህም ተሳክቶለት ነበር (ቍ 36-37 ይመ)።

3፥35 *እግዚአብሔር ይህን ያድርግብኝ፤ ከዚህም የባሰ ያምጣብኝ፤* የተለመደ የርግማን ቃል አገላለጽ ነው (የ1ሳሙ 3፥17 ማብ ይመ)።

3፥39 *እግዚአብሔር ለክፉ አድራጊ የእጁን ይስጠው፤* የቍ 29 ማብ ይመ።

4፥1 *ደነገጠ፤* ኢያቡስቴ ያለ አበኔር እንደማይሳካለት ተገንዝቦ ነበር (የ2፥8 ማብ ይመ)። *መላው እስራኤልም ደነገጠ፤* የእርስ በርስ ብጥብጥ ሊነሣ ይችላል የሚል ሥጋትም ነበረ፤ የሰሜን ነገዶችም ጠንካራ መሪ አልነበራቸውም።

4፥2 *ብኤሮት፤* ለብንያም ነገድ ከተመደቡት (ኢሱ 18፥25)፣ ከገባዖን ከተሞች አንዷ ናት (ኢሱ 9፥17)።

4፥4 *የሳኦል ልጅ የዮናታን ሁለት እግሮቹ ሽባ የሆኑ አንድ ልጅ ነበረው፤* ኢያቡስቴ ከሞተ በኋላ (ቍ 6)፣ ከሳኦል ቤት ዘውድ ይገኛል የሚል ሰው እንዳልነበረ ጸሐፊው በአጽንዖት ይገልጻል። *የሳኦልና የዮናታን... ወሬ፤* 1፥4፤ 1ሳሙ 31፥2-4 ይመ። *ሜምፊቦስቴ፤* 9፥1-13፤ 16፥1-4፤ 19፥24-30፤ 21፥7-8 ይመ። የቀድሞው ስሙ መሪበኣል ሲሆን፣ ትርጕሙም በበኣል የተወደደ ማለት ነው፤ 1ዜና 8፥34 ይመ፤ የ2፥8 ማብ ይመ።

4፥7 *በዓረባም፤* የዘዳ 1፥1 ማብ ይመ።

ንጉሡን፣ "እንተን ሊገድል ይፈልግ የነበረው የጠ
ላትህ የሳኦል ልጅ የኢያቡስቴ ራስ ይኸውልህ፤
እነሆ እግዚአብሔር በዛሬው ቀን ስለ ጌታዬ ስለ
ንጉሡ ሳኦልንና ዘሩን ተበቅሎአል" አሉት።
9ዳዊትም ለብኤሮታዊው ለሬሞን ልጆች ለሬካ
ብና ለወንድሙ ለበዓና እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
'ከመከራ ሁሉ ያዳነኝ ሕያው እግዚአብሔርን
10የምሥራች ያመጣልኝ መስሎት፣ 'እነሆ ሳኦል
ሞተ' ብሎ የነገረኝን ሰው ይዤ ጺቅላግ ላይ ገደ
ልሁት፤ እንግዲህ ለዚያ ሰው ስላመጣው ምሥ
ራች የሸለምሁት ይህን ነበር። 11ታዲያ በገዛ
ቤቱ፣ በገዛ ዐልጋው ላይ ዐርፎ የተኛውን ንጹሕ
ሰው የገደሉትን ክፉ ሰዎች እንዴት የባሰ ቅጣት
አይገባቸውም? ደሙን ከእጃችሁ መፈለግ፣ እና
ንተን ከምድሪቱ ማጥፋት የለብኝምን?"
12ስለዚህም ዳዊት የራሱን ሰዎች አዘዘ፤ እነርሱ
ንም ገደሏአቸው፤ እጅና እግራቸውንም ቈርጠው
በኬብሮን ካለው ኩሬ አጠገብ ሰቀሏቸው። ነገር
ግን የኢያቡስቴን ራስ ወስደው ኬብሮን በሚገ
ኘው በአበኔር መቃብር አጠገብ ቀበሩት።

## ዳዊት በእስራኤል ላይ ነገሠ

5፥1-3 ተጓ ምብ - 1ዜና 11፥1-3

**5** የእስራኤል ነገዶች በሙሉ ወደ ኬብሮን ወደ
ዳዊት መጥተው እንዲህ አሉ፤ "እነሆ፤ እኛ
የዐጥንትህ ፍላጭ፣ የሥጋህ ቍራጭ ነን፤ 2ባለ
ፈው ሳኦል በእኛ ላይ ነግሦ በነበረ ጊዜ፣ እስራ
ኤልን በጦርነት የምትመራቸው አንተ ነበርህ፤
እግዚአብሔርም 'ሕዝቤን እስራኤልን ትጠብ
ቃለህ፤ መሪያቸውም ትሆናለህ' ብሎህ ነበር።"
3ስለዚህም የእስራኤል ሽማግሌዎች በሙሉ
ወደ ኬብሮን መጡ፤ ንጉሥ ዳዊትም ኬብሮን
ላይ በእግዚአብሔር ፊት ከእነርሱ ጋር ቃል
ኪዳን አደረገ፤ እነርሱም ዳዊትን ቀብተው
በእስራኤል ላይ አነገሡት።
4ዳዊት በነገሠ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት
ነበረ፤ አርባ ዓመትም ገዛ። 5በኬብሮን ተቀምጦ
በይሁዳ ላይ ሰባት ዓመት ከስድስት ወር፣ ኢየሩ
ሳሌም ሆኖም በመላው እስራኤልና በይሁዳ
ላይ ሠላሳ ሦስት ዓመት ነገሠ።

## ዳዊት ኢየሩሳሌምን ድል አደረገ

5፥6-10 ተጓ ምብ - 1ዜና 11፥4-9
5፥11-16 ተጓ ምብ - 1ዜና 3፥5-9፤ 14፥1-7

6ንጉሡና ሰዎቹ በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን ኢያ
ቡሳውያንን ለመውጋት ወደዚያ ሄዱ። ኢያቡሳ
ውያንም፣ "ዳዊት እዚህ ሊገባ አይችልም" ብለው
ስላሰቡ ዳዊትን፣ "ዕውሮችና አንካሶች እንኳ
ይከለክሉሃልና ወደዚህች አትገባም" አሉት።
7ይሁን እንጂ ዳዊት የጽዮንን ዐምባ ያዘ፤ ይህ
ችም የዳዊት ከተማ የተባለችው ናት።

4፥9 ዘፍ48፥16፤ 1ነገ1፥29
4፥10 2ሳሙ1፥2-16
4፥11 ዘፍ4፥10፤ 9፥5፤መዝ9፥12፤ 72፥14
4፥12 2ሳሙ1፥15
5፥1 ዘፍ29፥14፤ 35፥26፤2ሳሙ19፥43
5፥2 ዘፍ48፥15፤ 1ሳሙ11፥6፤12፥12፤ 13፥14፤16፥1፤18፥5፡ 13:16፤2ሳሙ6፥21፤ 7፥7፤ማቴ2፥6፤ ዮሐ21፥16
5፥3 ዘጸ17፥15፤ 2ሳሙ2፥4፤3፥21
5፥4 ዘፍ37፥2፤ 1ነገ2፥11፤1ዜና3፥4፤ 26፥31፤ሉቃ3፥23
5፥5 2ሳሙ2፥11፤ 1ነገ2፥11፤1ዜና3፥4
5፥6 ኢሱ15፥8፤ መሳ1፥8
5፥7 2ሳሙ6፥12፡ 16፤1ነገ2፥10፤8፥1፤ መዝ76፥2፤ኢሳ29፥1፤ ኤር21፥13፤25፥29

4፥8 *እግዚአብሔር በዛሬው ዕለት ስለ ጌታዬ ስለ ንጉሡ ሳኦልንና ዘሩን ተበቅሎአል፤* ሬካብና በዓና ዳዊት በድርጊታቸው የሚያመሰግናቸው መስሎአቸው፣ የኢያቡስቴን ግድያ የነገሩት በመቈርቈር ስሜትና የእምነት ሰው በመምሰል ነበር፤ ሆኖም ግን ድርጊቱ ሕይወታቸውን ለአደጋ ዳረገው።

4፥9 *ሕያው እግዚአብሔርን፤* የተለመደ የመሐላ አገላለጽ ነው (የ1ሳሙ 14፥39 ማብ ይመ)።

4፥11 *ደሙን ከእጃችሁ መፈለግ፤* የሞት ፍርድ የሚፈረድባቸው መሆኑን የሚገልጥ ነው (ዘፍ 9፥5-6 ይመ)። ዳዊት በኢዮአብ ላይ መውሰድ ያልቻለውን ርምጃ በዚህ ላይ ሲወስድ ይታያል (የ3፥29 ማብ ይመ)።

4፥12 *እጅና እግራቸውንም፤* የኢያቡስቴን ሕይወት ያጠፉ እጆችና የአሟሟቱን ወሬ ለመንገር የተጣደፉ እግሮች ናቸው።

5፥1-24፥25፤ ከም 5 ጀምሮ ያሉት ክፍሎች በመጽሐፈ ዜና መዋዕል አንደኛ ከሚገኙ ምንባቦች ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ እነዚህ ተጓዳኝ ትረካዎች ሙሉ በሙሉ አንድ ዐይነት ሲሆኑ፣ በሌሎች ክፍሎች ደግሞ ልዩነቶች ይታዩባቸዋል።

5፥1 *የእስራኤል ነገዶች በሙሉ፤* ሽማግሌዎችንና ወታደሮችን ጨምሮ የእያንዳንዱን ነገድ ተወካዮች ያካትታል (1ዜና 12፥23-40 ይመ)። *የዐጥንትህ ፍላጭ፣ የሥጋህ ቍራጭ፤* የልዩ ልዩ ነገድ ተወካዮች ዳዊትን ንጉሥ አድርገው ለመቀበላቸው ሦስት ምክንያቶች አሏቸው፤ ከእነዚህ ምክንያቶች የመጀመሪያው፣ ዳዊት እስራኤላዊ መሆኑን መቀበላቸው ነው። ሳኦል ከሞተ በኋላ (2፥8-3፥1) የእርስ በርስ ጦርነት በመነሣቱ ብሔራዊ አንድነት ቢፈርስም እንኳ፣ በዘር ሐረግ ላይ የተ መሠረተው ግንኙነት አልተዘነጋም ነበር።

5፥2 *እስራኤልን በጦርነት የምትመራቸው አንተ ነበርህ፤* ዳዊትን በንጉሥነት ለመቀበላቸው (1ሳሙ 18፥5፡ 13-14፡16፡30 ይመ) ሁለተኛ ምክንያት ይህ ነው (የቍ 1 ማብ ይመ)። *እግዚአብሔርም... ብሎህ ነበር፤* ሦስተኛውና ዐቢይ የሆነው ምክንያት ደግሞ ይህ ነው (1ሳሙ 13፥13-14፤ 16፥1፡13፤ 23፥17፤ 25፥26-31 ይመ)።

5፥3 *ንጉሥ ዳዊትም... በእግዚአብሔር ፊት ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፤* ዳዊትና የእስራኤል ሕዝብ የየበኩላቸውን ኀላፊነት የሚወጡ ለመሆናቸው በእግዚአብሔር ፊት ራሳቸውን ግዴታ ውስጥ ያስገቡበትን ኪዳን አደረጉ (2ነገ 11፥17 እና ማብ ይመ)። ስለዚህ ዳዊት የይሁዳ ንጉሥ ይሆን ዘንድ በዙፋን ላይ እንዲቀመጥ የተደረገው በራሱ ነገዶች ነው። ከጊዜ በኋላም የኢየሩሳሌም ንጉሥ የሆነው በጦርነት ድል አድርጎ ነው (ቍ 6-10)፤ በሰሜን ነገዶች ላይ ገዥ ለመሆን የበቃው ግን የሰሜን ነገዶች የተሸነፉ መሆናቸውን ተቀብለው በመስማማታቸው ነው። የዳዊት የልጅ ልጅ ሮብዓም በነገሠ ጊዜ የስምምነቱን ቃል ለማክበር ፈቃደኛ ባለ መሆኑ፣ ውሉ አልታደሰም ነበር (1ነገ 12፥1-16)። *እነርሱም ዳዊትን ቀብተው በእስራኤል ላይ አነገሡት፤* ዳዊት ለሦስተኛ ጊዜ ተቀባ (የ2፥4 ማብ ይመ)።

5፥5 *በኬብሮን ተቀምጦ በይሁዳ ላይ ሰባት ዓመት ከስድስት ወር... ነገሠ፤* 2፥11 ይመ። *በመላው እስራኤልና በይሁዳ፤* ዳዊት ግዛቱ ከሆኑት ከእነዚህ ሁለት ክፍሎች ጋር የነበረው ልዩ ግንኙነት ክፍሎቹ የየራሳቸውን ማንነት ይዘው እንዲዘልቁ ያደረገ ይመስላል (የቍ3 ማብ ይመ)።

5፥6 *ኢየሩሳሌም፤* በዳዊት የአገዛዝ ዘመን ከተከናወኑት ዐበይት ተግባራት ውስጥ አንዱና ዋናው ኢየሩሳሌም የዙፋኑና የአገሪቱ ዋና ከተማ መሆኗ ነበር (መግቢያውን ይመ)። ቦታው በመጀመሪያ ከክርስቶስ ልደት በፊት በሦስት ሺህ ዓመት የተያዘና አብርሃም በነበረበት ዘመን መናገሻ ከተማ የነበረ ቦታ ነው (የዘፍ 14፥18 ማብ ይመ)። የኢየሩሳሌም ከተማ የምትገኘው በይሁዳና በብንያም ድንበር መካከል ነው፤ ይሁን እንጂ አንዳቸውም አልያዟትም ነበር። በወረራው ጊዜ ይሁዳና ብንያም ይህቺኑ ከተማ አጥቅተው ይዘዋታል (የመሳ 1፥8፡21 ማብ ይመ)፤ ሆኖም ግን ኢያቡሳውያን ወዲያውኑ እጃቸው ውስጥ አስገብተዋታል (ኢሱ 15፥63)፤ በዚህም ምክንያት አንዳንድ ጊዜ ኢያቡስ ተብላ ትጠራ ነበር (መሳ 19፥10፤ 1ዜና 11፥4 ይመ)። ዳዊት አሸንፎ የያዛት ከተማ ስፋቷ ከሩብ ጋሻ መሬት በታች ስለ ነበረ፣ ነዋሪዎቿ ከ3500 አይበልጡም ነበር። ዳዊት በሁለቱ የግዛቱ ክፍሎች ድንበር ላይ የያዛትን አዲስ ከተማ መናገሻው በማድረግ አንዱ በሌላው ጥገኛ በማይሆንበት መልክ መንግሥቱን በአገዛዙ ሥር አንድ አደረገው። *ኢያቡሳውያን፤* በኢየሩሳሌምና (ኢሱ 15፥8፤ 18፥16) በአካባቢዋ (ዘኁ 13፥29፤ ኢሱ 11፥13) ይኖሩ የነበሩ የከነዓን ሰዎች ናቸው (ዘፍ 10፥15-16)። *ዕውሮችና አንካሶች እንኳ ይከለክሉሃልና፤* ከሦስት አቅጣጫ ጥልቀት ባላቸው ሸለቆዎች በተከበበ ኰረብታ ላይ የምትገኝ በመሆኗ፣ ኢየሩሳሌም የተፈጥሮ ዐምባ ናት፤ ከዚህም የተነሣ ኢያቡሳውያን ምሽጋቸው ከጠላት ጥቃት በቀላሉ መከላከል እንደሚያስችላቸው ተማምኑ።

5፥7 *ዐምባ፤* ምናልባት የተመሸገችውን ከተማ ራሷን የሚመለከት ሊሆን ይችላል። *ጽዮን፤* ይህ ስም በብሉይ ኪዳን ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ነው (ትርጕሙ አይታወቅም)። በመጀመሪያ ይህ ስም የኢያቡሳውያን ምሽግ ለሚገኝበት የከተማዋ የደቡብ ጫፍ ኰረብታ ተሰጥቶ የነበረ መጠሪያ ይመስላል። ከተማዋ እየተስፋፋች ስት ሄድ (ከሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ጀምሮ)፣ ይህ ስም የመላዋ ከተማ

[8]በዚያም ዕለት ዳዊት፣ "ኢያቡሳውያንን ድል
ማድረግ የሚፈልግ፣ የዳዊት ጠላቶችᶜ ወደሚ
ሆኑ፣ 'አንካሶችና ዕውሮች' ለመድረስ በውሃ
መተላለፊያውᵃ ሽቅብ መውጣት አለበት" አለ።
እንግዲህ፣ "'አንካሶችና ዕውሮች' ወደ ቤተ
መንግሥት አይገቡም" ያሉት ለዚህ ነው።
[9]ከዚያም ዳዊት መኖሪያውን በዐምባዪቱ ላይ
አደረገ፤ የዳዊት ከተማም ብሎ ጠራት። ዳዊ
ትም ከሚሎ አንሥቶ ወደ ውስጥ ዙሪያዋን ገነ
ባት። [10]የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር
ስለ ነበር፣ ዳዊት ከዕለት ወደ ዕለት እየበረታ
ሄደ።
[11]በዚህ ጊዜ የጢሮስ ንጉሥ ኪራም ወደ
ዳዊት መልእክተኞችን ላከ፤ እንዲሁም የዝግባ ዕን
ጨት፣ አናጢዎችንና ድንጋይ ጠራቢዎችን
አብሮ ሰደደ፤ እነርሱም ለዳዊት ቤተ መንግሥት
ሠሩለት። [12]እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥ
ነቱን እንዳጸናለት፣ ስለ ሕዝቡ ስለ እስራኤልም
መንግሥቱን እንዳስፋለት ዳዊት ዐወቀ።
[13]ዳዊት ከኬብሮን ከሄደ በኋላ፣ ከበፊቶቹ
በተጨማሪ በኢየሩሳሌም ሌሎች ቁባቶች አስ
ቀመጠ፤ ሚስቶችም አገባ፤ ሌሎች ወንዶችና
ሴቶች ልጆችም ተወለዱለት። [14]በኢየሩሳሌም የተ
ወለዱለትም ልጆች ሳሙስ፣ ሶባብ፣ ናታን፣
ሰሎሞን፣ [15]ኢያቤሐር፣ ኤሊሱዔ፣ ናፌቅ፣ ያፍያ፣
[16]ኤሊሳማ፣ ኤሊዳሄ፣ ኤሊፋላት ይባላሉ።

## ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን ድል አደረገ

5፥17-25 ተጓ ምብ - 1ዜና 14፥8-17

[17]ዳዊት በእስራኤል ላይ ንጉሥ ሆኖ መቀባቱን
ፍልስጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፣ እርሱን ለመ
ፈለግ በሙሉ ኀይላቸው ወጡ፤ ዳዊት ግን
ይህን ሰምቶ ወደ ምሽጉ ወረደ። [18]በዚህ ጊዜም

ᵃ8 ወይም ማንጠልጠያ ኮላቦች
ᶜ8 ወይም በዳዊት የተጠሉ

5፥8 2ነገ20፥20፤ 2ዜና 32፥30፤ ማቴ21፥14
5፥9 1ነገ9፥15፡24
5፥10 2ሳሙ3፥1፤ 7፥9፤ መዝ24፥10
5፥11 1ነገ5፥1፡18፤ 2ዜና2፥3
5፥12 ዘኍ24፥7
5፥13 ዘዳ17፥17
5፥14 1ዜና3፥5፤ ሉቃ3፥31
5፥17 2ሳሙ23፥14 ፤1ዜና11፥16

መጠሪያ ሆነ (ኢሳ 1፥8፤ 2፥3 ይመ)።

5፥8 *በዚያም ዕለት ዳዊት... አለ፤* ታሪኩን በበለጠ የተ ሟላ ለማድረግ፣ 1ዜና 11፥6 ከዚህ ጋር ተጣምሮ ሊታይ ይችላል። ከተማዋን ለመያዝ በተካሄደው ጦርነት ኢዮአብ የነበረው ድርሻ፣ ከፍተኛ ወታደራዊ ችሎታውን ከማሳየቱም በላይ፣ የዳዊት ተዋጊ ሰራዊት የበላይ አዛዥ መሆኑንም በድጋሚ አረጋግጦለታል። *በውሃ መተላለፊያው፤* ለዚህ ሐረግ የተሰጠው አቻ የዕብራይስጥ ቃል ግልጽ ባይሆንም እንኳ፣ ምናልባት ከተማዋ በተከበበችበት ጊዜ ውሃ ለማግኘት የሚያስችለውን ከከተማዋ ውጭ ከግዮን ምንጭ እስከ ምሽጉ መግቢያ ድረስ ያለውን ምስጢራዊ የመተላለፊያ ቦይ ዳዊት ያወቀው ይመስላል (2ዜና 32፥30 ይመ)። *አንካሶችና ዕውሮች፤* ኢያቡሳውያንን የሚመለከት ምፀት (ከቍ 6 ጋር ያነጻጽሩ)። *ዕውሮችና አንካሶች ወደ ቤተ መንግሥት አይገቡም፤* ምሳሌው ምንም እንኳ ኢያቡሳውያን በከተማዋና በአካባቢዋ እንዲኖሩ ቢፈቀድላቸውም፣ ወደ ቤተ መንግሥት የመቅረብ ዕድል ያልነበራቸው መሆኑን ያሳያል።

5፥9 *ዙሪያዋን ገነባት፤* ለሕንጻዎች ተጨማሪ ቦታ በማመቻቸት በኰረብታው መዳፊያ ላይ የድንጋይ እርከን ተሠራ (የመሳ 9፥6 ማብ ይመ)።

5፥11 *የጢሮስ ንጉሥ ኪራም፤* የፊንቄ ንጉሥ አዲስ መንግሥት ለመሠረተው ለዳዊት በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ዕውቅና የሰጠ የመጀመሪያው መሪ ነበር። እስራኤል ወደ ጢሮስ የሚወስደውን የንግድ መተላለፊያ መስመር በቍጥጥሯ ሥር አድርጋ ስለ ነበርና፣ ጢሮስም አብዛኛውን የምግብ ሰብሏን የምታገኘው ከእስራኤል በመሆኑ፣ ኪራም ከእስራኤል ንጉሥ ጋር መልካም ግንኙነት መመሥረት እጅግ አስፈልጎት ነበር (ከጊታ ልደት በኋላ በመጀመሪያው ምእተ ዓመትም፤ ይህ ግንኙነት እንደዚሁ ቀጥሎ አል፤ ሐሥ 12፥20 ይመ)። ሁለቱ መንግሥታት እስከ ባቢሎናውያን ወረራ ድረስ የቀረበ ግንኙነት ነበራቸው። *ጢሮስ፤* በሜዲትራንያን ጠረፍ ከእስራኤል በስተ ሰሜን የምትገኝ የታወቀች የፊንቄ የባሕር ወደብ ነበረች (ሕዝ 26፥27 ይመ)።

5፥12 *እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ንጉሥነቱን እንዳጸናለት... ዐወቀ፤* በጥንቱ የቅርብ ምሥራቅ አመለካከት መሠረት አንድ ሰው በትረ መንግሥት ይዞ ዙፋኑን ላይ መውጣቱ የክብሩ መግለጫ ነው። *ስለ ሕዝቡ ስለ እስራኤልም፤* ልክ እንደ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ መሳፍንትና ሳሙኤል አገልግሎት ሁሉ፣ ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ በንጉሥነት ደረጃ ላይ መድረሱ፣ የእግዚአብሔር ሥራ እንደሆነና እየቀጠለ ላለው እስራኤልን የመታደግ አምላካዊ ዕቅድ አካል መሆኑን መሰከረ።

5፥13 *ከበፊቶቹ በተጨማሪ... ሌሎች ቁባቶች፤* የ3፥2 ማብ ይመ።

5፥14 *ሳሙስ፣ ሶባብ፣ ናታን፣ ሰሎሞን፤* 1ዜና 3፥5 የእነዚህ ሁሉ እናት ቤርሳቤህ መሆኗን ይገልጻል።

5፥17 *ዳዊት በእስራኤል ላይ ንጉሥ ሆኖ መቀባቱን ፍልስጥኤማውያን በሰሙ ጊዜ፤* በድርጊት ቅደም ተከተል መሠረት ሲታይ ፍልስጥኤማውያን ጥቃት የጀመሩት በቍ 3 ላይ የተጠቀሱት ክሥተቶች ከተፈጸሙ በኋላ ኢየሩሳሌም ገና ሳትማረክ የጀመረ ይመስላል (ቍ 6-14)፤ (ጸሐፊው ትረካውን ያዘጋጀው በአርእስት መልክ ነው፤ የ7፥1 ማብ ይመ)። ዳዊት የይሁዳ ንጉሥ መሆኑ ፍልስጥኤማውያንን ይህን ያህል አላሳሰባቸውም ነበር፤ ሳኦል ከተሸነፈ በኋላ ግን በአብዛኛው ተቈጣጥረውት በነበረው በሰሜኑ ክፍል ያላቸውን ጥቅም ለማስከበር ታጥቀው ተነሡ (1ሳሙ 31)። *ምሽጉ፤* በደቡብ ይሁዳ ውስጥ የሚገኝ ዳዊት በሳኦል በተሰደደ ጊዜ የተሸሸገበትን በረሓማ ስፍራ የሚያመለክት ሳይሆን አይቀርም (የ1ሳሙ 22፥4፤ 23፥14 ማብ ይመ)። ይህ

አስተማማኝ መጽሐፍ ቅዱሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ታሪካዊ መረጃዎች የሄሮድስን ቤተ መቅደስ (ከዚህም በፊት የዘሩባቤልንና የሰሎሞንን ቤተ መቅደሶች) ንጉሥ ዳዊት ለእግዚአብሔር መሠዊያ የሠራበት ቦታ ላይ እንደተሠራ ይናገራሉ። ዳዊት ይህን መሬት ለአውድማ ከሚገለገልበት ከኢያቡሳዊው ከኦርና ገዛ (2ሳሙ 24፡18-25)። በትውፊት ይህን ቦታ አብርሃም በሞሪያም ተራራ (ዘፍ 22፡1-19) ላይ ከሠራው መሠዊያ ጋር በማመሳሰል ልዩ ቅድስና ይሰጡዋል። የዘፍጥረት መጽሐፍ ጸሐፊ የሞሪያ ተራራን «ከእግዚአብሔር ተራራ» ጋር እና ሌሎች በአብርሃም መሠዊያዎች ላይ ከተጀመሩት የብሉይ ኪዳን መቅደሶች ጋር ያስተካክለዋል።



1. የኢያቡሳውያን ከተማ
2. የዳዊት ኢየሩሳሌም

1000 ዓ.ቅ.ክ.

ወደ 5 ሄክታር ስፋት ያላት
የከነዓናውያን ከተማ ኢያቡስ
በከፍታ ላይ ከተሠሩት ቅጥሮችና
በመሬት ውስጥ ካለው የውሃ
መስመር የተነሣ ራሷን ከጥቃት
መከላከል የምትችል ነበረች።
ዳዊት በ 1000 ዓ.ቅ.ክ.
ይህችን ከተማ ይዞ የመናገሻ
ከተማው አደረጋት።

ፍልስጥኤማውያን መጥተው በራፋይም ሸለቆ
ተበታትነው ሰፈሩ:: [19]ስለዚህም ዳዊት *እግዚ
አብሔርን*፣ "ፍልስጥኤማውያንን ወጥቼ ልው
ጋቸው? በእጄስ አሳልፈህ ትሰጠኛለህ?" ሲል
ጠየቀ::
*እግዚአብሔርም*፣ "አዎን ሂድ፤ በእርግጥ
ፍልስጥኤማውያንን በእጅህ አሳልፌ እሰጥሃ
ለሁ" አለው::
[20]ስለዚህም ዳዊት ወደ በአልፐራሲም[°] ሄዶ
ፍልስጥኤማውያንን ድል አደረጋቸው:: እር
ሱም "የጐርፍ ውሃ ጥሶ በመውጣት እንደሚያ
ፈራርስ፣ *እግዚአብሔርም* ጠላቶቼን በፊቴ አፈ
ራረሳቸው" አለ:: ከዚህ የተነሣም የዚያ ቦታ
ስም በአልፐራሲም ተባለ:: [21]ፍልስጥኤማውያ
ንም ጣዖቶቻቸውን ትተው ሸሽተው ስለ ነበር፣
ዳዊትና ሰዎቹ ወስደው አቃጠሏቸው::
[22]ፍልስጥኤማውያን እንደ ገና መጥተው
በራፋይም ሸለቆ ተበታትነው ሰፈሩ:: [23]ስለ
ዚህም ዳዊት *እግዚአብሔርን* ጠየቀ፤ *እግዚ
አብሔርም* እንዲህ አለው፤ "በስተ ኋላቸው
በኩል በመክበብ በበለሳኑ ፊት ለፊት ግጠ
ማቸው እንጂ በቀጥታ ወዳሉበት አትውጣ፤
[24]በበለሳኑ ዛፎች ጫፍ ላይ የሰልፍ ጉዞ
ድምፅ ስትሰማም፣ *እግዚአብሔር* የፍልስጥ
ኤማውያንን ሰራዊት ለመምታት ቀድሞህ
ወጥቶአል ማለት ነውና በዚያን ጊዜ በፍ
ጥነት ወደ ፊት ሂድ::" [25]ስለዚህም ዳዊት
*እግዚአብሔር* እንዳዘዘው አደረገ፤ ፍልስጥ
ኤማውያንንም ከገባዖን[″] እስከ ጌዝር ድረስ
እያሳደደ መታቸው::

5፥18 ኢሱ15፥8፤ 17፥15
5፥19 መሳ18፥5፤ 1ሳሙ23፥2
5፥20 ዘፍ38፥29
5፥21 ዘዳ7፥5፤ኢሳ 46፥2
5፥24 ዘፀ14፥24፤ መሳ4፥14
5፥25 ኢሱ10፥33፤ 2ሳሙ8፥12፤21፥15፤ ኢሳ28፥21
6፥2 ዘፍ3፥24፤ዘፀ 25፥22፤ዘሌ24፥16፤ ዘዳ28፥10፤ኢሱ 15፥9፤1ሳሙ4፥4፤ 7፥1፤መዝ99፥1፤ 132፥14፤ኢሳ63፥14
6፥3 ቁ7፤ዘኁ 7፥4-9፤1ሳሙ6፥7፤ 2ሳሙ7፥1
6፥5 ዘፀ15፥20፤ ዕዝ3፥10፤ነህ12፥27፤ መዝ150፥5
6፥6 ዘኁ4፥15፡ 19-20
6፥7 ዘፀ19፥22፤ 1ሳሙ5፥6፤6፥19፤25፥ 38፤1ዜና15፥13-15
6፥8 ዘፍ38፥29፤ መዝ7፥11

## ታቦቱ ወደ ኢየሩሳሌም መጣ

6፥1-11 ተጓ ምብ - 1ዜና 13፥1-14
6፥12-19 ተጓ ምብ - 1ዜና 15፥25-16፥3

**6** ዳዊት እንደ ገና ከእስራኤል የተመረጡ
በአጠቃላይ ሠላሳ ሺህ ሰዎች ሰበሰበ::
[2]እርሱና አብረውት ያሉት ሰዎች ሁሉ በታቦቱ
ላይ ባለው ኪሩቤል ላይ በተቀመጠው በሰራ
ዊት ጌታ *በእግዚአብሔርም* ስም[+] የተጠራውን
የእግዚአብሔርን ታቦት ከዚያ ለማምጣት በይሁዳ
ወዳለችው ወደ በአል ሄዱ:: [3]የእግዚአብሔርንም
ታቦት በአዲስ ሠረገላ ላይ አኑረው፣ በኮረብታ
ላይ ካለው ከአሚናዳብ ቤት አውጥተው አመጡ፤
ሠረገላውን ይነዱ የነበሩትም የአሚናዳብ ልጆች
ዖዛና አሒዮ ሲሆኑ፣ [4]የእግዚአብሔርም ታቦት በሠረ
ገላው ላይ ሆኖ[ᵅ]፣ አሒዮ ፊት ፊት ይሄድ ነበር::
[5]ዳዊትና የእስራኤል ቤት በሙሉ በዝማሬ፣ በበ
ገና፣ በመሰንቆ፣ በከበሮ፣ በጽናጽልና በቃጭል
ባለ ኀይላቸው ሁሉ *በእግዚአብሔር* ፊት ያሸበ
ሽቡ ነበር::
[6]ወደ ናኮን ዐውድማ ሲደርሱም በሬዎቹ
ስለ ተደናቀፉ፣ ዖዛ እጁን ዘርግቶ የእስራኤልን
ታቦት ያዘ:: [7]ዖዛ በድፍረት ይህን ስላደ
ረገ፣ *የእግዚአብሔር* ቍጣ በላዩ ላይ ነደደ፤
ስለዚህም *እግዚአብሔር* ቀሠፈው፤ እርሱም
በእግዚአብሔር ታቦት አጠገብ እዚያው ሞተ::
[8]*የእግዚአብሔር* ቍጣ ዖዛን ስለ ሰበረው፣
ዳዊት ተከፋ፤ እዘንም፤ ያም ቦታ እስከ ዛሬ
ድረስ ፔሬዝ ዖዛ[+] ተብሎ ይጠራል::

[°]20 *በአልፐራሲም* ማለት የሰባበረ ጌታ ማለት ነው::
[″]25 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል (1ዜና 14፥16 ይመ)፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ጌባ ይላል:: [+]2 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ግን፣ *ስም* የሚለውን አይጨምርም:: [ᵅ]4 የሙት ባሕር ጥቅልና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቲኩ ቅጅ ግን፣ *ኮረብታው ላይ ካለው ከአቢናዳብ ቤት ከእግዚአብሔር ታቦት ጋር አመጡት* ይላል:: [+]8 *ፔሬዝ ዖዛ* ማለት *ዖዛን ማፍረስ* ማለት ነው

ድርጊት ዳዊት ኢየሩሳሌምን ገና በእጁ እንዳላስገባ ያመለክታል::

5፥19 *ዳዊት እግዚአብሔርን... ጠየቀ፤* የ2፥1፤ የ1ሳሙ 2፥28፣ 22፥20፤ 23፥2 ማብ ይመ::

5፥20 *እግዚአብሔርም... አፈራረሳቸው... በአልፐራሲም፤* የዚህን ክፍል ማብ ይመ:: በእውነተኛው የእግዚአብሔር ፈቃድና ሥልጣን የሚመራው ንጉሥ ዳዊት ድሉ የእግዚአብሔር መሆኑን አመነ፤ ክብሩንም ለራሱ አላደረገም (የ1ሳሙ 10፥18፡27፤ 11፥13፤ 12፥11፤ 14፥23፤ 17፥11፡45-47 ማብ ይመ)::

5፥21 *ጣዖቶቻቸውን ትተው፤* እስራኤላውያን ታቦቱን ወደ ጦር ሜዳ እንደ ወሰዱት ሁሉ (የ1ሳሙ 4፥3 ማብ ይመ)፣ ፍልስጥኤማውያንም ድል የሚያስገኙላቸው ስለ መሰላቸው፣ ጣዖቶቻቸውን ወደ ጦሩ ሜዳ ይዘው ሄዱ:: *ወስደው አቃጠሉአቸው፤* ይህ የተፈጸመው በዘዳ 7፥5 ላይ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ነው (1ዜና 14፥12)::

5፥23 *አለው፤* ኢያሱ በተዋጋበት ጊዜ እንደ ታየው ሁሉ፣ ጦርነቱን የመራውና ከሰማያዊ ሰራዊቱ ጋር ሄዶ ጠላትን የወጋው ራሱ እግዚአብሔር ነው (ኢሱ 6፥2-5፤ 8፥1-2፤ 10፥8፡14፤ 11፥6 ይመ)፡ ዳዊት ያደረገው ጦርነት ኢያሱ ላካሄደው ጦርነት ተከታይና መደምደሚያ ነበር::

5፥24 *የሰልፍ ጉዞ ድምፅ፤* የጌታ ሰማያዊ ሰራዊት ወደ ጦርነት ሲጓዝ የተሰማው ድምፅ ነው::

6፥2 *በይሁዳ ወዳለችው ወደ በአል፤* የዚህን ክፍል ማብ ኢሱ 15፥60፤ 18፥14፤ 1ሳሙ 7፥1 ይመ:: *የእግዚአብሔርንም ታቦት፤* ዘፀ 25፥10-22፤ እንዲሁም የ1ሳሙ 4፥3-4፥21 ማብ ይመ:: በሳኦል ዘመነ መንግሥት ታቦቱ የተቀመጠው በቂርያት ይዓሪም ነበር:: *ስም የተጠራውን፤* ይህ ሐረግ በሌላ ቦታ ጥቅም ላይ የዋለው ባለቤትነትን ለማመልከት ነው (12፥28፤ ዘፀ 28፥19፤ ኢሳ 4፥1፤ 63፥19 ይመ):: *በኪሩቤል ላይ በተቀመጠው፤* የ1ሳሙ 4፥4 ማብ፤ እንዲሁም 1ዜና 28፥2 ("ለአምላካችን እግር ማረፊያ" የሚለውን ይመ):: የእስራኤል አምላክ ምድራዊ ዙፋን የሆነውን የታቦቱን ታላቅ ክብር ዳዊት አስተዋለ:: በእግዚአብሔር የሚመራ እውነተኛ ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን፣ በአገሪቱ ውስጥ እጅግ ወደሚታወቅና ምርጥ ወደ ሆነ ስፍራ ታቦቱን አምጥቶ በማስ ቀመጥ፣ እግዚአብሔር በእርሱና በሕዝቡ ላይ ንጉሥና ባለ ሥልጣን መሆኑን ለማረጋገጥ ፈለገ:: *ጌታ በእግዚአብሔርም፤* የ1ሳሙ 1፥3 ማብ ይመ::

6፥3 *በአዲስ ሠረገላ፤* ዳዊት ሌዋውያን ታቦቱን በትከሻቸው እንዲሸከሙ (1ዜና 15፥13-15 ይመ) የሚያዘውን የዘፀ 25፥12-14 እና የዘኍ 4፥5-6፡15 በመከተል ፈንታ የፍልስጥኤማውያንን ምሳሌ ተከተለ (1ሳሙ 6፥7 ይመ)፡ *ከአሚናዳብ ቤት፤* 1ሳሙ 7፥1 ይመ:: *የአሚናዳብ ልጆች ዖዛና አሒዮ፤* 1ሳሙ 7፥1 አልዓዛር የአሚናዳብ ልጅ መሆኑን ይገልጣል፤ "ልጅ" የሚለው የዕብራይስጡ ቃል "ወገን" ወይም "ዘር" የሚለውን ሰፋ ያለ ትርጒም ይይዛል::

6፥7 *በድፍረት... ስላደረገ፤* ምንም እንኳ መልካም ያደረገ ቢመስልም፣ ታቦት እንዴት መያዝ እንዳለበት ጌታ የሰጠውን ግልጽ ትእዛዝ ተላልፎአል (የቍ 3 ማብ ይመ፤ ከዘፀ 25፥15፤ ከዘኍ 4፥5-6፡15፤ ከ1ዜና 15፥13-15 ጋር ያነጻጽሩ፤ እንዲሁም የ1ሳሙ 6፥19 ማብ ይመ):: ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር እስራኤል በወጠነችው በዚህ ጠቃሚ አዲስ የሕይወት ጅማሬ ወቅት፣ እግዚአብሔርን እና ዝለማለን የሚሉ ሁሉ ሕጉን በከፍተኛ ጥንቃቄ ማክበር እንዳለባቸው፣ ጌታ ለዳዊትና ለእስራኤል አስደንጋጭና የማይረሳ ማሳሰቢያ ሰጣቸው (ዘሌ 10፥1-3፤ ኢሱ 7፥24-25፤ 24፥19-20፤ ሐሥ 5፥1-11 ይመ)::

6፥8 *ዳዊት ተከፋ፤* ዳዊት እግዚአብሔርን ለማክበር ያደረገው ጥረት የእግዚአብሔርን ቍጣ በማስከተሉ፣ ወዲያውኑ ተበሳጨ:: *እስከ ዛሬ፤* መጽሐፈ ሳሙኤል ሁለተኛ እስከ ተጻፈበት ጊዜ ድረስ ማለት ነው:: *ፔሬጽ ዖዛ፤* የዚህን ክፍል ማብ ይመ:: የቦታው ስም በቀላሉ የማይደረሰውን መለኮታዊ ማስጠንቀቂያ

9ዳዊት በዚያን ቀን *እግዚአብሔርን* ስለ
ፈራ “የእግዚአብሔር ታቦት እንዴት ወደ እኔ
ይመጣል?” አለ። 10ስለዚህ ዳዊት የእግዚአ
ብሔር ታቦት አብሮት እንዲሆን ወደ ዳዊት
ከተማ ይዞት ለመሄድ አልፈለገም፤ በዚህ
ፈንታ አቅጣጫ ለውጦ የጌት ሰው ወደ
ሆነው ወደ አቢዳራ ቤት ወሰደው። 11የእግዚአ
ብሔርም ታቦት የጌት ሰው በሆነው በአቢዳራ
ቤት ሦስት ወር ተቀመጠ፤ *እግዚአብሔርም*
አቢዳራንና ቤተ ሰዉን ሁሉ ባረከ።
12በዚህ ጊዜ፣ “በእግዚአብሔር ታቦት ምክንያት
የአቢዳራን ቤተ ሰብና ያለውን ሁሉ *እግዚአብሔር*
ባርኮለት” ብለው ለዳዊት ነገሩት። ስለዚህ ዳዊት
ወደዚያው ወርዶ፣ *የእግዚአብሔርን* ታቦት ከአቢ
ዳራ ቤት ወደ ዳዊት ከተማ በታላቅ ደስታ
አመጣው። 13እነዚያ የእግዚአብሔርን ታቦት ተሸክ
መው የነበሩት ሰዎች ስድስት ርምጃ በሄዱ
ቍጥር፣ አንድ በሬና አንድ የሰባ ጥጃ ይሠዋ
ነበር። 14ዳዊትም የበፍታ ኤፉድ በወገቡ
ታጥቆ በሙሉ ኀይሉ *በእግዚአብሔር* ፊት ይጨ
ፍር ነበር። 15እንዲህ ባለ ሁኔታም ዳዊትና
መላው የእስራኤል ቤት ሆ! እያሉና ቀንደ
መለከቱን እየነፉ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ
ላይ አመጡ።
16የእግዚአብሔር ታቦት ወደ ዳዊት ከተማ
ሲገባ፣ የሳኦል ልጅ ሜልኮል በመስኮት ሆና
ትመለከት ነበር፤ ንጉሥ ዳዊት *በእግዚአብሔር*
ፊት ሲዘልና ሲያሸበሽብ ባየችው ጊዜ በልቧ
ናቀችው።
17ከዚያም የእግዚአብሔርን ታቦት አምጥተው፣
ዳዊት በተከለለት ድንኳን ውስጥ አግብተው
በተዘጋጀለት ስፍራ አኖሩት፤ ዳዊትም የሚ
ቃጠል መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት*
*በእግዚአብሔር* ፊት አቀረበ። 18ዳዊት የሚ
ቃጠለውን መሥዋዕትና የኅብረቱን መሥዋዕት
ካቀረበ በኋላ ሕዝቡን በሰራዊት ጌታ *በእግዚ
አብሔር* ስም ባረከ። 19የእስራኤል ወገን ለሆ
ነው ለሕዝቡ ሁሉ፣ ለወንዱም ለሴቱም ለእያን
ዳንዱ ሰው አንዳንድ እንጀራ፣ አንዳንድ ሙዳ
ሥጋና አንዳንድ የዘቢብ ጥፍጥፍ ሰጠ፤ ከዚህ በኋላ
ሁሉም ወደየቤቱ ሄደ።
20ዳዊት ቤተ ሰዉን ለመመረቅ ወደ ቤቱ በተ
መለሰ ጊዜ፣ የሳኦል ልጅ ሜልኮል ልትቀበለው
ወጥታ፣ “ዛሬ የእስራኤል ንጉሥ በሎሌዎቹ ገረ
ዶች ፊት እንደ አንድ ተራ ሰው ራቍቱን
መታየቱ ክብሩ ሆኖ ነው!” አለችው።
21ዳዊትም እንዲህ አላት፤ “እምን ከአባትሽና
በቤቱ ካሉት ሁሉ አስበልጦ *በእግዚአብሔር* ሕዝብ
በእስራኤል ላይ ገዥ አድርጎ በመረጠኝ *በእግዚ
አብሔር* ፊት አሸብሽቤአለሁ፤ አሁንም አሸበሽባ
ለሁ። 22እንዲያውም ከዚህ ይልቅ ራሴን በፊቱ
ዝቅ አደርጋለሁ፤ ከዚህም የባሰ የተናቅሁ እሆና
ለሁ፤ ነገር ግን በጠቀስሻቸው ገረዶች ፊት እከበ
ራለሁ።”
23የሳኦልም ልጅ ሜልኮል እስከሞተችበት
ጊዜ ድረስ ልጅ አልወለደችም ነበር።

## እግዚአብሔር ለዳዊት የሰጠው ተስፋ

7፥1-17 ተጓ ምብ - 1ዜና 17፥1-15

7 ንጉሡ በቤተ መንግሥቱ ተደላድሎ ከተቀ
መጠና *እግዚአብሔርም* በዙሪያው ካሉት
ጠላቶቹ ሁሉ ካሳረፈው በኋላ፣ 2ነቢዩን ናታ
ንን፣ “እነሆ፤ እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤተ መን
ግሥት ውስጥ እኖራለሁ፤ የእግዚአብሔር ታቦት ግን
በድንኳን ውስጥ ይኖራል” አለው።

*17 በትውፊት *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል።

6፥9 1ሳሙ 6፥20
6፥10 1ዜና 15፥18፤ 26፥4-5
6፥11 ዘፍ 30፥27፤ 39፥5
6፥12 1ነገ 8፥1
6፥13 1ነገ 8፥5፡62፤ ዕብ 6፥17
6፥14 ዘፀ 15፥20፤ 19፥6፤1ሳሙ 2፥18
6፥15 ኢሱ 6፥5፤ መዝ 47፥5፤98፥6
6፥16 1ሳሙ 18፥27፤2ሳሙ 5፥7
6፥17 ዘሌ 1፥1-17፤ 1ነገ 8፥6፡62-64፤ 1ዜና 15፥1፤2ዜና 1፥4
6፥18 ዘፀ 39፥43፤ 1ነገ 8፥22
6፥19 ዘዳ 26፥13፤ ነህ 8፥10፤ሆሴ 3፥1
6፥20 1ሳሙ 19፥24
6፥21 1ሳሙ 13፥14፤15፥28፤2ሳሙ 5፥2፤ 7፥8፤1ዜና 5፥2፤ 17፥7፤ሚክ 5፥2
7፥1 ቍ 11፤2ሳሙ 6፥3፤1ዜና 22፥18
7፥2 ዘፀ 26፥1፤2ሳሙ 5፥11፤12፥1፤1ነገ 1፥8፡22፤3፥1፤7፥1፡2፡7፤ 9፥1፤1ዜና 29፥29፤ 2ዜና 8፥1፤9፥29፤ መዝ 132፥3፤ኢር 22፥14፤ሐጌ 1፥4፤ ሐሥ 7፥45-46

ያመለክታል (ኢሱ 7፥26 እና የዚህን ክፍል ማብ ይመ)።

6፥9 *ዳዊት... እግዚአብሔርን ስለ ፈራ፤* የዳዊት ንዴት ፍርሀት የተቀላቀለበት ነበር፤ ይህም ለእግዚአብሔር ተገቢ ከሆነው አክብሮት የመነጨ ፍጹም ፍርሀት ሳይሆን (1ሳሙ 12፥24፤ ኢሱ 24፥14)፣ የበደሉ ጥልቅ ስሜት ከፈጠረበት ጭንቀት የተነሣ የተከሠተ ፍርሀት ነበር (ዘፍ 3፥10፤ ዘዳ 5፥5)።

6፥10 *አቢዳራ፤* ምናልባት ትርጕሙ “የሰው አገልጋይ” ማለት ነው። *የጌት ሰው፤* ሌዋዊ ሳይሆን አይቀርም (የ1ዜና 13፥13 ማብ ይመ፤ ከ1ዜና 15፥18፡24፤ 16፥5፤ 26፥4-8፡15፤ 2ዜና 25፥24 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ብዙዎች ግን “የጌት ሰው” የሚለው ቃል አቢዳራ ጌት በተባለው በፍልስጥኤም ከተማ የተወለደ መሆኑን እንደሚያመለክት ያስባሉ (15፥18 ይመ)፤ ይሁን እንጂ የጌት ሰው የሚለው ቃል በዳን ወይም በምናሴ የምትገኘውን የሌዋውያንን ከተማ ጋትሪሞንን ሊያመለክት ይችላል (ኢሱ 21፥20-25)።

6፥12 *ዳዊት... ታቦት... አመጣው፤* የአቢዳራ ቤት መባረክ እግዚአብሔር ከቍጣው የተመለሰ መሆኑን ለዳዊት ግልጽ አደረገለት።

6፥13 *ታቦት ተሸክመው የነበሩት፤* ዳዊት በዚህ ጊዜ ከዚህ ቀደም የፈጸመውን ስሕተት አስታውሶታል (1ዜና 15፥13-15)። *ስድስት እርምጃ፤* በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር በረከት በሌዋውያን ላይ መሆኑን ለማሳየት በቂ ነው (1ዜና 15፥26 ይመ)።

6፥14 *የበፍታ ኤፉድ፤* የ1ሳሙ 2፥18 ማብ ይመ።

6፥16 *ናቀችው፤* ሜልኮል በዕለቱ በታየው ታላቅ ክሥተት አልተደሰተችም፤ ዳዊት ንጉሥ ሆኖ ሳለ፣ በአደባባይ ያደረገው ከንጉሥ ክብር ጋር እንደማይስማማ በማሰብ፣ የዳዊትን በሕዝብ ፊት እንደዚህ መሆን አጥብቃ ጠላችው (ቍ 20፥23 ይመ)።

6፥17 *የሚቃጠል መሥዋዕትና፤* ዘሌ 1 ይመ። *የኅብረት መሥዋዕት፤* የ1ሳሙ 11፥15 ማብ ይመ።

6፥18 *ሕዝቡን ... ባረከ፤* ከዚህ በኋላ ሰሎሞን በቤተ መቅደሱ የምረቃ በዓል ላይ እንዳደረገው ማለት ነው (1ነገ 8፥55-61)።

6፥20 *እንዲህ ሆኖ መቅረቡ፤* ዳዊት ልብሰ መንግሥቱን በመልበስ ፈንታ የበፍታ ኤፉድ መልበሱን (ቍ 14) ለመግለጥ ስትል ሜልኮል የተጠቀመችበት ምፀት ነው።

6፥23 *ሜልኮም... ልጅ አልወለደችም፤* ምናልባት ላሳየችው ትዕቢት የተሰጠ ቅጣት ሊሆን ይችላል፤ እንደዚሁም በሳኦል ቤት ላይ የመጣ ሌላው የእግዚአብሔር ፍርድ ሳይሆን አይቀርም።

7፥1-29፤ እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለት ታላቅ ተስፋ (ከመግቢያው “የመጽሐፉ ይዘትና መሪ ሐሳብ” የሚለውን ይመ)። እዚህ ላይ በግልጽ ኪዳን ተብሎ ባይጠቀስም፣ በሌላ ቦታ ግን ተመልክቶአል (23፥5፤ መዝ 89፥3፡28፡ 34፡39 ይመ፤ ከመዝ 132፥11 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ዳዊትም ኪዳን ተመሥርቶ እንደ ነበረ መረዳቱን በሚጠቀም ቋንቋ ምላሽ ይሰጣል (የ20፥28 ማብ ይመ)።

7፥1 *ንጉሡ በቤተ መንግሥቱ ተደላድሎ ከተቀመጠና... በኋላ፤ 5፥11፤* የ5፥12 ማብ ይመ። *እግዚአብሔርም በዙሪያው ካሉት ጠላቶቹ ሁሉ ካሳረፈው፤* በጊዜ ቅደም ተከተል ሲታይ፣ በ8፥1-14 የተመለከቱት ድሎች በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሱትን ክሥተቶች ሳይቀድሙ አልቀሩም። የሐሳቡ አቀራረብ ርእሳዊ ጥንቅር የሚታይበት ነው (የ5፥17 ማብ ይመ)፤ ም 6 የታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም መምጣት መዝግቦ ይዞአል፤ ም 7 ደግሞ የታቦቱ ማደሪያ ይሆን ዘንድ ዳዊት በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለማሠራት ያለውን ፍላጎት ይነግረናል።

7፥2 *ናታን፤* ይህ ነቢይ ማንነቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ነው (12፥1-14፤ 1ነገ 1 ይመ)። *በድንኳን፤* ቍ 6፤ 6፥17 ይመ። ዳዊት ራሱ በቤተ መንግሥቱ ተደላድሎ እየኖረ ኀያሉ አምላክ የእስራኤል ንጉሥ በድንኳን ውስጥ ማደሩ ተገቢ መስሎ አልታየውም (የ6፥2 እንዲሁም መዝ 132፥2-5፤ ሐሥ 7፥46 ይመ)። ዳዊት በመናገሻ ከተማው ለኀያሉ አምላክ ለእስራኤል ንጉሥ ማደ

[3]ናታንም፣ “እግዚአብሔር ካንተ ጋር ስለ
ሆነ፣ ያሰብኸውን ሁሉ አድርግ” አለው።
[4]በዚያች ሌሊት የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ
ሲል ወደ ናታን መጣ፤

[5]“ሂድና ባሪያዬን ዳዊትን፣ ‘እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ የምኖርበትን ቤት የምትሠ
ራልኝ አንተ አይደለህም፤ [6]እስራኤላውያንን
ከግብፅ ምድር ካወጣሁበት ቀን አንሥቶ
እስከ ዛሬ ድረስ ድንኳንን ማደሪያዬ አድ
ርጌ ከቦታ ወደ ቦታ ተጓዝሁ እንጂ
በቤት ውስጥ አልተቀመጥሁም። [7]ከእስ
ራኤላውያን ሁሉ ጋር በተንቀሳቀስሁበት ስፍራ
ሁሉ ሕዝቤን እስራኤልን እንዲጠብቁ ካዘ
ዝኋቸው መሪዎቻቸው አንዱን፣ “ከዝግባ ዕን
ጨት ለምን ቤት አልሠራህልኝም?” ያል
ሁት አለን?

[8]“አሁንም ባሪያዬን ዳዊትን እንዲህ
በለው፤ ‘የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ በሕዝቤ በእስራኤል ላይ
ገዥ እንድትሆን ከሜዳ አነሣሁህ፤ ከበግ
ጥበቃም ወሰድሁህ፤ [9]በሄድህበት ሁሉ
እኔ ከአንተ ጋር ነበርሁ፤ ጠላቶችህንም
ሁሉ ከፊትህ አጠፋሁልህ፤ አሁንም ስማ
ቸው በምድር ላይ ከገነነው እጅግ ታላ
ላቅ ሰዎች እንደ አንዱ ስምህን ገናና
አደርገዋለሁ፤ [10]የራሱ የሆነ መኖሪያ እን
ዲኖረውና ከእንግዲህ ወዲያ እንዳይናወጥ፣
ለሕዝቤ ለእስራኤል ቦታ እሰጠዋለሁ፤ እጸ
ናዋለሁም። ከዚህ በፊት እንደሆነውም ከእ
ንግዲህ ወዲህ ክፉ ሕዝብ አይጨቍናቸውም፤
[11]ለሕዝቤ ለእስራኤልም መሪዎች[a] ከሾም
ሁለት ጊዜ አንሥቶ እንዳደረጉበት ሁሉ
ከእንግዲህ አያደርጉበትም፤ እንዲሁም ከጠ
ላቶችህ ሁሉ እጠብቅሃለሁ። “ ‘እግዚአ
ብሔር ራሱ ቤት እንደሚሠራልህ ይነግር
ሃል፤ [12]ዕድሜህን ጨርሰህ ከአባቶችህ ጋር
በምታንቀላፋበት ጊዜ፣ በእግርህ እንዲተካ
ከአብራክህ የተከፈለ ዘር አስነሣልሃለሁ፤
መንግሥቱንም አጸናለሁ። [13]ለስሜ ቤት
የሚሠራ እርሱ ነው፤ እኔም የመንግሥቱን
ዙፋን ለዘላለም አጸናለሁ። [14]አባት እሆነዋ
ለሁ፤ እርሱም ልጄ ይሆናል። በደል ቢፈ
ጽም ግን ሰዎች በሚቀጡበት በትር እቀ
ጣዋለሁ፤ የሰው ልጆችም በዐለንጋ እንደ
ሚገረፉ እገርፈዋለሁ። [15]ምሕረቴን ከአ
ንተ በፊት ካስወገድሁት ከሳኦል እንዳራቅሁ
ሁሉ ከእርሱ አላርቅም። [16]ቤትህና መንግሥ
ትህ በፊቴ[b] ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤ ዙፋን
ህም እንደዚሁ ለዘላለም የጸና ይሆናል።’ ”

7፥3 1ሳሙ 10፥7፤ መዝ 132፥1-5
7፥5 1ነገ 5፥3-5፤ 8፥19፤1ዜና 22፥8፤ 28፥3
7፥6 ዘፀ 40፥18:34፤ ኢያ 18፥1፤1ነገ 8፥16፤ሐሥ 7፥45
7፥7 ዘሌ 26፥11-12፤ ዘዳ 23፥14፤2ሳሙ 5፥2፤1ነገ 8፥27፤ ኢሳ 66፥1
7፥8 1ሳሙ 2፥7-8፤ 9፥16፤16፥1:11፤ 2ሳሙ 6፥21፤1ዜና 21፥17፤መዝ 74፥1፤ 78፥70-72፤አሞ 7፥15 ፤2ቆሮ 6፥18
7፥9 ዘፀ 11፥3፤1ሳሙ 18፥14፤2ሳሙ 5፥10፤ መዝ 18፥37-42
7፥10 ዘፀ 15፥17፤ 2ነገ 21፥8፤2ዜና 33፥8 ፤መዝ 89፥22-23፤ 147፥14፤ኢሳ 5፥1-7፤ 54፥14፤60፥18
7፥11 ቍ 1፤ዘፀ 1፥21 ፤መሳ 2፥16፤1ሳሙ 12፥ 9-11፤25፥28፤1ነገ 2፥ 24፤መዝ 89፥35-37፤ ኢሳ 7፥2፤ማቴ 1፥1፤ ሉቃ 1፥32-33፤ሐሥ 13፥22-23፤2ጢሞ 2፥8
7፥12 ዘፍ 15፥15፤ 1ነገ 2፥1፤8፥20፤2ዜና 23፥3፤መዝ 132፥11- 12፤ኤር 30፥21፤33፥ 15፤ሐሥ 13፥36
7፥13 ቍ 16፤ዘፍ 9፥16፤ዘዳ 12፥5፤ 16፥11፤2ሳሙ 22፥51፤1ነገ 2፥4:45፤5፥5፤6፥12፤8፥19:29፤2ነገ 21፥4:7 ፤1ዜና 22፥10፤28፥6፤2ዜና 6፥16፤7፥18፤13፥5፤21፥7፤መዝ 89፥3-4:29: 35-37ምሳ 25፥5፤ኢሳ 9፥7፤16፥5፤ኤር 17፥25፤33፥17:21፤ዳን 7፥27
7፥14 ዘዳ 8፥5፤1ነገ 11፥34፤1ዜና 22፥10፤መዝ 2፥7፤89፥26:30-33፤ ምሳ 13፥24፤ኤር 3፥19፤ማቴ 3፥17፤ዮሐ 1፥49፤2ቆሮ 6፥18፤ዕብ 1፥5፤12፥ 7፤ራእ 21፥7 7፥15 ቍ 25፤1ሳሙ 13፥13፤15፥28፤16፥14፤1ነገ 2፥4፤ 6፥12፤8፥25፤9፥5፤11፥13:32፤2ነገ 19፥34፤2ዜና 6፥16፤7፥18፤21፥7፤ መዝ 89፥24:33፤ኤር 33፥17 7፥16 ቍ 13፤መዝ 9፥7፤89፥36-37፤ 93፥2፤103፥19፤ሉቃ 1፥33

[a] 11 በትውፊት፣ መሳፍንት ይባላል
[b] 16 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆችና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *በፊትህ* ይላሉ

ሪያ ይሆነው ዘንድ ቤተ መቅደስ መሥራት ፈለገ። ዳዊት ለታቦቱ
ማደሪያ ይሆን ዘንድ ቤተ መቅደስ ለማሠራት መፈለጉ ለእግዚአብሔር
ያለው ፍቅር የቱን ያህል መሆኑን ያሳያል።

7፥3 *ናታንም... አለው፤* ዳዊት ነቢይን በማማከር የእግዚ
አብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ለማወቅ ፈለገ፤ ነገር ግን ነቢዩ
ናታን ከእግዚአብሔር ሳይገለጥለት በድፍረት አበረታታው።

7፥5 *አንተ አይደለህም፤* የዳዊት ምኞት የሚደገፍ ነው
(1ነገ 8፥18-19)፤ ነገር ግን የእርሱ ተሰጥኦና ተልእኮ እስራኤል
በተደላደለና አስተማማኝ በሆነ ሰላም በተስፋዪቱ አገር እስከ
ሚያርፍ ድረስ፣ የእግዚአብሔርን ጦርነት መዋጋት ነበር (ቍ
10፤ 1ነገ 5፥3 ይመ)።

7፥7 *ለምን ቤት አልሠራህልኝም? ያለሁት አለን?* ጌታ
በቅድሚያ የሚፈልገውን ጕዳይ ዳዊት ለይቶ ለማስተዋል አል
ቻለም፤ እግዚአብሔር ለእስራኤል መሪዎች መርጦ በሥልጣን
ላይ ያስቀመጣቸው ሕዝቡን በትክክል እንዲያስተዳድርና እንዲን
ከባከቡ ነው (ዳዊትን ከበግ እረኛነት ያመጣውም ለዚሁ ዐቢይ
ጕዳይ ነው ቍ 8)።

7፥9 *ጠላትህንም ሁሉ ከፊትህ አጠፋሁልህ፤* የቍ 1 ማብ ይመ።

7፥10 *ለሕዝቤ ለእስራኤል ቦታ እሰጠዋለሁ፤* እግዚአብሔር
ዳዊትን ንጉሥ ያደረገው ለዚህ ዐላማ ነው፤ ይህንኑ ዐላማውን
ከፍጻሜ የሚያደርሰውም በዳዊት አማካይነት ነው። *ከዚህ በፊት፤*
በግብፅ የነበሩትን ሁኔታ የሚመለከት ነው።

7፥11 *መሪዎች፤* በመሳፍንት ዘመን የነበሩትን የሚመ
ለከት ነው (የዚህን ክፍል ማብ ይመ)። *ከጠላቶችህ ሁሉ እጠብ
ቅሃለሁ፤* ቍ 1 እና 9 ይመ። ዳዊት አስቸጋሪ በሆኑ መንግ
ሥታት ላይ የተቀዳጃቸው ድሎች እዚህ ላይ የተሟሉ ይሆናሉ፤
ከዚህም የተነሣ የተገኘው ዕረፍት ለወደፊቱም የተረጋገጠ ይሆ
ናል። *እግዚአብሔር ራሱ ቤት እንደሚሠራልህ ይነግርሃል፤* ይህን ዐረ
ፍተ ነገር በቍ 5 ላይ ከተመለከተው መልስ አዘል ጥያቄ ጋር
ያነጻጽሩ። ዳዊት ለጌታ ቤት (ቤተ መቅደስ) የማይሠራ መሆኑን
እግዚአብሔር ውብ በሆኑ ቃላት ገለጸለት፤ ይልቁንም እግዚአ
ብሔር ለዳዊት ዘላለማዊ ቤት (ሥርወ መንግሥት) ይመሠርት
ለታል (ቍ 16)። ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር እስራ
ኤልን በመገንባት ላይ ነው፤ አሁን ደግሞ “በተስፋ ምድር ላይ
አሳርፋችኋለሁ” የሚለው ተስፋ ይፈጸም ዘንድ፣ የዳዊትን መንግ
ሥት ለማጠናከር ቃል ይገባል፤ መንግሥቱ ውጤታማ ሲሆን
የቻለውም እግዚአብሔር ስለ ገነባው ነው። እግዚአብሔር ከዳዊት
ጋር የገባው ይህ ቃል ኪዳን እንደ ኖኅ፣ አብርሃምና ፊንሐስ
ሁሉ፣ ጽኑና አዎንታዊ በሆነው የእግዚአብሔር ዐላማ ላይ የተመ
ሠረተ ምክንያት አልባ ኪዳን ነበረ (የዘፍ 9፥9 ማብ ይመ)። ይህ
ኪዳን በመጨረሻ ተፈጻሚነት የሚያገኘው፣ ከይሁዳ ነገድና ከዳ
ዊት ቤት በተወለደው በክርስቶስ ንግሥና ነው (መዝ 89፥30-38፤
ኢሳ 9፥1-7፤ ማቴ 1፥1፤ ሉቃ 1፥32-33:69፤ ሐሥ 2፥30፤ 13፥23፤
ሮሜ 1፥2-3፤ 2ጢሞ 2፥8፤ ራእ 3፥7፤ 22፥16)።

7፥12 *ከአብራክህ የተከፈለ ዘር አስነሣልሃለሁ፤* ከሳኦል
ጋር ሲነጻጸር የዳዊት ሥርወ መንግሥት በዘሮቹ ቀጥሎአል።

7፥13 *ለስሜ ቤት የሚሠራ እርሱ ነው፤* እግዚአብሔር በቅ
ድሚያ የሚፈልገው፣ እስራኤል ዕረፍት እስከሚያገኝና የዳዊት መን
ግሥትም ደኅንነት እስከሚረጋገጥ ድረስ (በልጁ የሥልጣን ዘመን )፤
ዙፋኑ (ታቦቱ) በመጨረሻ መጥቶ ሊያርፍበት የሚችለው የራሱ ንጉ
ሣዊ ቤት ሥራ እንዲቆይ ነው (1ዜና 6፥31፤ 28፥2-3)። በቍ 5 ላይ
“ስሜ” የሚለው ቃል “እኔ” ከሚለው ጋር አንድ ነው (የ1ሳሙ
25፥25 ማብ ይመ)።

7፥14 *አባት እሆነዋለሁ... ልጄ፤* ይህ ቤተ ሰባዊ አባ
ባል እግዚአብሔር በዳዊት ዙፋን ላይ ወደፊት ከሚያስቀም
ጣቸው የዳዊት ዘሮች ጋር እንዲኖረው ቃል የገባበትን ልዩ
ግንኙነት ይገልጣል፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለሚመራበት ሕጉ
ዋና ወኪል በመሆን ሕዝቡን በእግዚአብሔር ስም ለመምራት
ዳዊት በእግዚአብሔር ተመርጦ የነገሠ መሆኑንም ያመለክ
ታል (የመዝ 2፥7፤ 45፥6፤ 89፥27 ማብ ይመ)፤ ይህ ተስፋ
በመጨረሻ ተፈጻሚነት የሚያገኘው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ
ነው (ማቴ 1፥1፤ ማር 1፥11፤ ዕብ 1፥5 ይመ)።

7፥15 *ምሕረቴን፤* ምን ጊዜም የማይሻርና የማይደበዝዝ የእግ
ዚአብሔር ፍቅር (የመዝ 6፥4 ማብ ይመ)።

7፥16 *መንግሥትህ... ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፤* የቍ 11
ማብ ከመግቢያው “የመጽሐፉ ይዘትና መሪ ሐሳብ” የሚለውን
ይመ። ለዳዊት ቤት የተሰጠው የዘላለም መንግሥት የተስፋ ቃል
ከዘመን በኋላ ለተነገሩት ትንቢቶች ማእከላዊ መሠረት ሲሆን፣

17ናታንም የዚህን የጠቅላላውን ራእይ ቃል
በሙሉ፣ ለዳዊት ነገረው።

## የዳዊት ጸሎት

7፥18-29 ተጓ ምብ - 1ዜና 17፥16-27

18ከዚያም ንጉሥ ዳዊት ገብ፤ *በእግዚአብሔር*
ፊት ተቀምጦ እንዲህ አለ፤
"ልዑል *እግዚአብሔር* ሆይ፤ እስከዚህ
ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ
ምንድን ነው? 19ልዑል *እግዚአብሔር*
ሆይ፤ ይህ በፊትህ ጥቂት ሆኖ ሳለ፤
አንተ ግን ስለ ወደፊቱ የባሪያህ ቤት
ተናገርህ፤ ልዑል *እግዚአብሔር* ሆይ፤
ከሰው ጋር የምታደርገው ግንኙነት ለካ
እንዲህ ነው?
20"ዳዊት ከዚህ በላይ ምን ሊልህ ይች
ላል? ልዑል *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ባሪያ
ህን አንተ ታውቀዋለህና! 21ስለ ቃልህና
እንደ ልብህ ሐሳብ ይህን ታላቅ ነገር
አድርገሃል፤ ባሪያህም እንዲያውቀው ገል
ጸህለታል።
22ልዑል *እግዚአብሔር* ሆይ፤ እንዴት
ታላቅ ነህ! ከቶ የሚመስልህ ማንም የለም፤
በጆሮአችን እንደሰማነው ሁሉ፣ ከአንተ
በቀር ስምሳክ የለም።
23ለራሱ ሕዝብ ይሆን ዘንድ ሊታደገው፣
*እግዚአብሔር* በፊቱ እንደሄደለት ሕዝብ፣
ለራሱም ስም ያደርግ ዘንድ አሕዛብንና አማ
ልክቶቻቸውን ከፊቱ አሳዶ ታላቅና አስፈሪ
ታምራት እንዳደረገለትና ከግብፅም እንደ
ተቤዠው እንደ ሕዝብህ እንደ እስራኤል
ያለ በምድር ላይ ማን አለ? 24ሕዝብህን
እስራኤልን ለዘላለሙ ያንተው የራስህ

7፥18 ዘፀ3፥11
7፥19 ኢሳ55፥8-9
7፥20 1ሳሙ16፥7፤ ኢሳ38፥15፤ዮሐ 21፥17
7፥22 ዘፀ8፥10፤ 9፥14፤10፥2፤20፥4፤ ዘዳ3፥24፤መሳ6፥13፤ መዝ44፥1፤48፥1፤ 77፥13፤86፥10፤ ኤር10፥6
7፥23 ዘኍ6፥27፤ ዘዳ4፥32-38፤7፥7-8፤ 9፥26፤10፥21፤33፥29፤ 1ሳሙ12፥22
7፥24 ዘፀ6፥6-7፤ ዘዳ26፥18፤መዝ 48፥14
7፥25 ቍ15፤ዘኍ 23፥19፤2ዜና1፥9
7፥26 ዘፀ6፥3፤ነህ 9፥5፤1ሳሙ25፥28፤ መዝ72፥19፤96፥8፤ ሚል6፥9
7፥28 ዘፀ34፥6፤ ዮሐ17፥17
7፥29 ዘኍ6፥23-27
8፥1 መዝ60፥8፤ 87፥4፤108፥9፤ ዕብ11፥32-33
8፥2 ዘፍ19፥37፤ ዘኍ21፥29፤መሳ 3፥15፤ኢሳ45፥14

ሕዝብ አድርገህ አጽንተኸዋል፤ *እግዚአ
ብሔር* ሆይ፤ አንተም ስምሳክ ሆንኸዋል።
25"አሁንም *እግዚአብሔር* ስምሳክ ሆይ፤
ለባሪያህና ለቤቱ የሰጠኸውን ተስፋ ለዘላ
ለም ጠብቅለት፤ እንደተናገርኸውም
ፈጽም፤ 26ስለዚህ ስምህ ለዘላለም ታላቅ
ይሆናል፤ ሰዎችም፣ 'የሰራዊት ጌታ *እግ
ዚአብሔር* የእስራኤል ስምሳክ ነው!' ይላሉ።
የባሪያህ የዳዊትም ቤት በፊትህ የጸና
ይሆናል።
27"አቤቱ የእስራኤል ስምሳክ የሰራዊት
ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ 'እኔ ለአንተ ቤት
እሠራልሃለሁ' ብለህ ይህን ለባሪያህ ገል
ጸህለታል። ስለዚህ ባሪያህ ይህችን ጸሎት
ወደ አንተ ለማቅረብ በልቡ ደፈረ። 28ልዑል
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ስምሳክ ነህ፤ ቃል
ህም የታመነ ነው፤ ይህንንም መልካም ነገር
ለማድረግ ለባሪያህ ተስፋ ሰጥተኸዋል፤
29በፊትህ ለዘላለም ጸንቶ እንዲኖር፣ አሁ
ንም የባሪያህን ቤት እባክህ ባርክ። ልዑል
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ይህን አንተው ራስህ
ተናግረሃል፤ በበረከትህም የባሪያህ ቤት ለዘ
ላለም ይባረካል።

## ዳዊት የተቀዳጃቸው ድሎች

8፥1-14 ተጓ ምብ - 1ዜና 18፥1-13

8ከዚህ በኋላ ዳዊት ፍልስጥኤማውያንን
ድል አደረጋቸው፤ በቍጥጥሩም ሥር አዋ
ላቸው፣ ሜቴግ አማ የተባለችውንም ከተማ
ከፍልስጥኤማውያን ቍጥጥር ነጻ አደረጋት።
2እንዲሁም ዳዊት ሞዓባውያንን ድል አደረገ፤
በመሬት ላይ አጋድሞ በገመድ ለካቸው፤ በገ
መድ ከተለኩትም ሁለት እጅ ሲገድል፣ አንድ

---

መሲሓዊው ተስፋ በእስራኤል ውስጥ እያደገ እንዲሄድ ኀይለኛ ግፊት አድርጓል።

7፥18-29፤ እግዚአብሔር ይህን የመሰለ ተስፋ ለእርሱና ለዘሮቹ መስጠቱ ያስደነቀው መሆኑን ዳዊት በጸሎት ይገልጣል። ነገር ግን ዳዊት እግዚአብሔር ለእርሱ የገባለት ቃል ለእስራኤል መሆኑን፣ ይኸውም ዐላማው እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን ኪዳናዊ ተስፋ ለመፈጸም እንደ ሆነ፣ የተስፋው ፍጻሜ የመጨረሻ ግብም በዓለም ዙሪያ እግዚአብሔር እንዲመሰገንና እንዲከበር መሆኑን ያውቃል።

7፥18 *ገባ፤* ምናልባት ታቦቱ ወደ ዐረፈበት ወደ ድንኳኑ ውስጥ (6፥17) ሊሆን ይችላል። *በእግዚአብሔር ፊት ተቀምጦ፤* ታቦቱ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የመገኘቱ ምልክት ነበር (ዘፀ 25፥22፤ እንዲሁም የ1ሳሙ 4፥3-4:21 ማብ ይመ)።

7፥19 *ከሰው ጋር የምታደርገው ግንኙነት ለካ እንደዚህ ነው?* የዚህ ዐረፍተ ነገር ትርጕም በትክክል አይታወቅም (ከ1ዜና 17፥17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ "ልዑል እግዚአብሔር ሆይ፣ ለሰው የምትሰጠው ሕግ ከቶ ይህ ይሆን እንዴ!" በማለትም በቃለ አጋኖ መልክ ተገልጦአል፤ ከዚያም ዳዊትንና ቤቱን በተመለከተ ለተሰጠው መለኮታዊ ትእዛዝ መደምደሚያ እንደሆነም ግንዛቤ አግኝቶአል።

7፥20 *ታውቀዋለህና!፤* ወይም "ለይተኸዋል" አሊያም "መርጠኸዋል" በዘፍ 18፥19፤ አሞ 3፥2 "መርጬዋለሁ" የሚለውን ይመ። ዳዊት የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል እንደ ኪዳን አድርጎ ይመለከተዋል (23፥5)።

7፥21 *ቃልህና፤* ምናልባት እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን የኪዳን ተስፋ ሊያመለክት ይችላል።

7፥22 *ከቶ የሚመስልህ ማንም የለም፤* 22፥32፤ 1ሳሙ 2፥2 ይመ።

7፥23 *ለራሱ ሕዝብ ይሆን ዘንድ ሊታደገው፣ እግዚአብሔር በፊቱ እንደሄደለት ሕዝብ፣... እንደ እስራኤል ያለ በምድር ላይ ማን አለ?* እስራኤል የተለየ ሕዝብ መሆኑ ከእግዚአብሔር ምርጫ የተገኘ እንጂ፣ ከሕዝቡ ማንነት የተነሣ የመጣ አይደለም (ዘዳ 7፥6-8፤ 33፥26-29 ይመ)። *ለራሱም ስም ያደርግ ዘንድ፤* ከእስራኤል ጋር በነበረው ግንኙነት የታየው የእግዚአብሔር የምርጫ ፍቅር መሠረት በእግዚአብሔር በራሱ ሉዓላዊ ዐላማ ላይ እንጂ፣ በእስራኤል ሕዝብ ባሕርይ ወይም መልካምነት ላይ አልቆመም (ዘዳ 7፥6-8፤ 9፥4-5፤ 1ሳሙ 12፥22፤ ነህ 9፥10፤ ኢሳ 63፥12፤ ኤር 32፥20-21፤ ሕዝ 36፥22-38 ይመ)።

7፥24 *እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተም አምላክ ሆንኸዋል፤* እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ እንደ መሆኑ፣ መጠን ለዳዊት የገባውን ቃል ለሕዝቡም ገባላቸው።

7፥27 *እነሆ ባሪያህ ይህችን ጸሎት ወደ አንተ ለማቅረብ በልቡ ደፈረ፤* ዳዊት ለጸሎቱ መታመኛ ያደረገው እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ነው።

7፥28 *መልካም ነገር ለማድረግ፤* በኪዳኑ አማካይነት የተገኘውን በረከት ለመግለጽ የተለመደ የመደምደሚያ ቃል ነው (ለምሳሌ 1ሳሙ 2፥32 "በረከት" ዘኍ 10፥29:32፤ ዘዳ 26፥11፤ ኢያ 21፥45፤ 23፥14 "መልካም ነገር"፤ ኢሳ 63፥7፤ ኤር 29፥32፤ 32፥40-41 "ቸርነት"፣ "መልካም ነገር" የሚሉትንና 33፥9 ይመ)።

8፥1 *ከዚህ በኋላ፤* ከጊዜ ቅደም ተከተል አኳያ ሲታዩ፣ የዚህ ምዕራፍ ድርጊቶች ወይም ደግሞ ከእነዚህ ውስጥ ብዙዎቹ ምናልባት በም 5 ና 6 መካከል መሆን የሚገባቸው ነበሩ (7፥1 እና ማብ ይመ)። *ሜቴግ አማ፤* ቦታው አይታወቅም፤ ነገር ግን ከጌት አጠገብ የሚገኝ ስፍራ ሳይሆን አይቀርም (1ዜና 18፥1 ይመ)።

8፥2 *ሞዓባውያን፤* በሙት ባሕር ምሥራቅ የሰፈሩ የሎጥ የልጅ ልጆች ናቸው (ዘፍ 18፥37 ይመ)። ሳኦል ከሞዓባውያን ጋር ተዋግቶአል (1ሳሙ 14፥47)፤ ዳዊትም በስደቱ ወቅት ለወላጆቹ መጠጊያ ያገኘላቸው በዚሁ ስፍራ ነበር (1ሳሙ 22፥3-4)፤

እጅ ግን በሕይወት ይተው ነበር። ስለዚህ ሞዓ
ባውያን የዳዊት ተገዦች ሆኑ፤ ገበሩለትም።
[3]ከዚህም በቀር ዳዊት በኤፍራጥስ ወንዝ አጠ
ገብ ያለውን ግዛት መልሶ ለመያዝ በሄደ ጊዜ፣
የሱባን ንጉሥ የረአብን ልጅ አድርአዛርን ወጋው።
[4]ዳዊትም አንድ ሺህ ሠረገሎች፣ ሰባት ሺህ ፈረ
ሰኞችና[ፐ] ሃያ ሺህ እግረኞች ማረከበት። ቍጥራ
ቸው መቶ የሆነ የሠረገላ ፈረሶች ብቻ ሲቀሩ
ሌሎቹን በሙሉ ቋንጃቸውን ቈረጠ።
[5]የደማስቆዎቹ ሶርያውያን የሱባን ንጉሥ
አድርአዛርን ለመርዳት በመጡ ጊዜ ዳዊት
ሃያ ሁለት ሺህ ሰው ገደለባቸው። [6]ከዚያም
የደማስቆ ክፍል በሆነው የሶርያውያን ግዛት
የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ። ሶርያውያን ተገ
ዙለት፤ ገበሩለትም። እግዚአብሔርም ዳዊት
በሄደበት ሁሉ ድልን ሰጠው።
[7]ዳዊት የአድርአዛር ሹማምንት ያነገቧ
ቸውን የወርቅ ጋሻዎች ወስዶ ወደ ኢየሩሳ
ሌም አመጣቸው። [8]ንጉሡ ዳዊት ቤጣህና[አ]
ቤሮታይ ከተባሉ ከአድርአዛር ከተሞችም እጅግ
ብዙ ናስ አጋዘ።
[9]የሐማት ንጉሥ ቶው ዳዊት መላውን የአድ
ርአዛርን ሰራዊት ማሸነፉን በሰማ ጊዜ፣ [10]ቶው
ከአድርአዛር ጋር ሁልጊዜ ይዋጋ ስለ ነበር፣ ሰላ
ምታና በአድርአዛር ላይ ስለ ተቀዳጀውም ድል
የደስታ መግለጫ እንዲያቀርብለት፣ ልጁን ዮራ
ምን ወደ ንጉሥ ዳዊት ላከው፤ እርሱም የብር፣
የወርቅና የናስ ዕቃ ይዞ መጣ።
[11]ንጉሥ ዳዊትም፣ ቀድሞ ካስገበራቸው መን
ግሥታት ሁሉ በገኘለት ብርና ወርቅ እንዳደ
ረገው እነዚህንም ዕቃዎች ለእግዚአብሔር ቀደሳ
ቸው። [12]የገበሩትም መንግሥታት ኤዶምና[ከ]

8፥3 ዘፍ2፥14፤1ሳሙ14፥47፤2ሳሙ10፥16፡19፤1ነገ11፥23
8፥4 ዘፍ49፥6፤ኢያ11፥9
8፥5 ዘፍ14፥15፤2ሳሙ10፥6፤1ነገ11፥24፤2ነገ8፥7፤14፥28
8፥6 2ሳሙ3፥18፤10፥19፤1ነገ20፥34
8፥7 1ነገ10፥16፤14፥26፤2ነገ11፥10
8፥8 ሕዝ47፥16
8፥9 1ነገ8፥65፤2ነገ14፥28፤2ዜና8፥4፤ሉቃ14፥31-32
8፥11 ቍ12፤1ነገ7፥51፤15፥15፤1ዜና26፥26፤2ዜና5፥1
8፥12 ቍ2፤ዘኍ24፥18፡20፤1ሳሙ27፥8፤2ሳሙ5፥25፤10፥14
8፥13 2ሳሙ7፥9፤2ነገ14፥7፤1ዜና18፥12፤መዝ60 ርዕስ
8፥14 ዘፍ27፥29፡37-40፤ዘኍ24፥17-18፤2ሳሙ22፥44፤መዝ108፥9፤144፥10፤ኢሳ34፥5፤63፥1፤ኤር49፥7፤ሕዝ25፥12
8፥15 ዘፍ18፥19፤1ነገ11፥38፤14፥8፤15፥11፤22፥43፤2ነገ12፥2፤ኢዮ29፥14፤መዝ5፥12፤119፥121፤ዕብ11፥33
8፥16 2ሳሙ2፥13፤20፥24፤1ነገ4፥3፤ኢሳ36፥3፡22
8፥17 1ሳሙ2፥35፤2ሳሙ15፥24፡29፤20፥25፤1ነገ1፥8፤4፥3፡4፤2ነገ12፥10፤19፥2፤22፥3፤1ዜና6፥8፡53፤16፥39፤24፥3፤27፥17፤2ዜና31፥10፤ኢሳ36፥3፤ኤር36፥12፤ሕዝ40፥46፤43፥19፤44፥15፤48፥11፤ማር2፥26

ሞዓብ፣ አሞናውያን፣ ፍልስጥኤማውያንና
አማሌቃውያን ነበሩ። እንዲሁም ከሱባ ንጉሥ
ከረአብ ልጅ ከአድርአዛር የወሰደውን ምርኮ
ለእግዚአብሔር ቀደሰ።
[13]ዳዊት የጨው ሸለቆ በተባለው ስፍራ
ዐሥራ ስምንት ሺህ ኤዶማውያንን[ኸ] ገድሎ
ከተመለሰ በኋላ ስሙ ገነነ።
[14]በመላው ኤዶም የጦር ሰፈሮችን አቋቋመ፤
ኤዶማውያን ሁሉ ለዳዊት ተገዙ፤ እግዚአብሔ
ርም ዳዊት በሄደበት ስፍራ ሁሉ ድልን ሰጠው።

## የዳዊት ሹማምት

8፥15-18 ተጓ ምብ - 1ዜና 18፥14-17

[15]ዳዊት በመላው እስራኤል ላይ ነገሠ፤
ለሕዝቡም ሁሉ ፍትሕና ርትዕ አሰፈነላቸው።
[16]የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ የሰራዊቱ አለቃ ሲሆን፣
የአሒሉድ ልጅ ኢዮሣፍጥም ታሪክ ጸሓፊ
ነበረ። [17]እንዲሁም የአኪጦብ ልጅ ሳዶቅና
የአብያታር ልጅ አቢሜሌክ ካህናት ሲሆኑ፣

[ፐ]4 የሰብዓ ሊቃናት ትርጉም (እንዲሁም የሙት ባሕር ጥቅልና 1ዜና 18፥4 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *ሰባት መቶ ሠረገለኞቹን* ይላል።
[አ]8 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞች (እንዲሁም 1ዜና 18፥8 ይመ)፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ቱባ* ይላሉ።
[ከ]12 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉምና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል (እንዲሁም 1ዜና 18፥11 ይመ)፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *አራም* ይላሉ።
[ኸ]13 ጥቂት የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉምና የሱርስቱ ቅጅ (እንዲሁም 1ዜና 18፥11 ይመ)፤ ከዚህ ጋር ይስማማል አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *አራም* ይላሉ።

የሩት 1፥22 ማብ ይመ።

8፥3 አድርአዛር፤ "አድር ረዳት(ቴ) ነው" ማለት ነው። አድር ከከነዓናውያን አምላክ ከበአል ጋር የሚተካከል የአራማውያን አምላክ ነበር። *ሱባን፤* ሳኦል ከዚህ ቀደም በሊባኖስ ተራሮችና በአንጻሩ ባሉት ተራሮች መካከል በሚገኘው በቤካ ሸለቆ ውስጥ በእስራኤል ሰሜናዊ ድንበር ግዛት ከነበረው ከሱባን ንጉሥ ጋር ተዋግቶአል (1ሳሙ 14፥47)፤ *መልሶ ለመያዝ፤* በሱባን ንጉሥ ላይ ቀደም ሲል የተገኙት የሳኦል ድሎች ለአጭር ጊዜ ቢሆንም እንኳ፣ እስከ ኤፍራጥስ ሸለቆ ድንበር የእስራኤልን የቍጥጥር አድማስ አስፍተውታል። *በኤፍራጥስ ወንዝ፤* ለአብርሃም ቃል የተገባለት ምድር ከግብፅ ወሰን ጀምሮ እስከ ኤፍራጥስ ድረስ ያለውን የሚያካትት ነበር (ዘፍ 15፥18-21፤ ዘዳ 1፥7፤ 11፥24፤ ኢያ 1፥4 ይመ)። እዚህ ላይ በመጠኑም ቢሆን፣ የተሰጠው ተስፋ ለጊዜው ሲፈጸም ይታያል (1ነገ 4፥21-24፤ እንዲሁም ዘፍ 17፥8፤ ኢያ 21፥43-45 ይመ)።

8፥4 የዚህን ክፍል ማብ ይመ። *የሠረገላ ፈረሶች… ቋንጃቸውን ቈረጠ፤* ኢያ 11፥6 እና ማብ ይመ። በዚህ ጊዜ ዳዊት ፈረስ ለውጊያ ምን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ አላስተዋለም ይሆናል።

8፥5 *አድርአዛርን ለመርዳት፤* በሰሜን በኩል የእስራኤል መስፋፋት ሶርያውያንን አስግቶአቸው ነበር።

8፥7 *የወርቅ ጋሻዎች፤* በወርቅ የተለበጡ ጋሻዎች ለማለት ነው፤ ሐረጉ፣ "የብረት ሠረገሎች" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው (ኢያ 17፥16 እና ማብ ይመ)።

8፥8 *ናስ፤* በኋላ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ለመሥራት ተገልግሎበታል።

8፥9 *ሐማት፤* ከሱባን በስተ ሰሜን በኦሮንጤስ ወንዝ ዳር ላይ የተመሠረተ መንግሥት ነው (ቍ 3 እና ማብ ይመ)።

8፥13 *የጨው ሸለቆ፤* 2ነገ 14፥7፤ እንዲሁም የመዝ 60 ርእስ ይመ።

8፥15 *ፍትሕና ርትዕ፤* ዳዊት በእግዚአብሔር የሚመራ ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን፣ አገዛዙ ሳሙኤል እንደ ጻፈው "ለንጉሥ የሚገባውን ወግና ሥርዐት" የተከተለ ነበር (1ሳሙ 10፥25 እና ማብ፤ 1ነገ 2፥3-4 ይመ)፤ የእግዚአብሔርን ሥርዐትም በመጠበቅ የሚታወቅ ነበረ (የ1ሳሙ 8፥3፤ 12፥3 ማብ ይመ)።

8፥16 *የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ፤* የሰራዊቱ አለቃ የ2፥13፤ 5፥8 ማብ ይመ። *ታሪክ ጸሓፊ፤* ይህ ሥልጣን በነገሥታቱ ዘመን በቤተ መንግሥት ውስጥ የሚሠራበት ቢሆንም እንኳ (2ነገ 18፥18:37፤ 2ዜና 34፥8፤ ኢሳ 36፥3:11:22 ይመ)፣ የዚህ ዐይነቱ የሥራው ምንነት በውል አይታወቅም። ከበርካታ ተግባሮቹ ጋር ተደምሮ ቤተ መንግሥታዊ ጉዳዮች ተመዝግበው በሰነድ እንዲያዙ የሚያደርግ የቤተ መንግሥቱ ዋና አስተዳዳሪ ሳይሆን አልቀረም።

8፥17 *የአኪጦብ ልጅ ሳዶቅ፤* ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው እዚህ ላይ ነው (1ዜና 6፥4-8:50-52፤ 24፥1-3 ይመ)። ሳዶቅ የአሮን ልጅ የሆነው የአልዓዛር ዘር ነው። አባቱ አኪጦብ ተመሳሳይ ስም ከነበረው ከኢካቦድ ወንድም ጋር እንደ አንድ ሊቈጠር አይገባውም (1ሳሙ 14፥3)። ሳዶቅ ዳዊት በነገሠበት ዘመን ሁሉ ታማኙ ነበር (15፥24-29፤ 17፥15-16፤ 19፥11)፤ በመጨረሻም ሰሎሞንን ቀብቶ በዳዊት ዙፋን ላይ ያስቀመጠው እርሱ ነው (1ነገ 1፥8:45፤ 2፥35፤ 4፥4)። *የአብያታር ልጅ አቢሜሌክ* እነዚህ ሁለት ስሞች እዚህና በ1ዜና 24፥3:6:31 ላይ ቦታ ተለዋውጠው ሊገኙ የቻሉት ምናልባት ጽሑፉ ሲገለበጥ ከተፈጠረ ስሕተት የተነሣ ሳይሆን አይቀርም። በ1ሳሙ 22፥20 ላይ አብያታር የአቢሜሌክ ልጅ መሆኑ ተጠቅሶአል፤ በ1ሳሙ 22፥20 ላይ የተጠቀሰው አብያታር በአያቱ ስም የሚጠራ አቢሜሌክ የሚባል ልጅ ሊኖረው እንደሚችል ሲታመን፣ ይህ ዐይነቱ ሰው የሳዶቅ የሥራ ባልደረባ ተብሎ በሳሙኤልና በነገሥት ውስጥ በየትኛውም ስፍራ አልተጠቀሰም። አብያታር ግን ተደጋግሞ ተጠቅሶአል (15፥29: 35፤ 17፥15፤ 19፥11፤ 20፥25፤ 1ነገ 1፥7-8:19፤ 2፥27:35፤ 4፥4)። አብያታር በዔሊ የዘር ሐረግ ውስጥ በኢታምር በኩል (1ዜና 24፥3) የአሮን ልጅ ነው (የ1ሳሙ 2፥31:33ን

ሠራያ ጸሓፊ ነበረ፤ 18የዮዳሔ ልጅ በናያስ
የከሬታውያንና የፈሊታውያን አለቃ ሲሆን፣
የዳዊት ወንዶች ልጆች ደግሞ የቤተ መንግ
ሥት አማካሪዎች▪ ነበሩ።

## ዳዊትና ሜምፊቦስቴ

9 ዳዊትም፣ "ስለ ዮናታን ስል ቸርነት አደ
ርግለት ዘንድ ከሳኦል ቤት የቀረ ሰው
ይኖር ይሆን?" በማለት ጠየቀ።
2በዚያን ጊዜ ከሳኦል ቤት ሲባ የሚባል
አንድ አገልጋይ ስለ ነበር፣ ወደ ዳዊት እንዲ
ሄድ ነገሩት። ንጉሡም፣ "ሲባ የምትባለው
አንተ ነህን?" ሲል ጠየቀው።
እርሱም፣ "አዎን እኔ አገልጋይህ ነኝ" አለ።
3ንጉሡም፣ "የእግዚአብሔርን ቸርነት እን
ዳደርግለት ከሳኦል ቤት የቀረ ሰው የለምን?"
ሲል ጠየቀው።
ሲባም ለንጉሡ፣ "እግሮቹ ሽባ የሆኑ አንድ
የዮናታን ልጅ አለ" ብሎ መለሰለት።
4ንጉሡም፣ "የት ነው ያለው?" ብሎ ጠየቀ።
ሲባም፣ "ሎዶባር በተባለ ስፍራ በዓሚ
ኤል ልጅ በማኪር ቤት ይገኛል" ብሎ መለ
ሰለት።
5ስለዚህም ንጉሥ ዳዊት፣ ሜምፊቦስቴን ከዓ
ሚኤል ከማኪር ቤት ከሎደባር ልኮ አስመጣው።
6የሳኦል ልጅ፣ የዮናታን ልጅ ሜምፊቦስቴ
ወደ ዳዊት በመጣ ጊዜ፣ አክብሮቱን ለመግለጥ
ለጥ ብሎ እጅ ነሣ።
ዳዊትም፣ "ሜምፊቦስቴ!" ብሎ ጠራው።
እርሱም፣ "እነሆ፤ አገልጋይህ" አለ።
7ዳዊትም፣ "አትፍራ፤ ስለ አባትህ ስለ ዮና
ታን ስል በእርግጥ ቸርነት አደርግልሃለሁና።
የአባትህን የሳኦልን ምድር በሙሉ እመልስ
ልሃለሁ፤ ዘወትርም ከማዕዴ ትበላለህ" አለው።
8ሜምፊቦስቴ ለጥ ብሎ እጅ ነሣና፣ "እንደ
ሞተ ውሻ ለምቈጥር ለእኔ ይህን ያህል
የምታደርግልኝ አገልጋይህ ኧረ ማን ነኝ?"
አለ።
9ከዚያም ንጉሡ የሳኦልን አገልጋይ ሲባን ጠርቶ
እንዲህ አለው፤ "የሳኦልና የቤተ ሰቡ የሆነውን
ሁሉ ለጌታህ የልጅ ልጅ ሰጥቼዋለሁ። 10አንተ፣
ልጆችህና አገልጋዮችህ የጌታችሁ የልጅ ልጅ
የሚበላውን እንዲያገኝ መሬቱን እረሱለት፣ ምር
ቱንም አግቡለት። የጌታህ የልጅ ልጅ ሜም
ፊቦስቴ ግን ምን ጊዜም ከማእዴ ይበላል።"
በዚያን ጊዜ ሲባ ዐሥራ አምስት ወንዶች
ልጆችና ሃያ አገልጋዮች ነበሩት።
11ከዚያም ሲባ ንጉሡን፣ "ጌታዬ ንጉሥ፣
አገልጋዩን ያዘዘውን ሁሉ፣ አገልጋይህም ይፈ
ጽመዋል" አለው። ስለዚህም ሜምፊቦስቴ
ከንጉሡ ልጆች እንደ አንዱ ሆኖ ከዳዊት°
ማእድ ይበላ ነበር።
12ሜምፊቦስቴ ሚካ የተባለ አንድ ትንሽ ልጅ
ነበረው፤ የሲባ ቤተ ሰዎች በሙሉ ሜምፊቦስ
ቴን ያገለግሉት ነበር። 13ሜምፊቦስቴም ሁል
ጊዜ ከንጉሥ ማእድ ስለሚበላ ይኖር የነበረው

8፥18 1ሳሙ30፥14፤ 2ሳሙ20፥23፤23፥20፤ 1ነገ1፥8:38፤2፥25:35:46፤4፥4
9፥1 1ሳሙ20፥14-17:42፤23፥18
9፥2 2ሳሙ16፥1-4፤19፥17:26:29
9፥3 ዘሌ21፥18፤ 1ዜና8፥34
9፥4 2ሳሙ17፥27-29
9፥6 ዘፍ37፥7
9፥7 ቍ13፤1ሳሙ20፥14-15፤2ሳሙ19፥28፤21፥7፤1ነገ2፥7፤2ነገ25፥29፤ ኤር52፥33
9፥8 2ሳሙ3፥8፤4፥4
9፥10 2ሳሙ16፥3
9፥11 ኢዮ36፥7፤ መዝ113፥8
9፥12 2ሳሙ4፥4

▪18 ወይም ካህናት ተብሎ መተርጐም ይችላል።
°11 የሰብዓ ሊቃናት ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ከእኔ ይላል።

ማብ ይመ)። *ሠራያ፤* "ሱሳ" ና "ሴባ" ተብሎአል (20፥25፤ 1ነገ 4፥3፤ 1ዜና 18፥16 ይመ)። *ጸሓፊ፤* ዋና ተግባሩ የአገር ውስጥና የውጭ ግንኙነት ጒዳዮችን፣ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ፖለቲካዊና ልዩ ልዩ አስተዳደራዊ ተግባርን መዝግቦ መያዝን ያካተተ ሳይሆን አይቀርም።

8፥18 *የከሬታውያንና የፈሊታውያን፤* የ1ሳሙ 30፥14 ማብ ይመ፤ በበናያስ መሪነት ዳዊትን ለመጠበቅ ተቋቁመው የነበሩ ልዩ የክብር ዘቦች ናቸው (23፥22-23)። "ፈሊታዊ" ምናልባት "ፍልስጥኤም" ለሚለው ስም ተለዋጭ ሊሆን ይችላል። *የቤተ መንግሥት አማካሪዎች፤* በዕብራይስጥ "ካህን" የሚለው ቃል ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። መጽሐፈ ዜና መዋዕል፣ "በንጉሡ አጠገብ አለቆች ነበሩ" (1ዜና 18፥17 እና ማብ ይመ) ስለሚል፣ "የቤተ መንግሥት አማካሪ" የሚለውን ትርጒም ይደግፋል።

9፥1-20፥26 እነዚህ ምዕራፎች ከ1ነገ 1፥1-2፥46 ጋር ተደምረው "የዳዊት የቤተ መንግሥቱ ታሪክ" በመባል የሚታወቁ ሲሆን፣ በጥንታዊው ዓለም ለተጻፈው ታሪክ እጅግ ከፍተኛ ምሳሌነት አላቸው ከሚባሉት መካከልም ተቈጥረዋል። የዝርዝር ሐሳባቸው ትስስርና ግልጽነት የዐይን ምስክር ሥራ መሆናቸውን ያመለክታል።

9፥1-13፤ የዚህ ምዕራፍ ሁነቶች መቼ እንደ ተፈጸሙ በግልጽ ማየት አይቻልም፤ ሆኖም ዳዊት ኢየሩሳሌምን ከያዘ በኋላ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የተከናወኑ ሳይሆኑ አልቀረም። ሜምፊቦስቴ አባቱ ዮናታን ሲሞት የአምስት ዓመት ልጅ ነበር (4፥4)፤ በዚህ ጊዜ ግን የራሱ ልጅ ነበረው (ቍ 12)።

9፥1 *ስለ ዮናታን ስል ቸርነት አደርግለት ዘንድ፤* ዳዊት ለዮናታን የገባውን ቃል አልረሳም (1ሳሙ 20፥15:42 ይመ)።

9፥2 *ሲባ፤* የሳኦል የበኵር ልጅ የዮናታን ልጅ ሜምፊቦስቴ ወርሶት ለነበረው የሳኦል ንብረትና ርስት ጠባቂ ነበር (16፥1-4፤ 19፥17 ይመ)።

9፥3 *አንድ የዮናታን ልጅ አለ፤* ሳኦል ሌሎች ልጆች ነበሩት (21፥8)፤ ነገር ግን ሲባ አለ ያለው፣ ዳዊት ሊረዳው በእጅጉ ደስተኛ የሆነበትን ልጅ ብቻ ነበር።

9፥4 *ማኪር፤* ለሜምፊቦስቴ ርዳታ ያደረገለት በኋላም ዳዊትን ለማገዝ የመጣ (17፥27) ሀብታም ሰው ነበር። *ሎዶባር፤* ከዮርዳኖስ በአሻገር ባለው በገለዓዳውያን ምድር ውስጥ ዝቅ ብሎ የሚገኝ ከተማ ሲሆን (ኢሱ 13፥26 "ዳቤር")፣ ከሳኦል ርስትና ከዳዊት ቤተ መንግሥት ራቅ ብሎ የሚገኝ ቦታ ነው (የ2፥8 ማብ ይመ)።

9፥7 *እመልስልሃለሁ፤* ሳኦል ንጉሥ በነበረበት ዘመን ያከማቸው ንብረት አንድም በዳዊት ተወርሶአል፤ ያለዚያም ደግሞ የንጉሡ ንብረት ጠባቂ የነበረው ሲባ የራሱ አድርጎታል፤ ጥቅምም አግኝቶበታል (16፥1-4፤ 19፥26-30 ይመ)፤ *ዘወትርም ከማዕዴ ትበላለህ፤* እንደዚህ የተደረገው ለሳኦል የልጅ ልጅ ለሜምፊቦስቴ የገንዘብ ርዳታ ለማድረግ ሳይሆን፣ ከዚያ በላይ የሆነውን የክብር ስፍራ ሊሰጠው ፈልጎ ነው። ሜምፊቦስቴ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከሳኦል ርስት ነበር (ቍ 10)።

9፥8 *እንደ ሞተ ውሻ ለምቈጥር፤* ራስን እጅግ ዝቅ አድርጎ የሚገልጽ ሐረግ ነው። "የሞተ ውሻ" የሚለውን አባባል ጸሐፊው በዚህና በሌላም ቦታ ላይ ታላቅ ስሜትን ሊያሳድር በሚችል መልክ ተጠቅሞበታል፤ በመጀመሪያ ጎልያድ፣ ወጣቱን ተጋጣሚ ዳዊትን በመናቅ፣ "እኔ ውሻ ነኝን?" ሲለው (1ሳሙ 17፥43) እና ይህም አባባል ሳይታሰብ ድንገት የጎልያድን የራሱን የመጨረሻ ዕድል ምን እንደሚመስል አስቀድሞ ሲያመለክት ይታያል። በኋላም ጠቃሚ ሰው እንደ ሆነ በማሰብ፣ የእስራኤል ንጉሥ ክትትል ሊያደርግበት እንደሚያስፈልግ ለሳኦል ለመንገር ዳዊት "የሞተ ውሻ" በማለት ራሱን ዋጋ እንደሌለው ሰው አድርጎ ይገልጣል (1ሳሙ 24፥14)። ስለ ናባል በተጻፈው ማብራሪያ ውስጥ፣ "ውሻ" (ካሌባዊ) የሚለው ቃልና ድንገተኛ አሟሟቱ የሳኦልን ጠባይ ያሳስባሉ፤ አሳዛኙንም የሕይወቱ ፍጻሜ ያመላክታሉ (የ1ሳሙ 25፥3 ማብ ይመ)። እዚህ ላይ የሳኦል የልጅ ልጅ ሜምፊቦስቴ በ16፥9 ላይ ደግሞ ዳዊትን የረገመው የሞተው ንጉሥ የሳኦል ዘመድ በተመሳሳይ መልክ ተገልጠዋል፤ "ጸሐፊው የሞተ ውሻ" በሚለው ሐረግ እግዚአብሔር ቀብቶ ያነገሠውን የሚቃወሙትን ወይም የሚሰድቡትን ሰዎች ጠባይ በተስማማ መንገድ ሲገልጥበት፣ ዳዊት ራሱን ዝቅ አድርጎ ማቅረብ ግን (1ሳሙ 18፥18፤ 2ሳሙ 7፥18)፣ ክብሩንና ሥልጣኑን የሚያረጋግጥ ነው።

9፥12 *ሚካ፤* የትውልድ ሐረጉን በ1ዜና 8፥35-39 ላይ ይመ።

በኢየሩሳሌም ነው፤ ሁለት እግሮቹም ሽባ ነበሩ።

## ዳዊት አሞናውያንን ድል አደረገ

10፥1-19 ተጓ ምብ - 1ዜና 19፥1-19

10 ከዚህ በኋላ የአሞናውያን ንጉሥ ሞተ፤
ልጁ ሐኖንም በእግሩ ተተክቶ ነገሠ።
[2]ዳዊትም፣ "አባቱ ቸርነትን እንዳደረገልኝ
ሁሉ፣ እኔም ለናዖስ ልጅ ለሐኖን ወሮታውን
ልክፈል" ሲል አሰበ። ስለዚህ ስለ አባቱ ሞት
የተሰማውን ሐዘን እንዲገልጹለት ዳዊት
መልክተኞችን ላከ።

የዳዊት ሰዎች ወደ አሞናውያን ምድር
በደረሱ ጊዜ፣ [3]የአሞናውያን መኳንንት ጌታ
ቸውን ሐኖንን፣ "ዳዊት የተሰማውን ሐዘን
ለመግለጽ ሰዎች መላኩ አባትህን ለማክበር
አስቦ ይመስልሃል? የላካቸው ሰዎች ከተማ
ዪቱን እንዲመረምሩ፣ እንዲሰልሉና እንዲ
ያጠፏት አይደለምን?" አሉት። [4]ስለዚህ
ሐኖን የዳዊትን ሰዎች ይዞ፣ የእያንዳንዳቸ
ውን ጢም በከፊል ላጨ፣ ልብሳቸውንም
ወገባቸው ድረስ አሳጥሮ በመቀረጥ መልሶ
ሰደዳቸው።

[5]ዳዊት ይህን በሰማ ጊዜ፣ ሰዎቹ እጅግ ዐፍ
ረው ስለ ነበር መልክተኞቹን ላከባቸው፤ ንጉ
ሡም፣ "ጢማችሁ እስኪያድግ በኢያሪኮ ቈዩና
ከዚያ በኋላ ተመለሱ" አላቸው።

[6]አሞናውያን፣ ዳዊት እንደ ጠላቸው ባወቁ
ጊዜ፣ ከቤትሮኦብና ከሱባ ሃያ ሺህ ሶርያውያን
እግረኛ ወታደሮችን እንዲሁም ንጉሥ መዓካን
ከአንድ ሺህ ሰዎቹ ጋር ደግሞም ከጦብ ዐሥራ
ሁለት ሺህ ሰዎች ቀጠሩ።

[7]ዳዊት ይህን ሲሰማ፣ ኢዮአብን ከመላው ተዋጊ
ሰራዊት ጋር ላከው። [8]አሞናውያን ወጥተው
በከተማቸው መግቢያ በር ላይ ተሰለፉ፤ የሱባና
የረአብ ሶርያውያን እንዲሁም የጦብና የመዓካ
ሰዎች ለብቻ ሜዳው ላይ ተሰለፉ።

[9]ኢዮአብም ከፊትና ከኋላው ጦር እንደ
ከበበው ባየ ጊዜ፣ በእስራኤል ጀግንነታቸው
ከታወቀው ጥቂቶቹን መርጦ በሶርያውያን
ግንባር አሰለፋቸው። [10]የቀሩትን ሰዎች ደግሞ
በወንድሙ በአቢሳ ሥር መድቦ በአሞናው
ያን ግንባር አሰለፋቸው።

10፥2 1ሳሙ11፥1
10፥3 ዘኍ21፥32
10፥4 ዘሌ19፥27፤
ኢሳ7፥20፤15፥2፤
20፥4፤50፥6፤52፥14፤
ኤር48፥37፤ሕዝ5፥1
10፥6 ዘፍ34፥30፤
ዘኍ13፥21፤ዘዳ3፥14፤
መሳ11፥3-5፤1ሳሙ
14፥47፤2ሳሙ8፥5
10፥7 2ሳሙ2፥18
10፥10 1ሳሙ26፥6
10፥12 ዘዳ1፥21፤
31፥6፤መሳ10፥15፤
ነህ4፥14፤ኤፌ6፥10
10፥14 2ሳሙ8፥12
10፥19 2ሳሙ8፥6፤
1ነገ11፥25፤22፥31፤
2ነገ5፥1

11፥1 ዘዳ3፥11፤
2ሳሙ2፥18፤1ነገ
20፥22፡26፤
1ዜና20፥1

[11]ኢዮአብም እንዲህ አለ፤ ሶርያውያን የሚያይ
ሉብኝ ከሆነ አንተ መጥተህ ትረዳኛለህ፤ አሞናው
ያን የሚያይሉብህ ከሆነ እኔ መጥቼ እረዳ
ሃለሁ። [12]እንግዲህ በርታ፤ ለሕዝባችንና ስለ
ምላካችን ከተሞች በጀግንነት እንዋጋ፤ እግዚ
አብሔርም በፊቱ መልካም መስሎ የታየ
ውን ያድርግ።

[13]ከዚያም ኢዮአብና አብሮት የነበረው ሰራ
ዊት ሶርያውያንን ለመውጋት ወደፊት ገሠገሡ፤
ሶርያውያንም ከፊቱ ሸሹ። [14]ሶርያውያን መሸ
ሻቸውን አሞናውያን ባዩ ጊዜ፣ እነርሱም ከአቢሳ
ፊት ሸሽተው ወደ ከተማዪቱ ውስጥ ገቡ። ስለ
ዚህም ኢዮአብ አሞናውያንን መውጋቱን አቁሞ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።

[15]ሶርያውያን በእስራኤላውያን እንደ ተሸ
ነፉ ባዩ ጊዜ፣ እንደ ገና ተሰባሰቡ። [16]አድ
ርአዛር መልክተኞችን ሰዶ ከወንዙ″ ማዶ
ያሉትን ሶርያውያን አስመጣ፤ እነርሱም በአ
ድርአዛር ሰራዊት አዛዥ በሶባክ መሪነት ወደ
ኤላም ሄዱ።

[17]ዳዊት ይህን በሰማ ጊዜ፣ መላውን እስ
ራኤልን ሰበሰበ፤ ከዚያም ዮርዳኖስን ተሻግሮ
ወደ ዔላም ሄደ። ሶርያውያንም ለጦርነት
ተሰልፈው ዳዊትን በግንባር ገጠሙት፤ [18]ይሁን
እንጂ ከእስራኤል ፊት ሸሹ፤ ዳዊትም ሰባት
መቶ ሠረገለኞችንና አርባ ሺህ እግረኛ ወታ
ደሮች‴ ገደለባቸው። እንዲሁም የሰራዊታ
ቸውን አዛዥ ሶባክን አቍስሎት ስለ ነበር፣
እዚያው ሞተ። [19]በአድርአዛር ሥር የነበሩት
ነገሥታት ሁሉ በእስራኤል መሸነፋቸውን ባዩ
ጊዜ ከእስራኤላውያን ጋር ሰላም መሠረቱ፤
ተገዙላቸውም።

ስለዚህም ሶርያውያን ከዚያ በኋላ አሞና
ውያንን መርዳት ፈሩ።

## ዳዊትና ቤርሳቤህ

11 ነገሥታት ለጦርነት በሚወጡበት፣
በጸደይ ወራት ዳዊት ኢዮአብን ከን
ጉሡ ሰዎችና ከመላው የእስራኤል ሰራዊት

″16 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።
‴18 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም እንዲሁም (1ዜና 19፥18 ይመ)
ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የዕብራይስጡ፣ *ፈረሰኞች* ይላል።

10፥1 *ንጉሥ*፤ ናዖስ ነው (ቍ 2፤ 1ሳሙ 11 ይመ)።
*አሞናውያን*፤ የ1ሳሙ 11፥1 ማብ ይመ።

10፥2 *ቸርነትን እንዳደረገልኝ ሁሉ*፤ ይህን ሐሳብ መግለጥ
የሚችለው አቻ የዕብራይስጥ ቃል በእስራኤላውያንና በአሞናውያን
ሁሉ መካከል የጋራ ስምምነት ተፈጥሮ እንደ ነበረ ያመለክታል።
ይህ ምናልባት በአሞናውያን ላይ የተካሄደ የጦርነት ታሪክ በም 8
ላይ ላለመመዝገቡና አሞናውያንም ሞዓባውያንን ለማገዝ ለምን
እንዳልመጡ ምክንያት ሳይሆን አልቀረም።

10፥3 *ከተማዪቱ*፤ ዋና ከተማዪቱ ረባት ናት (11፥1፤
12፥26)።

10፥4 *የእያንዳንዳቸውን ጢም በከፊል ላጨ*፤ በዚያ ዘመን
ይህ ድርጊት በምሥራቁ ዓለም እንደ ትልቅ ውርደት ይቈጠር
ነበር። አንድ ሰው ጢሙን የሚላጨው መሪር ሐዘኑን ለመግለጽ ነው
(ኢሳ 15፥2፤ ኤር 41፥5፤ ሕዝ 5፥1 ይመ)። *ልብሳቸውንም ወገባቸው
ድረስ አሳጥሮ በመቍረጥ*፤ የጦር ምርኮኞችን ለማዋረድ ሲባል
የሚደረግ ልማድ ነበር (ኢሳ 20፥4 ይመ)።

10፥5 *በኢያሪኮ*፤ የኢያ 6፥1፡26፤ 1ነገ 16፥34 ማብ ይመ።
ኢያሱ ድል አድርጎ ባያዘበትና አክዓብ ይገዛ በነበረበት ጊዜ መካከል
ባሉት ዘመናት ውስጥ ኢያሪኮ አልተመለሰችም ነበር።

10፥6 *ከቤትሮኦብ*፤ ዘኍ 13፥21፤ መሳ 18፥28 ይመ። *ሱባ*፤ የ8፥3
ማብ ይመ። *መዓካ*፤ ዘዳ 3፥14፤ ኢሱ 12፥5፤ 13፥13 ይመ። *ጦብ*፤
መሳ 11፥3፡5 ይመ።

10፥10 *አቢሳ*፤ የ1ሳሙ 26፥6 ማብ ይመ።

10፥16 *አድርአዛር*፤ የ8፥3ን ማብ ይመ። *ኤላም*፤ በገለዓድ
ሰሜናዊ ድንበር አጠገብ የምትገኝ ከተማ ናት።

10፥18 *ሰባት መቶ*፤ ይህ የቍጥር ልዩነት ረቂቁን ከገለ
በጠው ሰው ስሕተት የተነሣ የመጣ መሆኑ የታወቀ ነው፣ በ1ዜና
19፥18 ላይ ቍጥሩ ገላጭ ነው።

10፥19 *ከእስራኤላውያን ጋር ሰላም መሠረቱ*፤ ከዚህ ሽን
ፈት በኋላ በተፈጠረው ሁኔታ ሳቢያ ረዳቶቹ እንዳደረጉት ሁሉ
አድርአዛር ከእስራኤላውያን ጋር የዕርቀ ሰላም ስምምነት ስለማድ
ረጉ ፍንጭ የለም፤ እነዚህ ሁነቶች ዳዊት በእርሱ ላይ ተባብረው
በተነሡበት ጠላቶቹ ላይ ያደረገውን የመጨረሻ ዘመቻ ይወክላሉ።

11፥1 *በጸደይ ወራት*፤ በም 10 ላይ ከተገለጡት ድርጊ
ቶች ቀጥሎ የነበረውን ዓመት የሚመለከት ነው። ጊዜው ዳዊት
በኢየሩሳሌም ተደላድሎ ከተቀመጠ በኋላ ዐሥር ዓመት ገደማ
ላይ ነው። *ነገሥታት ለጦርነት በሚወጡበት*፤ በሚያዝያና

ጋር አዘመተው፤ እነርሱም አሞናውያንን
አጠፉ፤ ረባት የተባለችውንም ከተማ ከበቡ፤
በዚህ ጊዜ ግን ዳዊት በኢየሩሳሌም ቀርቶ
ነበር።

2አንድ ቀን ማታ፣ ዳዊት ከዐልጋው ተነ
ሥቶ በቤተ መንግሥቱ ሰገነት ወዲያና ወዲህ
ይመላለስ ነበር፤ ከሰገነቱ ላይ እንዳለም፣ አን
ዲት ሴት ገላዋን ስትታጠብ አየ፤ ሴቲቱም
እጅግ በጣም ውብ ነበረች። 3ዳዊትም ሰው
ልኮ ስለ ሴቲቱ አጠያየቀ። ሰውየውም፣
"ይህች የኤልያብ ልጅ፣ የኬጢያዊው የኦ
ርዮን ሚስት ቤርሳቤህ አይደለችምን?" አለ።
4ከዚያም ዳዊት መልእክተኞች ልኮ አስመ
ጣት፤ እርሱ ወዳለበት ገባች፤ አብሮአትም
ተኛ። በዚህም ጊዜ ወርሐዊ የመንጻት ጊዜ
ዋን ፈጽማ ነበር። ከዚያም ተመልሳ ወደ
ቤቷ ሄደች። 5ሴቲቱ ፀነሰች፤ ለዳዊትም፣
"አርግዣለሁ" ብላ ላከችበት።

6ስለዚህም ዳዊት ለኢዮአብ፣ "ኬጢያዊ
ውን ኦርዮንን ወደ እኔ ስደደው" ሲል ላከ
በት፤ ኢዮአብም ወደ ዳዊት ላከው። 7ኦር
ዮን በመጣ ጊዜም፣ ዳዊት የኢዮአብንና
የሰራዊቱን ሁሉ ደኅንነት እንዲሁም ጦር
ነቱ እንዴት እየተካሄደ እንዳለ ጠየቀው።
8ከዚያም ዳዊት ኦርዮንን፣ "በል እንግዲህ
ወደ ቤትህ ወርደህ እግርህን ታጠብ" አለው።
ኦርዮን ከቤተ መንግሥት ተሰናብቶ ወጣ፤
ንጉሡም ማለፊያ ምግብ አስከትሎ ላከለት።
9ነገር ግን ኦርዮን ከጌታው አገልጋዮች ሁሉ
ጋር በቤተ መንግሥቱ ቅጽር በር ተኛ እንጂ፣
ወደ ቤቱ አልወረደም ነበር።

10ዳዊት፣ "ኦርዮ ወደ ቤቱ አልሄደም"
መባሉን ሲሰማ ኦርዮንን፣ "ከመንገድ ገና
አሁን መምጣትህ አይደለምን? ወደ ቤትህ ያል
ሄድኸው ለምንድን ነው?" ሲል ጠየቀው።

11ኦርዮም ዳዊትን፣ "ታቦቱ፣ እስራኤልና
ይሁዳ በድንኳን ሆነው፣ ጌታዬ ኢዮአብና
የጌታዬም ሰዎች አውላላ ሜዳ ላይ ሰፍረው፣
ለመብላትና ለመጠጣት እንዲሁም ከሚስቴ
ጋር ለመተኛት እንዴት ወደ ቤቴ እሄዳለሁ?
እንዲህ ያለውን ነገር እንደማላደርገው በነፍ
ስህ እምላለሁ" አለው።

12ከዚያም ዳዊት፣ "እንግዲያውስ ዛሬ እዚህ
እደርና ነገ አሰናብትሃለሁ" አለው። ስለዚህ
ኦርዮ በዚያ ዕለትና በማግስቱ እዚያው ኢየሩ
ሳሌም ቈየ። 13በማግስቱም ዳዊት ራቱ ባለ
በት ግብዣ አድርጎለት በላ፤ ጠጣ፤ አሰከ
ረውም፤ ሲመሽም ኦርዮ በምንጣፉ ላይ ለመ
ተኛት የጌታው አሽከሮች ወዳሉበት ወጥቶ
ሄደ እንጂ ወደ ቤቱ አልወረደም።

14ሲነጋም ዳዊት ለኢዮአብ ደብዳቤ ጽፎ
በኦርዮን እጅ ላከለት፤ 15በደብዳቤውም ላይ፣
"ኦርዮን ውጊያው በተፋፋመበት ግንባር መድ
በው፤ ከዚያም ተመትቶ እንዲሞት ትታችሁት
ሽሹ" ብሎ ጻፈ።

16ስለዚህም ኢዮአብ ከተማዪቱን በከበባት
ጊዜ፣ እጅግ ጠንካራ ተከላካዮች እንዳሉ
በት በሚያውቀው ግንባር ኦርዮንን መደበው።
17የከተማዪቱም ሰዎች ወጥተው ከኢዮአብ
ጋር ጦርነት ገጠሙ፤ ከዳዊት ሰራዊት ውስጥ
ጥቂቶቹ ወደቁ፤ እንዲሁም ኬጢያዊው ኦርዮ
ንም ሞተ።

18ኢዮአብም በጦርነቱ የሆነውን ሁሉ ለዳ
ዊት ላከ። 19መልእክተኛውንም እንዲህ አለው፤

11፥2 ዘዳ22፥8፤ ኢሱ2፥8፤ማቴ5፥28
11፥3 2ሳሙ23፥34፡39፤1ዜና3፥5
11፥4 ዘሌ15፥25-30፤20፥10፤ዘዳ22፥22፤መዝ51 ርእስ፤ ያዕ1፥14-15
11፥6 1ዜና11፥41
11፥8 ዘፍ18፥4
11፥11 1ሳሙ 21፥5፤2ሳሙ7፥2
11፥14 1ነገ21፥8
11፥15 ቍ14-17፤ 2ሳሙ12፥9፡12

በግንቦት ወራት የሚሰበሰበው የእህል መከር ወቅት ካለፈ በኋላ ማለት ነው። *ረባት*፤ የ10፥3 ማብ ይመ። በዚህ ጊዜ የቀሩት አሞናውያን ብቻ ቢሆኑም (10፥19)፣ ገና አልተሸነፉም ነበር።

11፥2 *ሰገነት... ይመላለስ ነበር*፤ በዚያ ዘመን የነበሩት የቤት ጣራዎች ደልዳላ ነበሩ (1ሳሙ 9፥25 ይመ)። ዳዊት በዚህ ጊዜ ሰገነቱ ላይ ሊገኝ የቻለው በምሽቱ ተስማሚ አየር ለመናፈስ ፈልጎ ሊሆን ይችላል።

11፥3 *ኤልያብ*፤ ምናልባት የዳዊት የጥበቃ ዘብ (23፥34) አባልና የአማካሪው የአኪጦፌል ልጅ ሳይሆን አይቀርም። *ኦርዮ*፤ ይህም ሰው ከዳዊት የክብር ዘብ አባላት መካከል አንዱ ነው። ኬጢያዊ ቢሆንም እንኳ ስሙ እንደሚያመለክተው የእስራኤልን እምነት የተቀበለ ሰው ሳይሆን አይቀርም። የስሙ ትርጒም "ብርሃኔ እግዚአብሔር ነው" የሚል ነው። *ኬጢያዊ*፤ የ1ሳሙ 26፥6 ማብ ይመ።

11፥4 *ከዚያም ዳዊት መልእክተኞች ልኮ አስመጣት*፤ ዳዊት በዚህ ድርጊቱ ስድስተኛውን፣ ሰባተኛውን፣ ዘጠነኛውንና ዐሥረኛውን ትእዛዝ በመተላለፍ በደለኛ ሆነ (ዘፀ 20፥13-17)። *ወዳለበት ገባች፤ አብሮአትም ተኛ*፤ በዚህ የዝሙት ተግባር ቤርሳቤህ ራሷን ከዚህ ነውር አልጠበቀችም (በዚህም ጊዜ ወርሓዊ የመንጻት ሥርዐቷን ፈጽማ ነበር)፤ በቅንፍ ውስጥ የተቀመጠው ዐረፍተ ነገር ቤርሳቤህ ከዳዊት ጋር ዝሙት በፈጸመችበት ጊዜ በምን ሁኔታ እንደ ነበረች ያመለክታል። ቤርሳቤህ ከሰባት የወር አበባ መምጫ ቀኖች በኋላ (ዘሌ 15፥19-30)፣ በሥርዐቱ መሠረት ንጽታ ነበር (ዘሌ 15፥28-30)። ይህ ሐሳብ በዚህ ዐውደ ንባብ ውስጥ በትኩረት የተገለጠው ዳዊት ቤርሳቤህን በወሰዳት ጊዜ ከባሏ ፀንሳ እንዳልነበር ለማመልከት ነው።

11፥5 *አርግዣለሁ*፤ ቤርሳቤህ ከዚህ በኋላ የሚመጣውን ችግር ዳዊት እንደሚወጣው በማሰብ ሁሉን ነገር ለእርሱ ተወች፤ ዳዊትና ቤርሳቤህ በሚገባ እንደሚያውቁት ሕጉ ሁለቱም በሞት እንደሚቀጡ ይናገራል (ዘሌ 20፥10፤ ዘዳ 22፥22)።

11፥6 *ኦርዮንን ወደ እኔ ስደደው*፤ ጦርነቱ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የሚጠይቅ አስመስሎ ዳዊት ኦርዮንን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ አስጠራው።

11፥8 *ወደ ቤትህ ወርደህ እግርህን ታጠብ*፤ ዳዊት ለኦርዮ የነገረው ወደ ቤቱ ሄዶ እንዲዝናና ነበር። በንግግሩ ውስጥ ግልጥ ያልሆነ፣ በጣም ጠቃሚና ኦርዮንም በሚገባ የተረዳው (ቍ 11) ሐሳብ ነበረበት። *ማለፊያ ምግብ አስከትሎ ላከለት*፤ ዳዊት፣ ኦርዮና ቤርሳቤህ በዚያ ምሽት በአንድ ላይ እንዲሆኑ ፈልጎአል።

11፥11 *ታቦቱ*፤ የኦርዮ አነጋገር የሚያመለክተው፣ ታቦቱ ዳዊት በኢየሩሳሌም ባዘጋጀው ድንኳን ውስጥ መገኘቱን ሳይሆን (6፥17)፣ በጦር ሜዳ በሚገኘው ድንኳን ከሰራዊቱ ጋር መሆኑን ነው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ ታቦቱ በጦር ሜዳ የተገኘው ምናልባት ለአምልኮና በጦርነቱም ላይ አመራር ለመስጠት ሳይሆን አልቀረም። እግዚአብሔር ከሰራዊቱ ጋር በጦር ሜዳ እያለ ዳዊት ግን እቤቱ ቀርቶ በመዝናናት ላይ በመገኘቱ ሁኔታዎች ለእርሱ የባሰ የኀሊና ወቀሳ የሚያስከትሉበት ነበር። *እንዴት ወደ ቤቴ እሄዳለሁ?* ኦርዮ ለተሰጠው የሥራ ኀላፊነት ያሳየው ፍቅር ዳዊት የበለጠ እንዲሳጣ አድርጎታል፤ ሰራዊቱ በጦር ሜዳ እየተዋጋ ሳለ ዳዊት በቤቱ ውስጥ የፈጸመውን የሞኝነት ተግባር በከፍተኛ ሁኔታ የሚያጋልጥ ነው። *በነፍስህ እምላለሁ፤* የ1ሳሙ 1፥26 ማብ ይመ።

11፥13 *ዳዊት... አሰከረውም*፤ ዳዊት፣ ኦርዮ ከመጠጡ የተነሣ ሐሳቡን በመለወጥ ከቤርሳቤህ ጋር ይተኛል የሚል ተስፋ ነበረው።

11፥15 *ተወግቶ እንዲሞት*፤ ከቤርሳቤህ የሚወለደው ልጅ አባት ኦርዮ እንደ ሆነ ለማስመሰል የተደረገው ጥረት ሁሉ ባለመሳካቱ፣ ዳዊት በተቻለ መጠን በቶሎ ቤርሳቤህን ለማግባት ሲል፣ ኦርዮ እንዲገደል ቈረጠ።

"ይህን የጦርነቱን ወሬ ለንጉሡ ከነገርኸው
በኋላ፣ 20ንጉሡ በቍጣ ቱግ ብሎ 'ለመዋ
ጋት ስትሉ ይህን ያህል ወደ ከተማዪቱ
የተጠጋችሁት ስለምንድን ነው? ከግንቡ
ቅጥር በላይ ፍላጻ እንደሚሰዱባችሁ አታው
ቁም ኖሮአል? 21የይሩቤሼትዣ ልጅ አቤሜሌክን
የገደለው ማነው? በቴቤስ ከግንብ ቅጥር የወፍጮ
መጅ ሊቃበት የገደለችው አንዲት ሴት አይ
ደለችምን? ታዲያ እናንተስ ወደ ግንቡ ቅጥር
ይህን ያህል የተጠጋችሁት ለምንድን ነው?' በማ
ለት ቢጠይቅህ፣ አንተም መልሰህ፣ 'አገልጋይህ
ኬጢያዊው ኦርዮም ሞቶአል' ብለህ ንገረው።"

22ስለዚህ መልእክተኛው ተነሥቶ ሄደ፤
እዚያ እንደ ደረሰም፣ ከኢዮአብ የተቀበለ
ውን መልእክት በሙሉ ለዳዊት ነገረው።
23መልእክተኛውም ለዳዊት እንዲህ አለው፤
"ሰዎቹ አየሉብን፤ እኛንም ለመውጋት ወጥተው
እስከ ሜዳው ድረስ መጡ፤ እኛ ግን እስከ
ከተማዪቱ ቅጽር መግቢያ ድረስ አሳደን
መለስናቸው። 24ከዚያም ባለ ፍላጻዎቹ ከግ
ንቡ ላይ ሆነው በእኛ በአገልጋዮችህ ላይ
ቀስት ስለ ለቀቁ፣ ከንጉሡ አገልጋዮች ጥቂ
ቶቹን ገደሉ፤ አገልጋይህ ኬጢያዊው ኦር
ዮም ሞተ።"

25ዳዊትም፣ መልእክተኛውን፣ "እንግዲህ
እንዲህ ብለህ ይህን ለኢዮአብ ንገረው፤
'መቼም ሰይፍ አንድ ጊዜ ይህን፣ ሌላ ጊዜም
ሌላውን ትበላለችና በዚህ አትዘን'" አለው።

26የኦርዮ ሚስት ባሏ መሞቱን በሰማች ጊዜ
አዘነች፤ አለቀሰችለትም። 27የሐዘኑ ጊዜ ካበቃ
በኋላም፣ ዳዊት ልኮ ቤርሳቤህን ወደ ቤቱ
አስመጣት፤ ሚስቱ ሆነች፤ ወንድ ልጅም
ወለደችለት፤ ነገር ግን ዳዊት የሠራው ሥራ
*እግዚአብሔርን* አላስደሰተውም ነበር።

## ናታን ዳዊትን ገሠጸው

11፥1፤ 12፥29-31 ተን ምብ - 1ዜና 20፥1-3

**12** *እግዚአብሔር* ናታንን ወደ ዳዊት
ላከው፤ እርሱም ወደ ዳዊት መጥቶ
እንዲህ አለው፤ "በአንድ ከተማ የሚኖሩ
ሁለት ሰዎች ነበሩ፤ ከእነርሱም አንዱ ባለ ጠጋ
ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ድኻ ነበረ። 2ባለ ጠጋው
እጅግ ብዙ በጎችና የቀንድ ከብቶች ነበሩት፤
3ድኻው ግን ከገዛት ከአንዲት ጠቦት በግ
በስተቀር ሌላ አልነበረውም። ተንከባከባት፤
አብራውም ከልጆቹ ጋር አደገች፤ አብራው
ትበላ፤ ከጽዋው ትጠጣ እንዲሁም በዕቅፉ
ትተኛ ነበር፤ ልክ እንደ ገዛ ልጁ ነበረች።

4ወደ ባለ ጠጋውም ቤት እንግዳ መጣ፤
ባለ ጠጋው ግን ከራሱ በጎች ወይም ቀንድ
ከብቶች ወስዶ ለመጣበት እንግዳ ምግብ
ማዘጋጀት አልፈለገም፤ ከዚህ ይልቅ የድኻ
ውን እንስት ጠቦት በግ ወስዶ ቤቱ ለመ
ጣው እንግዳ አዘጋጀው።

5ዳዊት በዚያ ሰው ላይ እጅግ ተቈጥቶ
ናታንን እንዲህ አለው፤ "ሕያው *እግዚአ
ብሔርን* ይህን ያደረገው ሰው ሞት ይገባ
ዋል! 6እንዲህ ያለውን ነገር በማድረጉና
ባለ ማዘኑም ስለ በጊቱ አራት ዕጥፍ መክ
ፈል አለበት።"

7ከዚያም ናታን፣ ዳዊትን እንዲህ አለው፤
"ያ ሰው አንተ ነህ፤ የእስራኤል አምላክ *እግ
ዚአብሔር* የሚለው ይህን ነው፤ በእስራኤል
ላይ ንጉሥ ትሆን ዘንድ ቀባሁህ፤ ከሳኦልም
እጅ ታደግሁህ፤ 8የጌታህን ቤት ሰጠሁህ፣
የጌታህንም ሚስቶች በብብትህ አስታቀፍ
ሁህ፤ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ፤
ይህም ሁሉ አንሶህ ቢሆን ኖሮ፣ ከዚህ በላይ
ጨምሬ በሰጠሁህ ነበር። 9ታዲያ በፊቱ
ክፉ ነገር በማድረግ፣ *የእግዚአብሔርን* ቃል
ያቃለልኸው ስለምንድን ነው? ኬጢያዊውን
ኦርዮን በሰይፍ መታህ፤ ሚስት እንድትሆ
ንህም ሚስቱን ወሰድሃት፤ እርሱንም በአሞ
ናውያን ሰይፍ ገደልኸው። 10ስለዚህ ሰይፍ
ለዘላለም ከቤትህ አይርቅም፤ እኔን አቃለኸ
ኛል፤ ሚስት እንድትሆንህም የኬጢያዊውን
የኦርዮን ሚስት ወሰድሃታልና።'

'21 ጌዴዎን፣ *ይሩበአል* በመባልም ይታወቃል።

11፥21 መሳ8፥31፤ 9፥50-54
11፥27 ዘዳ34፥8፤ 2ሳሙ12፥9፤ መዝ51፥4-5
12፥1 2ሳሙ7፥2፤ 14፥4፤መዝ51ርእስ
12፥5 ዘፍ34፥7፤ 1ሳሙ14፥39፤ 1ነገ20፥40፤ሮሜ2፥1
12፥6 ዘፀ22፥1
12፥7 1ሳሙ2፥35፤ 2ሳሙ14፥13፤1ነገ 20፥42፤ዳን4፥22
12፥8 2ሳሙ9፥7
12፥9 ዘኍ15፥31፤ 1ሳሙ13፥14፤ 2ሳሙ11፥15፤1ነገ 15፥5፤መዝ26፥9፤ 51፥14
12፥10 2ሳሙ13፥ 28፤18፥14-15፤ 1ነገ2፥25
12፥11 ዘዳ17፥17፤ 28፥30፤2ሳሙ16፥ 11:21-22

11፥21 *ይሩቤሼትዣ*፤ በመጽሐፈ መሳፍንት ይሩበአል ተብ ሎአል (የመሳ 6፥32 ማብ ይመ)። በመጽሐፈ ሳሙኤል ጸሓፊ ለመጣው የተመሳሳይ ስሞች ለውጥ የ2፥8፤ 4፥4 ማብ ይመ። *የወፍጮ መጅ*፤ መሳ 9፥52-53 ይመ። *ኦርዮም ሞቶአል*፤ ይህ ዜና ለዳዊት እጅግ አስፈላጊ እንደ ሆነ ኢዮአብ ያውቃል፤ ዳዊት በውጊያው ስልት ላይ ሊሰነዝር የሚችለውን ማንኛውንም ነቀፋ ለመቋቋምም ይጠቀምበታል።

11፥25 *ዳዊትም መልእክተኛውን... ንገረው*፤ ዳዊት፣ "ጦር ነት መቾም ጦርነት ነውና የኦርዮ መሞት ተስፋ ሊያስቈርጥ አይገባም" በሚለው የግብዝነት አነጋገሩ በዚህ ዜና እፎይታ ያገኘ መሆኑን ደበቀ።

11፥27 *የሐዘኑ ጊዜ ካበቃ በኋላም*፤ ምናልባት የሰባት ቀን ሐዘን ሊሆን ይችላል (ዘፍ 50፥10፤ 1ሳሙ 31፥13)። *ሚስቱ ሆነች*፤ የ3፥2-5፤ 5፥14 ማብ ይመ። *ዳዊት የሠራው ሥራ እግዚአብሔርን አላስደሰተውም*፤ የዳዊት ችግር የእግዚአብሔርን ሕግ ያለ አን ዳች ሐፍረት መጣስ ብቻ (የቍ 4 ማብ ይመ) አይደለም፤ ይልቁ ንም ከዚህ በባሰ ሁኔታ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመምራት የሰጠ ውን ዐደራ ማክበርና መጠበቅ አልቻለም (5፥2፤ 7፥7-8)።

12፥1 *እግዚአብሔር... ላከው*፤ ነቢያት ከጌታ የተላኩ መል እክተኞች ነበሩ፤ እዚህ ላይ ታላቁ ንጉሥ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ያነገሠውን የአገር መሪ እንዲወቅሰውና ፍርዱንም እንዲነግረው መል እክተኛውን ይልካል። *ናታንን*፤ የ7፥2 ማብ ይመ። *ሁለት ሰዎች ነበሩ*፤ ናታን በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ እጅግ በጣም ልብን ከሚነኩት ምሳሌዎች አንዱን ይነግረዋል።

12፥5 *ሕያው እግዚአብሔርን*፤ የ1ሳሙ 14፥39 ማብ ይመ።

12፥6 *አራት ዕጥፍ*፤ ዘፀ 7:22፥1 በሚያዝዘው መሠረት ማለት ነው።

12፥8 *የጌታህንም ሚስቶች*፤ ቀደም ያሉ ታሪኮች እንደሚያ ወሡት ሳኦል አንድ ሚስትና (አኪናሆም 1ሳሙ 14፥50) አንድ ቁባት (ሪጽፋ 2ሳሙ 3፥7፤ 21፥8) እንደ ነበሩት ያመለክታሉ፤ ይህ ዐረፍተ ነገር ሳኦል ሌሎች ቁባቶች እንደ ነበሩትም ያሳያል፤ ነገር ግን የቀ ደሙት ነገሥታት ሴቶች ተተኪዎች ነገሥት መውረሳቸው ስለ ነበር (የ3፥7 ማብ ይመ)፣ እግዚአብሔር በሳኦል ዙፋን ላይ ዳዊትን ያስቀ መጠው መሆኑን ለመግለጽ፣ ናታን ምናልባት በተለመደው አባባል ተጠቅሞ ሊሆን ይችላል። *የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ*፤ 2፥4፤ 5፥2-3 ይመ።

12፥9 *የእግዚአብሔርን ቃል ያቃለልኸው*፤ የ11፥4:27 ማብ ይመ። *በሰይፍ መታህ*፤ ኦርዮ የሞተው በጦርነት ላይ ቢሆንም እንኳ፣ ዳዊት ለኦርዮ ሞት በቀጥታ ተጠያቂ ነው (11፥15 ይመ)።

12፥10 *ሰይፍ ለዘላለም ከቤትህ አይርቅም*፤ ሦስቱ የዳዊት ልጆች አምኖን (13፥28-29)፣ አቤሴሎም (18፥14) እና አዶንያስ (1ነገ 2፥25) አሟሟታቸው ክፉ ነበር።

11“እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ ‘እነሆ ከራ
ስህ ቤት ክፉ ነገር አስነሣብሃለሁ፤ ዐይንህ
እያየም ሚስቶችህን ወስጄ ለአንተ ቅርብ
ለሆነ ሰው ለአንዱ እሰጣለሁ፤ እርሱም በቀን
ብርሃን ከሚስቶችህ ጋር ይተኛል:: 12አንተ
ይህን በስውር አድርገኸዋል፤ እኔ ግን ይህ
ንኑ ነገር በቀን ብርሃን በእስራኤል ሁሉ
ፊት እገልጠዋለሁ::’ ”
13ከዚያም ዳዊት ለናታን፣ “እግዚአብሔ
ርን በጣም በድያለሁ” አለው::
ናታንም እንዲህ አለው፣ “እግዚአብሔር
ኀጢአትህን አስወግዶልሃል:: አንተ አትሞ
ትም፤ 14ይህን በመፈጸምህ ግን፣ የእግዚአብ
ሔር ጠላቶች እጅግ እንዲያቃልሉት[a] ስላ
ደረግህ፣ የተወለደልህ ልጅ ይሞታል::”
15ናታን ወደ ቤቱ ከሄደ በኋላ፣ የኦርዮን
ሚስት ለዳዊት የወለደችለትን ሕፃን እግዚ
አብሔር ከባድ ሕመም ላይ ጣለው:: 16ዳዊት
ስለ ሕፃኑ እግዚአብሔርን ለመነ፤ ጾመም፤
ከዚያም ወደ ክፍሉ ገብቶ በተከታታይ
ሌሊቱን መሬት ላይ ተኝቶ ዐደረ:: 17የቤተ
ሰው ሽማግሌዎችም ከመሬት ሊያስነሡት
በአጠገቡ ቆሙ፤ እርሱ ግን እምቢ አለ፤
አብሮአቸውም አንዳች ነገር አልበላም::
18በሰባተኛው ቀን ሕፃኑ ሞተ፤ የዳዊት
አገልጋዮችም፣ “እነሆ ሕፃኑ በሕይወት እያለ
የነገርነውን ዳዊት አልሰማንም ታዲያ አሁን
የሕፃኑን መሞት እንዴት አድርገን ልንነ
ግረው እንችላለን? በራሱ ላይ ጒዳት ሊያ
ደርስ ይችላል” ብለው መንገሩን ፈሩ::
19ዳዊት አገልጋዮቹ በሹክሹክታ ሲነጋገሩ
አይቶ፣ ሕፃኑ መሞቱን ዐወቀ፤ ስለዚህ፣
“ሕፃኑ ሞተ?” ብሎ ጠየቃቸው::
እነርሱም፣ “አዎን ሞቶአል” ብለው መለ
ሱለት::
20በዚህ ጊዜ ዳዊት ከመሬት ተነሣ፤ ከታጠበ፣
ከተቀባና ልብሱን ከለወጠ በኋላ ወደ እግዚ
አብሔርም ቤት ሄዶ ሰገደ:: ከዚያም ወደ
ክፍሉ ገባ፤ በራሱም ጥያቄ ምግብ አቅርበ
ውለት በላ::
21አገልጋዮቹም፣ “እንደዚህ ያደረግኸው
ለምንድን ነው? ሕፃኑ በሕይወት እያለ ጾምህ፤
አለቀስህ፤ ሕፃኑ ከሞተ በኋላ ግን ተነሥተህ
በላህ” ብለው ጠየቁት::
22እርሱም እንዲህ አለ፤ “በእርግጥ ሕፃኑ
በሕይወት እያለ፣ ‘እግዚአብሔር ይቅር
ብሎኝ ሕፃኑን በሕይወት ያኖረው ይሆናል’
ብዬ ጾምሁ፤ አለቀስሁ:: 23አሁን ግን ሕፃኑ
ስለ ሞተ፣ የምጾመው ለምንድን ነው? መልሼ
ላመጣው እችላለሁን? እኔ ወደ እርሱ እሄዳ
ለሁ እንጂ፣ እርሱ ወደ እኔ አይመለስ!”
24ከዚያም ዳዊት ሚስቱን ቤርሳቤህን አጽ
ናናት፤ ወደ እርሷም ገብቶ አብሮአት ተኛ፤
ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሰሎሞን
አለው:: እግዚአብሔርም ወደደው፤ 25እግዚ
አብሔር ሕፃኑን ስለ ወደደም ስሙ ይዲ
ድያ[b] ተብሎ እንዲጠራ በነቢዩ በናታን
በኩል ቃል ላከ::
26በዚያን ጊዜም ኢዮአብ የአሞናውያንን
ከተማ ረባትን ወግቶ የቤተ መንግሥቱን
ምሽግ ያዘ:: 27ከዚያም ኢዮአብ እንዲህ በማ
ለት ወደ ዳዊት መልክተኞችን ላከ፤ “ረባ
ትን ወግቼ የውሃውን ከተማ ይዤአለሁ፤
28እንግዲህ የቀረውን ሰራዊት አሰባስበህ
ከተማዪቱን ከበብና ያዛት፤ ያለበለዚያ እኔ
ከተማዪቱን እይዛትና በስሜ መጠራቷ ነው::”
29ስለዚህ ዳዊት መላውን ሰራዊት አሰባ
ስቦ ወደ ረባት በመሄድ ወግቶ ያዛት::
30የንጉሣቸውንም ዘውድ ከራሱ ላይ ወሰደ፤
የዘውዱ ክብደት የሚመዝን አንድ መክሊት
ወርቅ ሲሆን፣ በከበረ ዕንቍም ያጌጠ ነበር፤
ይህም በዳዊት ራስ ላይ ተጫነ:: ዳዊትም
ከከተማዪቱ እጅግ ብዙ ምርኮ ወሰደ፤

12፥12 2ሳሙ 11፥4-15፤16፥22
12፥13 ዘፍ13፥13፤ 20፥6፤ዘሌ20፥10፤ 24፥17፤ዘኍ22፥34፤ መዝ32፥1-5፤51፥1፡9፤ 103፥12፤ምሳ28፥13፤ ኢሳ43፥25፤44፥22፤ ኤር2፥35፤ሚክ 7፥18-19፤ዘካ3፥4፡9
12፥14 ኢሳ52፥5፤ ሮሜ2፥24
12፥15 1ሳሙ 25፥38
12፥16 መዝ5፥7፤ 95፥6
12፥17 ዘፍ37፥35፤ 1ሳሙ1፥7፤2ሳሙ 3፥35፤ዳን6፥18
12፥20 ዘፍ41፥14፤ ማቴ6፥17
12፥21 መሳ20፥26
12፥22 ኢሳ 38፥1-5፤ዮና3፥9
12፥23 ዘፍ37፥35፤ 1ሳሙ31፥13፤2ሳሙ 13፥39፤ኢዮ7፥10፤ 10፥21
12፥24 1ነገ1፥10፡ 11፤1ዜና22፥9፤ 28፥5፤ማቴ1፥6
12፥25 ነህ13፥26
12፥26 ዘዳ3፥11
12፥30 አስ8፥15፤ መዝ21፥3፤132፥18
12፥31 1ሳሙ 14፥47

[a]14 የማሶሬቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ጥንታዊው የዕብራ ይስጥ የጸሓፍት ትውፊት ግን፤ *በዚህም እግዚአብሔርን እጅግ ስላቃለልህ* ይላል::
[b]25 *ይዲድያ ማለት በእግዚአብሔር (ያህዌ) የተወደደ ማለት ነው*

12፥11 ***እነሆ፣ ከራስህ ቤት ክፉ ነገር አስነሣብሃለሁ፤*** አቤሴሎም ከገዛ አባቱ ላይ የንጉሥነት ሥልጣን ለመቀማት ካካሄደው ሤራ የተነሣ (15፥1-15)፣ ዳዊት ከኢየሩሳሌም ለመውጣት ተገድዶ ነበር:: ***እርሱም በቀን ብርሃን ከሚስቶችህ ጋር ይተኛል፤*** ይህም በአቤሴሎም ዐመፅ ተፈጽሞአል (የ16፥22 ማብ ይመ)::

12፥13 ***እግዚአብሔርን በጣም በድያለሁ፤*** ዳዊት መተላለፉን ተገንዝቦአል፤ ከናታን ግሣጼ የተነሣም ኀጢአቱን ተናዞአል (መዝ 51 ይመ):: የዳዊት ንስሓ ከሳኦል ንስሓ ምን ያህል የተለየ እንደ ሆነ አስተውል (የ1ሳሙ 15፥24 ማብ ይመ):: ***እግዚአብሔር ኀጢአትህን አስወግዶልሃል፤*** ዳዊት ኀጢአቱ ይቅር ስለ ተባለለት ከኀጢአት ሥርየት የተነሣ የሚገኘውን ሐሤት ተለማምዶታል (መዝ 32፥1፡5 ይመ፤ ከመዝ 51፥8፡12 ጋር ያነጻጽሩ):: ***አንተ አትሞትም፤*** ዳዊት የፈጸመው የዝሙትና የነፍስ ማጥፋት በደል በነበረው ሥርዐት መሠረት የሞት ቅጣት የሚያስከትልበት መሆኑ ቢታወቅም፣ (ዘሌ 20፥10፤ 24፥17)፣ ጌታ በቸርነቱ ከሚደርስበት የሞት ቅጣት ነጻ አድርጎታል::

12፥14 ***ይህን በመፈጸምህ ግን የእግዚአብሔር ጠላቶች እጅግ እንዲያቃልሉት ስላደረግህ፤*** ምንም እንኳ እግዚአብሔር ኀጢአቱንና በደሉን ይቅር ያለው ቢሆንም በሰው ፊት ስለተ ገለጠው ኀጢአቱ ግን መቀጣቱ ተገቢ ነው::

12፥15 ***ናታን ወደ ቤቱ ከሄደ በኋላ፤*** ዳዊት ኀጢአተኛ መሆኑን ለናታን አምኖአል (ቍ 13) ኀጢአቱን ለእግዚአብሔር ተናዞአል (ስለ ዳዊት የኑዛዜና የንስሓ ጸሎት መዝ 51 ይመ)::

12፥20 ***ወደ እግዚአብሔርም ቤት ሄዶ ሰገደ፤*** ዳዊት ኀጢአቱ ያስከተለበትን ቅጣት በትሕትና የተቀበለ መሆኑን በዚህ መልክ በግልጥ አረጋገጠ:: አሁንም (የቍ 13 ማብ ይመ) በዳዊትና በሳኦል ጠባይ መካከል ያለውን ልዩነት አስተውል (የ1ሳሙ 15፥25 ይመ)::

12፥23 ***እኔ ወደ እርሱ እሄዳለሁ፤*** ልጁ እንደ ሞተ ሁሉ ዳዊትም ይሞታል፤ ወደ መቃብርም ይወርዳል (የዘፍ 37፥35 ማብ ይመ)::

12፥24 ***ሰሎሞን*** 1ዜና 22፥9 እና የዚህን ክፍል ማብ ይመ::

12፥25 ***ይዲድያ፤*** የዚህን ክፍል ማብ ይመ:: የዚህ ስም መሰጠት፣ ሰሎሞን ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ ልዩ የእግዚአብሔር ምርጫ በእርሱ ላይ ያረፈ መሆኑን ያመለክታል፤ ይህም ስም የዳዊትን ስም መልሶ የሚያስተጋባ በመሆኑ፣ እግዚአብሔር እርሱንም እንደሚወደውና ሥርወ መንግሥቱም ወደፊት እንደሚቀጥል ለዳዊት አረጋገጠለት::

12፥26 ***ኢዮአብ... ረባትን ወግቶ፤*** አሁን ደግሞ ጸሓፊው ለዳዊትና ለቤርሳቤህ ግንኙነት ምክንያት ወደ ሆነው፣ ከአሞናውያን ጋር ወደ ተካሄደው ጦርነት ውጤት ይመለሳል (11፥1፡25):: ዳዊት እግዚአብሔርን አሳዝኖት በነበረበት ጊዜ እንኳ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ባዋረዳቸው ሕዝብ ላይ ድልን ሰጣቸው::

12፥30 ***ይህም በዳዊት ራስ ላይ ተጫነ፤*** ታላቅ ክብደት

31እዚያ የነበሩትንም ሕዝብ አውጥቶ መጋዝ፣
የብረት መቈፈሪያና መጥረቢያ ተጠቅመው
ሥራ እንዲሠሩ አደረጋቸው፣ እንዲሁም
የሸክላ ጡብ አሠራቸው[ሀ]:: እንዲህ ያለውም
ሥራ በሌሎቹ የአሞናውያን ከተሞች ሁሉ
እንዲፈጸም አደረገ:: ከዚያም ዳዊትና ሰራ
ዊቱ በሙሉ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ::

## አምኖን ትዕማርን ደፈረ

13 የዳዊት ልጅ አቤሴሎም ትዕማር የም
ትባል ቈንጆ እኅት ነበረችው፤ እር
ሷንም የዳዊት ልጅ አምኖን ወደዳት::
2አምኖን እኅቱን ትዕማርን ከማፍቀሩ
የተነሣ እስኪታመም ድረስ ተጨነቀ፤ ድን
ግል ስለ ሆነች እርሷን ማግኘት የማይቻል
ሆኖ አግኝቶታልና::
3አምኖን ኢዮናዳብ የተባለ ወዳጅ ነበረው፤
እርሱም የዳዊት ወንድም የሳምዓ ልጅ ነው::
ኢዮናዳብ እጅግ ተንኰለኛ ሰው ነበር:: 4አም
ኖንንም፣ "የንጉሥ ልጅ ሆይ፤ ሰውነትህ
ቀን በቀን የሚከሳበትን ምክንያት ለምን
አትነግረኝም?" ሲል ጠየቀው::
አምኖንም፣ "የወንድሜን የአቤሴሎምን
እኅት ትዕማርን አፍቅሬ ነው" አለው::
5ኢዮናዳብም፣ "እንግዲያው 'ታምሜአለሁ'
ብለህ ዐልጋ ላይ ተኛ፤ አባትህ ሊጠይቅህ
ሲመጣም፣ 'እኅቴ ትዕማር መጥታ የምበላ
ውን ነገር ብትሰጠኝ ደስ ይለኛል፤ መብሉ
ንም እዚሁ አጠገቤ ሆና እያየሁ አዘጋጅታ
በእጇ እንድታጐርሰኝ እባክህ ፍቀድልኝ ብለህ
ንገረው" አለው::
6ስለዚህ አምኖን የታመመ ሰው መስሎ
ተኛ፤ ንጉሡም ሊጠይቀው መጣ፤ አምኖ
ንም፣ "እኅቴ ትዕማር መጥታ፣ እያየሁ ሁለት
እንጀራ ጋግራ በእጇ እንድታጐርሰኝ እለም
ንሃለሁ" ብሎ ጠየቀው::
7ዳዊትም፣ "ወንድምሽ አምኖን ቤት ሂደሽ
ምግብ እንድታዘጋጂለት" በማለት ለትዕማር
እንዲነግሯት ወደ ቤተ መንግሥቱ ላከ::
8ስለዚህም ትዕማር ወንድሟ አምኖን ወደ
ተኛበት ቤት ሄደች፤ ጥቂት ሊጥ ወስዳ ካቦ
ካች በኋላ እያየ አዘጋጅታ ጋገረችው፤ 9ከዚ
ያም መጋገሪያውን አውጥታ እንጀራውን አቀ
ረበችለት፤ እርሱ ግን መብላት አልፈለገም::
አምኖንም፣ "ሰውን ሁሉ ከዚህ አስወጡ
ልኝ" አለ፤ ያለውም ሰው ሁሉ ትቶት ወጣ::
10ከዚያም አምኖን ትዕማርን፣ "እንድታጐር
ሺኝ ምግቡን እዚሁ መኝታ ክፍሌ አምጪ
ልኝ" አላት:: ትዕማርም ያዘጋጀችውን እን
ጀራ ይዛ ወንድሟ አምኖን ወዳለበት መኝታ
ክፍል ገባች:: 11ነገር ግን ምግቡን ስታቀር
ብለት አፈፍ አድርጎ ያዛትና፣ "እህቴ ነዪ
አብረን እንተኛ" አላት::
12እርሷም እንዲህ አለችው፤ "እባክህ ወን
ድሜ ተው አይሆንም! አታስገድደኝ፤ እንዲህ
ያለው ነገር በእስራኤል ተደርጎ አያውቅም፤
ይህን አሳፋሪ ድርጊት አታድርግ:: 13እኔስ
እንዴት እሆናለሁ? ነውሬንስ ተሸክሜ የት
እገባለሁ? አንተስ ብትሆን በእስራኤል ከወ
ራዳዎቹ እንደ አንዱ መቈጠርህ አይደለ
ምን? እባክህ ለንጉሡ ንገረው፤ እንዳላገባ
ህም አይከለክለኝም::" 14እርሱ ግን ሊሰማት
አልፈለገም፤ ከእርሷ ይልቅ ብርቱ ስለ ነበር፣
በግድ አስነወራት፤ ከእርሷም ጋር ተኛ::
15ከዚያም አምኖን እጅግ ጠላት፤ እንዲ
ያውም ቀድሞ ካፈቀራት የበለጠ ጠላት::
አምኖንም፣ "ተነሽ ውጭልኝ!" አላት::
16እርሷም፣ "ይህ አይሆንም! እኔን አስወ
ጥቶ መስደድ፣ አስቀድመህ ካደረስህብኝ በደል
የባሰ መፈጸምህ ነው" አለችው:: እርሱ ግን
አልተቀበላትም፤ 17በግል የሚያገለግለውን
ወጣት ጠርቶ፣ "ይህቺን ሴት ከዚህ አስወ
ጣና በሩን ዝጋባት" አለው:: 18ስለዚህም
አገልጋዩ አስወጥቶ በሩን ዘጋባት፤ ጌጠኛ[ለ]
የሆነና በዚያን ጊዜ ድንግል የሆኑት የንጉሥ
ልጆች የሚለብሱትን ዐይነት ልብስ ለብሳ
ነበር:: 19ትዕማርም በራሷ ላይ ዐመድ ነሰነ
ሰች፤ ጌጠኛ[ሐ] ልብሷን ቀደደች፤ ከዚያም
እጇን በራሷ ላይ አድርጋ እያለቀሰች ሄደች::

[ሀ]31 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጉም በትክክል አይታወቅም::
[ለ]18 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጉም በትክክል አይታወቅም::
[ሐ]19 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጉም በትክክል አይታወቅም::

13፥1 2ሳሙ3፥2:3፤ 14፥27፤1ዜና3፥9
13፥3 1ሳሙ16፥9
13፥9 ዘፍ45፥1
13፥11 ዘፍ38፥16፤ 39፥12
13፥12 ዘፍ34፥7፤ ዘሌ20፥17
13፥13 ዘሌ18፥9፤ ዘዳ22፥21:23-24
13፥14 ዘፍ34፥2፤ ሕዝ22፥11
13፥18 ዘፍ37፥23
13፥19 ኢሱ7፥6፤ አስ4፥1፤ዳን9፥3
13፥21 ዘፍ34፥7

ያለው እንደዚህ ዐይነቱ ዘውድ (የዚህን ክፍል ማብ ይመ)፣ ለአ ጭር ጊዜና ታላቅ በዓል ሲከበር ብቻ ይደፉ ነበር፤ ምናልባት ዳዊት በአሞን ላይ ያለውን የበላይ ገዢነት ለአንድ ጊዜ ብቻ በምልክትነት ለመግለጽ ሲባል ሳይጫን አልቀረም::

12፥31 *እንዲሠሩ አደረጋቸው፤* ድል የተቀዳጁ ነገሥታት የጦር ምርኮኞችን በቤተ መንግሥት ሕንጻ ሥራ ላይ በጕልበት ሥራ እንዲሰማሩ ያደርጉ ነበር (1ነገ 9፥20-21 ይመ፤ ከዘፀ 1፥11 ጋርም ያነጻጽሩ)::

13፥1-39፤ በዳዊት ቤተ ሰብ ውስጥ ብጥብጥ ተጀመረ (የ12፥10 ማብ ይመ)::

13፥1 *አምኖን፤* የዳዊት የበኵር ልጅ ነው (3፥2):: *ትዕማር፤* ከመዓካ የተወለደች የዳዊት ልጅ ሳትሆን፣ ለአቤሴሎም የአባት የእናቱ ልጅ እኅቱ ናት::

13፥2 *ተጨነቀ፤* ጭንቀቱ የመጣው ከፍትወተ ሥጋው ፍላ ጎት መቀስቀስ የተነሣ ነው፤ የአባት ወይም የእናት ልጅ የሆነች ውን ማግባት በሙሴ ሕግ የተከለከለ ነበር (ዘሌ 18፥11)::

13፥3 *ሳምዓ፤* በ1ሳሙ 16፥9 ላይ ሣማ ተብሎአል::

13፥13 *አንተስ ብትሆን፤* ይህ ድርጊት አምኖን በዐልጋ ወራ ሽነቱና በልዑልነቱ የነበረውን ሥልጣን አደጋ ላይ የሚጥል ነው:: *እንዳላገባህም አይከለክለኝም፤* ትዕማር ይህን ያለችው ከአምኖን እጅ ለማምለጥ ለጊዜው የፈጠረችው መላ እንጂ እውነትም ከዳር መድረስ የሚችል ከልብ የሆነ ሐሳብ አልነበረም፤ ምክንያቱም እንዲህ ዐይነቱ ጋብቻ በሙሴ ሕግ የተከለከለ ነበርና (ዘሌ 18፥9፤ 20፥17፤ ዘዐ 27፥22 ይመ)::

13፥15 *አምኖን እጅግ ጠላት፤* የአምኖን ስሜት ወደ ጥላቻ ተለውጦ መታየቱ (ቍ 1)፣ የቀድሞ "ፍቅር" ስሜታዊ እንጂ ልባዊ እንዳልነበረ ያረጋግጣል::

13፥16 *እኔን አስወጥቶ መስደድ አስቀድመህ ካደረስህብኝ በደል የባሰ መፈጸምህ ነው፤* ክብረ ንጽሕናዋን ስለ አስወሰደች፣ ከዚህ በኋላ አብቷ ለሌላ ባል ሊድራት አይችልም (ቍ 21 እና ማብ ይመ)::

13፥18 *ጌጠኛ የሆነና... ልብስ፤* ዘፍ 37፥ 3 እና ማብ ይመ::

13፥19 *በራሷ ላይ ዐመድ ነሰነሰች፤* የጥልቅ ሐዘን ምል ክት ነው:: *ጌጠኛ ልብሷን ቀደደች፤* ይህን ርምጃ የወሰደችው ያደረባትን ጭንቀት በመግለጽና ክብረ ንጽሕናዋ የተደፈረ መሆ ኑን ይፋ በማድረግ ነው:: *እጇን በራሷ ላይ አድርጋ፤* ይህም የሐ ዘን ምልክት ነው (ኤር 2፥37 ይመ)::






# ዳዊት በድል የያዛቸው ስፍራዎች


በእስራኤል ሁሉ ላይ ከነገሠ በኋላ (2ሳሙ 5:1-5) ዳዊት:-

1. የኢያቡሳውያንን አምባ ጽዮንን (ኢየሩሳሌምን) ያዘ፥ የዙፋን መቀመጫ ከተማ አደረጋት (2ሳሙ 5:6-10)፡
2. የፊንቂያውያን ንጉሥ የጢሮሱ ኪራም የዳዊትን ንግሥና ተቀበለ (2 ሳሙ 5:11-12)፡
3. ፍልስጥኤማውያንን በብርቱ በመምታት የእስራኤልን ግዛት ለቅቀው እንዲወጡና ዳግመኛ ማስፈራራታቸው እንዲያከትም አደረገ (2ሳሙ5:17-25፥8:1)
4. ሞአባውያንን ገባር በማድረግ ከግዛቱ ሥር አደረገ (2ሳሙ8:2)
5. የአድርአዛርን፣ የደማስቆንና የመዓካ ነገሥታትን አሸንፎ እንዲገብሩ አደረገ (2ሳሙ8:3-8፥10:6-19) የጌሹር ንጉሥ ተልማይ ዳዊት በኬብሮን በነገሠ ጊዜ የሰላም ስምምነት በማድረግ ልጁን መዓካን ሚስት እንድትሆነው ሰጠው (2ሳሙ 3:3፥1ዜና 2:23)
6. ኤዶማውያንን ገባር በማድረግ ከግዛቱ ሥር አደረገ (2ሳሙ8:13-14)
7. አሞናውያንን አሸንፎ በመንግሥቱ ሥር እንዲተዳደሩ አደረገ (2ሳሙ 12:19-31)
8. ቀድሞ ራሳቸውን ከእስራኤል ነጻ ያደረጉትንና ከእስ ራኤል ጋር ይዋጉ የነበሩትን ቀሪዎቹን የከነዓን ከተ ሞች እንዲገብሩ አድርጓል (እንደ ቤትሳን፣ ሚጌዶ፣ ትናቅ ያሉ) ::

ዳዊት አማሌቃውያንን አስቀድሞ መትቶአቸው ስለነበር (1ሳሙ 30:17) ጦርነቱ በኢያሱ የተጀመረው ውርስ መጠናቀቅና የእስራኤል ድንበር መከበር ፍጻሜ ሆኗል:: እስራኤልንና ገባር አገሮችን የሚጠቀልለው ግዛቱ በሰሜን ከኤፍራጥስ ወንዝ እስከ ቀይ ባሕር ምሥራቃዊ ክፍል የሚያጠቃልል ነበር::







20ወንድሟ አቤሴሎምም፣ “ያ ወንድምሽ
አምኖን ካንቺ ጋር ነበርን? እኅቴ ሆይ፣ በይ
አሁን ዝም በዪ፤ ወንድምሽ ስለ ሆነ፤ ነገሩን
በልብሽ አትያዢው” አላት። ትዕማርም በወ
ንድሟ በአቤሴሎም ቤት ብቸኛ ሴት ሆና
ኖረች።
21ንጉሥ ዳዊት ይህን ሁሉ በሰማ ጊዜ
እጅግ ተቈጣ፤ 22አቤሴሎም አምኖንን ክፉም
ሆነ ደግ አንዳች ቃል አልተናገረውም፤ ምክ
ንያቱም አምኖን እኅቱን ትዕማርን ስላስነወ
ራት ጠልቶት ነበር።

## አቤሴሎም አምኖንን ገደለው

23ከሁለት ዓመት በኋላ አቤሴሎም በኤፍ
ሬም ድንበር አቅራቢያ ባለችው በቤላሶር
ከተማ በጎቹን ይሸልት ነበር፤ በዚህን ጊዜ
የንጉሡን ወንዶች ልጆች ሁሉ በዚያ እንዲ
ገኙለት ጋበዛቸው። 24አቤሴሎምም ወደ ንጉሡ
ሄዶ፣ “እነሆ፤ ባሪያህ በጎቹን እየሸለተ ነው፤
ታዲያ ንጉሡና ሹማምንቱ ፈቃዳቸው ሆኖ
እባክህ ይገኙልኝ?” ሲል ጠየቀው።
25ንጉሡም፣ “ልጄ ሆይ፣ ሁላችንም መሄድ
የለብንም፤ ሸክም እንሆንብሃለን” ሲል መለ
ሰለት። አቤሴሎም አጥብቆ ቢለምነውም
ንጉሡ መሄድ አልፈለገም፤ ነገር ግን መርቆ
አሰናበተው።
26አቤሴሎምም፣ “እንግዲያውስ ወንድሜ
አምኖን አብሮን ይሂድ” አለው።
ንጉሡም፣ “አብሮአችሁ የሚሄደው ስለ
ምንድን ነው?” ሲል ጠየቀው። 27ነገር ግን
አቤሴሎም አጥብቆ ስለ ለመነው፣ አምኖ
ንና ሌሎቹ የንጉሡ ወንዶች ልጆች ሁሉ
አብረውት እንዲሄዱ አደረገ።
28አቤሴሎምም አገልጋዮቹን፣ “አምኖን የወ
ይን ጠጅ ጠጥቶ መንፈሱ መለወጡን ተጠ
ባበቁ፤ ከዚያም እኔ አምኖንን፣ ‘ምቱት’ ስላ
ችሁ ግደሉት፤ ያዘዝኋችሁ እኔ ነኝ አት
ፍሩ፤ በርቱ፤ ጠንክሩ” ብሎ አዘዛቸው።

13፥22 ዘፍ31፥24፤ ዘሌ19፥17-18፤ 1ዮሐ2፥9-11
13፥23 1ሳሙ25፥7
13፥28 ሩት3፥7፤ 2ሳሙ3፥3፤12፥10
13፥31 ዘኍ14፥6
13፥37 2ሳሙ3፥3

29የአቤሴሎምም አገልጋዮች ጌታቸው ያዘዛ
ቸውን በአምኖን ላይ ፈጸሙ። ከዚያም የን
ጉሡ ልጆች በሙሉ ተነሥተው በየበቅሎ
ዎቻቸው ላይ ተቀምጠው ሸሹ።
30እነርሱ በመንገድ ላይ ሳሉም፣ “አቤሴ
ሎም የንጉሡን ልጆች በሙሉ ፈጃቸው፤
አንድም የተረፈ የለም” የሚል ወሬ ለዳ
ዊት ደረሰው። 31ንጉሡም ተነሥቶ ቆመ፤
ልብሱን ቀደደ፤ በመሬትም ላይ ተዘረረ፤
በአጠገቡ ቆመው የነበሩት አገልጋዮቹም
ሁሉ ልብሳቸውን ቀደዱ።
32የዳዊት ወንድም የሳምዓ ልጅ ኢዮና
ዳብ ግን እንዲህ አለ፤ “የንጉሡን ልጆች
በሙሉ እንደ ፈጇቸው አድርጎ ጌታዬ አያ
ስብ፤ እኅቱን ትዕማርን በግድ ካስነወራት
ጊዜ አንሥቶ አቤሴሎም ቈርጦ የተነሣበት
ጕዳይ ስለ ሆነ፣ የሞተው አምኖን ብቻ
ነው። 33እንግዲህ የሞተው አምኖን ብቻ ስለ
ሆነ፣ ‘የንጉሡ ልጆች በሙሉ ተገደሉ’ ተብሎ
የተነገረውን ንጉሥ ጌታዬ ማመን የለበትም።”
34አቤሴሎምም ፈጥኖ ሸሸ።
ለዘብ ጥበቃ የቆመውም ሰው ቀና ብሎ
ሲመለከት፣ ከእርሱ በስተ ምዕራብ ካለው
መንገድ ብዙ ሰዎች በተራራው ጥግ ቍል
ቍል ሲወርዱ አየ፤ ዘብ ጠባቂውም ሄዶ
ለንጉሡ፣ “ከበስተ ሖሮናይም አቅጣጫ በኰ
ረብታው ጥግ ላይ ሰዎች ቍልቍል ሲወ
ርዱ አያለሁ”[ሀ] ብሎ ነገረው።
35ኢዮናዳብም ዳዊትን፣ “እነሆ፣ የንጉሡ
ልጆች መጥተዋል፤ አገልጋይህም እንዳለው
ሆኖአል” አለው።
36ገና ተናግሮ ሳይጨርስ፣ የንጉሡ ልጆች
ጮኸው እየተላቀሱ ገቡ፤ እንደዚሁም ንጉ
ሡና አገልጋዮቹ ሁሉ እጅግ አለቀሱ።
37አቤሴሎም ኩብልሎ የጌሹር ንጉሥ ወደ
ሆነው ወደ ዓሚሁድ ልጅ ወደ ተልማይ ሄደ፤

[ሀ]34 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን ይህን ዐረፍተ ነገር አይጨምርም።

13፥20 *እኅቴ ሆይ፤ በይ አሁን ዝም በዪ… ነገሩ አያበሳጭሽ፤* የተፈጸመባት አስነዋሪ ድርጊት የሕዝብ ነቀፋና ስድብ እንዳያስከትል፣ አቤሴሎም እኅቱን ሲመክርና የጭንቀቷንም ክብደት አቅልሎ በማቅረብ ሊያረጋጋት ሲሞክር ይታያል። በዚሁም መካከል አቤሴሎም የበቀል ርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለውን የራሱን ዕቅድ አውጠነጠነ።

13፥21 *እጅግ ተቈጣ፤* አምኖን ትዕማርን በመድፈሩ ዳዊት ቢቈጣም እንኳ፣ በአምኖን ላይ የቅጣት ርምጃ ስለ መውሰዱ፣ የተጻፈ ማስረጃ የለም። ምናልባት ከቤርሳቤህ ጋር የፈጸመው ኀጢአት ትዝ ብሎት ነገሩን በቸልታ ሊያልፈው ፈልጎ ይሆናል። ምንም ዐይነት ምክንያት ይኑር፣ ዳዊት ንጉሣዊና አባታዊ ኀላፊነቱን አልተወጣም። በልጆቹ ላይ ያሳየው የሥነ ሥርዐት ልልነት (የ14፥33፤ የ1ነገ 1፥6 ማብ ይመ)፣ በመጨረሻ የአምኖንን ሞት፣ የአቤሴሎምንና የአዶንያስን ዐመፅ አስከተለበት።

13፥22 *አቤሴሎም አምኖንን ክፉም ሆነ ደግ አንዳች ቃል አልተናገረውም… ጠልቶት ነበር፤* እርምጃ የሚወስድበትን ዝም ብሎ ይጠብቅ ነበር።

13፥23 *የንጉሡን ወንዶች ልጆች ሁሉ በዚያ እንዲገኙለት ጋበዛቸው፤* በግ በሚሸለትበት ጊዜ ግብዣ የሚደረግበት የደስታ ወቅት ነበር (1ሳሙ 25፥4፡8 ይመ)።

13፥26 *ወንድሜ አምኖን አብሮን ይሂድ፤* ዳዊት ግብዣውን ስላልተቀበለው፣ በኵር ልጁና ዐልጋ ወራሹ የሆነው አምኖን ወክሎት ይገኝ ዘንድ አቤሴሎም አባቱን በማግባባት ለመነው። *አብሮአችሁ የሚሄደው ስለምንድን ነው?* በሁለቱ የአባት ልጆች መካከል የነበረው ሁኔታ ሻክሮ ስለ ነበር፣ የዳዊት ጥያቄ ጥርጣሬ እንዳለበት ያመለክታል።

13፥28 *ግደሉት፤* በምሥራቅ ምድር ይሠራበት የነበረውን የመስተንግዶ ሥርዐት በመጣስ፣ አቤሴሎም የአባቱ ልጅ ይገደል ዘንድ ሁሉን ነገር አመቻቸ። የዳዊት አንጋፋ ልጆች የሆኑት አምኖንና አቤሴሎም፣ ከክፉ ሥራቸው የተነሣ እነርሱም እንደ አባታቸው በዝሙትና በነፍስ ግድያ ኀጢአት በደሉ። አቤሴሎም አምኖንን በመግደል በእኅቱ ላይ የደረሰውን በደል መበቀሉ ብቻ ሳይሆን፣ የዐልጋ ወራሽነቱንም ቦታ አመቻቸ (3፥3፤ 15፥1-6 ይመ)። የዳዊት ሁለተኛ ልጁ ኪልአብ (3፥3)፣ ስለ መወለዱ ከመናገሩ በቀር ስለ እርሱ የተገለጸ ሌላ ነገር ባለ መኖሩ፣ ምናልባትገና በወጣትነቱ ሳይሞት አልቀረም።

13፥29 *በየበቅሎዎቻቸው፤* በዳዊት ዘመነ መንግሥት የቤተ መንግሥት ሰው የሚያሳየው የተለመደ የበቅሎ ላይ አቀማመጥ ነበር (18፥9፤ 1ነገ 1፥33፡38፡44፤ እንዲሁም የ1ነገ 1፥33 ማብ ይመ)።

13፥31 *ልብሱን ቀደደ፣ በመሬትም ላይ ተዘረረ፤* የተለመደ የሐዘን መግለጫ ነው (ኢሱ 7፥6፤ 1ነገ 21፥27፤ ኢሳ 4፥1፡3፤ ኢዮ 1፥20፤ 2፥8 ይመ)።

13፥37 *የጌሹር ንጉሥ ወደ ሆነው ወደ ዓሚሁድ ልጅ ወደ ተልማይ፤* የአቤሴሎም አያት ነው (3፥3 ይመ)።

ነገር ግን ዳዊት ስለ ሞተው ልጁ ዘወትር
ያለቅስ ነበር።
38አቤሴሎም ሸሽቶ ወደ ጌሹር ከሄደ በኋላ፣
በዚያ ሦስት ዓመት ተቀመጠ። 39ንጉሥ
ዳዊት በልጁ በአምኖን ሞት ከደረሰበት ሐዘን
ከተጽናና በኋላ፣ ወደ አቤሴሎም ለመሄድ
መንፈሱ ተነሣሣ።

## አቤሴሎም ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ

14 የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ የንጉሡ ልብ
አቤሴሎምን እንደ ናፈቀ ተረዳ።
2ስለዚህም ኢዮአብ ወደ ቴቁሔ፣ ሰው ልኮ
አንዲት ብልኅ የሆነች ሴት አስመጣ፤ እን
ዲህም አላት፤ "ሐዘንተኛ በመምሰል የሐዘን
ልብስ ልበሺ፤ ዘይት አትቀቢ፤ ለሞተ ሰው
ብዙ ጊዜ እንዳዘነች ሴት መስለሽም ታዪ።
3ከዚያም ወደ ንጉሡ ሄደሽ እንዲህ በዪው።"
ከዚያም ኢዮአብ የምትናገራቸውን ቃላት
ነገራት።
4የቴቁሔዪቱም ሴት ወደ ንጉሡ ገብታ፣[*]
በንጉሡ ፊት ወደ መሬት በግምባሯ ተደፍታ
እጅ በመንሣት አክብሮቷን ከገለጠች በኋላ፣
"ንጉሥ ሆይ! እርዳኝ" አለች።
5ንጉሡም፣ "ችግርሽ ምንድን ነው?" ብሎ
ጠየቃት።
እርሷም እንዲህ አለች፤ "እኔ በእርግጥ
ባሌ የሞተብኝ መበለት ነኝ፤ 6እኔ አገልጋ
ይህ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩኝ፤ ሜዳ
ላይ እርስ በርሳቸው ተጣሉ፤ ገላጋይም ስላ
ልነበረ፣ አንዱ ሌላውን መትቶ ገደለው።
7እነሆ ቤተ ዘመዱ ሁሉ በባሪያህ ላይ ተነ
ሥተው፣ 'ወንድሙን ስለ ገደለ እንገድለ
ዋለንና ወንድሙን የገደለውን ሰው አሳል
ፊሽ ስጪን፣ ከዚያም ወራሽ አልባ ትሆኛ
ለሽ' ይሉኛል፤ ስለዚህ የቀረኝን አንዱን
መብራቴን አጥፍተው፣ ባሌን በምድር ላይ
ያለ ስምና ያለ ዘር ሊያስቀሩት ነው።"
8ንጉሡም ሴቲቱን፣ "አንቺ ወደ ቤትሽ
ሂጂ፤ ስለ ጉዳይሽ አስፈላጊውን ትእዛዝ እሰ
ጣለሁ" አላት። 9ነገር ግን የቴቁሔዪቱም
ሴት፣ "ንጉሥ ጌታዬ፣ በደሉ በእኔና በአ
ባቴ ቤተ ሰብ ላይ ይሁን፤ ንጉሡና ዙፋኑ
ከበደል የነጹ ይሁኑ" አለች።
10ንጉሡም፣ "ማንም ሰው አንዳች ነገር
ቢናገርሽ እኔ ዘንድ አምጪው፤ ዳግም አያ
ስቸግርሽም" ሲል መለሰላት።
11እርሷም፣ "ደም ተበቃዮቹ ልጄን በማ
ጥፋት የባሰ ጉዳት እንዳያደርሱ፣ ንጉሡ ስም
ላኩን እግዚአብሔርን ይለምን" አለች።
ንጉሡም፣ "ሕያው እግዚአብሔርን! ከል
ጅሽ ራስ ላይ አንዲት ጠጕር እንኳ አትነ
ካም" አላት።
12ከዚያም ሴቲቱ፣ "እኔ አገልጋይህ ለጌ
ታዬ ለንጉሡ አንዲት ቃል እንድናገር ፍቀ
ድልኝ" አለችው። እርሱም፣ "እሺ ተናገሪ"
አላት።
13ሴቲቱም መልሳ እንዲህ አለችው፣ "እን
ዲህ ያለውን ነገር በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ
ያሰብሽው ለምንድን ነው? ንጉሡ ከአገር የተ
ሰደደውን ልጁን አልመለሰውም፤ ታዲያ ይህን
ሲናገር በራሱ ላይ መፍረዱ አይደለምን?

13፥39 2ሳሙ 12፥19-23፤14፥13
14፥1 2ሳሙ 2፥18
14፥2 ሩት 3፥3፤ 2ሳሙ 20፥16፤ነህ 3፥5፤ኢሳ 1፥6፤ ኤር 6፥1፤አሞ 1፥1
14፥3 ቊ 19
14፥7 ዘኍ 35፥19፤ ዘዳ 19፥10-13፤ ማቴ 21፥38
14፥8 1ሳሙ 25፥35
14፥9 1ሳሙ 25፥24፡ 28፤ማቴ 27፥25
14፥11 ዘኍ 35፥12፡ 21፤1ሳሙ 14፥45፤ ማቴ 10፥30
14፥13 2ሳሙ 12፥7፤13፥38-39፤ 1ነገ 20፥40

*39 የሙት ባሕር ጥቅልና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *የንጉሥ ዳዊት መንፈስ ተነሣሣ* ይላል።
*4 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት፣ የቡልጌትና የሱርስት ትርጒሞች፣ *ሄዳ* ይላሉ፤ አብዛኞቹ ቅጆች ግን፣ *ለንጉሡ ተናገረች* ይላሉ።

13፥39 *ወደ አቤሴሎም ለመሄድ... ተነሣሣ፤* አቤሴሎም ሸሽቶ በስደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ፣ ዳዊት ሁለት አንጋፋ ወንዶች ልጆቹን ከአጠገቡ አጥቶአል።

14፥1 *የጽሩያ ልጅ ኢዮአብ፤* የ2፥13ን ማብ ይመ። *የንጉሡ ልብ አቤሴሎምን እንደ ናፈቀ፤* ዳዊት ቍጣና ፍቅር (ምናልባትም ከባድ ጸጸት) ተፈራርቀውበት ከመጨነቁ የተነሣ፣ በነገሩ ሌሎች ሰዎች እንዲገቡበት መንገድ ሲከፍት ይታያል።

14፥2 *ኢዮአብ... ልኮ፤* ኢዮአብ ዐልጋውን በሚመለከት ረገድ በዳዊትና በልጁ በአቤሴሎም መካከል የነበረው ነገር አሳስቦት የተነሣ ይመስላል። በግልጥ ወደ ተግባር የሚተረጐም መልስ ለማግኘት የሚያስችል ታሪክ ካጋጠመው ችግር ጋር በሚዛመድ መልኩ ለዳዊት እንዲነገር በማድረግ፣ ኢዮአብ ዳዊትን ወደ ተግባር ሊያሸጋግረው ሲሞክር ይታያል። ነቢዩ ናታንም፣ ዳዊት በዚሁ ዐይነት የተግባር እርምጃ ይወስድ ዘንድ ተመሳሳይ ዘዴ ተጠቅሞ ነበር (12፥1-7፤ 1ነገ 20፥38-43 ይመ)። *ቴቁሔ፤* ከቤተልሔም በስተ ደቡብ ጥቂት ምዕራፍ ርቃ የምትገኝ የነቢዩ አሞጽ ከተማ ናት (አሞ 1፥1)።

14፥7 *እነሆ ቤተ ዘመዱ ሁሉ በባሪያህ ላይ ተነሥተው፤* በእስራኤል ኅብረተ ሰብ አንድ ሰው ቢገደል፣ ቅርብ ዘመድ የሚች ወንድሙን ደም መበቀሉ የተለመደ ሥርዐት ነበር (የ3፥27 ማብ፤ እንዲሁም ዘኍ 35፥12፤ ዘዳ 19፥11-13 ይመ)፤ በዚህ ታሪክ ግን በሥርዐቱ መሠረት የደም ብቀላ ቢደረግ፣ የቤተ ሰቡን ዘር በሙሉ የሚያስጨርስ ይሆናል፤ እንዲህ ያለውን ሁኔታ የእስራኤል ሕግ በተቻለ መጠን ፈጽሞ ሊያስወግደው ይሞክር ነበር (የዘዳ 25፥5-6፤ የሩት 2፥20 ማብ ይመ)። *እንገድለዋለን፤* ሴትዮዋ ደም የመበቀሉ ፍላጎት የተቀሰቀሰው ለፍትሕ ሲባል ሳይሆን፣ በግል ጥቅም በመነሣሣት ሀብት ለመውረስ እንደ ሆነ ሐሳብ ታቀርባለች (ዘኍ 27፥11 ይመ)። *ባሌን... ያለ ስምና ያለ ዘር ሊያስቀሩት ነው፤* ይህም ደም በመበቀል ነፍሰ ገዳይን ሳይቀጣ እንዲቀር ከማድረግ የበለጠ የሴትዮዋን ቤተ ሰብ ለማጥፋት ከፍተኛ ጥቃት እንደ መሰንዘር የሚያስቈጥር ነው። ኢዮአብ በዘዴ ዳዊትን ለማሳሰብ የፈለገው፣ አቤሴሎምን ወደ ቦታውና ወደ ቀድሞ መብቱ በወቅቱ እንዲመለስ ካላደረገ፣ ዘውድ ለመጨበጥ ሲባል፣ ብጥብጥ መነሣቱ የማይቀር መሆኑን ነው።

14፥8 *አንቺ ወደ ቤትሽ ሂጂ፤ ስለ ጉዳይሽ አስፈላጊውን ትእዛዝ እሰጣለሁ፤* ዳዊት የሰጠው ፍርድ ታስቦ ባልተፈጸመ የወንጀል ሕግ ላይ ተመርኵዞ የተወሰነ ሳይሆን አይቀርም (ዘዳ 19፥4፡6 ይመ)።

14፥9 *በደሉ፤* የቅጣት ውሳኔ ያልተሰጠበትን ወንጀል የሚያመለክት ነው።

14፥11 *የአምላኩን የእግዚአብሔር ስም እንዲጠራ፤* ሴትዮዋ ዳዊት የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት የሰጣትን ተስፋ እንዲያጸድቅላት ትፈልጋለች። ሕያው እግዚአብሔርን፤ የተለመደ ቃለ መሐላ ሲሆን (ዘፍ 42፥15፤ 1ሳሙ 14፥39)፣ ዳዊት የገባውን ቃል እንዲያከብር የሚያደርግ ነው።

14፥13 *በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ፤* የሴትዮዋ ሐሳብ ቤተ ዘመድ በራሷ ላይ የፈጸመውን ተመሳሳይ ድርጊት ዳዊት በእስራኤል ሕዝብ ላይ እንዳደረገ የሚገልጥ ነው። የእስራኤል ሕዝብ ዐልጋ ወራሻቸው ያላንዳች ጉዳት ወደ ምድራቸው እንዲመለስላቸው ይፈልጋሉ። *ታዲያ ይህን ሲናገር በራሱ ላይ መፍረዱ አይደለምን?* ዳዊት በሐሳብ የተፈጠረውን ነፍሰ ገዳይ ከበቀል ነጻ ሲያደርገው፣ ተመሳሳይ ችግር ላለበት ለአቤሴሎም ግን ይህንኑ ተመሳሳይ ዕድል ባለመስጠቱ ራሱን እንደ በደለኛ ማስቈጠሩን የሚያመለክት ነው። ምሳሌው ዳዊትን በደም ተበቃዩ ጕራ መድቦታል።

14በመሬት ላይ የፈሰሰ ውሃ እንደማይታፈስ
ሁሉ፣ እኛም እንደዚሁ እንሞታለን፤ እግዚ
አብሔር ግን ከአገር የተሰደደ ሰው ከእርሱ
እንደ ራቀ በዚያው እንዳይቀር የሚመለ
ስበትን ሁኔታ ያመቻቻል እንጂ ሕይወቱ
እንድትጠፋ አይፈቅድም።
15“አሁንም ወደዚህ የመጣሁት ሕዝቡ ስላ
ስፈራኝ ይህን ለንጉሥ ጌታዬ ለመንገር ነው።
እኔም አገልጋይህ ይህን አሰብሁ፤ ‘ለንጉሡ
እነግረዋለሁ፤ ምናልባትም አገልጋዩ የጠየቀ
ችውን ይፈጽምላት ይሆናል፤ 16እግዚአብሔር
ከሰጠን ርስት እኔንም ልጄንም ሊነቅለን
ከተነሣው ሰው እጅ ንጉሡ አገልጋዩን ሊታ
ደግ ይፈቅድ ይሆናል።’
17“አሁንም አገልጋይህ፤ ‘ንጉሥ ጌታዬ በጎ
ውንና ክፉውን በመለየት እንደ እግዚአ
ብሔር መልአክ ስለ ሆነ፣ የጌታዬ የንጉሡ
ቃል ያጽናናኝ፤ እግዚአብሔር አምላክህም ካን
ተው ጋር ይሁን’ ትላለች።”
18ከዚያም ንጉሡ ሴቲቱን፣ “እኔም ለምጠ
ይቅሽ ነገር አንቺም መልሱን አትደብቂኝ”
አላት።
ሴቲቱም፣ “ንጉሥ ጌታዬ፤ እሺ ይናገር”
አለችው።
19ንጉሡም፣ “በዚህ ሁሉ የኢዮአብ እጅ
የለበትምን?” ሲል ጠየቃት።
ሴቲቱም መልሳ እንዲህ አለች፤ “ንጉሥ
ጌታዬ ሆይ በሕያው ነፍስህ እምላለሁ፤ ንጉሥ
ጌታዬ ከተናገረው ሁሉ ወደ ቀኝም ወደ
ግራም የሚል ማንም የለም። አዎን ይህን
እንዳደርግ ያዘዘኝና ይህም ሁሉ ቃል በእኔ
በአገልጋይህ አንደበት እንዲነገር የላከኝ አገ
ልጋይህ ኢዮአብ ነው። 20አገልጋይህ ኢዮአብ
ይህን ያደረገውም ያለውን ሁኔታ ለመለወጥ
ሲል ነው፤ ነገር ግን ጌታዬ የእግዚአብሔርን
መልአክ ጥበብ የመሰለ ጥበብ ስላለው፣ በም
ድሪቱ ላይ የሚሆነውን ነገር ሁሉ ያውቃል።”
21ንጉሡም ኢዮአብን፣ “መልካም ነው፤
ፈቅጃለሁ፤ ሂድና ወጣቱን አቤሴሎምን መል
ስህ አምጣው” አለው።
22ኢዮአብም አክብሮቱን ለንጉሡ ለመግ
ለጥ ወደ መሬት በግምባሩ ተደፍቶ እጅ ነሣ፤
ንጉሡንም ባረከ፣ ኢዮአብም በመቀጠል፣
“ንጉሡ የአገልጋዩን ልመና ስለ ተቀበለው፣
ባሪያህ በፊትህ ሞገስ ማግኘቱን ዛሬ ለማ
ወቅ ችሎአል” አለ።
23ከዚያም ኢዮአብ ወደ ጌሹር ሄዶ አቤ
ሴሎምን ወደ ኢየሩሳሌም መልሶ አመጣው።
24ንጉሡ ግን፣ “እዚያው እቤቱ ይሂድ፤ ዐይ
ኔን ማየት የለበትም” አለ። ስለዚህም አቤ
ሴሎም ወደ ቤቱ ሄደ፤ የንጉሡንም ፊት
አላየም።
25መቼም በመልኩ ማማር አቤሴሎምን የሚ
ያህል አንድም ሰው በመላው እስራኤል አልነ
በረም፤ ከራስ ጠጕሩ እስከ እግር ጥፍሩ የሚ
ወጣለት እንከን አልነበረም። 26የራስ ጠጕሩ
ሲከብደው በዓመት አንድ ጊዜ ይቈርጠው
ነበር፤ የተቈረጠውን በሚመዝነው ጊዜ ክብ
ደቱ በቤተ መንግሥቱ ሚዛን ሁለት መቶ
ሰቅል[+] ይሆን ነበር።
27አቤሴሎም ሦስት ወንዶች ልጆችና ትዕ
ማር የተባለች አንዲት ሴት ልጅ ተወለ
ዱለት፤ ሴት ልጁም በጣም ውብ ነበረች።
28አቤሴሎም የንጉሡን ዐይን ሳያይ ሁለት
ዓመት በኢየሩሳሌም ኖረ። 29ከዚያም አቤ
ሴሎም ወደ ንጉሡ እንዲሄድለት ኢዮአብን
አስጠራው፤ ኢዮአብ ግን ወደ እርሱ መም
ጣት አልፈለገም፤ ለሁለተኛ ጊዜም ላከበት፤
ኢዮአብ አሁንም መምጣት አልፈለገም።
30ከዚያም አቤሴሎም ለአገልጋዮቹ “ተመ
ልከቱ የኢዮአብ ዕርሻ የሚገኘው ከእኔ ዕርሻ
አጠገብ ነው፤ በዕርሻው ላይ የገብስ አዝመራ
አለው፤ ሂዱችሁም እሳት ልቀቁበት” አላቸው።
ስለዚህ የአቤሴሎም አገልጋዮች ሄደው የኢ
ዮአብን ዕርሻ በእሳት አቃጠሉት።
31ከዚያም ኢዮአብ ወደ አቤሴሎም ቤት
ሄደ፣ “አገልጋዮችህ ለምንድን ነው ዕርሻዬን
ያቃጠሉት?” ብሎ ጠየቀው።

[+]26 2.3 ኪሎ ግራም ያህል ነው።

14፥14 ዘኍ35፥15፡ 25-28፤ኢዮ10፥8፤ 14፥11፤17፥13፤ 30፥23፤መዝ22፥15፤ 58፥7፤ኢሳ19፥5፤ ዕብ9፥27
14፥16 ዘዳ34፥9፤ 1ሳሙ26፥19
14፥17 1ሳሙ 29፥9፤1ነገ3፥9፤ ዳን2፥21
14፥19 ቍ3
14፥20 2ሳሙ 18፥13፤1ነገ3፥12፡28፤ 10፥23-24፤ኢሳ28፥6
14፥22 ዘፍ47፥7
14፥26 2ሳሙ18፥9
14፥27 2ሳሙ 13፥1፤18፥18
14፥30 ዘፀ9፥31
14፥31 መሳ15፥5

14፥14 *የፈሰሰ ውሃ እንደማይታፈስ፤* የፈሰሰ ውሃ እንደማ ይታፈስ ሁሉ፣ ደም መበቀልም የተገደለውን ሰው ሕይወት እንዲ መለስ አያደርግም። *እግዚአብሔር ግን... ሕይወቱ እንድትጠፋ አይፈቅድም፤* ደም ብቀላ ከእግዚአብሔር የአሠራር መንገዶች ጋር አይስማማም በሚለው ሐሳቧ ውስጥ ሴትዮዋ ስለ እግዚአብሔር ፍትሕ የተሰጠውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት አጣማዋለች (የዘፍ 9፥6 ማብ ይመ)። ሆኖም ግን ሕይወትን ከማጥፋት ይልቅ ሕይወትን በሚጠብቀው በእግዚአብሔር ቸርነት ትደገፋለች (ሕዝ 18፥23፡32፥11 ይመ)። የዳዊት የግል በደልና የሚመጣው የእግዚ አብሔር ምሕረት ልምምድ የተገለጡት ለሴትዮዋ ክርክር ተጨማሪ ክብደት ለመስጠት ነው (የ12፥13፤ 13፥21 ማብ ይመ)።

14፥15 *ሕዝቡ ስላስፈራኝ፤* ሴትዮዋ ወደ ፈጠራ ታሪኳ ትመለሳለች። “ሕዝቡ” የተባለው ደም በቀልን የሚፈልጉ የቤተ ሰቧ አባላት ናቸው።

14፥17 *በጎውንና ክፉውን በመለየት እንደ እግዚአብሔር መልአክ፤* በመሠረቱ አንድ ንጉሥ ማድረግ እንደሚገባው፣ ከማን ኛውም ሰው በላቀ ሁኔታ ክፉውንና ደጉን መለየት ይችላል ማለት ነው (ቍ 20፤ 19፥27 ይመ)።

14፥21 *ኢዮአብ፤* ምንጊዜም ከንጉሥ ዳዊት ተለይቶ የማ ያውቅ ሰው ይመስላል።

14፥23 *ኢዮአብ ወደ ጌሹሩ ሄዶ፤* 13፥37 ይመ

14፥24 *ዐይኔን ማየት የለበትም፤* ዳዊት አሁንም በአንድ ሐሳብ ላይ አለመርጋቱን ያመለክታል (የቍ 1 ማብ ይመ)፤ ለአቤሴሎም ይቅርታ አላደርግለትም፤ ወደ ቀድሞ ሁኔታውም አይመልሰም።

14፥25 *አንድም ሰው... አልነበረም፤* የአቤሴሎም መልከ ቀናነቱ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን አትርፎለታል።

14፥26 *የራስ ጠጕሩ፤* በዚያን ጊዜ በነበረው ሕዝብ ዘንድ ጠጕር የጥንካሬ ምልክት ተደርጎ ይታይ ነበር። ነገሥታትና ጀግኖችም ጠጕራቸው ተጐንጒኖ መልካቸው በሥዕል ይቀረጽ የነበረ ሲሆን፣ መላጣነት ግን እንደ ነውር ይቈጠር ነበር (2ነገ 2፥23 ይመ)፤ ከዚህ አንጻር ሲታይ አቤሴሎም ለዙፋኑ ብቁ ሰው ይመስላል። *በቤተ መንግሥቱ... ሰቅል፤* ከቤተ መቅደሱ ሰቅል ይልቅ የቤተ መንግሥቱ ሰቅል ሚዛን የሚደፋ ይመስላል (ዘፀ 30፥13፤ ዘሌ 5፥15፤ ዘኍ 3፥47 ይመ)።

14፥27 *ሦስት ወንዶች ልጆች፤* ስማቸው አይታወቅም፤ 18፥18 በልጅነታቸው መሞታቸውን ያመለክታል። *ትዕማር፤* አቤ ሴሎም ልጁን በእኅቱ በትዕማር ስም ሰየማት (13፥1)። *መዓካ፤* (1ነገ 15፥2) የትዕማር ልጅ የአቤሴሎም የልጅ ልጅ ሳትሆን አትቀርም (የ2ዜና 11፥20 ማብ ይመ)።

32አቤሴሎምም፣ ኢዮአብን፣ “ከጌሹር ለምን
መጣሁ? ለእኔ እስካሁንም እዚያው ብሆን
ይሻለኝ ነበር ብሎአል ብለህ እንድ ትነግ
ርልኝ ‘ወደ ንጉሡ እልክህ ዘንድ ወደ እኔ
ና’ ብዬ አስጠራሁህ፤ አሁንም ቢሆን፤ የንጉ
ሡን ዐይን ማየት እፈልጋለሁ፤ ምንም ዐይ
ነት በደል ከተገኘብኝ ይግደለኝ” አለው::
33ኢዮአብም ወደ ንጉሡ ሄዶ ይህንኑ ነገ
ረው:: ከዚያም ንጉሡ አቤሴሎምን አስጠራው፤
እርሱም መጥቶ በንጉሡ ፊት በግምባሩ
ተደፍቶ እጅ ነሣ፤ ንጉሡም አቤሴሎምን
ሳመው::

## የአቤሴሎም ዐመፅ

15ከዚህ በኋላ አቤሴሎም ሠረገላና
ፈረሶች እንዲሁም ፊት ፊቱ የሚ
ሮጡ አምሳ ሰዎች ለራሱ አዘጋጀ:: 2አቤሴ
ሎምም በማለዳ ተነሥቶ ወደ ከተማዪቱ
መግቢያ በር በሚወስደው መንገድ ዳር ሆን
ብሎ ይቆም ነበር:: ማናቸውም ባለ ጉዳይ
አቤቱታውን ለንጉሡ አቅርቦ ለማስወሰን
በሚመጣበት ጊዜ ሁሉ፣ አቤሴሎም ወደ
እርሱ እየጠራ፣ “አንተ ከየትኛው ከተማ
ነው የመጣኸው? በማለት ይጠይቀዋል፤ ያም
ሰው፣ “አገልጋይህ ከአንዱ የእስራኤል ነገ
ዶች ነው” ብሎ ይመልስለታል:: 3ከዚያም
አቤሴሎም፣ “ተመልከት! ጉዳይህማ ትክክ
ልና ተገቢም ነው፤ የትኛው የንጉሥ እንደ
ራሴ ነው ታዲያ የሚያይልህ?” ይለዋል::
4ቀጠል አድርጎም፣ “ምነው ዳኛ ሆኜ በም
ድሪቱ ላይ በተሾምሁ! አቤቱታ ወይም ክስ
ያለበት ሁሉ ወደ እኔ እየመጣ ፍትሕ እን
ዲያገኝ አደርገው ነበር” ይል ነበር::
5እንዲሁም ማናቸውም ሰው ወደ እርሱ
ቀርቦ እጅ በሚነሣው ጊዜ፣ አቤሴሎም እጁን
ዘርግቶ ይይዘውና ይስመው ነበር:: 6አቤሴ
ሎም ፍትሕ ለማግኘት ወደ ንጉሡ የሚመ
ጣውን እስራኤላዊ ሁሉ የሚቀርበው በዚህ
መንገድ ስለ ነበር፣ የእስራኤልን ሰዎች
ልብ ሰረቀ::
7ከአራት ዓመት[T] በኋላም አቤሴሎም ንጉ
ሡን እንዲህ አለው፤ “ለእግዚአብሔር የተ
ሳልሁትን ስእለት ለማድረስ ወደ ኬብሮን
እንድሄድ ፍቀድልኝ፤ 8እኔ አገልጋይህ በሶ
ርያ ምድር በጌሹር ሳለሁ ‘እግዚአብሔር
ወደ ኢየሩሳሌም የመለሰኝ እንደ ሆነ፣ በኬ
ብሮን[U] ለእግዚአብሔር እሰግዳለሁ’ ብዬ ተስ
ያለሁ::”
9ንጉሡም፣ “በሰላም ሂድ” አለው፤ ስለዚህ
አቤሴሎም ወደ ኬብሮን ሄደ::
10ከዚያም አቤሴሎም፣ “የቀንደ መለከት
ድምፅ ስትሰሙ፣ ‘አቤሴሎም በኬብሮን ነገሠ
በሉ” የሚሉ የምስጢር ሠራተኞችን በመ
ላው የእስራኤል ነገዶች አሰማራ:: 11ከኢ
የሩሳሌምም ሁለት መቶ ሰዎች አብረውት
ሄዱ፤ በእንግድነት ተጋብዘው በየዋህነት
ከመሄዳቸው በስተቀር፣ ስለ ጉዳዩ የሚያ
ውቁት አንዳችም ነገር አልነበረም:: 12አቤ
ሴሎም መሥዋዕት በሚያቀርብበት ጊዜ የዳ
ዊት አማካሪ የሆነው ጊሎአዊው አኪጦፌል
ከአገሩ ከጊሎ ወደ እርሱ እንዲመጣ ላከ
በት፤ ስለዚህ ሤራው ጥንካሬ አገኘ፤ የአቤ
ሴሎምም ተከታዮች ቍጥር እየጨመረ መጣ::

## የዳዊት ሽሽት

13መልእክተኛም መጥቶ፣ “የእስራኤል ሰዎች
ልብ ከአቤሴሎም ጋር ሆኖአል” ብሎ ለዳ
ዊት ነገረው::
14ከዚያም ዳዊት በኢየሩሳሌም ላሉት ሹማ
ምንቱ ሁሉ፣ “ተነሡ እንሽሽ፤ ያለበለዚያ
አንዳችንም ከአቤሴሎም እጅ ማምለጥ አን
ችልም፤ አሁኑኑ ከዚህ መውጣት አለብን፤

14፥32 1ሳሙ 20፥8፤2ሳሙ 3፥3
14፥33 ሉቃ 15፥20
15፥1 1ሳሙ 8፥11፤ 2ሳሙ 12፥11
15፥2 ዘፍ 23፥10፤ 2ሳሙ 19፥8
15፥3 ምሳ 12፥2
15፥4 መሳ 9፥29
15፥6 ሮሜ 16፥18
15፥8 ዘፍ 28፥20፤ 2ሳሙ 3፥3
15፥10 1ነገ 1፥34፡ 39፤2ነገ 9፥13
15፥12 ቍ 31:34፤ ኢሱ 15፥51፤2ሳሙ 16፥15:23፤17፥14፤ 23፥34፤1ዜና 27፥33፤ ኢዮ 19፥14፤መዝ 3፥1፤41፥9፤55፥13፤ ኤር 9፥4
15፥14 2ሳሙ 19፥9፤1ነገ 2፥26፤ መዝ3 ርእስ፤132፥1

[T]7 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም፣ የሱርስቱ ቅጅና የአይሁዳዊው የታሪክ ጸሓፊ የዮሴፍ ወልደ ኮሪዮን ጽሑፎች ከዚህ ጋር ይስማሙ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ አርባ ይላል::
[U]8 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማሙ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ኬብሮን* የሚለውን ቃል አይጨርም::

14፥32 *በደል ከተገኘብኝ ይግደለኝ፤* አቤሴሎም ሙሉ በሙሉ ምሕረት እንዲደረግለትና የልጅነት መብቱም እንዲመለስለት፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ የሞት ፍርድ እንዲፈረድበት ጠየቀ፤ ነገር ግን ንስሓ የመግባት አዝማሚያ አላሳየም::

14፥33 *ንጉሡም አቤሴሎምን ሳመው፤* ዳዊት ይቅርታ ያደረገለት መሆኑን አቤሴሎም ከመላው ንጉሣዊ ቤተ ሰብ ጋር መታረቁን የሚያመለክት ነው::

15፥1 *ሠረገላና ፈረሶች፤* እንደሚታወቀው መጀመሪያ በሠረገላና በፈረሶች የተገለገለው የእስራኤል መሪ አቤሴሎም ነበር (ከዘዳ 17፥16 ጋር ያነጻጽሩ):: *አምሳ ሰዎች፤* ምናልባት የክብር ዘብ በመሆን ሳያገለግሉትና በሕዝብም ፊት የክብር ሰልፍ ሳያሳዩ አልቀረም:: በኋላም አዶንያስ የአቤሴሎምን ምሳሌ ተከተለ (1ነገ 1፥5)::

15፥3 *ጉዳይህማ! ትክክልና ተገቢም ነው፤* አቤሴሎም የሕዝቡ አቤቱታ ተገቢ መሆኑን ሳያጣራ፣ በደፈናው በመቀበል ከእነርሱ ድጋፍ ለማግኘት ይፈልጋል::

15፥4 *ምነው ዳኛ ሆኜ በምድሪቱ ላይ በተሾምኩ፤* አቤሴሎም ለሕዝቡ ሕጋዊ አቤቱታ ራሱን እንደ መፍትሄ አድርጎ ያቀርባል:: አምኖንን በተመለከተ ከአባቱ ቸልተኝነት የተነሣ የበቀል እርምጃ የወሰደበት እርሱ ራሱ ነበር:: አቤሴሎም በአባቱ አገዛዝ ላይ ድክመት እንዳለ ተረድቶአል፤ ይህንንም ድክመት የራሱን የፖለቲካ ዐላማ ለማሳካት ተጠቅሞበታል::

15፥7 *ከአራት ዓመት፤* ወደ ቤተ መንግሥት ከተመለሰ በኋላ ማለት ነው (14፥33):: በዚህ ጊዜ አቤሴሎም የሠላሳ ዓመት ጕልማሳ ሳይሆን አይቀርም:: ስለዚህ አቤሴሎም ዐመፁን ያካሄደበት ጊዜ በመጨረሻዎቹ የአባቱ የአገዛዝ ዓመታት መጀመሪያ ላይ እንደ ነበረ መታወቅ አለበት:: *ኬብሮን፤* ዳዊት በመጀመሪያ ንጉሥ መሆኑ የታወጀበትና (የ2፥1:4፤ 5፥3:5 ማብ ይመ) አቤሴሎም የተወለደበት ከተማ ነው (3፥2-3):: ዳዊት ኬብሮንን ትቶ ኢየሩሳሌምን ዋና ከተማ በማድረጉ፣ አቤሴሎም ከዋና ከተማው መዛወር የተነሣ በተፈጠረው የሕዝብ ቅሬታ ለመጠቀም ሳይፈልግ አልቀረም:: ኬብሮን የታወቀ የአምልኮ ስፍራ ነበረባት::

15፥8 *በጌሹር፤* 13፥37 ይመ::

15፥12 *አኪጦፌል፤* የቤርሳቤህ አያት ሲሆን (11፥3፤ 23፥34 ይመ)፤ አስተዋይና የተከበረ፣ ምክር ዐዋቂ ሰው ነበር (16፥23):: ምናልባት ዳዊት በቤርሳቤህና በኦርዮ ላይ ካደረገው ነገር የተነሣ አቤሴሎም በዐቀደው ዐመፅ ውስጥ በስውር ሳይተባበር አልቀረም:: በመዝ 41፥9፤ 55፥12-14 ላይ የሚገኘውን ዳዊት እንዲናገር የገፋፋው ከቅርብ ወዳጅ የማይጠበቅ ይህ ዐይነቱ ክሕደት ስለ ደረሰበት ሊሆን ይችላል:: *ጊሎአዊው፤* ጊሎ የምትገኘው ከኬብሮን አጠገብ ነበር::

15፥14 *አንዳችንም ከአቤሴሎም እጅ ማምለጥ አንችልም፤* አቤሴሎም ምን ያህል ድጋፍ እንዳለው (ቍ 13 ይመ) ባለማወቁ፣ ዳዊት ኢየሩሳሌም ውስጥ እያለ እንዳይያዝ ሥጋት አድሮበታል፤

ካልሆነ ገሥግሦ መጥቶ ከያዘን እኛን ያጠ
ፋናል፤ ከተማዪቱንም በሰይፍ ይመታታል”
አላቸው።
[15]የንጉሡ ሹማምንትም፣ “ጌታችን ንጉሡ
የመረጠውን ሁሉ ለማድረግ እኛ አገልጋ
ዮችህ ዝግጁ ነን” ብለው መለሱለት።
[16]ንጉሡ ከመላው ቤተ ሰቡ ጋር ወጣ፤ ቤተ
መንግሥቱንም እንዲጠብቁ ዐሥር ቁባቶች
አስቀረ። [17]ስለዚህ ንጉሡ መላውን ሕዝብ
አስከትሎ ወጣ፤ ጥቂት ርቀው ከሄዱ በኋ
ላም በአንዲት ቦታ ቆሙ። [18]ሰዎቹ ሁሉ፣
ከሊታውያን፣ ፊሊታውያን እንዲሁም ከጌት
አብረውት የመጡትን ስድስት መቶ ጌታ
ውያንን ሁሉ ጨምሮ ተሰልፈው በንጉሡ
ፊት ዐለፉ።
[19]ንጉሡም ጌታውን ኢታይን እንዲህ
አለው፤ “ከእኛ ጋር የመጣኸው ለምንድን
ነው? ተመለስና ከንጉሡ ከአቤሴሎም ጋር
ተቀመጥ፤ አንተ ለራስህ ከአገርህ ተወስደህ
የመጣህ እንግዳ ነህ፤ [20]የመጣኸውም ገና
ትናንት ነው፤ ታዲያ የት እንደምሄድ የማ
ላውቅ ሰው እንዴት ዛሬ ከእኛ ጋር እንድ
ትንከራተት ላድርግ? በል አሁንም ሰዎች
ህን ይዘህ ተመለስ፤ በጎነትና ታማኝነትም
ከአንተ ጋር ይሁን” አለው።
[21]ኢታይ ግን፣ “ሕያው እግዚአብሔርን!
እንዲሁም በጌታዬ በንጉሡ እምላለሁ፤ ሕይ
ወትም ይሁን ሞት በየትም ቦታ ንጉሥ
ጌታዬ የሚሆነውን ሁሉ አገልጋይህም እን
ደዚያው ይሆናል” ብሎ መለሰለት።
[22]ዳዊትም ኢታይን፣ “በል እንግዲያው
ቅደምና ሂድ” አለው። ስለዚህ ጌታዊው ኢታይ
ሰዎቹን ሁሉና አብረውት የነበሩትን ቤተ
ሰቦቹን ይዞ ሄደ።
[23]ሕዝቡ ሁሉ በሚያልፍበትም ጊዜ ባላ
ገሩ በሙሉ እየጮኸ አለቀሰ፤ ንጉሡም የቄ
ድሮንን ሸለቆ ተሻገረ፤ ሕዝቡም ሁሉ ተሻ
ግሮ ወደ ምድረ በዳው ተጓዘ።

[24]ሳዶቅም በዚያ ነበር፤ አብረውት የነበሩ
ትም ሌዋውያን ሁሉ የእግዚአብሔርን የኪዳ
ኑን ታቦት ተሸክመው ነበር። እነርሱም የእ
ግዚአብሔርን ታቦት ዐኖሩ፤ አብያታርም ሕዝቡ
በሙሉ ከከተማዪቱ ለቆ እስኪወጣ ድረስ
መሥዋዕት አቀረበ[a]።
[25]ከዚያም ንጉሡ ሳዶቅን እንዲህ አለው፤
“አንተ የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ከተማዪቱ
ይዘህ ተመለስ፤ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ
አግኝቼ እንደ ሆነ፣ እርሱ እኔንም መልሶ
ታቦቱንና ማደሪያውን እንደ ገና ለማየት
ያበቃኛል፤ [26]ነገር ግን እርሱ፣ ‘ባንተ አል
ተደሰትሁም’ የሚል ከሆነ፣ መልካም መስሎ
የታየውን ነገር ያድርግብኝ፤ እኔም ለመቀ
በል ዝግጁ ነኝ።”
[27]እንዲሁም ንጉሡ ካህኑን ሳዶቅን እንዲህ
አለው፤ “አንተ ነቢይ አይደለህምን? እንግ
ዲህ አንተም ልጅህን አኪማአስን፣ የአብያ
ታርን ልጅ ዮናታንን ይዘህ በሰላም ወደ
ከተማዪቱ ተመለስ። አንተና አብያታር ሁለ
ቱን ልጆቻችሁን ይዛችሁ ሂዱ። [28]እኔም
ከአንተ ዘንድ ወሬ እስካገኝ ድረስ በምድረ
በዳው በሚገኘው በወንዙ መሻገሪያ እቈያለሁ”
[29]ስለዚህ ሳዶቅና አብያታር የእግዚአብሔርን
ታቦት ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም በመመለስ
እዚያው ቈዩ።
[30]ዳዊት ግን እያለቀሰ የደብረ ዘይትን ተራራ
ሽቅብ ወጣ፤ ራሱን ተከናንቦ፣ ባዶ እግሩን
ነበር፤ አብሮት ያለውም ሕዝብ ሁሉ እን
ደዚሁ ራሱን ተከናንቦ እያለቀሰ ሽቅብ ይወጣ
ነበር። [31]በዚህ ጊዜ፣ “ከአቤሴሎም ጋር ካሤሩት
መካከል አንዱ አኪጦፌል ነው” ብለው ለዳ
ዊት ነገሩት። ስለዚህ ዳዊት፣ “እግዚአብሔር
ሆይ፤ እባክህን የአኪጦፌልን ምክር ወደ
ከንቱነት ለውጠው” ብሎ ጸለየ።
[32]ዳዊትም ሕዝቡ እግዚአብሔርን ወደሚ
ያመልክበት ወደ ተራራው ጫፍ ሲደርስ፣

15፥16 2ሳሙ 16፥21-22፤20፥3
15፥18 1ሳሙ 30፥14፤2ሳሙ 20፥7፡23፤1ነገ 1፥38፡44፤1ዜና 18፥17
15፥19 ዘፍ 31፥15፤2ሳሙ 18፥2
15፥20 1ሳሙ 22፥2፤2ሳሙ 2፥6
15፥21 ሩት 1፥16-17፤ምሳ 17፥17
15፥23 1ሳሙ 11፥4፤1ነገ 2፥37፤2ነገ 23፥12፤2ዜና 15፥16፤29፥16፤30፥14፤ኢዮ 2፥12፤ኤር 31፥40፤ዮሐ 18፥1
15፥24 ዘኍ 4፥15፤10፥33፤1ሳሙ 22፥20፤2ሳሙ 8፥17፤19፥11
15፥25 ዘፀ 15፥13፤ዘሌ 15፥31፤መዝ 43፥3፤46፥4፤84፥1፤132፥7
15፥26 መሳ 10፥15፤2ሳሙ 22፥20
15፥27 ቍ 36፤1ሳሙ 9፥9፤2ሳሙ 17፥17፤1ነገ 1፥42
15፥28 2ሳሙ 17፥16
15፥30 ዘኍ 25፥6፤አስ 6፥12፤መዝ 30፥5
15፥31 ቍ 12
15፥32 ቍ 37፤ኢያ 7፥6፤16፥2፤2ሳሙ 16፥16፤17፥5፤1ነገ 4፥16

[a]24 ወይም *አብያታር ሄዶ*

ከተማዪቱንም በደም ከመጥለቅለቅ ትድን ዘንድ ሊታደጋት ፈልጎአል።

15፥16 *ቤተ መንግሥቱንም እንዲጠብቁ ዐሥር ቁባቶች አስቀረ፤* 5፥13 እንዲሁም የ3፥2 ማብ ይመ። ዳዊት ስለ እርሱ ናታን የተናገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ሳይታወቀው ሁኔታዎችን አመቻቸ (12፥11ን፤ እንዲሁም 20፥3 ይመ)።

15፥18 *ከሊታውያን፣ ፊሊታውያን፤* የ8፥18 ማብ ይመ። *ስድስት መቶ ጌታውያን፤* ከጌት የመጡ በኢታይ እዝ ሥር ቈይ ተው፣ በኋላ ባልታወቀ ምክንያት ከዳዊት የክብር ዘብ ጋር ተቀ ላቅለው የነበሩ ፍልስጥኤማውያን ወታደሮች ናቸው (18፥2 ይመ)።

15፥19 *ተመለስና ከንጉሡ ከአቤሴሎም ጋር ተቀመጥ፤* ዳዊት ይህን የፍልስጥኤም የጦር ክፍል ለእርሱ ከሚሰጠው ተከ ታታይ ወታደራዊ አገልግሎት ነጻ አድርጎ ለቆታል።

15፥21 *ሕያው እግዚአብሔርን፤* በእስራኤል አምላክ ስም የተሰጠ የታማኝነትና የአገልጋይነት መግለጫ መሐላ ነው (የ1ሳሙ 14፥39 ማብ ይመ)። ለተመሳሳይ መሐላ ሩት 1፥16-17 ይመ።

15፥24 *ሳዶቅም፤* የ8፥17 ማብ ይመ። *አብያታርም፤* የ8፥17 ማብ፤ እንዲሁም 1ሳሙ 22፥20-23 ይመ።

15፥25 *የእግዚአብሔርን ታቦት ወደ ከተማዪቱ ይዘህ ተመለስ፤* ዳዊት በእግዚአብሔር ታቦትና እግዚአብሔር በሕዝቡ ዘንድ በማደሩ መካከል ግንኙነት ያለ ለመሆኑ እውነተኛ ግንዛቤ እንዳለው ያሳያል። ታቦቱን ይዞ መገኘት ለእግዚአብሔር በረከት ዋስትና ሊሆን እንደማይችል ያውቃል (የ1ሳሙ 4፥2፡21 ማብ ይመ)። ታቦቱ በዋና ከተማው ውስጥ መቀመጡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለሚያስተዳድርበት ሕግ ምልክት እንደ ሆነም ያውቃል (የ6፥21 ማብ ይመ)።

15፥26 *መልካም መስሎ የሚታየውን ነገር ያድርግብኝ፤* ዳዊት ራሱን ብቻ የዙፋኑ ባለቤት አድርጎ የማቅረብ መብት እንደሌለውና እውነተኛ አምላክ የሆነው የእስራኤል ንጉሥ መንግሥቱን እርሱ ለሚመርጠው አሳልፎ መስጠት እንደሚችል በይፋ ይናገራል።

15፥27 *አንተ ነቢይ አይደለህምን?* ምናልባት መለኮታዊ መገለጥን ለማግኘት ሊቀ ካህናቱ በኡሪምና በቱሚም የሚያከናውነውን ተግባር በተዘዋዋሪ መንገድ ለማመልከት የተጠቀሰ ሊሆን ይችላል (የዘፀ 28፥30፤ የ1ሳሙ 2፥28 ማብ ይመ)፤ በተጨማሪም የ1ሳሙ 9፥9 ማብ ይመ።

15፥28 *በምድረ በዳው... መሻገሪያ፤* በጌልገላ አቅራቢያ የሚገኝ የዮርዳኖስ ወንዝ መሻገሪያ ነው።

15፥30 *ተከናንቦ... ነበር፤* የሐዘን ምልክት ነው (ኢሳ 6፥12፤ ኤር 14፥3-4 ይመ)። *ባዶ እግሩን ነበር፤* ሌላው የሐዘን ምልክት ነው (ኢሳ 20፥2፡4፤ ሕዝ 24፥17፤ ሚክ 1፥8 ይመ)።

15፥31 *አኪጦፌል፤* የቍ 12 ማብ ይመ።

አርካዊው ኩሲ ልብሱን ቀዶ ትቢያ በራሱ
ላይ ነስንሶ ሊገናኘው መጣ::
33ከዚያም ዳዊት እንዲህ አለው፤ “አብ
ረኸኝ ብትሄድ ሸክም ትሆንብኛለህ፤ 34ነገር
ግን ወደ ከተማዪቱ ተመልሰህ አቤሴሎምን፣
‘ንጉሥ ሆይ፤ አገልጋይህ እሆናለሁ፤ ቀድሞ
የአባትህ አገልጋይ እንደ ነበርሁ ሁሉ፣ ዛሬም
አንተን አገለግልሃለሁ’ ብትለው የአኪጦፌ
ልን ምክር በማፍረስ ትረዳኛለህ:: 35ካህናቱ
ሳዶቅና አብያታር እዚያው ከአንተው ጋር
ይሆኑ የለምን? ከቤተ መንግሥቱ የምትሰ
ማትን ሁሉ ንገራቸው:: 36የሳዶቅ ልጅ አኪ
ማአስና የአብያታር ልጅ ዮናታን፣ ሁለቱ
ወንዶች ልጆቻቸው እዚያው አብረዋቸው
ይገኛሉ:: የምትሰማትን ሁሉ በእነርሱ ላክ
ልኝ::”
37ስለዚህ የዳዊት ወዳጅ ኩሲ ልክ አቤ
ሴሎም ኢየሩሳሌም በገባበት ሰዓት እዚ
ያው ደረሰ::

## ዳዊትና ሲባ

16 ዳዊት ከተራራው ጫፍ ባሻገር ጥቂት
እልፍ ብሎ እንደ ሄደ፣ ሲባ የተባ
ለው የሜምፊቦስቴ አገልጋይ፣ ሁለት መቶ
እንጀራ፣ አንድ መቶ ጥፍጥፍ ዘቢብ፣ አንድ
መቶ ጥፍጥፍ በለስና አንድ አቍማዳ የወ
ይን ጠጅ የተጫኑ ሁለት አህዮች እየነዳ
ሊገናኘው መጣ::
2ንጉሡም ሲባን፣ “ይህን ሁሉ ያመጣኸው
ለምንድን ነው?” ሲል ጠየቀው::
ሲባም “አህዮቹን የንጉሡ ቤተ ሰዎች እን
ዲቀመጡባቸው፣ እንጀራውንና በለሱን ወጣ
ቶቹ እንዲበሉት፣ የወይን ጠጁን ደግሞ በም
ድረ በዳ የደከሙት እንዲጠጡት ነው”
አለው::
3ከዚያም ንጉሡ፣ “የጌታህ ልጅ የት ነው?”
ሲል ጠየቀው::
ሲባም፣ “‘የእስራኤል ቤት ዛሬ የአባቴን
መንግሥት ይመልስልኛል’ ብሎ ስለሚያ
ስብ፣ በኢየሩሳሌም ተቀምጦአል” አለው::
4ከዚያም ንጉሡ ሲባን፣ “የሜምፊቦስቴ የነ
በረው ሁሉ ከእንግዲህ ያንተ ነው” አለው::
ሲባም፣ “በታላቅ ትሕትና በግንባሬ ተደ
ፍቼ እጅ እነሣለሁ፤ ንጉሥ ጌታዬ ሆይ፤
በፊትህ ሞገስ ላግኝ” አለው::

## ሳሚ ንጉሥ ዳዊትን ረገመ

5ንጉሥ ዳዊት ወደ ብራቂም ሲደርስ፣ ከሳ
ኦል ቤተ ሰብ ነገድ የሆነ አንድ ሰው ብቅ
አለ፤ እርሱም የጌራ ልጅ ሳሚ ነው፤ እየተ
ራገመም ወጣ:: 6የንጉሡ ወታደሮችና የክ
ብር ዘቦቹ ሁሉ በዳዊት ግራና ቀኝ ቢኖሩም
እንኳ፣ በዳዊትና በሹማምንቱ ላይ ሁሉ
ድንጋይ ይወረውርባቸው ነበር:: 7ሳሚም
እንዲህ ብሎ ይራገም ነበር፤ “ውጣ! ከዚህ
ውጣ! አንተ የደም ሰው፤ አንተ ክፉ ሰው፤
8መንግሥቱን የወሰድክበትን የሳኦልን ቤተ
ሰው ደም ሁሉ *እግዚአብሔር* ወደ አንተው
እየመለሰው ነው:: *እግዚአብሔር* መንግሥ
ትህን ለልጅህ ለአቤሴሎም አሳልፎ ሰጥቶ
ታል፤ አንተ የደም ሰው ስለ ሆንህ እነሆ፣
መከራ መጥቶብሃል::”
9ከዚያም የጽሩያ ልጅ አቢሳ ንጉሡን፤
“ይህ የሞተ ውሻ፣ ንጉሥ ጌታዬን እንዴት
ይራገማል? ልሻገርና ራሱን ልቍረጠው” አለ።
10ንጉሡ ግን፣ “እናንተ የጽሩያ ልጆች እና
ንተንና እኔን የሚያገናኘን ምን ነገር አለ?
*እግዚአብሔር*፣ ‘ዳዊትን ርገመው’ ብሎት
የሚረግመኝ ከሆነ፣ ‘ይህን ለምን አደረግህ’
ብሎ ማን ሊጠይቀው ይችላል?” አለው::
11ከዚያም ዳዊት አቢሳንና ሹማምንቱን
ሁሉ እንዲህ አላቸው፤ “ከአብራኬ የወጣው
ልጄ ሕይወቴን ሊያጠፋት ከፈለገ፣ ይህ ብን
ያማዊ ቢያደርገው ምን ያስደንቃል? ስለዚህ
ተዉት፤ *እግዚአብሔር* በል ብሎት ነውና
ይራገም፤ 12ምናልባትም *እግዚአብሔር* ሐዘ
ኔን አይቶ በዛሬውም ርግማን ፈንታ በጎ

15፥33 2ሳሙ 19፥35
15፥34 2ሳሙ 16፥19፤17፥14፤ ምሳ11፥14
15፥35 2ሳሙ 17፥15-16
15፥36 ቍ27፤ 2ሳሙ17፥17፤ 18፥19፤1ነገ1፥42
15፥37 2ሳሙ 16፥15፤1ዜና27፥33
16፥1 1ሳሙ 25፥18፤2ሳሙ9፥1-13 ፤1ዜና12፥40
16፥2 2ሳሙ 17፥27-29
16፥3 2ሳሙ9፥2፡ 9-10
16፥4 2ሳሙ4፥4
16፥5 ዘፀ22፥28፤ 2ሳሙ3፥16፤ 19፥16-23፤ 1ነገ2፥8-9፡36፡44
16፥8 2ሳሙ19፥19፡ 28፤21፥9፤መዝ55፥3
16፥9 1ሳሙ26፥6፤ 2ሳሙ3፥8፡39፤ ሉቃ9፥54
16፥10 2ሳሙ 2፥18፤19፥22፤ ሮሜ9፥20
16፥11 ዘፍ45፥5፤ 1ሳሙ26፥19፤ 2ሳሙ12፥11
16፥12 ዘዳ23፥5፤ መዝ4፥1፤25፥18፤ 109፥28፤ሮሜ8፥28

15፥32 *አርካዊው ኩሲ፤* አርካውያን ከቤቴል በስተ ደቡብ ምዕራብ የሰፈሩ ጐሣዎች (አንዳንዶች ከእስራኤል ወገን አይደሉም ይላሉ) ናቸው (ኢያ 16፥2):: ኩሲ በዳዊት ቤተ መንግሥት ውስጥ ታማኝ እንደ መሆኑ (የቍ 37 ማብ ይመ)፣ የእርሱ መምጣት የዳዊት ጸሎት መልስ የማግኘት ጅማሬ ነበር (ቍ 31)::

15፥37 *የዳዊት ወዳጅ ኩሲ፤* 1ዜና 27፥33 “የንጉሡ ወዳጅ” ይለዋል፤ ታማኝ የሆነ የንጉሥ አማካሪ የማዕረግ ስም ይመስላል (“የንጉሥ ወዳጅ” የሚለው ሐረግ በዕብራይስጥ ቋንቋ “የንጉሥ የግል አማካሪ” ተብሎ የተተረጐመበትን 1ነገ 4፥5 ይመ)::

16፥1 *ሲባ፤* ም 9 ይመ:: *ሜምፊቦስቴ፤* የ4፥4 ማብ ይመ::

16፥2 *ሲባም... አለው፤* ዳዊት የሳኦልን ግዛት በቍጥጥሬ ሥር አስገብቻለሁ በማለቱ (9፥7-10)፣ ምንጊዜም ጥቅም አሳዳጅ የሆነው ሲባ፣ የተፈጠረውን የፖለቲካ ቀውስ የግል ፍላጎቱ ማሳኪያ ሊያደርገው ይፈልጋል::

16፥3 *የጌታህ ልጅ፤* ሜምፊቦስቴን ማለቱ ነው (9፥3፡9 ይመ)::

16፥4 *የሜምፊቦስቴ የነበረው ሁሉ ከእንግዲህ ያንተ ነው፤* ዐመፅ በየቦታው እየተስፋፋ ታማኝነትም እየጐደለ በመሄዱ ዳዊት መጥፎ እርምጃዎችን በፍጥነት ይወስድ ጀመረ::

16፥5 *ብራቂም፤* ከደብረ ዘይት ተራራ በስተ ምሥራቅ ባለው ተዳፋት ላይ የሚገኝ ከተማ ነው (የ3፥16 ማብ ይመ):: *ከሳኦል ቤተ ሰብ ነገድ፤* የማጥሪ ወገን ነው (1ሳሙ 10፥21 ይመ):: *ጌራ፤* ከሳኦል ጋር ያለው ዝምድና በትክክል አይታወቅም (የ1ነገ 2፥8 ማብ ይመ)::

16፥6 *ወታደሮችና የክብር ዘቦቹ፤* ከሊታውያን፣ ፈሊታውያንና 600 ጌታውያን ናቸው (15፥18 ይመ)::

16፥7 *አንተ ክፉ ሰው፤* የዘዳ 13፥13 ማብ ይመ::

16፥8 *የሳኦልን ቤተ ሰው ደም፤* ሳሚ እዚህ ላይ የሚጠቅሰው በ21፥1-14 ላይ የተገለጠውን የስቅላት ሞት ሳይሆን አልቀረም፤ ይሁን እንጂ ድርጊቱ መቼ እንደ ተፈጸመ በትክክል አይታወቅም (የ21፥1 ማብ ይመ)::

16፥9 *አቢሳ፤* የ1ሳሙ 26፥6 ማብ ይመ:: *ይህ የሞተ ውሻ፤* የመጨረሻ ንቀትን ለመግለጥ የሚሰነዘር አባባል ነው (የ9፥8 ማብ ይመ)::

16፥10 *እግዚአብሔር፣ ‘ዳዊትን ርገመው’ ብሎት የሚረግመኝ ከሆነ፤* ዳዊት የሥልጣን ዘመኑ ያበቃ ዘንድ ይህ ጊዜ ምቹ እንደ ሆነ እግዚአብሔር መመልከቱን ግልጥ አድርጎ ያሳያል፤ ይሁን እንጂ የፍርዱ ጊዜ ገና አልደረሰም ነበር (15፥26 ይመ):: ዳዊት በሳሚ ላይ በኋላ ስለ ወሰዳቸው እርምጃዎች 19፥18-23፤ 1ነገ 2፥8-9 ይመ::

ነገር ያደርግልኛ ይሆናል::"
13ስለዚህም ዳዊትና ሰዎቹ መንገዳቸውን
ቀጠሉ፤ ሳሚም በአንጻሩ ባለው ኰረብታ
ጥግ ጥግ እየሄደ ይራገም፣ ድንጋይ ይወረ
ውርበትና ዐፈር ይበትንበት ነበር:: 14ንጉ
ሡና አብረውት የነበሩት ሰዎች ሁሉ ለመ
ሄድ ወዳሰቡበት ስፍራ ደረሱ፤ በጣም ደክ
ሞአቸው ስለ ነበር በዚያ ዐረፉ::

## የኩሲና የአኪጦፌል ምክር

15በዚህን ጊዜ አቤሴሎምና የእስራኤል ሰዎች
ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም መጡ፤ አኪጦፌልም
አብሮት ነበር:: 16የዳዊት ወዳጅ አርካዊው
ኩሲም ወደ አቤሴሎም መጥቶ "ንጉሥ ሆይ፤
ለዘላለም ንገሥ፤ ንጉሥ ሆይ፤ ለዘላለም ንገሥ"
አለው::
17አቤሴሎምም፣ ኩሲን፣ "ለወዳጅህ ያለህ
ታማኝነት እስከዚህ ድረስ ነው? ለምን ከወ
ዳጅህ ጋር አልሄድህም?" ሲል ጠየቀው::
18ኩሲም፣ አቤሴሎምን እንዲህ አለው፤
"ይህንንስ አላደርገውም! እኔ *በእግዚአብሔር*፣
በዚህ ሕዝብና በእስራኤል ሰዎች ሁሉ ለተ
መረጠው ለእርሱ እሆናለሁ፤ አብሬውም
እኖራለሁ፤ 19እንግዲህ ልጁን ካላገለገልሁ
ማንን ላገለግል ነው? አባትህን እንዳገለገልሁ
ሁሉ፤ አንተንም አገለግላለሁ::"
20አቤሴሎምም አኪጦፌልን፤ "እስቲ ምክር
አምጣ፤ ምን እናድርግ?" አለው::
21አኪጦፌልም መልሶ፣ "ቤተ መንግሥቱን
እንዲጠብቁ አባትህ ከተዋቸው ቁባቶቹ ጋር
ግባና ተኛ፤ ከዚያም አንተ፣ አባትህን እጅግ
የጠላህ መሆንህን መላው እስራኤል ይሰማና
አብሮህ ያለው ሁሉ ክንዱ ይበረታል" አለው::
22ስለዚህ ለአቤሴሎም በሰገነቱ ላይ ድንኳን
ተከሉለት፤ እዚያም መላው እስራኤል እያ
የው ከአባቱ ቁባቶች ጋር ተኛ::
23በዚያም ጊዜ አኪጦፌል የሚሰጠው ምክር
ሁሉ *የእግዚአብሔርን* ቃል እንደ መጠየቅ
ይቈጠር ነበር፤ ዳዊትም ሆነ አቤሴሎም የአ
ኪጦፌልን ምክር የሚቀበሉት በዚህ ሁኔታ
ነበር::

# 17

17 አኪጦፌልም፣ አቤሴሎምን እንዲህ
አለው፤ "ዐሥራ ሁለት ሺህ ሰው
መርጬ*፣ በዛሬዪቱ ሌሊት አባትህን አሳድ
ደዋለሁ፤ 2በደከመውና ዐቅም ባነሰው ጊዜም
አደጋ እጥልበታለሁ፤ ሽብር እለቅበታለሁ፤
ከዚያም አብሮት ያለው ሕዝብ ሁሉ ትቶት
ይሸሻል፤ ንጉሡን ብቻ እመታዋለሁ፣ 3ሕዝ
ቡን ሁሉ ወደ አንተ እመልሳለሁ፣ አንተ
የምትፈልገው የአንድ ሰው ብቻ መሞት
ሁሉም እንዲመለሱ ያደርጋል። ከዚያም ሕዝቡ
ሁሉ በሰላም ይኖራል::" 4ምክሩም አቤሴሎ
ምንና አብረውት የነበሩትን የእስራኤልን
ሽማግሌዎች ሁሉ ደስ አሰኘ::
5አቤሴሎም ግን፣ "እስቲ ደግሞ አርካዊ
ውን ኩሲን ጥሩትና የሚለውን እንስማ"
አለ:: 6ኩሲ ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ አቤሴ
ሎም፣ "አኪጦፌል ይህን ምክር አቅርቦአል፤
ታዲያ እርሱ ያለውን እናድርግ? ካልሆነም
እስቲ የአንተን ሐሳብ ንገረን" አለው::
7ኩሲም አቤሴሎምን እንዲህ አለው፤ "አኪ
ጦፌል የሰጠው ምክር በዚህ ጊዜ የሚያዋጣ
አይደለም፤ 8አባትህና ሰዎቹ የማይበገሩ ተዋ
ጊዎችና ግልገሎቿም እንደ ተነጠቁባት የዱር
ድብ አስፈሪ መሆናቸውን አንተም ታውቃ
ለህ፤ በተጨማሪም አባትህ በቂ ልምድ ያለው
ነው፤ ሌሊቱን ከሰራዊቱ ጋር አያድርም፤
9እነሆ፤ አሁን እንኳ በአንዱ ዋሻ ወይም
በሌላ ቦታ ተደብቆ ይሆናል። እርሱ ቀድሞ
አደጋ በመጣል ከሰዎችህ ጥቂት ቢሞቱ**
ይህን የሰማ ሁሉ፣ 'አቤሴሎምን የተከተለው
ሰራዊት አለቀ' ብሎ ያወራል:: 10አባትህ
ታላቅ ጦረኛ፣ አብረውት ያሉትም ጀግኖች
መሆናቸውን እስራኤል ሁሉ ስለሚያውቅ፣
ልቡ እንደ አንበሳ ልብ ነው የተባለው ደፋሩ
ወታደር እንኳ በፍርሀት ይርዳል::
11"እንግዲህ እኔ የምመክርህ ይህ ነው፤
ቍጥሩ እንደ ባሕር ዳር አሸዋ የበዛው፣
ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ያለው እስራኤል ሁሉ
ወዳንተ ይሰብሰብና አንተው ራስህ ወደ ጦር
ነቱ ምራው፤ 12ከዚያም እርሱ እገባበት ቦታ
ሁሉ ገብተን አደጋ እንጥልበታለን፣ ጤዛ
በመሬት ላይ እንደሚወርድ እንወርድበታ
ለን፤ እርሱም ሆነ ሰዎቹ አንድ እንኳ አይ
ተርፉም፤ 13ከአንዲቱ ከተማ ቢገባ፣ እስራ
ኤል ሁሉ ገመድ አምጥቶ አንድ ድንጋይ
እንኳ እስከማይቀር ድረስ፣ ከተማዪቱን ወደ
ሸለቆ ስበን እንከታታለን::"
14አቤሴሎምና የእስራኤል ሰዎች ሁሉ፣

*1 ወይም፣ *ልምረጥ*
**9 ወይም *በመጀመሪያው ጥቃት አንዳንድ ሰዎች ቢወድቁ*

16፥14 2ሳሙ 17፥2
16፥15 2ሳሙ 15፥12:37
16፥16 2ሳሙ 15፥32
16፥17 2ሳሙ 19፥25
16፥19 2ሳሙ 15፥34
16፥22 2ሳሙ 3፥7፤ 12፥11-12፤15፥16
16፥23 2ሳሙ 15፥12፤17፥14:23:23
17፥2 2ሳሙ 16፥14፤1ነገ22፥31፤ ዘካ13፥7
17፥5 2ሳሙ 15፥32
17፥8 1ሳሙ 16፥18፤ሆሴ13፥8
17፥9 ኤር41፥9
17፥10 ኢሱ2፥9: 11፤2ሳሙ23፥8፤1ዜና 11፥11፤12፥8፤ሕዝ 21፥15
17፥11 ዘፍ12፥2፤ ኢሱ11፥4፤መሳ20፥1
17፥13 ሚክ1፥6
17፥14 2ሳሙ 15፥12:34፤16፥23፤ 2ዜና10፥8፤ነህ4፥15፤ መዝ9፥16

16፥15 *አኪጦፌልም፤* የ15፥12 ማብ ይመ::
16፥16 *የዳዊት ወዳጅ አርካዊው ኩሲም፤* የ15፥32:37 ማብ ይመ::
16፥21 *አባትህ... ቁባቶቹ ጋር ተኛ፤* ይህም አቤሴሎም ንጉሣዊ ሥልጣንን በእጁ ያስገባ ለመሆኑ ምልክት ነው፤ በአባትና በልጅ መካከል የተከሠተ፣ ሊታደስ የማይችል፣ ግልጥ የሆነ የግንኙነት መቋረጥንም ያመለክታል (የ3፥7፤ 12፥18፤ የ1ነገ 2፥22 ማብ ይመ)::
16፥22 *ከአባቱ ቁባቶች ጋር ተኛ፤* ናታን የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ, (12፥11-12):: ለተጨማሪ ማብራሪያ የቍ 21 ማብ ይመ::
17፥1-3፤ አኪጦፌል ለአቤሴሎም ያቀረበው ምክር አገሪቱ በጦርነት ሳትደክም፣ በቀላሉ ድል የሚያገኝበትን መንገድ የሚጠቍም ነበር::
17፥4 *የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሁሉ፤* የ3፥17 ማብ ይመ:: የአቤሴሎም ዐመፅ ታዋቂ የሆኑ የነገድ አለቆችን ሰፊ ድጋፍ ያስገኘ ይመስላል::
17፥5 *አርካዊውን ኩሲን፤* 16፥16-19፤ እንዲሁም የ15፥32:37 ማብ ይመ::
17፥7-13፤ የኩሲ ምክር በዘዴ የተቀነባበረና በአቤሴሎም ደካማ ጐን፣ ማለትም ባለመደላደሉ፣ በፍራቻውና በራስ ወዳድነቱ ላይ የተነጣጠረ ነበር::
17፥12 *እንወርድበታለን፤* ኩሲ ራሱን በዐመፁ ተግባር ውስጥ በጥንቃቄ ሲያስገባ ይታያል::

“ከአኪጦፌል ምክር ይልቅ የአርካዊው የኩሲ
ምክር ይሻላል” አሉ፤ እግዚአብሔር በአቤ
ሴሎም ላይ ጥፋት ለማምጣት ሲል መል
ካም የነበረው የአኪጦፌል ምክር ተቀባይነት
እንዲያጣ አድርጎአልና::
15ኩሲም ካህናቱን ሳዶቅንና አብያታርን
እንዲህ አላቸው፤ “አኪጦፌል አቤሴሎምንና
የእስራኤልን ሽማግሌዎች ምን ምን ማድ
ረግ እንዳለባቸው መክሮአቸው ነበር፤ እኔ
ግን እንዲህ እንዲህ አድርጉ ብዬ መክሬ
አቸዋለሁ:: 16አሁንም በፍጥነት ላኩና፣ ‘በም
ድረ በዳው ባለው የወንዙ መሻገሪያ እንዳ
ታድር፤ ሳትዘገይ ፈጥነህ መሻገር አለብህ፤
ያለዚያ ግን ንጉሡና አብሮት ያለው ሕዝብ
በሙሉ ትዋጣላችሁ’ ብላችሁ ለዳዊት ንገሩት::”
17በዚህ ጊዜ ዮናታንና አኪማአስ ወደ ከተ
ማዪቱ ከገቡ ስለሚታዩ በዓይንሮጌል ይጠባ
በቁ ነበር፤ አንዲት ልጃገረድ አገልጋይ ወደ
ዚያ እየሄደች በምትነግራቸው ጊዜ፣ እነርሱ
ደግሞ ይህንኑ ወስደው ለንጉሥ ዳዊት ይነ
ግሩት ነበር:: 18ሆኖም አንድ ወጣት አያ
ቸውና ለአቤሴሎም ነገረው፤ ስለዚህ ሁለቱም
በፍጥነት ተነሥተው በብራቂም ወደሚገኝ
ወደ አንድ ሰው ቤት ሄዱ፤ ሰውየው በግቢው
ውስጥ ጕድጓድ ስለ ነበረው ወደዚያው
ወረዱ:: 19ሚስቱም በጕድጓዱ አፍ ላይ የስጥ
ማስጫ ዘርግታ እህል አሰጣች፤ ማንም ይህን
አላወቀም ነበር::
20የአቤሴሎም ሰዎች እዚያ ቤት ወደ ሴቲቱ
ዘንድ መጥተው፣ “አኪማአስና ዮናታን የት
አሉ?” ብለው ጠየቁ::
ሴቲቱም፣ “ወንዙን ተሻግረው ሄደዋል”[ሙ]
ብላ መለሰችላቸው፤ እነርሱም ፈልገው ስላ
ጧቸው፣ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ::
21ሰዎቹ ከሄዱ በኋላ እነዚህ ሁለቱ ከጕ
ድጓዱ ወጥተው ሄዱ፤ ለንጉሥ ዳዊትም፣
“አኪጦፌል በአንተ ላይ እንዲህ እንዲህ ብሎ
ስለ መከረብህ ተነሥተህ በፍጥነት ወንዙን
ተሻገር” አሉት:: 22ስለዚህ ዳዊትና አብሮት
ያለው ሕዝብ በሙሉ ተነሥቶ ዮርዳኖስን
ተሻገረ፤ ሲነጋም ዮርዳኖስን ሳይሻገር የቀረ
አንድም ሰው አልነበረም::
23አኪጦፌልም ምክሩን እንዳልተከተሉት
ባየ ጊዜ፣ አህያውን ጭኖ ቤቱ ወደሚገኝ
በት ወደ መኖሪያ ከተማው ሄደ፤ ቤቱንም
መልክ መልክ ካስያዘ በኋላ በገዛ እጁ ታንቆ
ሞተ:: በዚህ ሁኔታም ሞቶ በአባቱ መቃ
ብር ተቀበረ::
24አቤሴሎም ከመላው የእስራኤል ሰዎች
ጋር ዮርዳኖስን ሲሻገር፣ ዳዊት ግን መሃና
ይም ደርሶ ነበር:: 25አቤሴሎምም በኢዮአብ
ምትክ አሜሳይን በሰራዊቱ ላይ ሾመ፤ አሜ
ሳይ የእስማኤላዊው[ሬ] የዮቴር ልጅ ነበረ፤ ዮቴ
ርም የኢዮአብን እናት፣ የጽሩያን እኅት፣ የና
ያስን ልጅ አቢግያን[ሰ] አግብቶ ነበር:: 26እስራ
ኤላውያንና አቤሴሎም በገለዓድ ምድር ሰፈሩ::
27ዳዊት መሃናይም ሲደርስ፣ ከአሞናው
ያን ከተማ ከራባ የመጣው፣ የናያስ ልጅ
ሾቢ፣ ከሎዶባር የመጣው የዓሚኤል ልጅ
ማኪርና ከሮግሊም የመጣው ገለዓዳዊው ቤር
ዜሊ 28መተኛ ምንጣፎች፣ ወጭቶችና የሸ
ክላ ዕቃዎች ይዘው መጡ፤ እንዲሁም ስን
ዴና ገብስ፣ዱቄትና የተጠበሰ እሸት፣ ባቄ
ላና ምስር[ሸ]፣ 29ማር፣ እርጎ፣ በጎችና የላም
አይብ እንዲበሉ ለዳዊትና ለሕዝቡ አመጡ
ላቸው፤ ይህን ያደረጉትም፣ “ሕዝቡ በም
ድረ በዳ ተርቦአል፤ ደክሞአል፤ ተጠምቶአል”
በማለት ነው::

### የአቤሴሎም መሞት

18 ዳዊት አብሮት የነበረውን ሕዝብ
ቈጠረ፤ የሻለቆችንና የመቶ አለቆ
ችን ሾመላቸው:: 2ዳዊትም ሰራዊቱን ሲሦ
ውን በኢዮአብ፣ ሲሦውን በኢዮአብ ወን
ድም በጽሩያ ልጅ በአቢሳ፣ ሲሦውን ደግሞ
በጌታዊው በኢታይ አዛዥነት ሥር ላካቸው::
ንጉሡም ለሰራዊቱ፣ “እኔ ራሴም አብሬአ
ችሁ በእርግጥ እወጣለሁ” አላቸው::

[ሙ]20 ወይም፣ በበጎች ጒረኖ አድርገው ወደ ውሃው ተሻገሩ
[ሬ]25 ዕብራይስጡና አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች፣ እስራ
ኤላዊ ይላሉ፤ አብዛኞቹ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ግን፣ እስ
ማኤላዊ ወይም ይዝራኤላዊ ይላሉ (1ዜና 2፥17 ይመ)::
[ሰ]25 በዕብራይስጥ፣ አቢግያ ማለትና፣ አቢጋኤል ማለት አንድ
ነው::

17፥16 2ሳሙ 15፥28:35
17፥17 ኢሱ15፥7፤ 18፥16፤2ሳሙ 15፥27:36፤1ነገ1፥9
17፥18 2ሳሙ3፥16
17፥19 ኢሱ2፥6
17፥20 ዘፀ1፥19
17፥23 2ሳሙ 16፥23፤2ነገ20፥1
17፥24 ዘፍ32፥2
17፥25 2ሳሙ 19፥13፤20፥4:9-12፤ 1ነገ2፥5:32፤1ዜና 2፥13-17፤12፥18
17፥27 ዘዳ3፥11፤ 1ሳሙ11፥1፤2ሳሙ 9፥4፤19፥31-39፤ 1ነገ2፥7፤ዕዝ2፥61
17፥29 2ሳሙ 16፥2፤1ዜና12፥40፤ ሮሜ12፥13
18፥2 መሳ7፥16፤ 1ሳሙ11፥11፤26፥6፤ 2ሳሙ15፥19

17፥14 *እግዚአብሔር... መልካም የነበረው የአኪጦፌል ምክር ተቀባይነት እንዲያጣ አድርጎአልና፤* ዳዊት ላቀረበው ጸሎት መልስ ነው (15፥31 ይመ፤ ከመዝ 33፥10፤ ከምሳ 21፥30 ጋር ያነጻጽሩ)::

17፥15 *ሳዶቅንና አብያታርን፤* 15፥24-29:35-36 ይ መ::

17፥16 *በምድረ በዳው... መሻገሪያ፤* 15፥28 እና ማብ ይመ:: *መሻገር፤* አቤሴሎም ሐሳቡን ሊለውጥና ወዲያውኑ ዳዊትን ሊያሳድደው እንደሚችል በማወቅ፣ በፍጥነት የዮርዳኖስን ወንዝ እንዲሻገር ኩሲ ለዳዊት ምክር ያቀርባል::

17፥17 *ዮናታንና አኪማአስ፤* 15፥36 ይመ:: *በዓይንሮጌል፤* ከኢየሩሳሌም ወጣ ብሎ በቄድሮን ሸለቆ የምትገኝ ምንጭ ናት:: *አንዲት ልጃገረድ አገልጋይ፤* ውሃ ለመቅዳት ወደ ምንጭ የምትሄድ አገልጋይ ትኵረት አትስብም::

17፥18 *ብራቂም፤* የ16፥5 ማብ ይመ::

17፥23 *ወደ መኖሪያ ከተማው ሄደ፤* ጊሎን የሚመለከት ነው (የ15፥12 ማብ ይመ):: *በገዛ እጁ ታንቆ ሞተ፤* ዐመፁ እንደሚከሽፍና ተባባሪ ወንጀለኛነቱ እንደሚደረስበት አኪጦፌል አመነ::

17፥24 *መሃናይም፤* ሳኦል ከሞተ በኋላ ኢያቡስቴ ጥገኝነት እንዲሰጠው የጠየቀበት ስፍራ ነው (2፥8)::

17፥25 *አሜሳይ፤* የዳዊት የእኅቱ ልጅ እንደዚሁም የአቤሴሎምና የጽሩያ ልጅ የኢዮአብ አጎት ልጅ ነው:: *የጽሩያን እኅት የናያስን ልጅ አቢግያን፤* ጽሩያ የዳዊት እኅት ናት (1ዜና 2፥16)፤ የአቢግያና የጽሩያ አባት እሴይ ሳይሆን ናያስ በመሆኑ፣ ስሟ ያልተጠቀሰው እናታቸው ናያስ ከሞተ በኋላ እሴይን ያገባች ይመስላል::

17፥27 *የናያስ ልጅ ሾቢ፤* ዳዊት በመጀመሪያዎቹ የአገዛዝ ዓመታት ያሸነፈው (12፥26-31) የሐኖንን ወንድም ነው (10፥2-4 ይመ):: *ከአሞናውያን ከተማ ከራባ፤* የ10፥3 ማብ ይመ:: *ማኪር፤* የ9፥4 ማብ ይመ:: *ቤርዜሊ፤* ዳዊት ወደ መሃናይም በሸሸ ጊዜ ርዳታ አድርጎለት የነበረ ሀብታም ሰው ነው (19፥32፤ 1ነገ 2፥7 ይመ):: ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ሥልጣነ ክህነት አለን በማለት የተነሡት ከቤርዜሊ ልጆች መካከል ነበር (ዕዝ 2፥61-63፤ ነህ 7፥63)::

18፥2 *በጌታዊው በኢታይ፤* 15፥18-22 ይመ::

3ሰዎቹ ግን፣ “አንተ መውጣት የለብህም፤
እንድንሸሽ ብንገደድ፣ ሰዎቹ ከቁም ነገር
አይቈጥሩንም፤ ግማሾቻችን እንኳ ብንሞት
ደንታቸው አይደለም፣ አንተ ግን ብቻህን
ከእኛ ከዐሥሩ ሺህ ትበልጣለህ[+]፤ ስለዚህ
በከተማ ሆነህ ብትረዳን ይሻላል” አሉት።
4ንጉሡም፣ “መልካም መስሎ የታያችሁን
ሁሉ አደርጋለሁ” አላቸው። ስለዚህ ሕዝቡ
ሁሉ በመቶና በሺህ እየሆነ ተሰልፎ ሲወጣ፣
ንጉሡ በቅጥሩ በር ቆሞ ነበር። 5ንጉሡም
ኢዮአብን፣ አቢሳንና ኢታይን፣ “ለእኔ ስትሉ
በወጣቱ ልጅ በአቤሴሎም ላይ ጕዳት እንዳ
ታደርሱበት” ብሎ አዘዛቸው። ንጉሡ ልጁን
አቤሴሎምን አስመልክቶ ለእያንዳንዱ አዛዥ
ትእዛዝ ሲሰጥ ሰራዊቱ ሁሉ ሰማ።
6ሰራዊቱ እስራኤልን ለመውጋት ተሰልፎ
ወደ ሜዳ ወጣ፤ ጦርነቱም በኤፍሬም ደን
ውስጥ ሆነ። 7እዚያም የእስራኤል ሰራዊት
በዳዊት ሰዎች ተመታ፤ በዚያም ቀን ታላቅ
እልቂት ሆነ፤ ሃያ ሺህም ሰው ተገደለ።
8ውጊያው በገጠሩ ሁሉ ተስፋፋ፤ በዚያን
ቀን ሰይፍ ከጨረሰው ይልቅ ጫካ ውጦ ያስ
ቀረው ሰው በለጠ።
9በዚህ ጊዜ አቤሴሎም ከዳዊት ሰዎች ጋር
ድንገት ተገናኘ፤ አቤሴሎም በበቅሎ ተቀ
ምጦ ይሄድ ስለ ነበር፣ በቅሎዋ ጥቅጥቅ ያለ
ቅርንጫፍ ባለው ትልቅ ወርካ ሥር በም
ታልፍበት ጊዜ፣ የአቤሴሎም ራስ በዛፉ
ቅርንጫፍ ተያዘ፤ የተቀመጠበትም በቅሎ
በሥሩ ስታልፍ፣ እርሱ በሰማይና በምድር
መካከል ተንጠልጥሎ ቀረ።
10አንድ ሰው ይህን አይቶ ለኢዮአብ፣
“እነሆ፤ አቤሴሎም በባሉጥ ዛፍ ላይ ተንጠ
ልጥሎ አየሁት” አለው።
11ኢዮአብም ይህን የነገረውን ሰው፣ “ምን
አልህ! ካየኸው ታዲያ ለምንድን ነው ያኔውኑ
መትህ መሬት ላይ ያልጣልኸው? ይህን አድ
ርገህ ቢሆን ኖሮ፣ ዐሥር ሰቅል[ሀ] ጥሬ ብርና
የጀግና ሰው ቀበቶም እሸልምህ ነበር” አለው።

12ሰውየው ግን እንዲህ አለ፤ “እኛ እየሰማን
ንጉሡ፣ ‘ወጣቱ አቤሴሎም ጕዳት እንዳያገ
ኘው ስለ እኔ ብላችሁ ጠብቁት’[+] ብሎ
አንተን፣ አቢሳንና ኢታይን ያዘዛችሁ ስለ
ሆነ፣ አንድ ሺህ ሰቅል[*] ጥሬ ብር በእጄ
ላይ ቢመዘንልኝ እንኳ፣ በንጉሡ ልጅ ላይ
እጄን አላነሣም። 13በሌላ በኩል ደግሞ
በነፍሴ ቈርጬ ሕይወቱን ባጠፋው ኖሮ[ነ]፣
ከንጉሡ ተደብቆ የሚቀር ነገር ስለ ሌለ፣
አንተም ራስህ አትቀርበኝም ነበር” ብሎ
መለሰለት።
14ኢዮአብም፣ “ከእንግዲህ በዚህ ሁኔታ
ከአንተ ጋር ጊዜ ማጥፋት አልችልም” አለው፤
ስለዚህ በእጁ ሦስት ጦር ይዞ ሄደና አቤ
ሴሎም እዛፉ ላይ ተንጠልጥሎ ገና በሕይ
ወት እያለ፣ ወርውሮ በልቡ ላይ ተከላቸው።
15እንዲሁም ከኢዮአብ ጋሻ ጃግሬዎች ዐሥሩ
አቤሴሎምን በመከበብ ወግተው ገደሉት።
16ከዚያም ኢዮአብ ቀንደ መለከት ነፍቶ
ስለ ከለከላቸው፣ ሰራዊቱ እስራኤልን ማሳ
ደዱን አቆመ። 17አቤሴሎምን ጫካ ወስ
ደው በትልቅ ጕድጓድ ውስጥ ወርውረው
ጣሉት፤ በላዩም ትልልቅ ድንጋይ ከመሩ
በት። በዚህ ጊዜ እስራኤላውያን ሁሉ ወደ
የቤታቸው ሸሹ።
18አቤሴሎም፣ “ስሜን የሚያስጠራ ልጅ
የለኝም” በማለት መታሰቢያ እንዲሆነው በሕ
ይወት እያለ የንጉሥ ሸለቆ በተባለው ስፍራ
በራሱ ስም ሐውልት አቆሞ ስለ ነበር፣ እስከ
ዛሬ ድረስ የአቤሴሎም ሐውልት ተብሎ
ይጠራል።

18፥3 1ሳሙ 18፥7፤ 2ሳሙ 21፥17
18፥6 ኢሱ 17፥15
18፥9 2ሳሙ 14፥26
18፥11 1ሳሙ 18፥4፤2ሳሙ 3፥39
18፥13 2ሳሙ 14፥19-20
18፥14 2ሳሙ 2፥18
18፥15 2ሳሙ 12፥10
18፥16 2ሳሙ 2፥28
18፥17 ኢሱ 7፥26፤ 8፥29
18፥18 ዘፍ 14፥17፤ 50፥5፤ዘኍ 32፥42፤ 2ሳሙ 14፥27

ሀ28 አብዛኞቹ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞችና የሱርስቱ ቅጅ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *ምስርና የተቈላ ባቄላ* ይላል።
+3 ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆች፣ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች እንዲሁም ቩልጌት ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ትርጕሞች ግን፣ *አሁን እንደኛ የሆኑ ዐሥር ሺህ አሉ* ይላል።
ሀ11 115 ግራም ያህል ነው።
+12 አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት፣ የቩልጌትና የሱርስት ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አብዛኞቹን የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *አቤሴሎም ምንም ዐይነት ሰው ብትሆን* ይላሉ።
*12 11 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
ነ13 ወይም፣ *ወይም እርሱን ባታልለው ኖሮ*

18፥3 *አንተ መውጣት የለብህም፤* ከቀረበው ምክንያት በተጨማሪ፣ ዳዊት በጣም እየሸመገለ በመሄዱ እንደ ቀድሞው ጦር መርቶ የመዋጋት ዐቅም አልነበረውም (የ15፥7 ማብ ይመ)። ይህ ሐሳብ አኪጦፌል ለአቤሴሎም ካቀረበው የምክር ሐሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው (17፥2 ይመ)።

18፥5 *ለእኔ ስትሉ... በአቤሴሎም ላይ ጕዳት እንዳታደርሱበት፤* ዳዊት ለአንጋፋ ልጁ ለአቤሴሎም የነበረው ፍቅር እጅግ ከፍተኛና ከልቡ ሊጠፋ የማይችል ነበር (19፥5-7)።

18፥6 *እስራኤልን፤* የአቤሴሎም ጦር ሰራዊት ነው (15፥13፤ 16፥15፤ 17፥4:11:24-26 ይመ)። *በኤፍሬም ደን፤* ውጊያው የተካሄደው በምሥራቅ ዮርዳኖስ በገለዓድ ምድር ነበር (17፥24:26)። ይህ ቦታ ለምን “የኤፍሬም ደን” እንደ ተባለ ግልጽ አይደለም (ምናልባት የኤፍሬም ዘሮች በቦታው ላይ ያላቸውን የባለቤትነት መብት ከማንሣት አኳያ የተሰጠ ስያሜ ሊሆን ይችላል፤ መሳ 12፥1-4 ይመ)።

18፥8 *ውጊያው... ተስፋፋ፤* ሰራዊቱ እጅግ ተበታተነ፤ ብዙዎቹም በጫካው ውስጥ ጠፍተው ቀሩ።

18፥9 *በበቅሎዋ፤* የ13፥29 ማብ ይመ። *የአቤሴሎም ራስ በዛፉ ቅርንጫፍ ተያዘ፤* ይህ የሆነው የተዘናፈለው ጠጕሩ በዛፍ ቅርንጫፍ ተይዞ ይሁን (14፥26) ወይም በሌላ ምክንያት የሚታወቅ ነገር የለም፤ ነገር ግን በዚህም ሆነ በዚያ ግርማ ሞገስ ሰጥቶት የነበረው ጠጕሩ (14፥25 ይመ)፣ በመጨረሻ መጥፊያው ሆነ።

18፥11 *እሸልምህ ነበር፤* ኢዮአብ አቤሴሎምን ለሚገድል ለማንኛውም ሰው ሽልማት እሰጣለሁ ማለቱ፣ የራሱ የሆነ አንድ የታወቀ ፍላጎት እንዳለው ሳያመለክት አይቀርም። የኢዮአብ ተግባርና ፍላጎት ከዳዊት ፈቃድ ጋር ብዙ ጊዜ አይጣጣምም ነበር (የ2፥13 ማብ ይመ)።

18፥15 *ገደሉት፤* ዐመፅን ፈጽሞ ማስወገድ የሚችል እጅግ ቀላሉና አስተማማኙ ርምጃ ነው። ይሁን እንጂ ይህ አረመኔያዊ አገዳደል በዳዊት ሰራዊትና በአቤሴሎም መካከል ሥር የሰደደ ጠላትነት እንደ ነበረ ያመለክታል።

18፥17 *ትልልቅ ድንጋይ ከመሩበት፤* ይህ በአቤሴሎም መቃብር ላይ የተቈለለው ድንጋይ፣ አቤሴሎም በሕይወት እያለ በስሙ አቁሞት የነበረውን ሐውልት (ቍ 18) መሣለቂያ አደረገው። *እስራኤላውያን ሁሉ፤* የቍ 6 ማብ ይመ።

18፥18 *ልጅ የለኝም፤* 14፥27 እና ማብ ይመ። *የንጉሥ ሸለቆ፤* በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ይገኛል (ዘፍ 14፥17 ይመ)። *በራሱ ስም ሐውልት አቁሞ፤* ሳኦልም እንደዚሁ አድርጎ ነበር (1ሳሙ 15፥12)። *የአቤሴሎም ሐውልት፤* ይህ ሐውልት

## የዳዊት ሐዘን

19በዚህ ጊዜ የሳዶቅ ልጅ አኪማአስ፣ “እግ
ዚአብሔር ጠላቶቹን የተበቀለለት መሆኑን
ሮጬ ሄጄ ለንጉሡ የምሥራች ልንገረው”
አለ::
20ኢዮአብም፣ “ዛሬ የምሥራቹን ወሬ የም
ትወስድለት አንተ አይደለህም፤ የንጉሡ ልጅ
ስለ ሞተ፣ ዛሬ ሳይሆን፣ የምሥራቹን ሌላ
ጊዜ ታደርስለታለህ” አለው::
21ከዚያም ኢዮአብ ለኢትዮጵያዊው፣ “ሂድና
ያየኸውን ለንጉሡ ንገር” አለው፤ ኢትዮጵ
ያዊውም ኢዮአብን እጅ ነሥቶ እየሮጠ
ሄደ::
22የሳዶቅ ልጅ አኪማአስም እንደ ገና ኢዮ
አብን፣ “የመጣው ይምጣ፤ እባክህ ኢትዮ
ጵያዊውን ተከትየው ልሩጥ” አለው::
ኢዮአብ ግን፣ “ልጄ ሆይ፣ መሄድ ለምን
አስፈለገህ? ሽልማት የሚያስጥህ ምን የም
ሥራች ይዘህ ነው?” ብሎ መለሰለት::
23አኪማአስም፣ “የመጣው ይምጣ፤ መሄድ
እፈልጋለሁ” አለ::
ስለዚህም ኢዮአብ፣ “እንግዲያውማ ሩጥ!”
አለው:: ከዚያም አኪማአስ በሜዳው መን
ገድ' ሮጦ ኢትዮጵያዊውን ቀድሞት ሄደ::
24ዳዊት በውስጠኛውና በውጭኛው በሮች
መካከል ተቀምጦ ሳለ፣ ጠባቂው ቅጥሩ
ላይ ወዳለው ወደ በሩ ሰገነት ጣራ ወጥቶ
ወደ ውጭ ሲመለከት አንድ ሰው ብቻውን
ሲሮጥ አየ:: 25ጠባቂውም ተጣራና ይህንኑ
ለንጉሡ ነገረው፤
ንጉሡም፣ “ብቻውን ከሆነ መልካም ወሬ
ይዞ የመጣ መሆን አለበት” አለ:: ሰውየ
ውም እየቀረበ መጣ::
26ከዚያም ጠባቂው ሌላ ሰው ሲሮጥ አይቶ፣
ዘበኛውን ተጣራና፣ “እነሆ ሌላም ሰው ብቻ
ውን እየሮጠ በመምጣት ላይ ነው!” አለ::
ንጉሡም፣ “ይኸኛውም መልካም ወሬ ይዞ
የመጣ መሆን አለበት” አለ::
27ጠባቂውም፣ “የመጀመሪያው ሰው ሩጫ
የሳዶቅን ልጅ የአኪማአስን ሩጫ ይመስለ
ኛል” አለ::
ንጉሡም፣ “እርሱማ ጥሩ ሰው ነው፤ የም
ሥራች ሳይዝ አይመጣም” አለ::
28አኪማአስም ጮኾ ንጉሡን፣ “ሁሉም ነገር
ተሳክቶአል” አለ፤ ከዚያም ወደ መሬት ለጥ
ብሎ በንጉሡ ፊት እጅ ነሣና፣ “በጌታዬ
በንጉሡ ላይ እጃቸውን ያነሡትን ሰዎች አሳ
ልፎ የሰጠ ስሙ የተባረከ እግዚአብሔር የተመሰገነ
ይሁን!” አለ::
29ንጉሡም፣ “ብላቴናው አቤሴሎም ደኅና
ነውን?” ሲል ጠየቀ::
አኪማአስም፣ “ኢዮአብ የንጉሡን አገል
ጋይና እኔንም ባሪያህን ሊልክ ሲል፣ ትልቅ
ሁካታ አይቻለሁ፤ ምን እንደ ሆነ ግን አላ
ወቅሁም” ብሎ መለሰ::
30ንጉሡም፣ “እልፍ በልና ቁም” አለው፤
ስለዚህ እልፍ ብሎ ቆመ::
31ከዚያም ኢትዮጵያዊው ደርሶ፣ “ንጉሥ
ጌታዬ ሆይ፤ የምሥራች! ዛሬ እግዚአብሔር
ከተነሡብህ ጠላቶችህ ሁሉ ታድጎሃል” አለው::
32ንጉሡም ኢትዮጵያዊውን፣ “ብላቴናው
አቤሴሎም ደኅና ነውን?” ሲል ጠየቀው::
ኢትዮጵያዊውም፣ “የጌታዬ የንጉሡ ጠላ
ቶችና ሊጐዱህ የሚነሡብህ ሁሉ እንደዚያ
ወጣት ይሁኑ” ሲል መለሰ::
33ንጉሡም እጅግ አዘነ፤ በቅጽር በሩ ዐናት
ላይ ወዳለችው ቤት ወጥቶ አለቀሰ፤ ሲሄ
ድም፣ “ልጄ አቤሴሎም ሆይ! ልጄ አቤሴ
ሎም! በአንተ ፈንታ ምነው እኔ በሞትሁ
ኖሮ! አቤሴሎም ሆይ፣ ልጄን፣ ወየው ልጄን!”
ይል ነበር::

19 ለኢዮአብ፣ “ንጉሡ ዳዊት ስለ ልጁ
ስለ አቤሴሎም እያለቀሰ እያዘነ ነው”
ተብሎ ተነገረው:: 2ንጉሡ፣ “ስለ ልጁ አዝ
ኖአል” መባሉን በዚያ ቀን ሰራዊቱ ሰምቶ
ስለ ነበር፣ የዚያ ዕለት ድል በመላው ሰራ
ዊት ዘንድ ወደ ሐዘን ተለውጦ ዋለ:: 3በዚ
ያችም ዕለት ከጦርነት ሸሽቶ በኀፍረት
እየተሸማቀቀ ወደ ከተማ እንደሚገባ ሰው ሕዝ
ቡም ተሸማቆ ወደ ከተማ ገባ:: 4ንጉሡ
ፊቱን ሸፍኖ፣ “ልጄ አቤሴሎም ሆይ፤
ልጄን! ወየው ልጄን!” እያለ ጮኸ::
5ከዚያም ኢዮአብ ወደ ንጉሡ ቤት ገብቶ
እንዲህ አለው፤ “የአንተን፣ የወንዶችንና የሴ
ቶች ልጆችህን፣ የሚስቶችህንና የቁባቶችህን
ሕይወት ያተረፉትን ሰዎች ሁሉ ዛሬ አሳፍ
ረሃቸዋል:: 6የሚጠሉህን ትወዳለህ፤ የሚወዱህን

'23 ይህ የዮርዳኖስ ሜዳማ ስፍራ ነው::

18፥19 መሳ11፥36፤ 2ሳሙ15፥36
18፥24 1ሳሙ14፥16፤ኢር51፥12
18፥26 1ነገ1፥42፤ ኢሳ52፥7፤61፥1
18፥27 2ነገ9፥20
18፥32 መሳ5፥31፤ 1ሳሙ25፥26
18፥33 ዘፍ43፥14፤ ዘፀ32፥32፤2ሳሙ19፥4

ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ባለው ሸለቆ ውስጥ ከሚታየው፣ በተመሳሳይ ስም ከሚጠራው ሐውልት ጋር አንድ ተደርጎ መቈጠር የለበትም::

18፥19 *የሳዶቅ ልጅ አኪማአስ፤* 15፥27፤ 17፥17-21 ይመ::

18፥20 *የምሥራቹን ወሬ የምትወስድለት... አይደለህም፤* መልእክተኛ የሚመረጠው እንደ መልእክቱ ክብደትና ቅለት እየታየ ነበር (ቍ 27 እና ማብ ይመ)::

18፥21 *ለኢትዮጵያዊው፤* መጻተኛ ነው የዘፍ 10፥6-8፤ አሞ 9፥7 ማብ ይመ::

18፥27 *የምሥራች ሳይዝ አይመጣም፤* አኪማአስን ያህል ታላቅ ሰው፣ ኢዮአብ መርዶ ነጋሪ አድርጎ ይልካል ብሎ ዳዊት አላሰበም ነበር (ቍ 20 እና ማብ ይመ)::

18፥29 *ትልቅ ሁካታ አይቻለሁ፤* አኪማአስ፣ አቤሴሎም እንደ ሞተ ቢያውቅም እንኳ፣ ዳዊት ላቀረበለት ጥያቄ ቀጥተኛ መልስ ሲሰጥ አይታይም::

18፥33 *ልጄ አቤሴሎም ሆይ፤* ምንም እንኳ አቤሴሎም በአባቱ በዳዊት ላይ ብዙ በደል ቢያደርስበትም እንኳ፣ አባት ለልጁ ያለውን ኀይለኛ ፍቅር ልብን በሚነካ አገላለጥ ከሚያቀርቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ይህ አንደኛው ነው::

19፥5 *ኢዮአብ ወደ ንጉሡ ቤት ገባ፤* በአቤሴሎም አሟሟት ኢዮአብ እጁን ያስገባ መሆኑን፣ ንጉሥ ዳዊት ያላወቀ መስሎት ነበር:: ዳዊት ጉዳዩን የሚያውቅ ስለ መሆኑ ፍንጭ አያሳይም (1ነገ 2፥5 ይመ):: *ሰዎች ሁሉ... አሳፍረሃቸዋል፤* ዙፋኑን ለመጠበቅ ሲሉ ሕይወታቸውን ሳይቀር መሥዋዕት ሳደረጉት ሰዎች ያለውን አድ ናቆት መግለጥ እስኪሳነው ድረስ ዳዊት በልጁ ሐዘን እጅግ

ትጠላለህ፤ የጦር አዛዦችህና ወታደሮቻቸው
ለአንተ ምንህም እንዳይደሉ ይኸው ዛሬ ግልጽ
አድርገሃል፤ ዛሬ አቤሴሎም በሕይወት ኖሮ
እኛ ሁላችን አልቀን ቢሆን ደስ እንደሚ
ልህ በዛሬው ዕለት ለማየት በቅቻለሁ። [7]በል
አሁን ተነሥተህ ውጣና ሰዎችህን አበረታታ፤
ባትወጣ ግን በዚች ሌሊት አንድም ሰው
አብሮህ እንደማይሆን *በእግዚአብሔር* እም
ላለሁ፤ ይህ ደግሞ ከልጅነትህ ጀምሮ እስ
ካሁን ድረስ ከደረሰብህ ክፉ ነገር ሁሉ የባሰ
መከራ ያስከትልብሃል።" [8]ስለዚህ ንጉሡ ተነ
ሥቶ በበሩ አጠገብ ተቀመጠ፤ ለሕዝቡም፣
"እነሆ ንጉሡ በበሩ አጠገብ ተቀምጦአል"
ተብሎ በተነገረ ጊዜ ሕዝቡ በሙሉ ወደ
ንጉሡ መጣ።

### ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ

በዚያን ጊዜ እስራኤላውያን በሙሉ ወደ
የቤታቸው ሸሽተው ነበር።
[9]በመላው የእስራኤል ነገዶችም፣ ሕዝቡ
እንዲህ እያለ እርስ በርሱ ይከራከር ነበር፤
"ንጉሡ ከጠላቶቻችን እጅ አውጥቶናል፤ ከፍ
ልስጥኤማውያንም እጅ የታደገን እርሱ ነው፤
አሁን ግን በአቤሴሎም ምክንያት ከአገር
ሸሽቶ ሄዶአል፤ [10]በላያችን ሆኖ እንዲገዛን
የቀባነው አቤሴሎም ደግሞ በጦርነት ሞቶ
አል፤ ታዲያ ንጉሡን የመመለሱን ጉዳይ ለም
ንድን ነው ዝም የምትሉት?"
[11]ንጉሥ ዳዊት ወደ ካህናቱ ወደ ሳዶቅና
ወደ አብያታር እንዲህ ሲል መልእክት ላከ፤
"የእስራኤል ሽማግሌዎችን እንዲህ በሏቸው
አለ፤ 'በመላው እስራኤል የሚባለው ሁሉ
ለንጉሡ ባለበት የደረሰው ስለሆነ፣ ንጉሡን
ወደ ቤተ መንግሥቱ ለመመለስ እንዴት
የመጨረሻ ሰዎች ትሆናላችሁ? [12]እናንተ
የዐጥንቴ ፍላጭ፣ የሥጋዬ ቊራጭ ወንድ
ሞቼ ናችሁ፤ ታዲያ ንጉሡን ለመመለስ
እንዴት የመጨረሻ ሰዎች ትሆናላችሁ?'
[13]አሜሳይንም፣ 'አንተስ የዐጥንቴ ፍላጭ፣
የሥጋዬ ቊራጭ አይደለህምን? ከአሁን ጀምሮ
እስከ ሕይወትህ ፍጻሜ በኢዮአብ ምትክ
የሰራዊቴ አዛዥ ባላደርግህ፣ *እግዚአብሔር*
ክፉ ያድርግብኝ፣ ከዚህ የባሰም ያምጣብኝ'
ብላችሁ ንገሩት።"
[14]እርሱም የይሁዳን ሰዎች ልብ ሁሉ እንደ
አንድ ሰው ልብ አድርጎ ማረከው፤ እነር
ሱም "አንተም ሰዎችህም ሁሉ ተመለሱ"
ብለው ላኩበት። [15]ከዚያም ንጉሡ ተመልሶ
እስከ ዮርዳኖስ ድረስ መጣ።
በዚህ ጊዜ የይሁዳ ሰዎች ንጉሡን ተቀ
ብለው ዮርዳኖስን ለማሻገር እስከ ጌልገላ
ድረስ መጥተው ነበር። [16]የብራቂም ሰው
የሆነው የጌራ ልጅ ብንያማዊው ሳሚ ከይ
ሁዳ ሰዎች ጋር ሆኖ ንጉሥ ዳዊትን ለመ
ቀበል ፈጥኖ ወረደ። [17]ከእርሱም ጋር አንድ
ሺህ ብንያማውያን፣ እንዲሁም የሳኦል ቤተ
ሰብ አገልጋይ ሲባ ከዐሥራ አምስት ወን
ዶች ልጆቹና ከሃያ አሽከሮቹ ጋር ሆኖ
አብረውት ነበሩ። ከዚያም ንጉሡ ወዳለበት
ወደ ዮርዳኖስ በጥድፊያ ወረዱ። [18]የንጉ
ሡን ቤተ ሰው ለማምጣትና እርሱ የሚፈ
ልገውንም ሁሉ ለማድረግ በመልካው ተሻ
ገሩ።
የጌራ ልጅ ሳሚ ዮርዳኖስን ተሻገረ፤ በን
ጉሡም ፊት ተደፍቶ፣ [19]እንዲህ አለ፤
"ጌታዬ በደሌን አይቍጠርብኝ፤ ንጉሥ
ጌታዬ ከኢየሩሳሌም በወጣህባት ዕለት የፈ
ጸምሁትን ስሕተት እርሳው፤ ከአእምሮህም
አውጣው። [20]እኔ አገልጋይህ ኀጢአት መሥ
ራቴን አውቃለሁና፤ ዛሬ ግን ጌታዬን ንጉ
ሡን ለመቀበል ከዮሴፍ ቤት ሁሉ የመ
ጀመሪያ ሆኜ እነሆ መጥቻለሁ።"
[21]ከዚያም የጽሩያ ልጅ አቢሳ፣ "ሳሚ *በእ
ግዚአብሔር* የተቀባውን የረገመ ስለ ሆነ፣
መሞት አይገባውምን?" አለ።
[22]ዳዊትም፣ "እናንት የጽሩያ ልጆች፣ እና
ንተንና እኔን ምን የሚያገናኘን ነገር አለ?
ዛሬ ጠላት ሆናችሁኛል! ማንስ ቢሆን ዛሬ
በእስራኤል ዘንድ ሰው መሞት አለበት? እኔ
በእስራኤል ላይ ንጉሥ መሆኔን ያወቅሁበት

19፥7 ምሳ14፥28
19፥8 2ሳሙ15፥2
19፥9 2ሳሙ8፥1-14፤15፥14
19፥11 2ሳሙ15፥24
19፥13 ዘፍ29፥14፤ ሩት1፥17፤ 2ሳሙ2፥13፤17፥25
19፥15 1ሳሙ11፥15
19፥16 2ሳሙ16፥5-13
19፥17 ዘፍ43፥16፤ 2ሳሙ9፥2
19፥19 2ሳሙ16፥6-8
19፥21 ዘፀ22፥28፤ 1ሳሙ12፥3፤26፥6፡9
19፥22 1ሳሙ11፥13፤2ሳሙ2፥18፤16፥10

በመነካቱ ኢዮአብ በድፍረት ሲወቅሰው ይታያል። ዳዊት ለአቤ
ሴሎም ያለው ፍቅር አሁንም ጉዳት ላይ ሊጥለው እንደሚችል
ኢዮ አብ ያስጠነቅቀዋል።

19፥9 *ንጉሡ ከጠላቶቻችን እጅ አውጥቶናል፤* አቤሴሎም በመሞቱ ዳዊት የቱን ያህል እንደ ታደጋቸው የሰሜን ነገዶች አስታወሱ (3፥17-18፤ 5፥2 ይመ)።

19፥11 *የእስራኤል ሽማግሌዎችን እንዲህ በሏቸው፤* ዐመፁ በይሁዳ ምድር በኬብሮን የተቀሰቀሰ ቢሆንም እንኳ (15፥9-12)፣ ወደ መናገሻ ከተማው ወደ ኢየሩሳሌም ይመልሱት ዘንድ ዳዊት የራሱን ነገድ አለቆች ይማጸናል (2፥4፤ 1ሳሙ 30፥26 ይመ)፤ ይህም ጥረቱ የተፈለገውን ውጤት አስገኝቶአል፤ ይሁን እንጂ በነገዶች መካከል ዐጉል ቅናት እንዲፈጠር በር ከፍቶአል (ቍ 41፥42 ይመ)።

19፥13 *አሜሳይ፤* 17፥25 እና ማብ ይመ። አሜሳይ ለታየበት ክሕደት ሞት የሚገባው ሰው ቢሆንም እንኳ፣ ዳዊት በኢዮአብ ምትክ የሰራዊት አለቃ እንዲሆን ሹሞታል፤ ይህንም ያደረገው የአሜሳይን ተከታዮች በተለምዶ የይሁዳ ወገን የሆኑትን ሰዎች ድጋፍ ለማግኘት ሲል ነበር (20፥5 ይመ)። *እግዚአብሔር ክፉ ያድርግብኝ፤ ከዚህ የባሰም ያምጣብኝ፤* የተለመደ ቃለ መሐላ ነው።

19፥15 *ጌልገላ፤* የኢሱ 4፥19 ማብ ይመ።

19፥17 *አንድ ሺህ ብንያማውያን፤* በሳሚ መጥፎ ድርጊት ተባብራችኋል ተብለው በንጉሡ እንዳይጠረጠሩ በመፍራት አብረውት ሄዱ።

19፥20 *እኔ አገልጋይህ ኀጢአት መሥራቴን ዐውቃለሁና፤* ሳሚ በንጉሥ ዳዊት ላይ የፈጸመው በደል በይፋ የሚታወቅ ነበር፤ ማድረግ የነበረበት ምሕረት ለመለመን የሚያስችለውን ምቹ አጋጣሚ መፈለግ ብቻ ነበር። *ከዮሴፍ ቤት፤* በጣም ታዋቂ የሆኑት ኤፍሬምና ምናሴ (የዮሴፍ ልጆች) (ዘኍ 26፥28፤ ኢሱ 18፥15፤ መሳ 1፥22 ይመ) የሚገኙባቸውን የሰሜን ነገዶች ለማመልከት የተለመደ አባባል ነው (1ነገ 11፥28፤ ሕዝ 37፥19፤ አሞ 5፥6፤ ዘካ 19፥6 ይመ)።

19፥21 *አቢሳ፤* 16፥9፤ እንዲሁም የ1ሳሙ 26፥6 ማብ ይመ። *በእግዚአብሔር የተቀባውን፤* የ1ሳሙ 9፥16 ማብ፤ እንዲሁም 1ሳሙ 24፥6፤ 26፥9-11፤ ሕዝ 22፥28፤ 1ነገ 21፥10 ይመ።

19፥22 *ማንስ ቢሆን ዛሬ በእስራኤል... መሞት አለበት?* ቀኑ ለሁሉም ምሕረት የሚደረግበት ቀን ነበር (1ሳሙ 11፥13 ይመ)።

ቀን አይደለምን?" ብሎ መለሰ:: 23ስለዚህ
ንጉሡ ሳሚን፣ "አትሞትም" አለው፤ ይህንንም
ንጉሡ በመሐላ አጸናለት::
24የሳኦል ልጅ ሜምፊቦስቴም ንጉሡን
ለመቀበል ወረደ:: ንጉሡ ከተሰደደበት ጊዜ
ጀምሮ እስከ ተመለሰበት ዕለት ድረስ ለእ
ግሩ ተገቢውን ጥንቃቄ አላደረገም፤ ጢሙን
አልተላጨም፤ ልብሱንም አላጠበም ነበር::
25እርሱም ንጉሡን ለመቀበል ከኢየሩሳሌም
በመጣ ጊዜ ንጉሡ፣ "ሜምፊቦስቴ፣ አብ
ረኸኝ ያልሄድኸው ለምንድን ነው?" ሲል
ጠየቀው::
26እርሱም እንዲህ አለው፤ "ጌታዬ ንጉሥ
ሆይ፤ እኔ አገልጋይህ ሽባ በመሆኔ፣ 'ከንጉሡ
ጋር መሄድ እንድችል አህያዬ ይጫንልኝና
ልቀመጥበት' ብዬ ነበር፤ ይሁን እንጂ አገ
ልጋዬ ሲባ አታለለኝ:: 27በጌታዬ በንጉሡ
ፊትም የእኔን የባሪያህን ስም አጥፍቶአል፤
መቼም ንጉሥ ጌታዬ እንደ እግዚአብሔር
መልአክ ስለ ሆንህ ደስ ያለህን ሁሉ አድ
ርግ:: 28የአባቴ ቤት ሁሉ ከንጉሥ ጌታዬ
ሞት እንጂ ሌላ የሚገባው አልነበረም፤
አንተ ግን ባሪያህን በማእድህ ከሚካፈሉት
ጋር አስቀመጥኸው፤ ከዚህ በላይ ይደረግ
ልኝ ብዬ ንጉሡን ለመጠየቅ ምን መብት
አለኝ?"
29ንጉሡም፣ "ነገርህን ለምን ታበዛለህ?
አንተና ሲባ ዕርሻውን ሁሉ እንድትካፈሉ
አዝዣለሁ" አለው::
30ሜምፊቦስቴም ንጉሡን፣ "ንጉሥ ጌታዬ
እንኳን በደኅና ተመለስ እንጂ፣ እርሱ ሁሉ
ንም ይውሰደው" አለው::
31እንዲሁም ገለዓዳዊው ቤርዜሊ ከሮግ
ሊም ወረደ፤ ንጉሡን ለመሸኘትም አብሮት
ዮርዳኖስን ተሻገረ:: 32በዚያን ጊዜ ቤርዜሊ
በዕድሜ የገፋ የሰማንያ ዓመት ሽማግሌ
ነበር፤ እጅግ ባለ ጸጋ ስለ ነበረም ንጉሡ
በመሃናይም ሳለ የሚመገበውን አምጥቶለት
ነበር:: 33ንጉሡም ቤርዜሊን፣ "ከእኔ ጋር
ተሻገርና በኢየሩሳሌም አብረኸኝ ኑር፤ እኔ
እመግብሃለሁ" አለው::
34ቤርዜሊ ግን ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለ
ሰለት፤ "ከንጉሡ ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የም
ሄደው ለየትኛው ዕድሜዬ ብዬ ነው? 35እኔ
አሁን የሰማንያ ዓመት ሽማግሌ ነኝ፤ ታዲያ
ደግና ክፉውን መለየት እችላለሁ? ከእንግ
ዲህ አገልጋይህ የሚበላውንና የሚጠጣውን
ጣዕሙን መለየት ይችላል? የሚዘፍኑትን
የወንዶችና የሴቶችን ድምፅ አሁንም መስ
ማት እችላለሁ? ታዲያ አገልጋይህ ለንጉሥ
ጌታዬ ለምን ተጨማሪ ሸክም ይሆናል?
36አገልጋይህ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ከንጉሡ ጋር
ጥቂት መንገድ ይሄዳል፤ ነገር ግን ንጉሡ
በዚህ ሁኔታ ወሮታ የሚመልስልኝ ለምንድን
ነው? 37በገዛ ከተማዬ ሞቼ በአባቴና በእ
ናቴ መቃብር አጠገብ እቀበር ዘንድ፣ አገ
ልጋይህን አሰናብተውና ይመለስ፤ ነገር ግን
አገልጋይህ ከመዓም እነሆ፤ ከጌታዬ ከንጉሡ
ጋር ይሻገር፤ ደስ ያለህንም ነገር አድርግ
ለት::"
38ንጉሡም፣ "ከመዓም ከእኔ ጋር ይሻገራል፤
አንተን ደስ የሚያሰኝህንም ሁሉ አደርግለ
ታለሁ፤ ከእኔ የምትፈልገውን ማናቸውንም
ነገር ለአንተም አደርግልሃለሁ" አለው::
39ስለዚህም ሕዝቡ በሙሉ ዮርዳኖስን ተሻ
ገረ፤ ከዚያ በኋላም ንጉሡ ተሻገረ:: ንጉሡ
ቤርዜሊን ስሞ መረቀው፤ ቤርዜሊም ወደ
ቤቱ ተመለሰ::
40ንጉሡ ወደ ጌልገላ ሲሄድ፣ ከመዓም
አብሮት ሄደ:: የይሁዳ ሰራዊት በሙሉ እን
ዲሁም ግማሹ የእስራኤል ሰራዊት ንጉሡን
አጅበው አሻገሩት::
41ወዲያውም የእስራኤል ሰዎች ሁሉ ወደ
ንጉሡ መጥተው፣ "ወንድሞቻችን የይሁዳ
ሰዎች ንጉሡን በሹልክታ ለብቻቸው ይዘው
እርሱንና ቤተ ሰውን ከተከታዮቹ ጋር ዮር
ዳኖስን ለምን አሻገሩ?" አሉት::
42የይሁዳም ሰዎች ሁሉ፣ ለእስራኤል ሰዎች፣
"ይህን ያደረግነው ንጉሡ የቅርብ ዘመዳ
ችን ስለሆነ ነው፤ ታዲያ ይህ እናንተን

19፥23 1ነገ2፥8:42
19፥24 2ሳሙ4፥4
19፥25 2ሳሙ16፥17
19፥26 ዘሌ21፥28፤ 2ሳሙ9፥2
19፥27 1ሳሙ29፥9
19፥28 2ሳሙ9፥7: 13፤16፥8
19፥31 2ሳሙ17፥27-29፤1ነገ2፥7
19፥32 1ሳሙ25፥2
19፥35 2ዜና35፥25፤ዕዝ2፥65፤ መዝ90፥10፤መክ2፥8፤12፥1
19፥37 ዘፍ49፥29፤ ኤር41፥17
19፥39 ዘፍ47፥7
19፥41 መሳ8፥1፤ 12፥1

19፥23 *አትሞትም፤* ዳዊት የገባውን ቃል ጠብቆአል፤ የደረሰበትን በደል እርሱ ራሱ አይበቀልም (የ1ሳሙ 25፥2-44 ማብ ይመ):: ዳዊት ሊሞት ተቃርቦ በነበረበት ጊዜ ግን የሳሚን ጉዳይ ችላ እንዳይለው ሳይቀጣው እንዳይቀር ለልጁ ለሰሎሞን መመሪያ ሰጠው (1ነገ 2፥8-9: 36-46 ይመ)::

19፥24 *ሜምፊቦስቴ፤* 9፥6-13 ይመ::

19፥25 *አብረኸኝ ያልሄድኸው ለምንድን ነው?* ዳዊት ከዚህ በፊት ሲባ ስለ ሜምፊቦስቴ የነገረውን ወሬ ያስታውሳል (16፥3 ይመ)::

19፥26 *ሽባ፤* 4፥4፤ 9፥3 ይመ::

19፥27 *የባሪያህን ስም አጥፍቶአል፤* 16፥3 ይመ:: *እንደ እግዚአብሔር መልአክ ስለ ሆንህ፤* 14፥17 እና ማብ ይመ:: *ደስ ያለህን ሁሉ አድርግ፤* ሜምፊቦስቴ ለሲባ የተሰጠበት ሀብቱ እንደ ገና ታይቶ እንዲመለስለት ዳዊትን በጥንቃቄ ያሳስባል (16፥4 ይመ)::

19፥29 *ዕርሻውን ሁሉ እንድትካፈሉ፤* ዳዊት ከግራ ቀኙ እርስ በርሱ የሚጋጭና ማረጋገጫም ሊገኝለት ያልቻለ ልዩ ልዩ አቤቱታ ቀርቦለት ከተመለከተው በኋላ፣ ፍርድ ከመስጠት ተቈጥቦ የሳኦል ዕርሻ እንዲከፋፈል እንዲሁ አዘዘ::

19፥31 *ቤርዜሊ፤* የ17፥27 ማብ ይመ::

19፥35 *ደግና ክፉውን መለየት፤* በሽምግልና ዘመኑ በፍርድ ቤት ተግባር ለሚገኘው ደስታ ሁሉ ቤርዜሊ ግድ የሌለው ሰው ሆኖአል::

19፥37 *ከመዓም፤* ምናልባት የቤርዜሊ ልጅ ሳይሆን አይቀርም (1ነገ 2፥7 ይመ)::

19፥41 *የይሁዳ ሰዎች ንጉሡን በሹልክታ ለብቻቸው ይዘው... ዮርዳኖስን ለምን አሻገሩ?* ኢያቡስቴ (2፥8)፣ ሜምፊቦስቴ (9፥4)፣ ዳዊት ራሱ እንኳ ሳይቀር (17፥22)፣ ከዮርዳኖስ ማዶ በጥገኝነት መኖር ለምን እንደ ፈለጉም ስለሚያብራራ፣ ዮርዳኖስ ለእስራኤል ወሬ እንደ ሥነ ልቡና ወሰን ተደርጎ የተወሰደ ይመስላል (ኢሱ 22፥19:25፤ መሳ 12፥4 ይመ):: ጉዳዩ ይህ ሆኖ ሳለ፣ የእስራኤላውያን ተቃውሞ የይሁዳ ሰዎች ዮርዳኖስን አቋርጠው ዳዊትን ከማምጣታቸው በፊት፣ መላው እስራኤል እስኪሰበሰብ አልጠበቁም የሚል ሳይሆን አልቀረም:: ዳዊት በዚህ አኳኋን እንዲመለስ መደረጉ፣ ለሕዝቡ መጥፎ ስም የሚያሰጥና ንጉሡ ሲመለስ ለመቀበል ፈቃደኛ እንዳልሆነ የሚያስቈጥር ሆኖ ታይቶአል (ቊ 43)::

የሚያስቈጣ ነው? እኛ ከንጉሡ ተቀብለን
እንዳች በልተናልን? ለራሳችንስ ምን የወሰ
ድነው ነገር አለ?" አሉአቸው::
43ከዚያም የእስራኤል ሰዎች ለይሁዳ ሰዎች፣
"እኛ እኮ ከንጉሡ ዐሥር እጅ ድርሻ አለን፤
ከዚህም በተጨማሪ በዳዊት ላይ ከእናንተ
ይልቅ እኛ የበለጠ መብት አለን፤ ታዲያ
እኛን የናቃችሁን ስለ ምንድን ነው? ንጉሣ
ችን እንዲመለስ በመጀመሪያ የጠየቅነው
እኛ አይደለንምን?" አሉ::
ነገር ግን የይሁዳ ሰዎች የሰጡት መልስ
የእስራኤል ሰዎች ከሰጡት መልስ ይልቅ
እጅግ የከረረ ነበር::

## ሳቤዔ በዳዊት ላይ ዐመፀ

20 በዚህ ጊዜ የቢክሪ ልጅ ስሙ ሳቤዔ
የተባለ አንድ ምናምንቴ ብንያማዊ
በዚያ ነበረ፤ እርሱም መለከት ነፍቶ እንዲህ
ሲል ጮኸ፤ "እኛ ከዳዊት ድርሻ የለንም፤
ከእሴይም ልጅ ርስት የለንም፤ እስራኤል
ሆይ፤ እያንዳንድህ ወደ ድንኳንህ ተመለስ!"
2ስለዚህ የእስራኤል ሰው ሁሉ ዳዊትን
ከድቶ የቢክሪን ልጅ ሳቤዔን ተከተለ:: የይ
ሁዳ ሰዎች ግን ከዮርዳኖስ አንሥቶ እስከ
ኢየሩሳሌም ድረስ ከንጉሣቸው ሳይለዩ አብ
ረውት ሄዱ::
3ዳዊት ኢየሩሳሌም ወዳለው ቤተ መንግ
ሥቱ በተመለሰ ጊዜ፤ ቤተ መንግሥቱን እን
ዲጠብቁ ትቶአቸው የሄደውን ዐሥሩን ቁባ
ቶቹን ወሰደ፤ በአንድ ቤትም ውስጥ እን
ዲጠበቁ አደረገ:: ቀለብ ሰጣቸው፤ ይሁን
እንጂ ወደ እነርሱ አልገባም ነበር፤ እነር
ሱም እስከ ሞቱበት ጊዜ ድረስ መበለት
ሆነው፣ ለብቻቸው ተገልለው ተቀመጡ::
4ከዚያም ንጉሡ አሜሳይን፣ "የይሁዳ
ሰዎች ሁሉ በሦስት ቀን ውስጥ፣ ወደ እኔ
እንዲመጡ ጥራልኝ፤ አንተ ራስህም ተገኝ"
አለው:: 5አሜሳይ ይሁዳን ለመጥራት ሄደ፤
ነገር ግን ንጉሡ ከወሰነው ጊዜ በላይ ቈየ::
6ዳዊትም አቢሳን፣ "ከአቤሴሎም ይልቅ
አሁን የቢክሪ ልጅ ሳቤዔ የበለጠ ጕዳት ሊያ
ደርስብን ስለ ሆነ የጌታህን ሰዎች ይዘህ
አሳደው፤ ያለዚያ የተመሸገ ከተማ አግኝቶ
ያመልጠናል" አለው:: 7ስለዚህ የኢዮአብ
ሰዎች፣ ከሊታውያን፣ ፈሊታውያን እንዲ
ሁም ሌሎች ኀያላን ጦረኞች በሙሉ በአቢሳ
አዛዥነት ወጡ፤ ከኢየሩሳሌም የወጡትም
የቢክሪ ልጅ ሳቤዔን ለማሳደድ ነበር::
8በገባዖን ከታላቁ ቋጥኝ አጠገብ ሳሉ፣
አሜሳይ ሊገናኛቸው መጣ፤ ኢዮአብ የጦር ሜዳ
ልብሱን ለብሶ ሰይፉን ከሰገባው በወገቡ
ላይ ታጥቆ ነበር፤ ወደ ፊት ራመድ እንዳ
ለም ሰይፉ ከሰገባው ወጥቶ ወደቀ::
9ኢዮአብም አሜሳይን፣ "ወንድሜ ሆይ፤
እንደምንድን ነህ?" አለው፤ ከዚያም አሜሳይን
የሚስም መስሎ በቀኝ እጁ ጢሙን ያዘው::
10አሜሳይ ግን በኢዮአብ እጅ ሰይፍ መኖሩን
ልብ ስላላለ ጥንቃቄ አላደረገም፤ ስለዚህ
ኢዮአብ ሰይፉን ሆዱ ላይ ሻጠበት፤ አንጀ
ቱም መሬት ላይ ተዘረገፈ፤ ከዚያም ኢዮአብ
መድገም ሳያስፈልገው፣ አሜሳይ በዚያው
ሞተ:: ከዚህ በኋላ ኢዮአብና ወንድሙ አቢሳ፣
የቢክሪን ልጅ ሳቤዔን ማሳደድ ጀመሩ::
11በአሜሳይ ሬሳ አጠገብ ከቆሙት ከኢ
ዮአብ ሰዎች አንዱ፤ "ኢዮአብን የሚወድ፣
የዳዊትም የሆነ ሁሉ ኢዮአብን ይከተል!"
አለ:: 12በዚህን ጊዜ የአሜሳይ ሬሳ በደም
ተጨማልቆ በመንገዱ መካከል ወድቆ ነበር፤
በዚያ የሚያልፈው ሰራዊት ሁሉ መቆሙን
ያ ሰው አየ፤ ወደ ሬሳው የደረሰው ሰራዊት
ሁሉ መቆሙን በተረዳ ጊዜም፣ የአሜሳይን
ሬሳ ከመንገድ ወደ ዕርሻ ፈቀቅ አድርጎ
ልብስ ጣል አደረገበት:: 13የአሜሳይ ሬሳ
ከመንገድ ላይ ከተነሣ በኋላ ሕዝቡ ሁሉ ኢዮ
አብን ተከትሎ የቢክሪን ልጅ ሳቤዔን ሊያ
ሳድድ ሄደ::

19፥43 2ሳሙ 5፥1
20፥1 ዘፍ 29፥14፤ 31፥14፤ 1ሳሙ 22፥7-8፤ 1ነገ 12፥16
20፥3 2ሳሙ 15፥16
20፥4 2ሳሙ 17፥25
20፥6 2ሳሙ 21፥17
20፥7 1ሳሙ 30፥14፤ 2ሳሙ 15፥18
20፥8 ኢሱ 9፥3፤ 2ሳሙ 2፥18
20፥10 መሳ 3፥21፤ 1ነገ 2፥5
20፥12 2ሳሙ 2፥23

19፥43 *ዐሥር እጅ፤* ከይሁዳና ከስምዖን በቀር ዐሥሩን ነገዶች የሚመለከት ነው (የ2፥4 ማብ ይመ):: *በዳዊት ላይ... እኛ የበለጠ መብት አለን፤* ይህ በሌሎች ዘንድ በድፍረት እንዲታወቅ የተደረገበት ምክንያት እግዚአብሔር ዳዊትን በሳኦል ምትክ እንዲነግሥ ስለ መረጠው ሊሆን ይችላል (3፥17-18፤ 5፥2 ይመ)::

20፥1 *ምናምንቴ፤* የዘዳ 13፥13 ማብ ይመ:: *ቢክሪ፤* ለብንያም ሁለተኛ ልጁ ነው (ቤኬር፣ ዘፍ 46፥21፤ 1ዜና 7፥6-9):: *ብንያማዊ፤* የመንግሥት ሥልጣን ከብንያም ቤት (የሳኦል ነገድ) ወደ ይሁዳ ቤት በመዛወሩ በብንያማውያን ዘንድ ወገናዊ ቅናት ተቀጣጥሉ ነበር:: *በዚያ፤* በጌልገላ ማለት ነው (19፥40-43):: *እኛ ከዳዊት ድርሻ የለንም፤* ዳዊት ከሌሎቹ ነገዶች ይልቅ የራሱ ለሆነው ለይሁዳ ነገድ ያደላል የሚለውን የእስራኤል ቤት ጥርጣሬ ሳቤዔ በዚህ ላይ ይጠቀማል (1ነገ 12፥16 ይመ)::

20፥2 *የእስራኤል ሰው ሁሉ፤* በ19፥41-43 ላይ የተጠቀሱት ሰዎች ናቸው::

20፥3 *ዐሥሩን ቁባቶቹን፤* የ15፥16፤ 16፥22 ማብ ይመ::

20፥4 *አሜሳይ፤* የ17፥25፤ 19፥13 ማብ ይመ:: ዳዊት ኢዮአብን ችላ አለው::

20፥6 *አቢሳን፤* ዳዊት አሁንም ኢዮአብን ለሁለተኛ ጊዜ ችላ አለው (ቊ 7):: *የጌታህን ሰዎች፤* "የኢዮአብን ሰዎች" ማለት ነው (ቊ 7)::

20፥7 *የኢዮአብ ሰዎች፤* 18፥2 ይመ:: ኢዮአብ በአዛዥነት ደረጃ ባይሆንም እንኳ (በንጉሡ ትእዛዝ)፣ ከወታደሮቹ ጋር እንዲሁ አብሮ ይጓዝ እንደ ነበረ በግልጥ ይታወቃል (ቊ 7:11:15 ይመ):: *ከሊታውያን፣ ፈሊታውያን፤* የ8፥18 ማብ ይመ:: *ኀያላን ጦረኞች፤* 23፥8-39 ይመ:: ዳዊት እስጊ ሁኔታ ሲያጋጥመው አሁንም የተማመነው፣ በግሉ ሰራዊት ውስጥ በሚገኙ፣ አነስተኛ ቊጥር ባላቸው ወታደራዊ ባለሙያዎች (አብዛኞቹ እስራኤላውያን አልነበሩም) ላይ ነው::

20፥8 *ገባዖን፤* የ2፥12 ማብ ይመ:: *አሜሳይ... መጣ፤* ጥቂት ወታደሮች አብረውት ነበሩ (ቊ 11 እና ማብ ይመ)::

20፥10 *ሆዱ ላይ ሻጠበት፤* 2፥23፤ 3፥27 ይመ:: ኢዮአብ በዳዊት ሰራዊት ውስጥ የነበረውን የአዛዥነት ቦታ እንደ ያዘ ለመቈየት ሲል ለሁለተኛ ጊዜ የሰው ሕይወት በእጁ አጠፋ (1ነገ 2፥5-6 ይመ):: *ኢዮአብና ወንድሙ አቢሳ፤* ኢዮአብ የዳዊትን ሥልጣን በመናቅ፣ በራሱ አነሳሽነት የአዛዥነቱን ሥልጣን ሲይዝ ይታያል (ቊ 23 ይመ)::

20፥11 *ኢዮአብን የሚወድ፣ የዳዊትም የሆነ ሁሉ፤* ኢዮአብ በሳቤዔ ሤራ ሳይተባበር አልቀረም የሚለውን ጥርጣሬ ለማስወገድ ነው፤ የአሜሳይ ወታደሮች በእውነት ለዳዊት ታማኝ ከሆኑ፣ ኢዮአብን እንዲደግፉ ጥሪ ቀርቦላቸዋል::

[14]ሳቤዔም በእስራኤል ነገዶች ሁሉ መካ
ከል ዐልፎ ወደ አቤል ቤትማዓካና ወደ
መላው የቢክሪያውያን ግዛት መጣ፤ የቢክሪ
ሰዎችም ተሰብስበው ተከተሉት። [15]ከኢዮ
አብ ጋር ያለውም ሰራዊት መጥቶ ሳቤዔን
በአቤል ቤትመዓካ በኩል ከበበው፤ በስተ
ውጭም እስከ ከተማዪቱ ግንብ ጫፍ ድረስ
ዙሪያውን የዐፈር ድልድል ሠሩ፤ ግንቡን
ለመናድ በኀይል በሚደበድቡበት ጊዜ፣
[16]አንዲት ብልኅ ሴት ድምፅዋን ከፍ አድ
ርጋ፣ "ስሙ! ስሙ! ለኢዮአብ የምነግረው
ነገር ስላለ ወደዚህ እንዲመጣ ንገሩት" አለ
ቻቸው። [17]ኢዮአብ ወደ እርሷ ሄደ፤ እር
ሷም፣ "ኢዮአብ አንተ ነህ?' ስትል ጠየ
ቀችው።

እርሱም፣ "አዎን እኔ ነኝ" ብሎ መለሰ
ላት።

እርሷም፣ "እንግዲህ አገልጋይህ የምትለ
ውን አድምጥ" አለችው።

እርሱም፣ "እሺ፣ አደምጣለሁ" አላት።

[18]ከዚያ በመቀጠልም እንዲህ አለች፤ "በቀ
ድሞው ጊዜ ሰዎች፣ 'ምክርን ከአቤል ጠይቁ'
ይሉ ነበር፤ ታዲያ እንዳሉትም ይፈጸም
ነበር፤ [19]በእስራኤል ሰላማዊና ታማኝ ከሆኑ
ሰዎች መካከል አንዷ እኔ ነኝ፤ አንተ በእስ
ራኤል እናት የሆነችውን ከተማ ለማጥፋት
ትሻለህ፤ *የእግዚአብሔርን ርስት* ለመዋጥ
የፈለግኸው ለምንድን ነው?"

[20]ኢዮአብም እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ይህስ
ከእኔ ይራቅ! መዋጡና ማጥፋቱ አሁንም
ከእኔ ይራቅ! [21]ነገሩስ እንዲህ አይደለም፤
የኰረብታማው የኤፍሬም አገር ሰው፣ የቢ
ክሪ ልጅ ሳቤዔ እጁን በንጉሡ በዳዊት ላይ
አንሥቶአል፤ እናንተ ይህን ሰው ብቻ ስጡኝ
እንጂ እኔ ከተማዪቱን ትቼ እሄዳለሁ" አላት።

ሴቲቱም ኢዮአብን፣ "የሰውየው ራስ ተቈ
ርጦ በግንቡ ላይ ይወረወርልሃል" አለችው።

[22]ከዚህም በኋላ ሴቲቱ ብልኀነት የተሞ
ላበት ምክሯን ይዛ ወደ ሕዝቡ ሁሉ ሄደች፤
እነርሱም የቢክሪን ልጅ የሳቤዔን ራስ ቈርጠው
ለኢዮአብ ወረወሩለት፤ ስለዚህ ኢዮአብ
መለከቱን ነፋ፤ ሰዎቹም ከከተማዪቱ ርቀው
በየአቅጣጫው ተበታተኑ፤ እያንዳንዳቸውም
ወደየቤታቸው ሄዱ፤ ኢዮአብም ወደ ንጉሡ
ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።

[23]ኢዮአብ በእስራኤል ሰራዊት ሁሉ ላይ
የበላይ ሆነ፤ የዮዳሄ ልጅ በናያስ ደግሞ
በከሊታውያንና በፈሊያታውያን ላይ አለቃ
ሆነ። [24]አዶኒራም[T] በግዳጅ ሥራ ላይ ለተሰ
ማሩት ሰዎች አለቃ ሆነ፤ የአሒሉድ ልጅ
ኢዮሣፍጥ ደግሞ ታሪክ ጸሓፊ ሆነ፤ [25]ሱሳ
ጸሓፊ፣ ሳዶቅና አብያታር ካህናት ነበሩ፤
[26]እንዲሁም የኢያዕር ሰው ዒራስ የዳዊት
አማካሪ ነበር።

20፥14 ዘኍ21፥16
20፥15 1ነገ15፥20፤ 2ነገ15፥29፤ኢሳ 37፥33፤ኤር6፥6፤ 32፥24
20፥16 2ሳሙ14፥2
20፥19 ዘዳ2፥26፤ 1ሳሙ26፥19
20፥21 2ሳሙ4፥8
20፥22 መክ9፥13
20፥23 2ሳሙ 2፥28፤8፥16-18፤24፥2
20፥24 2ሳሙ 8፥16፤1ነገ4፥6፤5፥14፤ 12፥18፤2ዜና10፥18
20፥25 1ሳሙ 2፥35፤2ሳሙ8፥17
21፥1 ዘፍ12፥10፤ ዘዐ32፥11፤ዘዳ32፥24

## የገባዖናውያን ብቀላ

**21** በዳዊት ዘመነ መንግሥት፣ በተከታ
ታይ ለሦስት ዓመት ራብ ሆነ፤ ስለዚህ
ዳዊት *እግዚአብሔርን* ጠየቀ፤ *እግዚአብሔርም*

[T]24 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች (እንዲሁም 1ነገ 4፥6 እና 5፥14 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *አዶራም* ይላል።

20፥14 *ቤትመዓካ፤* የዚህን ክፍል ማብ ይመ፤ ከዳን በስተ ሰሜን ትገኛለች (1ነገ 15፥20፤ 2ዜና 16፥4 ይመ)። ሳቤዔ ያዋጣኛል ብሎ የተጠቀመበት ስልት የተቻለውን ያህል ወደ ዘማች ወታደር ለዐመፁ ማሰባሰብ ነበር፤ ይሁን እንጂ የዳዊት ተከታዮች በቀላሉ ሊደርሱበት በሚችል በማ ንኛውም ቦታ ላይ ያን የማይረባ ጦር ለመሰብሰብ ፈራ። *ቢክሪ፤* ከዚህ ውጭ በሌላ ቦታ አይታወቅም።

20፥18 *ምክርን ከአቤል ጠይቁ፤* ከተማዪቱ በነዋሪ ዎቿ ጥበበኛነት ትታወቃለች።

20፥19 *በእስራኤል እናት የሆነችውን ከተማ፤* ታማ ኝና ተቈርቋሪ የሆኑ እስራኤላውያን ዜጎችን የምታፈራ ከተማ ናት፤ ከተማዎች ብዙውን ጊዜ በሴት ጾታ መጠራታቸው የተለመደ ነበር (ኤር 50፥12፤ ገላ 4፥26 ይመ)። *የእግዚ አብሔርን ርስት፤* የ1ሳሙ 10፥1 ማብ ይመ።

20፥21 *የኰረብታማው የኤፍሬም አገር፤* ብንያማ ዊው ሳቤዔ (ቍ 1ይመ)፤ በኤፍሬማውያን አገርኖሮአል፤ ወይም ይህ ቦታ የአንድን ነገድ ይዞታ ሳይሆን፣ እንዲሁ መልክዐ ምድራዊ ክልልን የሚያመለክት ነው።

20፥22 *ኢዮአብም ወደ ንጉሡ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ፤* የቍ 7፡10 ማብ ይመ።

*20፥23-26፤* እነዚህ የቤተ መንግሥት አለቆች ዳዊ ትን በአብዛኛው የአገዛዝ ዘመኑ አገልግለውታል (8፥15-18 ይመ)።

20፥23 *ኢዮአብ በእስራኤል ሰራዊት ሁሉ ላይ የበ ላይ ሆነ፤* በኢዮአብ ላይ ቅሬታ ቢኖረውም እንኳ፣ እስከ አዶንያስ ሤራ ድረስ ሥልጣኑን ይዞ ቈይቶአል (1ነገ 1፥7፤ 2፥28-35)። *ከሊታውያንና ፈሊታውያን፤* የ8፥18 ማብ ይመ።

20፥24 *አዶኒራም በግዳጅ ሥራ ለተሰማሩት ሰዎች አለቃ ሆነ፤* በመጀመሪያ የዳዊት አገዛዝ ዘመን ያልነበረ የኀ ላፊነት ቦታ ነው (8፥15-16 ይመ)። አዶኒራም በሰሎሞንም ዘመን ያገለገለ ሹም ስለ ነበረ፣ ዳዊት በመጨረሻ ዘመኑ ላይ ኀላፊነት የሰጠው ሰው ሳይሆን አይቀርም (1ነገ 4፥6፤ 5፥14)። በመጨረሻም በመጀመሪያው በሮብዓም የሥልጣን ዓመ ታት ውስጥ ተገደለ (1ነገ 12፥18፤ 2ዜና 10፥18)። *የግዳጅ ሥራ፤* በጦርነት ከተሸነፉ አገሮች የተማረኩ የጦር እስረ ኞች በአብዛኛው የሚሠሩት ሥራ ነው (12፥31፤ ኢሱ 9፥21፤ 1ነገ 9፥15፡20-21 ይመ)። *ታሪክ ጸሓፊ፤* የ8፥16 ማብ ይመ።

20፥25 *ሱሳ፤* የ8፥17 ማብ ይመ ("ሠራያ" ተብሎ አል)። *ጸሓፊ፤* የ8፥17 ማብ ይመ። *ሳዶቅና አብያታር፤* የ8፥17 ማብ ይመ።

20፥26 *የኢያዕር ሰው፤* ከምናሴ ነገድ የሆነውን ኢያዕርን (ዘኍ 32፥41) ወይም ከገለዓድ ወገን አንዱን ፈራጅ (መሳ 10፥3፡5) ሊያመለክት ይችላል። *አማካሪ፤* የ8፥18 ማብ ይመ።

21፥1-24፥25፤ ይህ የመደምደሚያ ክፍል ለአንደኛውና ለሁለተኛው የሳሙኤል መጻሕፍት ተጨማሪ ነው፤ (የጊዜ ቅደም ተከተልን ሳይጠብቅ) ከዳዊት የአገዛዝ ዘመን ጋር ግንኙነት ያላቸውን ተጨማሪ ሐሳቦች ይዞአል። የመጀመሪያውና የመጨ ረሻው ክፍል (21፥1-1፤ 24፥1-25) እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ ያሳየውን ቍጣ ዳዊት እንዴት መመልከት እንደ ነበ ረበት የሚያሳዩ የሁለት ድርጊቶች ትረካዎች ናቸው (የመ ጀመሪያው ቍጣ ሳኦል በፈጸመው ስሕተት የመጣ ሲሆን፣ ሁለ ተኛው ደግሞ በራሱ በዳዊት ስሕተት የመጣ ቍጣ ነው)። ሁለተኛውና አምስተኛው ክፍሎች (21፥15-22፤ 23፥8-39)፣ የዳዊትን ተዋጊ ወታደሮች የሚመለከቱ ታሪኮች ናቸው (ሁለ ተኛው ከመጀመሪያው ብዙ ይረዝማል)። ሁለት የዳዊት መዝ ሙሮች በዚህ ክፍል መካከል (22፥1-23፥7) ተጽፈው ይገኛሉ (የመጀመሪያው ከሁለተኛው ይልቅ ብዙ ይረዝማል)፤ አንደኛው መዝሙር ዳዊት ተዋጊ ንጉሥ እንደ መሆኑ መጠን፣ የተጉና ጸፋቸውን ድሎች የሚያሳይ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ መዝ

ሳኦል ገባዖናውያንን ስለ ገደለ፣ እርሱና
ቤቱ የደም ዕዳ አለባቸው" አለ።
²ንጉሡ ገባዖናውያንን ጠርቶ አነጋገራቸው።
ገባዖናውያን ከአሞራውያን የተረፉ እንጂ
ከእስራኤል ወገን አልነበሩም፤ እስራኤላው
ያን ሊጠብቋቸው ቢምሉላቸውም፣ ሳኦል
ግን ለእስራኤልና ለይሁዳ ካለው ቅናት የተ
ነሣ ሙሉ በሙሉ ሊያጠፋቸው ፈልጎ ነበር፤
³ዳዊትም ገባዖናውያንን፣ "ምን ላድርግላችሁ?
*የእግዚአብሔርን ርስት* ትባርኩ ዘንድ ማስ
ተሰረያውን ምን ማድረግ አለብኝ?" ሲል ጠየ
ቃቸው።
⁴ገባዖናውያንም፣ "ከሳኦልም ሆነ ከቤተ ሰቡ
ብር ወይም ወርቅ የመጠየቅ መብት የለንም፤
እንዲሁም ከእስራኤል ማንንም ለመግደል
መብት የለንም" ብለው መለሱለት።
ዳዊትም፣ "ታዲያ ምን ላድርግላችሁ?"
ሲል ጠየቃቸው።
⁵እነርሱም፣ "እንድንፈራርስና በእስራኤ
ልም ውስጥ በየትኛውም ስፍራ እንዳንኖር
ካጠፋንና ደባ ከፈጸመብን ሰው ⁶ከእርሱ ዘሮች
ሰባት ወንዶች ልጆች ይሰጠን፤ እኛም *ከእ
ግዚአብሔር* በተመረጠው በሳኦል አገር በጊ
ብዓ *በእግዚአብሔር ፊት* እንስቀላቸው" ብለው
መለሱለት።
ስለዚህ ንጉሡ፣ "እሺ እሰጣችኋለሁ" አለ።
⁷ንጉሥ ዳዊት በራሱና በሳኦል ልጅ በዮ
ናታን መካከል *በእግዚአብሔር ፊት* ስላደ
ረጉት መሐላ ሲል የሳኦልን ልጅ፣ የዮና
ታንን ልጅ ሜምፌቦስቴን ከሞት አተረፈ።
⁸ነገር ግን ንጉሡ የኢዮሄል ልጅ ሪጽፋ ለሳ
ኦል የወለደቻቸውን ሁለቱን ወንዶች ልጆች
ሄርሞንንና ሜምፌቦስቴን፤ የሳኦል ልጅ
ሜሮብ[a] ለምሖላታዊው ለቤርዜሊ ልጅ ለኤ
ስድሪኤል የወለደችለትን አምስት ወንዶች
ልጆች ጭምር ወሰደ፤ ⁹ለገባዖናውያን አሳ
ልፎ ሰጣቸው፤ እነርሱም ገድለው በኰረብ
ታው ላይ *በእግዚአብሔር ፊት* ሰቀሏቸው።
ሰባቱም በአንድነት ወደቁ፤ የተገደሉትም
በመከሩ ወራት የመጀመሪያ ቀኖች፣ የገ
ብስ ዐጨዳ በተጀመረበት ዕለት ነበር።
¹⁰የኢዮሄል ልጅ ሪጽፋ ማቅ ወስዳ፣ በቋ
ጥኝ ላይ ለራሷ አነጠፈች፤ ከመከር ወቅት
መጀመሪያ አንሥቶ ዝናብ ከሰማይ በሬሳ
ዎቹ ላይ እስከ ወረደ ጊዜ ድረስ ቀን የሰ
ማይ ወፎች ሌሊት የዱር አራዊት እንዲ
ነኳቸው አልፈቀደችም፤ ¹¹የሳኦል ቁባት
የኢዮሄል ልጅ ሪጽፋ ያደረገችውን ዳዊት
በሰማ ጊዜ፣ ¹²ሄዶ የሳኦልንና የልጁን የዮና
ታንን ዐፅም ከኢያቢስ ገለዓድ ሰዎች ወሰደ፤
የኢያቢስ ሰዎች፣ ፍልስጥኤማውያን ሳኦልን
በጊልቦዓ ከገደሉ በኋላ እነርሱን ከሰቀሉት
ከቤት ሳን አደባባይ በድብቅ ወስደዋቸው
ነበር። ¹³ዳዊትም የሳኦልንና የልጁን የዮና
ታንን ዐፅም ከዚያ አመጣ፤ እንዲሁም የእ
ነዚያን የተገደሉትን ሰዎች ዐፅም ሰበሰቡ።

[a]8 ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆች፣ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናትና የሱርስት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ (እንዲሁም 1ሳሙ 18፥19 ይመ)፤ አብዛኞቹ የዕብራይስጥና የሰብዓ ሊቃናት ቅጆች ግን ሜልኮል ይላሉ።

21፥2 ኢያሱ9፥15
21፥3 1ሳሙ26፥19
21፥4 ዘኍ 35፥33-34
21፥6 ዘኍ25፥4፤ 1ሳሙ10፥24
21፥7 1ሳሙ18፥3 ፤2ሳሙ4፥4፤9፥7
21፥8 1ሳሙ 18፥19፤2ሳሙ3፥7
21፥9 ሩት1፥22፤ 2ሳሙ16፥8
21፥10 ዘፍ40፥19፤ 1ሳሙ17፥44
21፥12 ኢያሱ17፥11፤ መሳ21፥8፤1ሳሙ 11፥1፤28፥4፤31፥10፡ 11-13

ሙረኛነቱን ይገልጣል (የ1ሳሙ 16፥14-17:58 ማብ ይመ)። እንደዚህ ዐይነቱን ቅንብር ለመጠቀም ከሥነ ውበት አስተሳሰብ ያለፈ ፍላጎት ስለ መኖሩ የሚታወቅ ነገር የለም። በም 22 ላይ ያለው የድል መዝሙርና በ1ሳሙ 2፥1-10 ላይ የሚገኘው የሐና መዝሙር በዘመኑ የነበረውን ዐይነተኛ የአጻጻፍ ስልት በግልጥ የሚያሳዩ የሥነ ጽሑፍ ሥርዐትንም የተከተሉ ናቸው (የ1ሳሙ 2፥1 ማብ ይመ)።

21፥1-14፤ ይህ ድርጊት ዳዊት ለሜምፊቦስቴ ቸርነት ካደረገበት ጊዜ በኋላና (ም 9)፣ አቤሴሎምም ከማመፁ (16፥7-8፤ የ16፥8 ማብ ይመ) በፊት የተፈጸመ ሳይሆን አይቀርም።

21፥1 *ገባዖናውያንን ስለ ገደለ፤* ሳኦል በገባዖናውያን ላይ የፈጸመው በደል በሌላ ቦታ አልተገለጸም፤ ሆኖም ቀደም ባሉት በሳኦል የአገዛዝ ዓመታት ውስጥ ከብሔርተኝነት ስሜት የተነሣ ሳይፈጸም አይቀርም (ገባዖናውያን ከሰፈሩበት ምድር ውስጥ ከፊሉ የብንያም ምድር ነው፤ የሳኦል ቅድመ አያትም "የገባዖናውያን አባት" በመባል ይታወቅ ነበር፤ 1ዜና 8፥29፤ 9፥35)።

21፥2 *ከአሞራውያን፤* ከእስራኤላውያን ቀደም ብለው በከነዓን ምድር የሰፈሩትን ሰዎች ለማመልከት ዐልፎ ዐልፎ ጥቅም ላይ የዋለ አጠቃላይ ስም ነው (ዘፍ 15፥16፤ ኢያሱ 24፥18፤ መሳ 6፥10፤ አሞ 2፥10)። ገባዖናውያን ይበልጥ በትክክል የሚታወቁባት ስም ኤዊያውያን የሚባል ነው (ኢያሱ 9፥7፤ 11፥19)። *እስራኤላውያን ሊጠብቋቸው ቢምሉላቸውም፤* በእግዚአብሔር (ያህዌ) ስም የተደረገ መሐላ ነበር (ኢያሱ 9፥15፤18፥26)። *ሊያጠፋቸው ፈልጎ ነበር፤* ሳኦል በምን ምክንያት ሊሳካለት እንዳልቻለ አይታወቅም።

21፥3 *ትባርኩ ዘንድ፤* የተገባላቸው ቃል በመታጠፉ በምድሪቱ ላይ እግዚአብሔር መዐት እንዲያወርድ መጠየቃቸው ተገቢ ነበር። *የእግዚአብሔርን ርስት፤* የ1ሳሙ 10፥1 ማብ ይመ።

21፥4 *ከእስራኤል ማንንም ለመግደል መብት የለንም፤* የነፍስ ግድያ ወንጀል ሊካካስ የሚችለው ተመሳሳይ ርምጃ በመውሰድ ወይም ደምን በመመለስ ነው፤ ገባዖናውያን ግን ባዕዳን እንደ መሆናቸው መጠን፣ እስራኤላውያንን ለመበቀል አይችሉም። ከሙሴ ሕግ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ፣ ይህን ርምጃ እንዳይወስዱ በእነርሱ ላይ እገዳ ያደረገባቸው ሳኦል ሳይሆን አይቀርም (ዘፀ 22፥21፤ ዘሌ 19፥34፤ 24፥22፤ ዘዳ 1፥16-17፤ 24፥17፤ 27፥19 ይመ)።

21፥5 *ሰው፤* ሳኦል ነው። *በእስራኤልም ውስጥ በየትኛውም ስፍራ እንዳንኖር፤* ከሳኦል በትር ያመለጡት ከመኖሪያ ከተማቸውና ከመሬታቸው እንዲባረሩ ተደርገው ነበር (4፥2-3 እና ማብ ይመ)።

21፥6 *ሰባት፤* ከዚህ ቍጥር የሚበልጥ ብዛት የነበራቸው ገባዖናውያን ያለቁ ቢሆንም፣ ቍጥር "ሰባት" ሙሉ ቍጥርን ይወክላል ("ሰባት" ምሉእነትን ያሳያል)። *ጊብዓ፤* የሳኦል መኖሪያ ስፍራ ነው (1ሳሙ 10፥26 ይመ)።

21፥7 *ዳዊት በራሱና... በዮናታን መካከል በእግዚአብሔር ፊት ስለ አደረጉት መሐላ፤* 4፥4፤ 9፥1-13፤ 1ሳሙ 18፥3፤ 20፥15 ይመ።

21፥8 *ሪጽፋ፤* 3፥7 ይመ። *ሜሮብ፤* 1ሳሙ 18፥19 ይመ። *ለምሖላታዊው ለቤርዜሊ፤* ከገለዓዳዊው ቤርዜሊ ጋር አንድ ተደርጎ መታየት የለበትም (17፥27፤ 19፥31)።

21፥9 *ሰባቱም በአንድነት ወደቁ፤* ይህ እግዚአብሔር የናቀው የሳኦል ቤተ ሰብ በማለቅ ላይ ይገኛል (1ሳሙ 13፥13-14፤ 15፥23-26 ይመ)። በ1ዜና 8፥29-39፤ 9፥35-44 ላይ ከዮናታን ልጆችና የልጅ ልጆች በቀር ሌላ የሳኦል ዘር አልተጠቀሰም። *የገብስ ዐጨዳ በተጀመረበት ዕለት፤* ሚያዝያ አጋማሽ ገደማ ነው (የሩት 1፥22 ማብ ይመ)።

21፥10 *ማቅ፤* የዘፍ 37፥34 ማብ ይመ። *ዝናብ... እስከ ወረደ፤* ራቡ የመጣው ከድርቅ የተነሣ መሆኑን የሚያመለክትና ለገባዖናውያን በመሐላ የተገባላቸውም ቃል በመጣሱ (ቍ 1 ይመ)፣ በእስራኤል ላይ የመጣው ፍርድ በዚህ ጊዜ መፈጸሙን የሚያሳይ ነው።

21፥12 *የሳኦልንና የልጁን የዮናታንን ዐፅም፤* 1ሳሙ 31፥11-13 ይመ። ዳዊት አሁን በመጨረሻ ለሳኦልና ለዮናታን ያደረገው፣ ያከበረው ለነበረው ንጉሥና ይወደው ለነበረው ጓደኛው ምን ያህል ጽኑ አክብሮትና ፍቅር እንደ ነበረው ያመለክታል።

14የሳኦልንና የልጁን የዮናታንን ዐፅም በብ
ንያም አገር ጼላ በተባለ ስፍራ በሳኦል አባት
በቂስ መቃብር ቀበሩት፤ ንጉሡ ያዘዘውንም
ሁሉ አደረጉ። ከዚያ በኋላም ስለ ምድሪቱ
የቀረበውን ጸሎት እግዚአብሔር ሰማ።

## በፍልስጥኤማውያን ላይ የተደረገ ጦርነት

21፥15-22 ተጓ ምብ - 1ዜና 20፥4-8

15እንደ ገና በፍልስጥኤማውያንና በእስራ
ኤል መካከል ጦርነት ተደረገ። ዳዊትም ከሰ
ዎቹ ጋር ሆኖ ፍልስጥኤማውያንን ለመው
ጋት ወረደ፤ በዚያም ደከመው። 16ከራፋይም
ዘሮች አንዱ የሆነ ይሽቢብኖብ የተባለ፣
የናስ ጦሩ ሦስት መቶ ሰቅል[ሀ] የሚመዝንና
አዲስ ሰይፍ የታጠቀ ሰው ነበረ፤ እርሱም
ዳዊትን ለመግደል አሰበ። 17የጽሩያ ልጅ
አቢሳ ግን ዳዊትን ለመታደግ መጣ፤ ፍል
ስጥኤማዊውንም ወግቶ ገደለው። ከዚያም
የዳዊት ሰዎች፣ “የእስራኤል መብራት እን
ዳይጠፋ ከእንግዲህ አንተ ከእኛ ጋር ወደ
ጦርነት መውጣት የለብህም” ብለው ማሉ
ለት።
18ከዚህ በኋላ ጎብ በተባለ ስፍራ ከፍልስ
ጥኤማውያን ጋር ሌላ ጦርነት ተደረገ። በዚ
ያን ጊዜም ኩሳታዊው ሴቦካይ፣ ከራፋይም
ዘሮች አንዱ የሆነውን፣ ሳፍን ገደለው።
19ጎብ ላይ ከፍልስጥኤማውያን ጋር በተ
ደረገ ሌላ ጦርነትም፣ የቤተልሔሙ የየዓ
ሬዓርጊም[ለ] ልጅ ኤልያናን፣ የጦሩ ዘንግ እንደ
ሸማኔ መጠቅለያ የሆነውን የጌት ሰው ጎል
ያድን ገደለ[ሐ]።
20እንደ ገና ጌት ላይ በተደረገው ጦርነት
በእያንዳንዱ እጁና በእያንዳንዱ እግሩ ስድ
ስት ስድስት ጣቶች ባጠቃላይ ሃያ አራት
ጣቶች የነበሩት አንድ ግዙፍ ሰው ነበረ፤
እርሱም ደግሞ ከራፋይም ዘር ነበረ። 21ይህም
ሰው እስራኤልን በተገዳደረ ጊዜ፣ የዳዊት
ወንድም የሣማ ልጅ ዮናታን ገደለው።
22እነዚህ አራቱ በጌት የራፋይም ዘሮች
የነበሩ ናቸው፤ እነርሱም በዳዊትና በሰዎቹ
እጅ ወደቁ።

## የዳዊት የምስጋና መዝሙር

22፥1-51 ተጓ ምብ - መዝ 18፥1-50

22 እግዚአብሔር ከጠላቶቹ ሁሉና ከሳ
ኦልም እጅ በታደገው ጊዜ፣ ዳዊት
የዚህን መዝሙር ቃል ለእግዚአብሔር ዘመረ፤
2እንዲህም አለ፤

“እግዚአብሔር ዐለቴ ዐምባዬና ታዳጊዬ ነው፤
3አምላኬ፣ የምጠጋበት ዐለቴ፣
ጋሻዬና የድነቴ ቀንድ[መ] ነው።
እርሱም ጠንካራ ምሽጌ፣ መጠጊያና አዳኜ ነው፤
ከኀይለኞች ሰዎች ታድነኛለህ።
4ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን
እጠራለሁ፤
ከጠላቶቼም እድናለሁ።
5“የሞት ማዕበል ከበበኝ፤
የጥፋትም ጐርፍ አሰጠመኝ።

21፥14 ኢሱ7፥26፤ 18፥28፤2ሳሙ24፥25፤ 1ዜና8፥34
21፥15 2ሳሙ5፥25
21፥17 2ሳሙ18፥3፤ 20፥6፤1ነገ11፥36፤15፥4፤2ነገ8፥19፤2ዜና21፥7፤ መዝ132፥17
21፥18 1ዜና11፥29፤ 27፥11
21፥19 1ሳሙ17፥4፡
21፥21 1ሳሙ16፥9፤ 17፥10
22፥1 ዘፀ15፥1
22፥2 1ሳሙ2፥2፤ መዝ31፥3፤91፥2፤ መዝ144፥2
22፥3 ዘፍ15፥1፤ ዘዳ23፥15፤32፥37፤ 33፥17፤መዝ9፥9፤14፥6፤ 31፥2፤52፥7፤59፥16፤ 71፥7፤91፥2፤94፥22፤ ምሳ10፥29፤ኢሳ25፥4፤ ኤር16፥19፤ኢል3፥16፤ ሉቃ1፥69
22፥4 መዝ48፥1፤ 96፥4፤145፥3
22፥5 መዝ69፥14-15፤ ዮና2፥3

[ሀ]16 3.5 ኪሎ ግራም ያህል ነው።
[ለ]19 ወይም፣ የሽማኔው የይዒር ልጅ
[ሐ]19 ዕብራይስጡና የሰብዓ ሊቃናት ትርጒሞች ከዚህ ጋር ይስማ ማሉ፤ ነገር ግን 1ዜና 20፥5 ላይ ያለው ከዚህ የተለየ ነው።
[መ]3 ቀንድ የጥንካሬ ወይም የኀይል ምልክት ነው።

21፥15-22፤ ፍልስጥኤማውያንን የሚመለከቱ እነዚህ አራት የታሪክ ክፍሎች በማንኛውም ማረጋገጫ በጊዜ ቅደም ተከተል መሠረት ሊቀመጡ የሚችሉ አይደሉም (የ21፥1-24:25 ማብ ይመ)። እያንዳንዱ ታሪክ የራፋይም ልጆች የተገደሉበት (ቍ 16:18:20 ይመ) ከዳዊት ታላላቅ የጦር አለቆች መካከል በአንዱ የተፈጸመ የጀብዱ ሥራ ይገኝበታል።

21፥16 *ከራፋይም፤* በዚህ ክፍል “የራፋይምን ልጆች” (ቍ 22) አራቱ አይበገሬ የጠላት ተዋጊዎች ብሎ በመጥራት ጸሓፊው በዘዳ 2፥10-11፤20፥21 ላይ ከተጠቀሱት ጋር አንድ ያደርጋቸዋል። ከዚህም የተነሣ ከዔናቅ ልጆች ጋር ዝምድና ሳይኖራቸው አይቀርም (ኢሱ 11፥21-22 ይመ)። በውጊያ ታሪኮች ውስጥ ጐልተው የሚታዩት ዔናቃውያን ቢሆኑም እንኳ (ዘኍ 13፥22:28:33፤ ዘዳ 1፥28፤ 9፥2፤ ከኢሱ 14፥12:15፤ ከመሳ 1፥20)፣ ከዐሥሩ የከነዓን ሰዎች ዝርዝር ውስጥ ዔናቃውያን ሳይሆኑ፤ የራፋይም ልጆች የተጠቀሱበትን ዘፍ 15፥19-20 ከዚህ ጋር ማነጻጸሩ አስፈላጊ ነው።

21፥17 *አቢሳ፤* የ1ሳሙ 26፥6 ማብ ይመ። *የእስራኤል መብራት እንዳይጠፋ፤* የእስራኤል ሕዝብ ለሕልውናውና ለደኅንነቱ መጠበቅ አሁንም በዳዊት ላይ የሚደገፍና የሚተማመን መሆኑን የሚገልጽ ማራኪ የሆነ ዘይቤያዊ አነጋገር ነው (22፥29፤ 23፥3-4፤ 1ነገ 11፥26 ይመ)።

21፥18 *ጎብ፤* ምናልባት በ1ዜና 20፥4 ላይ ይህ ተመሳሳይ ጦርነት እንደ ተካሄደበት በተጠቀሰው በጌዝር አጠገብ የምትገኝ ሳትሆን አትቀርም። *ሳፍ፤* በ1ዜና 20፥4 ላይ ሲፋይ ተብሎአል።

21፥19 *ኤልያናን…፣ ጎልያድን ገድሎ፤* የዚህን ክፍል ማብ ይመ። በ1ሳሙ 17 መሠረት ጎልያድን የገደለው ዳዊት መሆኑ ግልጽ ስለ ሆነ፣ “የጎልያድ ወንድም ለሕሚ” (1ዜና 20፥5 ይመ) የሚለውን ሐረግ በትክክል ካለማንበብ የተነሣ በመጀመሪያ ጽሑፉ ሲገለበጥ የተፈጠረ ስሕተት ሳይሆን አይቀርም።

21፥21 *በተገዳደረ፤* ጎልያድ በእስራኤል ላይ እንደ ተገዳደረ ማለት ነው (1ሳሙ 17፥10:25 ይመ)። *የሣማ፤* (1ሳሙ 16፥9፤ 17፥13 ይመ)።

22፥1 *የዚህን መዝሙር፤* በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ መዝ 18 በመባል ተጽፎ ይገኛል (የመዝ 18 ማብ ይመ)። ይህ መዝሙር ከመግቢያውና (ቍ 2-4) ከመደምደሚያው (ቍ 47-51) ሌላ ሦስት ዐበይት ክፍሎችን አካቶ ይዞአል፤ የመጀመሪያው ክፍል ዳዊት ከጠላቶቹ እጅ ከሞት እንዴት እንዳመለጠ የሚገልጽ ሲሆን (ቍ 5-20)፣ ሁለተኛው እግዚአብሔር የሚታደግበትን ግብረ ገባዊ ምክንያት ያሳያል (ቍ 21-30)፤ ሦስተኛው ደግሞ እግዚአብሔር ያደረገለትን ምሕረት ያስታውሳል (ቍ 31-46)። ይህ መዝሙር ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር በዝሙት ኀጢአት ከመውደቁ በፊት (ቍ 21-25 ከ1ነገ 15፥5 ጋር ያነጻጽሩ) በባዕዳን ጠላቶቹ ላይ ድል እንደ ተቀዳጀ ወዲያውኑ የተጻፈ መዝሙር ነው (8፥1-14) *ከጠላቶቹ ሁሉና፤* 8፥1-14 ይመ። *ከሳኦልም፤* 1ሳሙ 18፥31 ይመ።

22፥2 *ዐለቴ፤* የዳዊትን ተመክሮ የሚያሳይ ትክክለኛ ተምሳሌት ነው (ቍ 32:47፤ 23፥3፤ ዘዳ 32፥4:15:18:31፤ መዝ 28፥1፤ 31፥2፤ 61፥2፤ 78፥35፤ 89፥36፤ 94፥22፤ 95፥1 ይመ)። ዳዊት ከጠላቶቹ ጥቃት ለመከላከል ራሱን በምድረ በዳ ቋጥኞች መካከል ብዙ ጊዜ ይሸሽግ ነበር (1ሳሙ 23፥25፤ 24፥2)። እውነተኛው የደኅንነት ዋስትና እውን የሚሆነው ግን በጌታ ብቻ እንደ ሆነ ዳዊት አስተውሎአል። *ዐምባዬ፤* ቃሉ በዕብራይስጥ ዳዊት የተሸሸገባቸውን ዐለቶች ያመለክታል (በ5፥17፤23፥14፤ 1ሳሙ 22፥4-5፤ 24፥22 ላይ ይመ)።

22፥3 *ጋሻዬና፤* 31:36፤ ዘፍ 15፥1፤ ዘዳ 33፥29፤ ኤር 48፥25 ይመ። *የድነቴ ቀንድ፤* ሥልጣንን ወይም ኀይልን ያመለክታል የዚህን ክፍል ማብ እንዲሁም ዘዳ 33፥17፤ ኤር 48፥25፤ ሉቃ 1፥69 ይመ)። ተምሳሌታዊ አገላለጹ ቀንዳቸው ለጥበቃና ለመከላከል ከሚጠቅም እንስሳት የተወሰደ ነው።

22፥5 *የሞት ማዕበል፤* በቍ 5-6 ላይ ዳዊት ተመክሮውን መሠረት በማድረግ ለሞት የሚዳርጉትን አደጋዎች በቅኔ ተምሳሌት ይገልጻቸዋል።

6የሲኦል ገመድ ተጠመጠመብኝ፤
የሞትም ወጥመድ ተጋረጠብኝ።
7በጨነቀኝ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት፤
ወደ አምላኬም ጮኽሁ።
እርሱም ከመቅደሱ ድምፄን ሰማ፤
ጩኸቴም ከጆሮው ደረሰ።

8“ምድር ተንቀጠቀጠች፤ ተናወጠችም፤
የሰማያትም መሠረቶች[ሀ] ተናጉ፤
እርሱ ተቈጥቶአልና ራዱ።
9ከአፍንጫው የቍጣ ጢስ ወጣ፤
ከአፉ የሚባላ እሳት ነደደ፤
ከውስጡም ፍሙ ጋለ።
10ሰማያትን ሰንጥቆ ወረደ፤
ከእግሩም በታች ጥቅጥቅ ያለ ደመና
ነበረ።
11በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በረረ፤
በነፋስም ክንፍ መጠቀ።[ለ]
12ጨለማው በዙሪያው እንዲከበው፣
ጥቅጥቅ ያለውም የሰማይ ዝናም ደመና
እንዲሰውረው አደረገ።
13በእርሱ ፊት ካለው ብርሃን፣
የመብረቅ ብልጭታ ወጣ።
14እግዚአብሔር ከሰማያት አንጐደጐደ፤
የልዑልም ድምፅ አስተጋባ።
15ፍላጻውን ሰድዶ ጠላቶቹን በተናቸው፤
መብረቆቹንም ልኮ አወካቸው።
16ከእግዚአብሔር ተግሣጽ፣ ከአፍንጫው
ከሚወጣው፣ ከእስትንፋሱ ቍጣ የተነሣ፣
የባሕር ሸለቆዎች ታዩ፤ የምድር
መሠረቶችም ተገለጡ።

17“ከላይ እጁን ዘርግቶ ያዘኝ፤
ከጥልቅ ውሆችም ውስጥ አወጣኝ።
18ከብርቱ ጠላቶቼ፣
ከማልቋቋማቸውም ባላጋሮቼ ታደገኝ።
19በመከራዬ ቀን መጡብኝ፤
እግዚአብሔር ግን ደገፈኝ።
20ሰፊ ወደ ሆነ ስፍራ አወጣኝ፤
በእኔ ደስ ስለ ተሰኘም አዳነኝ።

21“እግዚአብሔር እንደ ጽድቄ መለሰልኝ፤
እንደ እጄም ንጹሕነት ብድራትን ከፈለኝ፤
22የእግዚአብሔርን መንገድ ጠብቄአለሁና፤
ከአምላኬም ዘወር ብዬ ክፉ ነገር
አላደረግሁም።
23ሕጉ ሁሉ በፊቴ ነው፤
ከሥርዐቱም ዘወር አላልሁም።
24በፊቱ ያለ ነውር ነበርሁ፤
ራሴንም ከኀጢአት ጠብቄአለሁ።
25እግዚአብሔር እንደ ጽድቄ፣
በፊቱም እንዳለኝ ንጽሕና[ሐ] ብድራትን
ከፈለኝ።

26“ለታማኝ ሰው አንተም ታማኝ መሆንህን፣
ለቅን ሰው አንተም ቅን መሆንህን
ታሳያለህ።
27ለንጹሕ ሰው አንተም ንጹሕ መሆንህን፣
ለጠማማ ሰው ግን አንተም ጠማማ
መሆንህን ታሳያለህ።
28አንተ የተጠቃውን ሕዝብ ታድናለህ፤
ዐይንህ ግን ያዋርዳቸው ዘንድ፣
ትዕቢተኞችን ይመለከታል።
29እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ መብራቴ ነህ፤
እግዚአብሔርም ጨለማዬን ያበራል።

22፥6 መዝ116፥3፤ ሐሥ2፥24
22፥7 ዘፍ35፥3፤ መሳ2፥15፤2ዜና15፥4፤መዝ4፥1፤34፥6፤15፤77፥2፤116፥4፤120፥1፤ኢሳ26፥16
22፥8 ዘፀ19፥18፤ መሳ5፥4፤ኢዮ9፥6፤26፥11፤መዝ68፥8፤75፥3፤77፥18፤97፥4፤ኤር10፥10
22፥9 መዝ50፥3፤97፥3፤ኢሳ6፥6፤ሕዝ1፥13፤10፥2፤ዕብ12፥29፤ራእ11፥5
22፥10 ዘፀ19፥9፤ ዘሌ16፥2፤ዘዳ33፥26፤1ነገ8፥12፤ኢዮ26፥9፤መዝ104፥3፤ኢሳ19፥1፤ኤር4፥13፤ናሆ1፥3
22፥11 ዘፍ3፥24፤ ዘፀ25፥22፤መዝ104፥3
22፥12 ዘፀ19፥9
22፥13 ኢዮ37፥3፤ መዝ77፥18
22፥14 1ሳሙ2፥10
22፥15 ዘዳ32፥23
22፥16 ዘፀ14፥21፤ መዝ6፥1፤50፥8፤21፤106፥9፤ኢሳ30፥33፤40፥24፤ናሆ1፥4
22፥17 ዘፀ2፥10፤ መዝ144፥7
22፥18 ሉቃ1፥71
22፥19 መዝ23፥4
22፥20 2ሳሙ15፥26፤ኢዮ36፥16፤መዝ22፥8፤31፥8፤118፥5፤ኢሳ42፥1፤ማቴ12፥18
22፥21 1ሳሙ26፥23፤ኢዮ17፥9፤22፥30፤42፥7-8፤መዝ24፥4፤26፥6
22፥22 ዘፍ18፥19፤ መዝ128፥1፤ምሳ8፥32
22፥23 ዘዳ6፥4-9፤ መዝ119፥30-32፤102
22፥24 ዘፍ6፥9፤ኤፌ1፥4 22፥25 1ሳሙ 26፥23 22፥27 ዘሌ 26፥23-24፤ማቴ5፥8 22፥28 ዘፀ3፥8፤1ሳሙ2፥8-9፤መዝ72፥12-13፤131፥1፤ምሳ30፥13፤ኢሳ2፥12፡17፤5፥15፤ዳን4፥31፤ሶፎ3፥11፤ሉቃ1፥51 22፥29 መዝ27፥1፤ኢሳ2፥5፤ሚክ7፥8፤ራእ21፥23፤22፥5

[ሀ]8 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ቩልጌትና ሱርስቱ ግን (እንዲሁም መዝ 18፥7 ይመ) *ተራሮች* ይላሉ።
[ለ]11 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች (እንዲሁም መዝ 18፥10 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ እጅግ ብዙ የሆኑ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን፣ *ተገለጠ* ይላሉ።
[ሐ]25 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናትና የቩልጊት ትርጒሞች (እንዲሁም መዝ 18፥24 ይመ) ግን፣ *እንደ እጄም ንጽሕ* ይላሉ።

22፥6 *የሲኦል፤* የዮና 2፥2 ማብ ይመ።

22፥7 *ከመቅደሱ፤* እግዚአብሔር (ያህዌ) በዙፋኑ የተቀመጠባትን መንግሥተ ሰማይን ያመለክታል (መዝ 11፥4፤ ኢሳ 6፥1፤ ዮና 2፥7 ይመ)።

*22፥8-16፤* የመዝ 18፥7-15 ማብ ይመ።

22፥9 *ከአፍንጫው የቍጣ ጢስ ወጣ፤* የእግዚአብሔር ኀይል ሌዋታን በመባል ከሚታወቀው እጅግ አስፈሪ የባሕር አውሬ ጋር ተነጻጽሮአል (ኢዮ 41፥19-21)።

22፥11 *በኪሩቤል፤* ኪሩቤል “የእግዚአብሔር ዙፋን ተሸካሚዎች” ተብለዋል፤ ሕዝ 1 እና 10 ይመ፤ እንዲሁም የዘፍ 3፥24፤ የ1ሳሙ 4፥4፤ የሕዝ 1፥5 ማብ ይመ።

22፥14 *እግዚአብሔር... አንጐደጐደ፤* በብሉይ ኪዳን ነጐድጓድን እንደ እግዚአብሔር ድምፅ አድርጎ ማሳየት የተለመደ ነው (መዝ 29፤ ኢዮ 37፥2-5 ይመ)። በተለይ የእግዚአብሔርን ኀይልና ክብር ለመግለጥ ነጐድጓድ ተገቢ የሆነ ቃል ነው።

22፥17 *ከላይ እጁን ዘርግቶ፤* ዳዊት የተደረገለትን ትድግና በቍ 17-20 ላይ መጀመሪያው በዘይቤያዊው አነጋገር (ቍ 17 ይመ፤ ከቍ 5 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ይበልጥ ቀጥተኛ በሆነ ቋንቋ ይገልጠዋል (18፥20)።

22፥20 *ደስ ስለ ተሰኘም፤* በዚህ አገላለጥ ላይ የተመሠረተ የዕብራይስጥ ቃል ተገልጦ የምናገኘው በ15፥26፤ በመዝ 22፥8 ላይ ነው (ከማቴ 3፥17 ጋር ያነጻጽሩ)። ቃሉ እግዚአብሔር በቀባው ንጉሥ ላይ ያለውን ቋሚያዊ ደስታና የማይለወጥ የፍቅር ሐሳብ ያመለክታል (ቍ 51)።

22፥21 *እንደ ጽድቄ፤* ዳዊት በቍ 21-25 ላይ እግዚአብሔር የታደገው ከራሱ የጽድቅ ሥራ የተነሣ መሆኑን ይገልጣል። እነዚህ ዐረፍተ ነገሮች በራስ የጽድቅ ሥራ የመመካትንና የእግዚአብሔርን በጎነትና ምሕረት በሥራ የማግኘትን ዝንባሌ የሚያሳድሩ ቢመስሉም እንኳ በዐውደ ምንባቡ መሠረት ማለትም፦ 1) ዳዊት በእግዚአብሔር የተቀባ ንጉሥ እንደ መሆኑ፣ በአገልግሎቱ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ታላቅ ፍላጎት ያለው ከመሆኑና 2) ቢታማኝነት ሊያገለግሉ የሚፈልጉትን ሁሉ የሚታደግና የሚባርክ አምላክ መሆኑን ዳዊት ከመገንዘቡ አንጻር ሊስተዋሉ ይገባል።

22፥22 *የእግዚአብሔርን መንገድ ጠብቄአለሁና፤* ዳዊት በእምነት ዘወትር ልቡን ወደ እግዚአብሔር በመመለስ እስከዚህ ጊዜ ድረስ እግዚአብሔርን ለማስደሰት የነበረውን ፍላጎት መግለጡ እንጂ፤ ኀጢአት ሠርቶ እንደማያውቅ ወይም ፍጹም ሰው እንደ ሆነ መናገሩ አይደለም። መዝሙሩ የተጻፈው ምናልባት እግዚአብሔር ከሳኦል እጅ ካዳነው በኋላ ወዲያውኑ ሲሆን (2፥4፤ 1ሳሙ 31፥6)፣ እንደዚሁም በዝሙትና በነፍስ ግድያ ኀጢአት ከመውደቁ በፊት ሊሆን ይችላል (11፥1-12፥15)።

*22፥26-30፤* እግዚአብሔር ለሰው ችግር በቸርነቱ የሚደርስ አምላክ ስለ ሆነ ነው (ኢዮ 24፥11፤ ምሳ 3፥34 ይመ)፤ ዳዊት በግል ሕይወቱ የእግዚአብሔርን ቸርነት ተለማምዶአል።

22፥28 *ያዋርዳቸውም ዘንድ ትዕቢተኞችን፤* በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተካተቱት ቃላት ከሳኦል ጋር ካጋጠመው ችግር የተነሣ ካሳለፈው ተሞክሮ ጋር በሚገባ ይስማማል (በ1 ሳሙ 2፥3-8 የሐናን መዝሙር ይመ)።

22፥29 *አንተ መብራቴ ነህ፤* እግዚአብሔር (ያህዌ) የዳዊት ሕይወትና ሥራ እየደረጀ እንዲሄድ አደረገ (ኢዮ 18፥5-6፤ 21፥17፤ እንዲሁም የመዝ 27፥1 ማብ ይመ)።

[30]በአንተ ርዳታ በጠላት ሰራዊት ላይ ወደ
ፊት ገፍቼ እሄዳለሁ[ሰ]፤
በአምላኬም ኀይል ቅጥሩን እዘላለሁ።
[31]"የአምላክ *መንገዱ ፍጹም ነው፤*
*የእግዚአብሔርም ቃል የነጠረ ነው፤*
*ለሚታመኑበትም ሁሉ ጋሻ ነው፤*
[32]*ከእግዚአብሔር* በቀር አምላክ ማን አለና፤
ከአምላካችንስ በቀር ዐለት ማን ነው?
[33]ኀይልን የሚያስታጥቀኝ[ሸ]፣
*መንገዴንም* የሚያቀና እርሱ አምላኬ ነው።
[34]እግሮቼን እንደ ብሆር እግር ያበረታል፤
በከፍታዎችም ላይ አጽንቶ ያቆመኛል።
[35]እጆቼን ለጦርነት ያሰለጥናል፤
ክንዶቼም የናስ ቀስት ይገትራሉ።
[36]የማዳንህን ጋሻ ሰጥተኸኛል፤
ድጋፍህ ታላቅ አድርጎኛል።
[37]እርምጃዬን አሰፋህ፤
እግሮቼም አልተሰነካከሉም።
[38]"ጠላቶቼን አሳደድሁ፤ አጠፋኋቸውም፤
እስኪደመሰሱም ድረስ ወደ ኋላ
አልተመለስሁም።
[39]ፈጽሜ አጠፋኋቸው፤ ተመልሰውም
መቆም አልቻሉም፤
ከእግሬም ሥር ወድቀዋል።
[40]ለጦርነት ኀይልን አስታጠቅኸኝ፣
ተቃዋሚዎቼንም ከእግሬ ሥር
አንበረከካቸው።
[41]ጠላቶቼ ፊታቸውን አዙረው እንዲሸሹ
አደረግሃቸው።
ባላንጣዎቼንም ደመሰስኋቸው።
[42]ለርዳታ ጮኹ፤ ያዳናቸው ግን አልነበረም፤
ወደ *እግዚአብሔር* ጮኹ፤ እርሱ ግን
አልመለሰላቸውም።
[43]በምድር ላይ እንዳለ ትቢያ አድቅቄ
ፈጨኋቸው፤
በመንገድም ላይ እንዳለ ጭቃ
ወቀጥኋቸው፤ ረገጥኋቸውም።
[44]"በሕዝቤ ከተቃጣብኝ አደጋ አዳንኸኝ፤
የመንግሥታትም ራስ አደረግኸኝ።
የማላውቀው ሕዝብ ተገዛልኝ፤

22፥31 ዘዳ15፥1፤ ዘዳ32፥4፤መዝ12፥6፤1 19፥140፤ምሳ30፥5-6፤ ማቴ5፥48
22፥32 1ሳሙ2፥2፤ 2ሳሙ7፥22
22፥34 ዘዳ32፥13፤ ኢሳ35፥6፤ዕን3፥19
22፥35 መዝ7፥12፤ 11፥2፤144፥1፤ዘካ9፥13
22፥36 ኤፌ6፥16
22፥37ምሳ4፥11
22፥39 መዝ44፥5፤ 110፥6፤ሚል4፥3
22፥40 ኢሱ10፥24፤ 1ነገ5፥3
22፥41 ዘፀ23፥27
22፥42 1ሳሙ 14፥37፤መዝ50፥22፤ ኢሳ1፥15
22፥43 1ነገ20፥10፤ 2ነገ13፥7፤መዝ7፥5፤ ኢሳ5፥25፤10፥6፤22፥ 5፤41፥2፡25፤አሞ1፥3 1ሚክ7፥10፤ዘካ7፥10
22፥44 ዘፀ11፥3፤ዘዳ 28፥13፤2ሳሙ3፥1፤ 8፥1-14፤ኢሳ55፥3-5
22፥45 ዘዳ33፥29፤ መዝ66፥3፤81፥15
22፥46 ሚክ7፥17
22፥47 ዘፀ15፥2፤ዘዳ 32፥15፤መዝ18፥31፤ 89፥26፤95፥1
22፥48 ዘኍ31፥3፤ መዝ144፥2
22፥49 መዝ27፥6፤ 140፥1
22፥50 መዝ9፥11፤ 47፥6፤68፥4፤ሮሜ15፥9
22፥51 1ሳሙ16፥ 13፤2ሳሙ7፥13፤መዝ 21፥1፤መዝ89፥20፡24 ፡29፤144፥9-10፤ሐሥ 13፥23
23፥1 ዘፀ11፥3፤ 1ሳሙ2፥10፡35፤መዝ 18፥50፤20፥6፤78፥70- 71፤84፥9፤ኢሳ45፥1 ፤ዕን3፥13
23፥2 ማቴ22፥43፤ ማር12፥36፤2ጴጥ1፥21
23፥3 ዘፍ42፥18፤ ዘዳ32፥4፤1ሳሙ2፥2፤ መዝ18፥31፤72፥3፤ ኢሳ11፥1-5

[45]ባዕዳን ሊለማመጡኝ መጡ፤
እንደ ሰሙኝም ወዲያውኑ ይታዘዙኛል።
[46]ባዕዳን ፈሩ፤
ከምሽጋቸውም እየተንቀጠቀጡ ወጡ[ቀ]።
[47]"*እግዚአብሔር ሕያው ነው፤* ዐለቴ
የተባረከ ይሁን፤
የድነቴ ዐለት አምላኬ ከፍ ከፍ ይበል።
[48]የሚበቀልልኝ አምላክ፣
*መንግሥታትንም* ከሥሬ የሚያስገዛልኝ
እርሱ ነው፤
[49]እርሱ ከጠላቶቼ እጅ ነጻ ያወጣኛል።
አንተ ከጠላቶቼ በላይ ከፍ ከፍ አደረግኸኝ፤
ከጨካኝ ሰዎችም እጅ ታደግኸኝ።
[50]ስለዚህ *እግዚአብሔር ሆይ፤*
*በመንግሥታት መካከል አመሰግንሃለሁ፤*
ለስምህም ምስጋና እዘምራለሁ።
[51]ለንጉሡ ታላቅ ድል ይሰጠዋል፤
ለቀባው ለዳዊትና ለዘሩ፣
ለዘላለም የማይለወጥ ፍቅሩን ያሳየዋል።"

## የዳዊት የመጨረሻ ቃል

**23** የዳዊት የመጨረሻ ቃሉ ይህ ነው፤
"በያዕቆብ አምላክ የተቀባው፣
ልዑል ከፍ ከፍ ያደረገው ሰው፣
የእስራኤል ተወዳጅ ዘማሪ፣
የእሴይ ልጅ የዳዊት የትንቢት
ቃል ይህ ነው፤
[2]"*የእግዚአብሔር መንፈስ* በእኔ ተናገረ፤
*ቃሉ* በአንደበቴ ላይ ነበረ።
[3]የእስራኤል አምላክ ተናገረ፤
የእስራኤልም ዐለት እንዲህ አለኝ፤
ሰዎችን በጽድቅ የሚገዛ፣
በፈሪሀ *እግዚአብሔርም* የሚያስተዳድር፣
[4]እርሱ፣ ደመና በሌለበት፣
በማለዳ ፀሓይ በምትወጣበት ጊዜ፣
እንዳለው ብርሃን ነው፤

[ሰ]30 ወይም *በጋሬጣዎች ውስጥ እሮጣለሁ*
[ሸ]33 የሙት ባሕር ጥቅል፣ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞች፣ የቩልጌትና የሱርስት ቅጆች (እንዲሁም መዝ 18፥32 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ የማሶሬቱ ቅጅ ግን፣ *ጠንካራ መጠጊያ የሚሆነኝ* ይላል።
[ቀ]46 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጉሞችና የቩልጌቱ ቅጅ (እንዲሁም መዝ 18፥32 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ማሶሬቱ ግን *ራሳቸውን ጎዱ* ይላል።

22፥31 ***መንገዱ ፍጹም ነው፤*** ከቍ 31-51 ያለው የዚህ መዝሙር ሐሳብ፣ ዳዊት እግዚአብሔር ላደረገለት ትድግና ያቀረበውን ምስጋና አጕልቶ ያሳያል።

22፥32 ***ዐለት፤*** የቍ 2 ማብ ይመ።

22፥47 ***እግዚአብሔር ሕያው ነው፤*** እግዚአብሔር በዳዊት ሕይወት ጣልቃ መግባቱና በዚህም የተገኙት በረከቶቹ ሁሉ፣ እግዚአብሔር ሕያው አምላክ መሆኑን ለዳዊት ገልጸውለታል (ዘዳ 5፥26 ይመ)።

22፥50 ***እግዚአብሔር ሆይ፤ በመንግሥታት መካከል አመሰግንሃለሁ፤*** ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ቃል በተመለከተ የጻፈውን በሮሜ 15፥9 ላይ ይመ።

22፥51 ***ለንጉሡ... ለቀባው፤*** የ1ሳሙ 10፥25፤ 12፥14-15 ማብ ይመ። ዳዊት የንጉሥነቱን ኪዳናዊ ባሕርይ በሚያስገነዝብ መልክ በሦስተኛ ምድብ ተውላጠ ስም ስለ ራሱ ይናገራል። ጠቅላላ መዝሙሩ መነብብና ግንዛቤ ማግኘት ያለበት (የቍ 21 ማብ ይመ)፣ ዳዊት በእግዚአብሔር የተቀባ ንጉሥ እንደ መሆኑ፣ ካለው የኀላፊነት ችሎታ አንጻር ነው። ***ለዘሩ፣ ለዘላለም፤*** ዳዊት በናታን አማካይነት ወደ እርሱ ስላመጣው የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ይናገራል (7፥12-16 ይመ)።

23፥1 ***የዳዊት የመጨረሻ ቃሉ፤*** ይህ በግጥም መልክ (በመዝሙር አጻጻፍ መንገድ) የቀረበ መጨረሻው የዳዊት ምስክርነት መሆኑ መታወቅ ያለበት ይመስላል፤ የተጻፈውም ምናልባት ዳዊት ለልጁ ለሰሎሞን የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ በሰጠበት ወቅት ሳይሆን አይቀርም (1ነገ 2፥1-10 ይመ)።

23፥2 ***የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ፤*** ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይናገር ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ በእርሱ ውስጥ በመሥራት እንደረዳው ዳዊት ራሱ ተገንዝቦአል (የ2ጢሞ 3፥16፤ 2ጴጥ 1፥21 ማብ ይመ)።

23፥3 ***ዐለት፤*** የ22፥2 ማብ፤ እንዲሁም 1ሳሙ 2፥2፤ ዘዳ 32፥4፡ 15፡18፡30-31 ይመ። ***በጽድቅ የሚገዛ፣ በፈሪሀ እግዚአብሔርም የሚያስተዳድር፣*** በታላቁ የዳዊት ልጅ በኢየሱስ በክርስቶስ አገዛዝ ወቅት ብቻ በተሟላ ሁኔታ የሚፈጸመውን መለኮታዊውን ንጉሣዊ አስተዳደር ዳዊት አጭርና ግልጥ በሆነ አነጋገር ይገልጠዋል። ይህ ትንቢታዊ ቃል በ7፥12-16 ላይ የተመለከተውን ሐሳብ የሚያሟላ ሲሆን፣ በኢሳ 9፥7፤ 11፥1-5፤ በኤር 23፥5-6፤ 33፥15-16፤ በዘካ 9፥9 ላይ የተገለጠውንም ሐሳብ አስቀድሞ ያሳያል።

23፥4 ***በማለዳ ፀሓይ... እንዳለው፤*** የመዝ 27፥1፤ 36፥9 ማብ ይመ።

በምድር ላይ ሣርን እንደሚያበቅለው፣
ከዝናብም በኋላ እንዳለው የብርሃን ጸዳል
ነው::'

5"የእኔስ ቤት *በእግዚአብሔር* ዘንድ ትክክል
አይደለምን?
ሁሉንም ነገር አዘጋጅቶና ጠብቆ፣
ከእኔ ጋር ዘላለማዊ ኪዳን ያደረገ አይደለምን?
ድነቴን ከፍጻሜ የሚያደርሰው፣
መሻቴን ሁሉ የሚሰጠኝ እርሱ
አይደለምን?
6ነገር ግን ክፉ ሰዎች ሁሉ፣
በእጅ እንደማይሰበሰብ እንደ እሾኽ
ይጣላሉ::
7እሾኽ የሚነካ ሁሉ፣
የብረት መሣሪያ ወይም የጦር ዘንግ
ይይዛል፤
ባሉበትም ቦታ ፈጽመው በእሳት
ይቃጠላሉ::

### የኀያላኑ የዳዊት ሰዎች ጀብዱ

23፥8-39 ተጓ ምብ - 1ዜና 11፥10-41

8የዳዊት ኀያላን ሰዎች ስም የሚከተለው
ነው፤ የታሕክሞን[መ] ሰው ዮሴብ በሴትቤት[ሠ]
የሦስቱ አለቆች አለቃ ሲሆን፣ እርሱም
ጦሩን ሰብቆ በአንድ ውጊያ ላይ ስምንት
መቶ ሰው የገደለ ነው::[ረ]
9ከእርሱ ቀጥሎ የአሆሃዊው የዱዲ ልጅ
ኤልዔዘር ነበረ፤ እርሱም ለጦርነት አንድ
ላይ ተሰብስበው[ሰ] የነበሩትን ፍልስጥኤማው
ያንን በተገዳደሩ ጊዜ፣ ከዳዊት ጋር ከነበሩት
ከሦስቱ ኀያላን ሰዎች አንዱ ነበር። ከዚያም
የእስራኤል ሰዎች ሸሹ:: 10እርሱ ግን የቆ
መበትን ስፍራ አለቀቀም፤ እጁ እስኪዝልና
ከሰይፉ ጋር እስኪጣበቅ ድረስ ፍልስጥኤማ
ውያንን ወጋ፤ በዚያችም ዕለት *እግዚአብሔር*
ታላቅ ድልን ሰጠ:: የሸሸውም ሰራዊት ወደ
ኤልዔዘር የተመለሰው የተገደሉትን ሰዎች
ለመግፈፍ ብቻ ነበር::
11ከእርሱም ቀጥሎ የአሮዳዊው የአጌ ልጅ
ሣማ ነበር፤ ፍልስጥኤማውያንም ሌሒ በተ
ባለ ስፍራ ምስር በሞላበት አንድ ዕርሻ ላይ፣
በአንድነት ተሰብስበው ሳሉ፣ የእስራኤል ሰራ
ዊት ከፍልስጥኤማውያን ፊት ሸሹ፤ 12ሣማ
ግን የቆመበትን ስፍራ አለቀቀም፤ ጦርነቱ
ንም ተቋቁሞ ፍልስጥኤማውያንን ገደለ፤ በዚ
ያችም ዕለት *እግዚአብሔር* ታላቅ ድል ሰጠ::
13በመከር ወራት፣ የፍልስጥኤም ሰራዊት
በራፋይም ሸለቆ ሰፍሮ ሳለ፣ ከሠላሳዎቹ አለ
ቆች ሦስቱ ዳዊት ወዳለበት ወደ ዓዶላም
ዋሻ መጡ:: 14በዚያም ጊዜ ዳዊት በምሽግ
ውስጥ ነበረ፤ የፍልስጥኤማውያንም ሰራዊት
በቤተልሔም ነበረ፤ 15ዳዊትም በናፍቆት፣
"በቤተልሔም በር አጠገብ ካለችው ጉድ
ጓድ ውሃ ማን ባመጣልኝ!" አለ:: 16ስለዚህ
ሦስቱ ኀያላን በፍልስጥኤማውያን ሰራዊት
መካከል ሰንጥቀው በማለፍ፣ በቤተልሔም
በር አጠገብ ካለችው ጉድጓድ ውሃ ቀድ
ተው ለዳዊት አመጡለት። እርሱ ግን አልጠ
ጣውም፤ ይልቁን *በእግዚአብሔር* ፊት መሥ
ዋዕት አድርጎ አፈሰሰው፤ 17"እርሱም፣ *እግ
ዚአብሔር* ሆይ፤ እንዲህ ያለውን ነገር ላደ
ርግ? ይህስ ከእኔ ይራቅ! ይህ በነፍሳቸው
ቈርጠው የሄዱ ሰዎች ደም አይደለምን?"
አለ፤ ዳዊትም ሊጠጣው አልፈለገም:: እንግ
ዲህ ሦስቱ ኀያላን ሰዎች ያደረጉት ጀብዱ
እንዲህ ነበር::
18የጽሩያ ልጅ የኢዮአብ ወንድም አቢሳ
የሦስቱ[ሸ] ኀያላን አለቃ ነበረ:: በሦስት መቶ
ሰዎች ላይ ጦሩን ሰብቆ የገደላቸውና እንደ
ሦስቱ ኀያላን ሁሉ እርሱም ዝናን ያተረፈ
ሰው ነበረ:: 19አቢሳ ከሦስቱ ይልቅ እጅግ
የከበረ አልነበረምን? ከእነርሱ እንደ አንዱ
ባይሆንም አለቃቸው ነበረ::

23፥4 ዘዳ32፥2፤ መሳ5፥31፤መዝ 119፥147፤130፥6፤ ምሳ4፥18፤ ማቴ13፥43፤ዮሐ1፥5
23፥5 ዘፍ9፥16፤ መዝ89፥29
23፥6 ኢሳ5፥6፤ 9፥18፤10፥17፤27፥4፤ 33፥12፤ሚክ7፥4፤ናሆ 1፥10፤ማቴ13፥40-41
23፥8 2ሳሙ17፥10፤ 1ዜና27፥2
23፥9 1ዜና8፥4፤ 27፥4
23፥13 ዘፍ38፥1፤ ኢሱ12፥15፤17፥15
23፥14 ሩት1፥19፤ 1ሳሙ22፥4-5፤ 2ሳሙ5፥17
23፥16 ዘፍ35፥14
23፥17 ዘሌ17፥10-12
23፥18 1ሳሙ26፥6

መ8 *የታሕክሞን ሰው ማለት ሐክሞናዊ* ማለት ሊሆን ይችላል:: (1ዜና 11፥11ይመ)::
ሠ8 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ግን፣ *ኢያሱስቴ* ይላሉ፣ ይኸውም፣ *ያሾብዓም* ነው (1ዜና 11፥11 ይመ)::
ረ8 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ከዚህ ጋር ይስማማሉ (1ዜና 11፥11 ይመ)፤ ዕብራይስጡና አብዛኞቹ የሰብዓ ሊቃናት ትር ጕሞች ግን *ስምንት መቶ ሰዎችን የገደለው አዜናዊው አዲኖ ነበር* ይላሉ:: ሰ9 1ዜና 11፥13 ይመ፤ ዕብራይስጡ ግን፣ *በዚያ ተሰብስበው* ይላል
ሸ18 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች (እንዲሁም 1ዜና 11፥20 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ሁለት የዕብራይስጥ ቅጆችና የሱርስቱ ትር ጕም፣ *ሠላሳ* ይላሉ::

23፥5 *የእኔስ ቤት በእግዚአብሔር ዘንድ ትክክል አይደለምን?* እግዚአብሔር ከዳዊት ጋር የገባውን ኪዳንና በእግዚአብሔር ፈቃድ የተመሠረተውን የዳዊትን መንግሥት የሚያስታውስ መልስ አዘል ጥያቄ ነው (7፥12-16 ይመ):: *ዘላለማዊ ኪዳን፤* ዳዊት እግዚ አብሔር ለእርሱ የገባለትን ኪዳን የማይሻር ኪዳን ብሎ በግልጥ ይጠ ራዋል (የ7፥20:28፤ የኢሳ 55፥3 ማብ፤ እንዲሁም መዝ 89፥3:28: 34:39፤ 132፥11 ማብ ይመ):: *ከፍጻሜ የሚያደርሰው፤* ይህ የሚሆ ነው ለዳዊት ተስፋ በተገባለት ልጆቹ አማካይነት ነው::

23፥6 *ክፉ ሰዎች... እንደ እሾኽ ይጣላሉ፤* ለጻድቁ ንጉሥ መገዛት የማይፈልጉ ኀጢአተኞች ይጠፋሉ (መዝ 2፥9፤ 110፥5-6 ይመ)::

23፥8-39፤ የ21፥1-24:25 ማብ ይመ፤ ይህ የ37ቱ (ቍ 39 ይመ) የዳዊት ኀያላን ተዋጊዎችና ከፊል የጀብዱ ሥራዎቻቸው ዝር ዝር በ1ዜና 11፥11-41 ላይ የተመዘገበ አቻ ሐሳብ አለው:: በሁለተኛ ዜና የተመለከተው ዝርዝር የ16 ስሞች ብልጫ አሳይቶአል (1ዜና 1፥41-47)::

23፥8 *የታሕክሞን፤* 1ዜና 11፥11 ላይ "የሐክሞናዊው" ይለዋል፤ (የዚህ ክፍል ማብ ይመ)፤ ከማይታወቅ የቦታ ስም የተ ገኘ ነው:: *የሦስቱ፤* ሦስት ሦስት ተዋጊዎች የሚገኙባቸው ሁለት ምድቦችና (ቍ 8፥12 እና 13፥23) 30 ተዋጊዎች ያሉበት አንድ ምድብ (ቍ 23-39) ተጠቅሰዋል (የተዋጊዎቹን ጠቅላላ ድምር ለማ የት የቍ 39 ማብ ይመ)::

23፥9 *የአሆሃዊው፤* ከብንያም ነገድ የተገኘ የአሖዋ ልጅ ነው (1ዜና 8፥4)::

23፥13 *በመከር ወራት፤* 11፥1 እና ማብ ይመ:: ዳዊት ከሳኦል ሸሽቶ ከሄደ በኋላ ወዲያውኑ፣ ሰዎች ዐላማውን በመደገፍ ወደ እርሱ መሰባሰብ በጀመሩበት ወቅት (1ሳሙ 22፥1-4 ይመ)፣ ወይም ኢየሩሳሌምን ተቈጣጥሮ ከያዘ በኋላ ብዙ ሳይቆይ (2ሳሙ 5፥17-18) እንደ ተፈጸመ ያመለክታል:: *ሦስቱ፤* ይህ አኃዝ በቍ 9 ላይ የተገለጹትን ሦስት ኀያላን ተዋጊዎች የሚያመለክት አይደለም:: *ከሠላሳዎቹ አለቆች፤* ቍ 23-24:39 ይመ:: *አዶላም ዋሻ፤* 1ሳሙ 22፥1 ይመ:: *በራፋይም፤* 5፥18 ይመ::

23፥14 *በምሽግ፤* የ1ሳሙ 22፥4 ማብ ይመ::

*23፥15-16፤* በ1ዜና 11፥15-19 ማብ ይመ::

23፥18 *አቢሳ፤* 10፥10:14፤ 18፥2፤ እንዲሁም የ1ሳሙ 26፥6 ማብ ይመ:: *የሦስቱ፤* ምናልባት በቍ 13-17 የተጠቀሱ ትን ሳያመለክት አይቀርም::

[20]የቀብጽኤል አገር ሰው የሆነው የዮዳሄ
ልጅ በናያስ ታላቅ ጀብዱ የሠራ ሌላው ጉበዝ
ተዋጊ ነበረ፤ እርሱም ሁለት በጣም የታ
ወቁ የሞዓብን ሰዎች ገደለ፤ እንዲሁም
በረዶ በጣለበት ዕለት በጕድጓድ ውስጥ ገብቶ
አንበሳ ገድሎአል፤ [21]ደግሞም አንድ ግዙፍ
ግብፃዊ ገድሎአል፤ ግብፃዊው በእጁ ጦር
የያዘ ቢሆንም፣ በናያስ ግን ሊገጥመው በትር
ይዞ ወደ እርሱ ሄደ፤ ከግብፃዊውም እጅ
ጦሩን በመንጠቅ በገዛ ጦሩ ገደለው።
[22]የዮዳሄ ልጅ የበናያስ ጀግንነት እንደዚህ
ያለ ነበረ፤ እርሱም እንደ ሦስቱ ኀያላን ሁሉ
ዝናን ያተረፈ ሲሆን፣ [23]ከሠላሳዎቹ ሁሉ
በላይ የከበረ ሰው ነበረ፤ ነገር ግን ከሦስቱ
እንደ አንዱ አልነበረም። ዳዊትም የክብር
ዘበኞቹ አለቃ አድርጎ ሾመው።
[24]ከሠላሳዎቹ መካከል የሚከተሉት ይገኙ
ባቸዋል፤
የኢዮአብ ወንድም አሣሄል፣
የቤተልሔሙ ሰው የዱዲ ልጅ
ኤልያናን፣
[25]አሮዳዊው ሣማ፣
አሮዳዊው ኤሊቃ፣
[26]ፊሊጣዊው ሴሌስ፣
የቴቁሐዊው የዒስካ ልጅ ዒራስ፣
[27]ዓናቶታዊው አቢዔዜር፤
ኩሳታዊው ምቡናይ[ሀ]፣
[28]አሆሃዊው ጸልሞን፣
ነጦፋዊው ማህራይ፣
[29]የነጦፋዊው የበዓና ልጅ ሔሌብ[ለ]፣
ከብንያም ወገን የጊብዓ ሰው የሆነው
የሪባይ ልጅ ኢታይ፣
[30]ጲርዓቶናዊው በናያስ፣
የገዓስ ሸለቆ ሰው ሂዳይ[ሐ]፣
[31]ዓረባዊው አቢዓልቦን፣
በርሑማዊው ዓዝሞት፣
[32]ሸዓልቦናዊው ኤሊያሕባ፣
የአሳን ልጆች፤
ዮናታን የተባለው፣
[33]የአሮዳዊው የሣማ ልጅ[መ]፣
የአሮዳዊው የሻራር[ሠ] ልጅ አሒአም፤
[34]የማዕካታዊው የአሖስባይ ልጅ ኤሊፋላት፣
የጊሎናዊው የአኪጦፌል ልጅ ኤሊአም፣
[35]ቀርሜሎሳዊው ሐጽሮ፤
አርባዊው ፈዓራይ፣
[36]የሱባ ሰው የሆነው የናታን ልጅ ይግዓል፣
[37]አሞናዊው ጻሌቅ፣
የጽሩያ ልጅ የኢዮአብ ጦር መሣሪያ ያዥ
የነበረው ብኤሮታዊው ነሃራይ፣
[38]ይትራዊው ዒራስ፣
ይትራዊው ጋሬብ፣
[39]እንዲሁም ኬጢያዊው ኦርዮ፤
በጠቅላላው ሠላሳ ሰባት ነበሩ።

## ዳዊት ተዋጊዎቹን ቈጠረ

22፥1-51 ተጓ ምብ - መዝ 18፥1-50

**24** እንደ ገናም እግዚአብሔር በእስራኤል
ላይ እጅግ ተቈጣ፤ ዳዊትንም በእነ
ርሱ ላይ በማስነሣት፣ "ሂድ እስራኤልንና
ይሁዳን ቍጠር" አለው።

23፥20 ኢሱ15፥21፤ 2ሳሙ8፥18፤ 1ዜና27፥5
23፥24 2ሳሙ2፥18
23፥25 መሳ7፥1
23፥26 1ዜና 27፥ 9:10
23፥27 ኢሱ21፥18፤ 1ዜና27፥12
23፥28 2ነገ25፥23፤ 1ዜና27፥13፤ዕዝ 2፥22፤ነህ7፥26፤ ኤር40፥8
23፥29 ኢሱ15፥57፤ 1ዜና27፥15
23፥30 ኢሱ24፥30፤ መሳ12፥13
23፥31 2ሳሙ3፥16
23፥34 ዘዳ3፥14፤ 2ሳሙ11፥ 3፤15፥12
23፥35 ኢሱ12፥22
23፥36 1ሳሙ 14፥47
23፥37 ኢሱ9፥17
23፥38 1ዜና2፥53
23፥39 2ሳሙ11፥3
24፥1 ዘፀ30፥12፤ ኢሱ9፥15፤1ዜና 27፥23፤ኢዮ1፥6፤ ዘካ3፥1

[ሀ]27 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትር ጕሞች (እንዲሁም 1ዜና 11፥29 ይመ) ግን፣ *ሲባካይ* ይላሉ።
[ለ]29 አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ አንዳንድ የዕብራይስጥ ቅጆችና ቩልጌት ( እንዲሁም 1ዜና 11፥30 ይመ) ግን፣ *ሔሌድ* ይላሉ።
[ሐ]30 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1ዜና 11፥32 ይመ) ግን፣ *ሁራይ* ይላሉ።
[መ]33 አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች ( እንዲሁም 1ዜና 11፥34 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማሉ፤ ዕብራይስጡ ግን *ልጅ* የሚለውን አይጨምርም።
[ሠ]33 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ አንዳንድ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕሞች (እንዲሁም 1ዜና 11፥35 ይመ) ግን፣ *ሳካር* ይላሉ።

23፥20 ***የዮዳሄ ልጅ በናያስ፤*** የከሊታውያንና የፈሊታውያን (8፥18፤ 20፥23፤ ቍ 23 ቀጥሎ ያለውን ይመ)፣ እንዲሁም በዓመቱ በሦስተኛ ወር ግዳጅ ላይ የነበረው ሰራዊት አዛዥ (1ዜና 27፥5) ነው። ሰሎሞን በአባቱ ዙፋን እንዲተካ ድጋፍ ሰጥቶአል (1ነገ 1-2)፤ በመጨረሻም በኢዮአብ ቦታ የሰራዊቱ አዛዥ ሆኖአል።

23፥24 ***ከሠላሳዎቹ፤*** ከቍ 29-39 ባለው ክፍል ሃያ ዘጠኝ ስሞች ተጽፈዋል፤ በቍ13-17 ላይ የተመለከቱት ሦስቱ በሠላሳው ቍጥር ውስጥ የተካተቱ በመሆናቸው፣ (ቍ 13 ይመ) የተዋጊዎች ጠቅላላ ብዛት 32 ነው። 1ዜና 11፥26-47 ደግሞ ለዚህ ምድብ 16 ተጨማሪ ስሞችን ይዘረዝራል፣ ስለዚህ ይህ ዝርዝር ምድቡን ለቀው በወጡት ወይም በሞት በተለዩት እግር የገቡትን አባላት ስም የሚያካትት ይመስላል። ***አሣሄል፤*** 2፥18-23 ይመ።

23፥34 ***ኤሊአም፤*** የቤርሳቤህ አባት ነው (11፥3 ይመ)፤ የዳዊት አማካሪ የአኪጦፌል ልጅ ሲሆን፣ አቤሴሎም በአባቱ በዳዊት ላይ በዐመፀ ጊዜ አባሪው ተባባሪው ነበር (15፥12፥31:34፤ 16፥20-23፤ 17፥1-23 ይመ)።

23፥39 ***ኦርዮ፤*** የቤርሳቤህ ባል ነው (11፥3-27 ይመ)። ***ሠላሳ ሰባት፤*** ከቍ 8-12 የተጠቀሱት ሦስቱና ከቍ 13-17 የሚገኙት ሌሎቹ ሦስት፣ አቢሳ (18-19)፣ በናያስና (20፥23) ስማቸው ከቍ 24-39 (የ24 ማብ ይመ) የተጻፈው 29 ሰዎች ተጨምረው፣ በቍ 8-39 ላይ የተዘረዘሩት ተዋጊዎች አጠቃላይ ብዛት ነው።

24፥1 ***እንደ ገናም፤*** ከዚህ በፊት እስራኤላውያንን የገጠማቸው ችግር ምናልባት በ21፥1 ላይ የተገለጸው ራብ ሊሆን ይችላል። ***እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ እጅግ ተቈጣ፤*** እግዚአብሔር ከምን የተነሣ እንደ ተቈጣ አልተገለጠም። አንዳንዶች እግዚአብሔር በቀባው ንጉሥ በዳዊት ላይ አቤሴሎምና ሲባ ላካሄዱት ዐመፅ ሕዝቡ ድጋፍ ከመስጠቱ የተነሣ እግዚአብሔር ተቈጣ ይላሉ (15፥12፤ 17፥11:24-26፤ 18፥7፤ 20፥1-2 ይመ)። እንደዚህ ከሆነ፣ በዚህ ምዕራፍ ላይ የሚታዩ ድርጊቶችና ቅደም ተከተል በም 15-20 ከተገለጡት ድርጊቶችና ከ980 ዓ.ቅ.ክ. በኋላ ይሆናል ማለት ነው (15፥7 ማብ ይመ)። ***ዳዊትንም በእነርሱ ላይ በማስነሣት፤*** 1ዜና 21፥1 "እስራኤልን ይቈጥር ዘንድ ሰይጣን ዳዊትን አንቀሳቀሰው" ይላል፤ እግዚአብሔር ማንንም ኀጢአት እንዲሠራ የማያደርግ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ቢያስረዳም (ያዕ 1፥13-15)፣ የሰውና የሰይጣን ክፉ ድርጊት ከሉዓላዊነቱ ቍጥጥር ውጭ ሊሆን እንደማይችልም እሙን ነው (ዘፀ 4፥21፤ 7፥3 9፥12፤ 10፥1:20:27፤ 11-10፤ ሕዝ 3፥20፤ 14፥9፤ ሐሥ 4፥28 ይመ)። ***እስራኤልንና ይሁዳን ቍጠር፤*** ዳዊት ሰራዊቱን መቍጠሩ (ቍ 2-3) ድንገተኛ በሆነ የውጭ ኀይል አስገዳጅነት የተካሄደ አልነበረም። "ብዛታቸው ምን ያህል እንደ ሆነ ለማወቅ እንድ ችልም" (ቍ 2) ማለቱ፣ ከሚያስተዳድረው ግዛት ስፋት የተነሣ ባደረበት ትዕቢት፣ ወይም ለደኅንነቱ መረጋገጥ ባለው የሰራዊት ብዛት ላይ በመደገፉ፣ ወይም ደግሞ በእነዚህ ምክንያቶች ተነሣሥቶ ድርጊቱን መፈጸሙ ግልጥ ነው። የሕዝብ ቈጠራ ማካሄድ በራሱ ኀጢአት አይደለም (ዘኍ 1፥2-3፤ 26፥2-4 ይመ)። እዚህ ላይ ግን የዳዊት ቈጠራ ርምጃ ያሳየው በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ ፈንታ በሰብአዊ ኀይል መተማመንንና መመካትን ነው (ይህን ድርጊት እስራኤላውያን ለደኅንነታቸው ይበጃል ብለው እግዚአብሔርን መተው፣ ምድራዊ ንጉሥ እንዲኖራቸው ካሳዩት የመጀመሪያ መሻታቸው ጋር ብዙ የሚለያይ አይደለም (1ሳሙ 8፥12 ይመ)። ዳዊት ግን እንደዚህ ያደርጋል ተብሎ የሚገመት ሰው አልነበረም (1ሳሙ 17፥26:37:45-47፤ 2ሳሙ 22፥2-4:47-51 ይመ)።

2ስለዚህም ንጉሡ ኢዮአብንና አብረውት
ያሉትን የጦር አዛዦችም*፣ "ከዳን እስከ ቤር
ሳቤህ ወዳሉት የእስራኤል ነገዶች ሁሉ ሂዱ፤
ብዛታቸው ምን ያህል እንደ ሆነ ለማወቅ
እንድችልም ተዋጊዎቹን መዝግቡ" አላቸው።
3ኢዮአብ ግን ንጉሡን፣ "አምላክህ እግዚአ
ብሔር ሰራዊቱን መቶ ዕጥፍ ያድርገው፤
የጌታዬ የንጉሡ ዐይን ይህን ለማየት ይብቃ፤
ንጉሡ ጌታዬ ግን ይህን ለማድረግ የፈለ
ገው ለምንድን ነው?" ሲል መለሰለት።
4ሆኖም የንጉሡ ቃል ኢዮአብንና የሰራዊቱን
አዛዦች ስላሸነፋቸው፣ የእስራኤልን ሰራዊት
ለመመዝገብ ከፊቱ ወጥተው ሄዱ።
5ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ፣ በሸለቆው ውስጥ
ካለችው ከተማ በስተ ደቡብ በምትገኘው በአ
ሮዔር አጠገብ ሰፈሩ፤ ከዚያም በጋድ በኩል
አድርገው ወደ ኢያዜር ሄዱ፤ 6እንዲሁም
ወደ ገለዓድና ወደ ተባሶን አዳሰይ፣ ቀጥሎም
ወደ ዳንየዓን ከዚያም ዞረው ወደ ሲዶና ሄዱ።
7ደግሞም ወደ ጢሮስ ምሽግ፣ ወደ ኤዊያ
ውያንና ወደ ከነዓናውያን ከተሞች፣ በመ
ጨረሻም በይሁዳ ደቡብ ወዳለችው ወደ ቤር
ሳቤህ ሄዱ።
8ምድሪቱን ሁሉ ዞረው ከዘጠኝ ወር ከሃያ
ቀን በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።
9ኢዮአብም የተዋጊዎቹን ጠቅላላ ቍጥር
ለንጉሡ አሳወቀ፤ በእስራኤል ስምንት መቶ
ሺህ፣ በይሁዳ አምስት መቶ ሺህ ሰይፍ መም
ዘዝ የሚችሉ ብቃት ያላቸው ሰዎች ተገኙ።
10ዳዊት ተዋጊዎቹን ከቈጠረ በኋላ ኅሊ
ናው ስለ ወቀሰው፣ "ባደረግሁት ነገር ታላቅ
ኀጢአት ሠርቻለሁ፤ አሁንም እግዚአብሔር
ሆይ፤ የአገልጋይህን በደል እንድታርቅ እለ
ምንሃለሁ፤ የፈጸምሁት ታላቅ የስንፍና ሥራ
ነውና" አለ።
11በማግስቱ ጠዋት ዳዊት ከመነሣቱ በፊት
የእግዚአብሔር ቃል የዳዊት ባለ ራእይ ወደ
ሆነው ወደ ነቢዩ ወደ ጋድ መጣ፤ 12እንዲ
ህም አለው፤ "ሂድና ዳዊትን፣ 'እግዚአብሔር
እንዲህ ይላል፤ ሦስት ነገሮችን ለምርጫ አቅ
ርቤልሃለሁ፤ በአንተ ላይ አደርግብህ ዘንድ
አንዱን ምረጥ' በለው።"
13ስለዚህም ጋድ ወደ ዳዊት ሄዶ፣ "በም
ድርህ የሦስት* ዓመት ራብ ይምጣብህ? ወይስ
ጠላቶችህ እያሳደዱህ ሦስት ወር ትሸሽ?
ወይስ ደግሞ በምድርህ ላይ የሦስት ቀን ቸነ
ፈር ይምጣ? እንግዲህ አሁን ለላከኝ ምን
መልስ እንደምሰጥ አስበህበት ወስን" አለው።
14ዳዊትም ጋድን፣ "እጅግ ተጨንቄአለሁ፤
ምሕረቱ ታላቅ ስለ ሆነ በእግዚአብሔር እጅ
እንውደቅ፤ በሰው እጅ ግን አልውደቅ" አለው።
15ስለዚህም እግዚአብሔር ከዚያች ዕለት ጥዋት
አንሥቶ እስከ ተወሰነው ቀን ድረስ በእስራ
ኤል ላይ ቸነፈር ላከ፤ በዚህም ከዳን እስከ
ቤርሳቤህ ድረስ ሰባ ሺህ ሰው አለቀ። 16የእ
ግዚአብሔር መልአክ ኢየሩሳሌምን ለማጥ
ፋት እጁን በዘረጋ ጊዜ፣ የደረሰው ጕዳት
እግዚአብሔርን ስላሳዘነው፣ ሕዝቡን የሚቀሥ
ፈውን መልአክ "በቃ! እጅህን መልስ" አለው።
በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በኢያ
ቡሳዊው በኦርና ዐውድማ አጠገብ ቆሞ ነበር።
17ዳዊት ሕዝቡን የሚቀሥፈውን መልአክ
ባየ ጊዜ እግዚአብሔርን፣ "እነሆ ኀጢአት የሠ
ራሁም የተሳሳትሁም እኔ ነኝ፤ እነዚህ ግን
በጎች ናቸው፤ ምን አጠፉ? እጅህ በእኔና በአ
ባቴ ቤት ላይ ትሁን" አለ።

## ዳዊት መሠዊያ ሠራ

24፥18-25 ተጓ ምብ - 1ዜና 21፥18-26

18በዚያን ቀን ጋድ ወደ ዳዊት ዘንድ ሄዶ፣
"ውጣና በኢያቡሳዊው በኦርና ዐውድማ ላይ
ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሥራ" አለው። 19ስለዚህ

24፥2 2ሳሙ 3፥10፤ 20፥23፤2ዜና2፥17፤ 17፥14፤25፥5
24፥3 ዘዳ1፥11፤ 2ሳሙ 2፥18
24፥5 ዘኁ 21፥32፤ ኢሱ13፥9
24፥6 ዘፍ10፥19፤ መሳ1፥31
24፥7 ዘፍ21፥31፤ ዘፀ3፥8፤ዘዳ1፥7፤ ኢሱ19፥29
24፥9 ዘኁ 1፥44-46
24፥10 ዘኁ 12፥11፤ 22፥34፤1ሳሙ 24፥5
24፥11 1ሳሙ 9፥9፤ 22፥5
24፥13 ዘፀ5፥3፤ 30፥12፤ዘሌ26፥25፤ ዘዳ28፥21-22፡27-28-35፤28፥38-42፡48፤ 32፥24፤ሕዝ14፥21
24፥14 ነህ9፥28፤ መዝ4፥1፤51፥1፤86፥5፤103፥8፡13፤119፥132፤130፥4፤ኢሳ54፥7፤ 55፥7፤ኤር33፥8፤ 42፥12፤ዳን9፥9
24፥15 1ዜና27፥24
24፥16 ዘፍ6፥6፤ 16፥7፤19፥13፤ዘፀ 12፥23፤ሐሥ12፥23
24፥17 ዘፍ18፥23፤ መዝ74፥1፤100፥3፤ ኤር49፥20፤ዮና1፥12
24፥18 ዘፍ22፥2፤ 2ዜና3፥1

*2 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም (እንዲሁም ቍጥር 4 እና 1ዜና 21፥2 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ የጦር አዛዡ ኢዮአብ ይላል።
*13 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ( እንዲሁም 1ዜና 21፥12 ይመ) ከዚህ ጋር ይስማማል፤ ዕብራይስጡ ግን፣ ሰባት ይላል።

24፥2 *ከዳን እስከ ቤርሳቤህ፤* የ1ሳሙ 3፥20 ማብ ይመ።

24፥3 *ለምንድን ነው?* ዳዊት የሰጠው መመሪያ ያለ አን ዳች ተቃውሞ እንዲሁ ተቀባይነት አላገኘም፤ ዳዊት መልስ አለመ ስጠቱ፣ ቈጠራው ላስፈለገበት ምክንያት ትክክለኛ መልስ እንደ ሌለው ያውቅ ስለ ነበር ነው። ያም ሆነ ይህ ኢዮአብ የሰነዘ ረው ሐሳብ የዳዊትን ጥፋት ያጕላዋል።

24፥5-8፤ የሰራዊት ቈጠራ ከደቡባዊ ዮርዳኖስ ማዶ ጀምሮ እስከ ሰሜን ዘልቋል፤ ከዚያም በዮርዳኖስ በኩል ወደ ኋላ ተመ ልሶ እንደ ገና ከሰሜን ወደ ደቡብ ቀጥሎአል።

24፥9 *ስምንት መቶ ሺህ፣... አምስት መቶ ሺህ፤* እዚህ ላይ የተጠቀሱት አኃዞች በ1ዜና 21፥5 (የ1ዜና 21፥56 ማብ ይመ) ላይ ካሉት ጋር አይመሳሰሉም።

24፥10 *ታላቅ ኀጢአት ሠርቻለሁ፤* የቍ1 ማብ ይመ።

24፥11 *የዳዊት ባለ ራእይ ወደ ሆነው ወደ ነቢዩ ጋድ፤* የ1ሳሙ 9፥9፤ 22፥5 ማብ ይመ።

24፥12 *ሂድና ዳዊትን... በለው፤* 12፥1 እና ማብ ይመ። *ሦስት ነገሮችን ለምርጫ አቅርቤአለሁ፤* እነዚህ ሦስት የፍርድ አማ ራጮች፣ ሙሴ ኪዳናዊ ኀላፊነታቸውን ለመወጣት ባልቻሉት የእግዚአብሔር ሰዎች ላይ ይመጣሉ ባላቸው መርገሞች ውስጥ ተካተው ይገኛሉ (ዘዳ 28፥15-25 ይመ)።

24፥14 *በሰው እጅ ግን አልውደቅ፤* እግዚአብሔርን ያወቀውና፣ የጦርነትንም አስከፊነት በሚገባ የተረዳው ዳዊት፣ በጦርነት ማዕበል ውስጥ ገብቶ በሚቅበዘበዝ ሰው እጅ ላይ ከመውደቅ ይልቅ፣ ቢቈጣም እንኳ እጅግ መሓሪ በሆነው በእግዚአብሔር መዳፍ ሥር መሆን የሚልቅ መሆኑን ተገንዝ ቦአል (መዝ 30፥5 ይመ)።

24፥15 *ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ፤* የ1ሳሙ 3፥20 ማብ ይመ።

24፥16 *መልአክ፤* መላእክት የእግዚአብሔር ፍርድ ማስ ፈጸሚያ መሣሪያ መሆናቸው በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ቦታ ተመልክቶአል (ዘፀ 33፥2፤ 2ነገ 19፥35፤ መዝ 35፥5-6፤ 78፥49፤ ማቴ 13፥41፤ ሐሥ 12፥23 ይመ)። *እግዚአብሔርን ስላሳዘነው፤* የ1ሳሙ 15፥29 ማብ ይመ። *በኦርና ዐውድማ፤* ቦታው በሞሪያ ተራራ ላይ የሚገኝ፣ በስተ ሰሜን በኩል ለዳ ዊት ከተማ ቅርብ ሲሆን፣ ከተማውንም ቍልቍል ለማየት የሚ ያስችል ነው፤ ከጊዜ በኋላም ቤተ መቅደስ ተሠርቶበታል (1ዜና 22፥1፤ 2ዜና 3፥1 ይመ)። *በኢያቡሳዊው፤* የ5፥6 ማብ ይመ።

24፥17 *እጅህ በእኔና በአባቴ ቤት ላይ ትሁን፤* የእስ ራኤል ሕዝብ ከበደል ነጻ ባይሆንም እንኳ (ቍ 1)፣ ዳዊት በግል ለፈጸመው ጥፋት ሙሉ በሙሉ ተጠያቂ እንደ ሆነ አምኖ፣ መቀበሉና በንጉሥነቱ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ደኅንነት ኀላፊ ነት ያለበት መሆኑን ተገንዝቦአል (5፥2፤ 7፥7-8 ይመ)።

ዳዊት፣ *እግዚአብሔር* በጋድ በኩል ባዘዘው
መሠረት ወጣ:: 20አርናም ቍልቍል ሲመ
ለከት፣ ንጉሡና ሰዎቹ ወደ እርሱ ሲመጡ
አየ፤ ከዚያም ወጥቶ ወደ መሬት ለጥ ብሎ
ለንጉሡ እጅ ነሣ::
21አርናም፣ "ንጉሥ ጌታዬ ወደ አገልጋዩ
የመጣው ለምንድን ነው?" አለ::
ዳዊትም መልሶ፣ "መቅሠፍቱ ከሕዝቡ
እንዲከለከል ለእግዚአብሔር መሠዊያ እን
ድሠራ ዐውድማህን ልገዛ ነው" አለው::
22አርናም ዳዊትን እንዲህ አለ፤ "ንጉሥ
ጌታዬ ደስ ያለውን ወስዶ መሥዋዕቱን ያቅ
ርብ፤ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሬዎች አሉ፤
ለሚነደውም ዕንጨት፣ የመውቂያው ዕቃና
የበሬ ቀንበር አለ:: 23ንጉሥ ሆይ፣ ይህን
ሁሉ አርና ለንጉሡ ይሰጣል::" እንዲሁም
አርና፣ "*እግዚአብሔር* ስጦታህን ይቀበልህ"
አለው::
24ንጉሡ ግን አርናን፣ "እንዲህማ አይሆ
ንም፤ ዋጋውን ሳንተ መክፈል አለብኝ፤ በስ
ጦታ ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥ
ዋዕት ያለ ዋጋ አላቀርብም" አለው::
ስለዚህም ዳዊት ዐውድማውንና በሬዎቹን
በአምሳ ሰቅል[ሬ] ብር ገዛ፤ 25በዚያም ዳዊት
*ለእግዚአብሔር* መሠዊያ ሠራ፤ የሚቃጠል
*መሥዋዕትና የኅብረት መሥዋዕት*[ሰ] አቀረበ::
ከዚያም *እግዚአብሔር* ስለ ምድሪቱ የቀረ
በውን ጸሎት ሰማ፤ በእስራኤል ላይ የመጣ
ውም ቸነፈር ቆመ::

24፥21 ዘኍ16፥44-50
24፥22 1ሳሙ6፥14
24፥23 ዘፍ23፥11
24፥24 ዘፍ23፥16፤ ሚል1፥13-14
24፥25 1ሳሙ 7፥17፤2ሳሙ21፥14

[ሬ]24 0.6 ኪሎ ግራም ያህል ነው::
[ሰ]25 በትውፊት፣ *የሰላም መሥዋዕት* ይባላል::

24፥19 *እግዚአብሔር... ባዘዘው መሠረት፤* የዳዊት ጸሎት መልስ እንዲያገኝ የማስተሰርያ መሥዋዕቱ እንዲቀርብ ራሱ እግዚአብሔር ወሰነ::

24፥21 *ዐውድማህን ልገዛ ነው፤* ዳዊት ለአገር ወይም ለመንግሥት ያስፈልጋል በማለት ተመጣጣኝ ዋጋ ሳይከፈልበት የሰው ንብረት መውሰድ አልፈለገም (1ሳሙ 8፥14 ይመ)::

24፥24 *የሚቃጠል መሥዋዕት፤* ዘሌ 1፥1-17 ይመ:: *ዳዊት ዐውድማውንና... ገዛ፤* በዚህ ሁኔታም ዳዊት ቤተ መቅደሱ ይገኝበት የነበረውን ቦታ (የቍ 16 ማብ ይመ) የቤተ መንግሥት ንብረት አደረገው:: *በሬዎቹን፤* ዳዊት መሥዋዕቱን ቶሎ ለማቅረብ ከመቸኰሉ የተነሣ፣ ራቅ ብሎ ከሚገኝ ከራሱ መንጋ በሬዎች እስኪመጡለት መቈየት አልቻለም:: *በአምሳ ሰቅል ብር፤* የ1ዜና 21፥25 ማብ ይመ::

24፥25 *የኅብረት መሥዋዕት፤* የ1ሳሙ 11፥15 ማብ ይመ:: ዕርቅና የኪዳን ኅብረት ተሐድሶ በንጉሥ ንስሓ፣ የምልጃ ጸሎትና መሥዋዕት ይገኛሉ::